የኢትዮጵያ የሰነደ
ሙዓለ ንዋዮች ገበያ
Ethiopian Securities
Exchange

# የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የገበያ መተዳደሪያ ደንብ

# የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ

# የገበያ መተዳደሪያ ደንብ

ታህሳስ 2017

## መግቢያ

የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ("አዋጁ") የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ("ኢሰሙንገ ወይም "ገበያው") እንዲቋቋም የሚያዝ በመሆኑ፣

በካፒታል ገበያ አዋጅ አንቀጽ 30 እና 31 እና በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ ተዛማጅ ውሎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የአሰራር እና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1009/2016 መሰረት ገበያው ከኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ("ኢካገባ" ወይም "ባለስልጣኑ") ፈቃድ የተሰጠው በመሆኑ፣

ሥርዓት ያለው፣ ግልጽና ቀልጣፋ ገበያ ማደራጀት ተልዕኮው እንደመሆኑ መጠን ገበያውን እና ገበያው የሚያንቀሳቅሳቸውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአግባቡና በብቃት ለመቆጣጠር፣ ለማስተዳደር፣ ለማሰራት እና ለመምራት አስፈላጊ ደንቦችና ሥርዓቶች ሊኖሩት የሚገባ በመሆኑ፣

ገበያው በአዋጁ አንቀጽ 35፣ 36፣ 37 እና 38 መሠረት የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ (የአክሲዮን እና የዕዳ ሰነድ ገበያዎች) መጽሐፈ ደንብን በ2017 ዓ.ም እንደሚከተለው አውጥቷል።

# ማውጫ


| ቅጽ | መግለጫ | ገጽ ቁጥር |
| --- | --- | --- |
| ሀ | ጠቅላላ ደንቦች | |
| ለ | የአባልነት ደንቦች | |
| ሐ | የምዝገባ ደንቦች | |
| መ | የግብይት ደንቦች | |
| ሠ | የዲስፕሊን ሥነ-ሥርዓቶች እና የአለመግባባት መፍቻ ደንቦች | |

# የደንብ ማውጫ

**ቅጽ ሀ፡ ጠቅላላ ደንቦች......22**

***ምዕራፍ 1 - ርዕስ፣ ወሰን እና ትርጓሜ......22***

1.1. አጭር ርዕስ......22

1.2. ትርጓሜ......23

1.3. የተፈፃሚነት ወሰን......34

**ምዕራፍ 2 - የደንብ አስተዳደር እና ስምምነቶች......34**

2.1. የደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የአሰራር ስርዓቶች እና ሌሎች ሰነዶች አስተዳደር እና አተገባበር......34

2.2. ደንብን ስለመተው ወይም ማሻሻያ ስለማድረግ......35

2.3. በተጠቀሱ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ የሕግጋት ስብስብ፣ ሰንጠረዦች ወይም ሌሎች ሰነዶች ላይ ስለሚደረጉ ማሻሻያዎች......35

2.4. የደንቦች፣ የአሰራር ሂደቶች እና ሌሎች ሰነዶች አተረጓጎም......36

2.5. በመጽሐፈ ደንቡ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ......36

2.6. ለጽሑፍ እና ለግንኙነት ስለሚውል ቋንቋ......36

2.7. አጠቃላይ ስነ-ምግባር፣ አሰራር እና ይፋ የማድረግ ግዴታዎች......36

2.8. የንግድ ሰነዶች መለያ......37

2.9. የተጠያቂነት ገደብ ........ 37

2.10. ለገበያው ስለሚቀርብ ካሳ ........ 40

***ምዕራፍ 3 - የገበያው እና የግብይት ክፍያዎች........41***

3.1. ክፍያዎችን እና ወጪዎችን የመወሰን እና የመከለስ ስልጣን ........ 41

3.2. የአባልነት ቅበላ እና የተሳትፎ ክፍያዎች........ 41

3.3. ለግብይት አባላት የሚከፈሉ የድለላ ክፍያዎች እና ኮሚሽኖች ........ 41

3.4. የግብይት ክፍያዎች ........ 42

**ቅጽ ለ: የአባልነት ደንቦች........43**

**ክፍል 1 —የግብይት አባላት........44**

*ምዕራፍ 1 — የግብይት አባላት ዕውቅና አሰጣጥ እና አመዳደብ........ 44*

1.1 አጭር ርዕስ ........ 44

1.2. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 44

1.3. የግብይት አባላት ምድቦች........ 44

*ምዕራፍ 2 ፦ የግብይት አባል ቅበላ ሂደቶች........ 45*

2.1. አባላትን የመቀበል ስልጣን........ 45

2.2. ለአባልነት ስለሚቀርብ ማመልከቻ ........ 45

2.3. በመርህ ደረጃ የማፅደቅ መስፈርቶች ........ 46

2.4. አባል ሥራ እንዲጀመር ስለሚሰጥ ማረጋገጫ ........ 49

2.5. የአባልነት ምስክር ወረቀቶች ላይ የገበያው የባለቤትነት መብት ........ 51

2.6. የግብይት መብቶች መቋረጥ ........ 51

2.7. የግብይት አባል ሁኔታ ........ 52

2.8. አባልነትን ስለመተው ........ 52

*ምዕራፍ 3 ቁጥጥር፣ የባለቤትነት መዋቅር እና ጉልህ ተፅዕኖ........ 53*

3.1 የቅድመ ማፅደቅ እና የቅድመ ማሳወቅ መስፈርቶች........ 53

3.2. የግብይት አባል ሕጋዊ ወይም የተጠቃሚ ባለቤትነት ላይ የሚደረግ ለውጥ .......... 53

3.3 የግብይት አባል በሌላ የንግድ ስራ ላይ መሰማራት .......... 54

3.4 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሰለማቋቋም .......... 56

3.5 ዋና ወይም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ስለማዛወር ወይም መዝጋት .......... 57

3.6 የንግድ ስም ስለመለወጥ .......... 57

*ምዕራፍ 4 - የካፒታል እና የሂሳብ ሪፖርት .......... 58*

4.1 ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርት .......... 58

4.2 የገንዘብ አከል ንብረት መስፈርቶች .......... 59

4.3 ሪፖርት ስለማቅረብ .......... 59

4.4 የፋይናንስ መግለጫን ወይም ሌሎች ሪፖርቶችን ማዘባት የተከለከለ ስለመሆኑ .......... 61

*ምዕራፍ 5 - አስተዳደር፤ ክትትል እና የውስጥ የቁጥጥር ስርዓት .......... 61*

5.1 ክትትል እና የውስጥ የቁጥጥር ስርዓት .......... 61

5.2 አስቀድሞ በጽሑፍ ስለሚሰጡ ፈቃዶች እና ማስታወቂያዎች .......... 62

5.3 የስጋት አስተዳደር .......... 62

5.4 ሕጋዊ እርምጃ .......... 62

5.5 በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን መከላከል .......... 63

5.6 ድርጅታዊ አስተዳደር .......... 63

*ምዕራፍ 6- ተሿሚ እንደራሴዎች እና ሌሎች ሠራተኞች .......... 64*

6.1 የተሿሚ እንደራሴዎች እና ሌሎች ሠራተኞች ኃላፊነት .......... 64

6.2 ተሿሚ እንደራሴዎችን የመሾም እና የማፀደቅ ግዴታ .......... 64

6.3 የግብይት አባል ተሿሚ እንደራሴዎች የስነ ምግባር ደንብ እና ግዴታዎቻቸው .......... 65

6.4 በቀድሞ ተሿሚ እንደራሴወች፣ ሰራተኞች እና ሌሎች ባለሙያዎች ላይ የሚቆይ ስልጣን .......... 66

6.5 የተሿሚ እንደራሴዎች መደብ ላይ ስለሚደረግ ለውጥ.......................................66

6.6 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት.......................................................................67

6.7 የሕግ ተገዢነት መኮንን ..........................................................................68

6.8 የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች.......................................................71

*ምዕራፍ 7 — **የሒሳብ ዶሴ እና መዝገቦች**.........................................................73*

7.1. የግብይት መዝገብ እና የምርመራ መብት.......................................................73

7.2. የደንበኛ መዝገብን ስለማስቀመጥ................................................................74

***ምዕራፍ 8 – የግብይት አባላት ከህዝብ ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት**...........................74*

8.1. ከህዝብ ጋር ለሚደረግ ግንኙነት አጠቃላይ መስፈርቶች.....................................74

8.2. የግብይት አባል ግንኙነቶች ውስጥ የሚካተቱ ምክሮች እና ምስክርነቶች................76

8.3. በህዝብ ፊት መቅረብ  እና ንግግር ማድረግ .....................................................77

8.4. የሶስተኛ ወገን ግንኙነት ..........................................................................77

8.5. የግንኙነት መዝገብ..................................................................................77

8.6. ለደንበኞች የሚሰጥ መረጃ.........................................................................77

***ምዕራፍ 9 – የገበያ ከፋቾች**...........................................................................79*

9.1. የገበያ ከፋች ሆኖ ስለመሾም እና የብቃት መስፈርቶች......................................79

9.2. የሂሳብ እና የስርዓት መስፈርቶች ...............................................................81

9.3. የገበያ ከፋች ቀጣይ ግዴታዎች ..................................................................81

9.4. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታዎች.......................................................................83

9.5. የገበያ ከፋች መውጣት..............................................................................84

***ምዕራፍ 10 - ስፖንሰር አድራጊ ደላላ፣ገበያ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ ዲጂታል ንውስ ደላላዎች**...........................................................................................85*

10.1. ለስፖንሰር አድራጊ ደላላነት፣ ለገበያ አከናዋኝነት ወይም ለኢንቨስትመንት ባንክ ዲጂታል ንውስ ደላላነት እውቅና ለማግኘት ቀዳሚ  መስፈርቶች .....................................85

10.2. የስፖንሰር አድራጊ ደላላ፣ ገበያ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ ቀጣይ ግዴታዎች ..... 86

***ክፍል 3 — የካሳ ፈንድ*** ..... **87**

***ምዕራፍ 11 — የደንበኞች ካሳ ፈንድ*** ..... **87**

11.1. የደንበኞችን የካሳ ፈንድ ማቋቋም እና የፈንዱ መዋጮ ..... 87

11.2. የፈንዱ አስተዳደር እና አመራር ..... 87

11.3. ወደ ደንበኞች የካሳ ፈንድ የሚከፈሉ ክፍያዎች ..... 89

11.4. የደንበኞችን የካሳ ፈንድ መለየት ..... 91

11.5. ከፈንዱ የሚከፈሉ ክፍያዎች ..... 91

11.6. ካሳ ..... 91

11.7. መዝገቦች እና ሪፖርት ማቅረብ ..... 92

11.8. የህዝብ ግንዛቤ ማስጨበጥ ..... 93

***ምዕራፍ 12 — የባለሀብቶች ካሳ*** ..... **93**

12.1. የይገባኛል ጥያቄዎችን ማረጋገጥ ..... 93

12.2. የካሳ ክፍያ ..... 93

12.3. በርካታ የይገባኛል ጥያቄዎች ..... 95

12.4. የካሳ መጠን ..... 95

12.5. የተስተካከሉ ክፍያዎች ..... 96

***የአስተዳደራዊ ቅጣት ሰንጠረዥ - የአባልነት ደንቦች*** ..... **98**

ቅፅ ሐ፡ የምዝገባ ደንቦች ..... 108

**ክፍል 1 - ጠቅላላ ድንጋጌዎች** ..... **109**

*ምዕራፍ 1 - መግቢያ ..... 109*

1.1. አጭር ርዕስ ..... 109

1.2. ዓላማ ..... 109

1.3. ጠቅላላ መርሆዎች .......... 109

1.4. የማክበር ግዴታ .......... 110

*ምዕራፍ 2 - የገበያው ስልጣን .......... 111*

2.1. ጠቅላላ ስልጣን .......... 111

2.2. ስልጣን ያለው አካል .......... 112

*ምዕራፍ 3 .......... 113*

*በገበያው የሚደረጉ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ጠቅላላ መስፈርቶች እና የምዝገባ ሥነ-ሥርዓቶች .......... 113*

3.1. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ ጠቅላላ መስፈርቶች .......... 113

3.2. የምዝገባ ቅድመ ሁኔታዎች .......... 116

**ክፍል 2: የአክሲዮን ምዝገባ .......... 117**

*ምዕራፍ 4: የገበያው የአክሲዮን የምዝገባ መስፈርቶች .......... 117*

4.1. ተፈፃሚነት .......... 117

4.2. የገበያው የአክሲዮን ምዝገባ ቦርድ .......... 117

4.3. የምዝገባ መንገዶች .......... 117

4.4. ጠቅላላ መስፈርቶች .......... 118

*ምዕራፍ 5 ፡ በዋናው የገበያ ቦርድ የመጀመሪያ ዙር ምዝገባ መስፈርቶች .......... 119*

5.1. የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በዋናው የገበያ ቦርድ ምዝገባ .......... 119

5.2. ተጨማሪ መስፈርቶች .......... 121

*ምዕራፍ 6፡ በገበያው የአዳጊ ገበያ ቦርድ የመጀመሪያ ምዝገባ መስፈርቶች .......... 122*

6.1. የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የአዳጊ ገበያ ቦርድ ምዝገባ .......... 122

6.2. ተጨማሪ መስፈርቶች .......... 124

*ምዕራፍ 7፡ አባሪ የአክሲዮን ምዝገባ መስፈርቶች .......... 124*

7.1. ተፈጻሚነት .......... 124

7.2. አጠቃላይ መስፈርቶች ........ 125

7.3. ልዩ የምዝገባ መስፈርቶች ........ 125

**ክፍል 3 - ቀጣይነት ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎች ........128**

*ምዕራፍ 8 - ጠቅላላ ቀጣይነት ያላቸው የአውጪዎች ግዴታዎች........ 128*

8.1. መረጃን ይፋ ማድረግ ........ 128

8.2. ወቅታዊ መግለጫ ........ 129

8.3. መረጃን ይፋ ማድረግ ተፈፃሚነት ስለማይኖርባቸው ሆኔታዎች ........ 130

8.4. የሚጢራዊነት መስፈርቶች ........ 131

8.5. በአውጪዎች አክስዮን ላይ የሚደረጉ ግብይቶችን ይፋ ስለማድረግ........ 131

8.6. የፋይናንስ መግለጫ፡ የሂሳብ አያያዝ ደረጃ........ 134

8.7. የሂሳብ መግለጫ፡ የሂሳብ መግለጫ ማስገባት ........ 134

8.8. የፋይናንስ መግለጫዎችን ማስገባት አለመቻል ........ 134

8.9. የፋይናንስ መረጃን በጊዜው ይፋ ባለማድረግ መታገድ ........ 135

8.10. ዓመታዊ ሪፖርት........ 135

8.11. የሕግ ተገዢነት ሥራ አስኪያጅ........ 136

*ምዕራፍ 9 - የኩባንያ ኃላፊነት........ 136*

9.1. ዓላማ ........ 136

9.2. የዳይሬክተሮች ግዴታዎች ........ 137

9.3. የቦርድ ስብሰባዎች ........ 137

9.4. የአባላት ጠቅላላ ጉባኢ ........ 138

*ምዕራፍ 10፡ የተዛማጅ ወገን ግብይቶች........ 139*

10.1. ጠቅላላ መስፈርቶች ........ 139

10.2. እንደ ተዛማጅ ወገን ግብይት የማይቆጠሩ ግብይቶች........ 139

10.3. የተዛማጅ ወገን ግብይት ሪፖርት ይዘቶች ........................................................ 139

10.4. ጠቅላላ ስልጣን ........................................................................................... 139

10.5. ስላለመተው .............................................................................................. 141

*ምዕራፍ 11፡ በአውጪዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ንግድ ላይ የሚጣል እገዳ........................... 141*

11.1. የግብይት እገዳ ........................................................................................... 141

11.2. በፈቃደኝነት መታገድ ................................................................................. 142

11.3. ከእገዳዎች ጋር በተያያዘ የአውጪው ቀጣይ ግዴታዎች..................................... 142

*ምዕራፍ 12፡ አውጭውን እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ከገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ መሰረዝ... 143*

12.1. የተፈፃሚነት ወሰን .................................................................................... 143

12.2. የተመዘገቡ አክሲዮኖችንማስወገድ ................................................................. 143

12.3. በፈቃደኝነት የተመሠረተ የአክስዮኖች ስረዛ........................................................ 143

12.4. ለመጨረሻ ጊዜ መሰረዝ የሚያበቁ ሁኔታዎች..................................................... 145

12.5. በተቆጣጣሪ አካል መሰረዝ .......................................................................... 145

12.6. በፈቃደኝነት ከተሰረዘ በኋላ እንደገና መመዝገብ ................................................ 146

**ክፍል 4፡ የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ..............................................146**

*ምዕራፍ 13፡ በገበያው ላይ የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መመዝገቢያ መስፈርቶች......... 146*

13.1. ጠቅላላ መስፈርቶች ..................................................................................... 146

13.2. የምዝገባ ዘዴዎች ወይም መንገዶች ................................................................. 148

13.3. ለባለልዩ ተልዕኮ ተቋም ተጨማሪ መስፈርቶች .................................................. 148

13.4. የምዝገባ ቅድመ ሁኔታዎች .......................................................................... 149

13.5. የኩባንያ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ........................................................................................................... 149

13.6. የኩባንያ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ድህረ-ምዝገባ መስፈርቶች ........................................................................................................... 151

13.7. በኢትዮጵያ መንግስት አውጪነት የቀረቡ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮችን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ........ 152

13.8. ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከምዝገባ መዝገብ ለመሰረዝ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ........ 152

**ክፍል 5: በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ለግብይት የሚቀርቡ ፈንዶች ምዝገባ ........153**

*ምዕራፍ 14፡ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ላይ ለግብይት የሚቀርቡፈንዶች ምዝገባ መስፈርቶች ........ 153*

14.1. የማመልከቻ መስፈርቶች........ 153

14.2. የምዝገባ ቅድመ ሁኔታዎች ........ 153

14.3. የሽያጭ ሰነድ ይዘቶች ........ 155

14.4. የገበያ ከፋች ሹመት........ 156

14.5. ዕለታዊ ህትመት ........ 156

**ክፍል 6 - ለሸሪዓ ህግ ተገዥ የሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ........157**

*ምዕራፍ 15 - በገበያው ላይ የሱኩክ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ........ 157*

15.1. ለሱኩክ አውጪዎች የብቃት መስፈርት፡-........ 157

15.2. ይፋ ማድረግ እና ግልጽነት........ 157

15.3. የሸሪዓ መርሆዎችን ማክበር ........ 157

15.4. የተገቢነት ጥናት እና የማጽደቅ ሂደት ........ 158

15.5. የሰነድ መስፈርቶች፡-........ 158

15.6. ቀጣይነት ያላቸው ግዴታዎች........ 158

*ምዕራፍ 16 - ለሸሪዓ ህግጋት ተገዥነት ያላቸው አክሲዮኖችን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች........ 158*

16.1. የሸሪዓን መስፈርት የሚያሟሉ አክሰዮኖችን ለመመዝገብ የብቃት መስፈርቶች፡-... 158

16.2. የማመልከቻ ሰነድ፡........ 159

16.3. የምዝገባ ሂደት፡- ........................................................................ 159

16.4. የቀጣይነት ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎች፡- ........................................... 159

**ክፍል 7፡ የምዝገባ ሰንጠረዦች ........................................................ 160**

*ሰንጠረዥ 1፡ የካሳ ሽፋን ደብዳቤ ናሙና ............................................... 160*

*ሰንጠረዥ 2— የህግ ተገዢነት ማረጋገጫ ደብዳቤ ናሙና ........................... 162*

*ሰንጠረዥ 3፡ የምዝገባ ውል ናሙና ........................................................ 163*

**የአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ _ የምዝገባ ደንቦች ............................ 168**

**ቅጽ መ: የግብይት ደንቦች ............................................................ 171**

**ክፍል 1 - ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........................................................ 172**

***ምዕራፍ አንድ - የደንቦች አስተዳደርና ስምምነቶች*** *........................... 172*

1.1. አጭር ርዕስ .................................................................. 172

1.2. የተፈጻሚነት ወሰን ............................................................ 172

1.3. የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ሌሎች ደንቦች ተፈፃሚነት ............ 172

**ክፍል 2 - የደንበኞች አስተዳደር .................................................... 173**

*ምዕራፍ 2 - የደንበኛ ሒሳቦች .......................................................... 173*

2.1. ደንበኛን ዕወቅ እና የተገቢነት ጥናት .......................................... 173

2.2. የደንበኛ ሒሳቦች ቁጥጥር ..................................................... 174

2.3. ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን ማረጋገጥ ............................................ 176

2.4. የደንበኛ ሒሳብ አያያዝና ልየታ ................................................ 177

2.5. ለደንበኞች የሚቀርብ ወርሃዊ የሒሳብ መግለጫ .................................. 177

*ምዕራፍ 3 - የደንበኞች ሀብቶች ....................................................... 178*

3.1. የደንበኞች ገንዘብ አጠቃቀምና ልየታ ......................................... 178

3.2. የደንበኞችን ገንዘብ መመዝበር .................................................. 180

3.3. ያልተፈቀደ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ ...................... 181

3.4. በደንበኞች ሒሳብ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ........................................ 182

3.5. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግዢ ወይም ሽያጭ ክፍያዎች ........................................ 183

**ክፍል 3 - ግብይት ........................................................................................183**

*ምዕራፍ 4 - የትዕዛዝ ክንውንና ምርጥ አፈጻጸም........................................................ 183*

4.1. የምርጥ አፈጻጸም መርሕና መስፈርቶች ........................................................ 183

4.2. በሒሳቡ ላይ እንዲወሰን ፈቃድ የሰጠ ኢንቨስተር............................................ 184

4.3. የዋጋ ሚና ........................................................................................ 185

4.4. የትዕዛዝ አፈጻጸም.............................................................................. 185

4.5. የደንበኞችን ዝርዝር መመሪያዎች መከተል...................................................... 187

4.6 የደንበኛን ትዕዛዝ ማስተናገድ ........................................................................ 188

4.7. ትዕዛዞችን በአንድ ላይ መደመርና መደልደል................................................... 189

4.8. የየግብይት ፈፃሚውን አባል የግል ሒሳብ ከደንበኞች ግብይት ጋር በአንድ ላይ መደመርና መደልደል የተከለከለ ስለመሆኑ.................................................................. 189

4.9. የኦዲት ዱካ መመዘኛዎች............................................................................ 189

4.10. የቋሚ ገቢ ገበያ ትዕዛዝ የሚስተናገድበት አግባብ ........................................... 190

4.11. የቋሚ ገቢ ገበያ የተቆረጡ ዋጋዎች ወይም የትዕዛዝ ደንብ ............................ 190

4.12. የግብይቶች የቋሚ ገቢ አፈጻጸም.................................................................. 190

4.13. የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ቁርጥ ዋጋዎችና ትዕዛዞች የጸኑ መሆን............ 191

4.14. የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የግብይት መጠናቀቅ........................................ 191

*ምዕራፍ 5 - የስህተት ግብይቶችና ትዕዛዞች................................................................ 191*

5.1. የትዕዛዞችን ትክክለኛነት የተመለከተ ኃላፊነት................................................... 191

5.2. የዋና መዝገብ  የስህተት ሒሳቦች ................................................................. 192

5.3. ግብይቶችን መሰረዝ..................................................................................... 193

5.4. የግልጽ ስህተቶች አስተዳደር......................................................................... 193

5.5. የግልጽ ስህተት ማስተካከል  አሠራር ........................................................ 194

5.6. ገበያው የስህተት ግብይቶችን አስመልክቶ የሚሰጣቸው ውሳኔዎችና ይግባኞች ....... 196

*ምዕራፍ 6 - የተከለከሉ ተግባራት ........................................................................ 196*

6.1. በዋስትና ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥራ ግንኙነት ስለ መከልከሉ ......................... 196

6.2. በደንበኞች መካከል ማበላለጥ ክልክል ስለመሆኑ ................................................ 196

6.3. ግዴታውን ካልፈጸመ ደንበኛ ጋር ግብይት ማድረግ ስለመከልከሉ።...................... 197

6.4. የገበያው መግለገያዎችና መረጃ ......................................................................... 197

*ምዕራፍ 7 - የገበያው የግብይት ሥራዎች ........................................................... 197*

7.1. የገበያው የሥራ ቀናትና ሰዓታት ...................................................................... 197

7.2. የግብይት መስፈርቶች ...................................................................................... 198

7.3. ትዕዛዛትና ትዕዛዛትን የማጣመር መርሆች ........................................................ 199

7.4. የግብይት ሥርዓቶች አያያዝ ............................................................................ 199

7.5. የጸደቁ የግብይት መድረኮች ወይም ሥርዓቶች ................................................... 200

7.6. የግብይት አባል ኃላፊነት ................................................................................. 200

7.7. የግብይት አባላት ስለሚሰይሟቸው ተጠቃሚዎች ................................................. 201

7.8. የግብይት ሥርዓት መግቢያ መለያዎች አጠቃቀም ............................................... 201

7.9. ገደቦችና ወሰኖች ........................................................................................... 201

7.10. የትልቅ አክሲዮኖች ስብስብ ግብይት ............................................................... 202

7.11. የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከገበያው ውጪ መገበያየት ስለመከልከሉ ...... 203

7.12. ከክፍያ ነጻ ማስተላለፍ .................................................................................. 203

7.13. የብድር ሽያጭ መፈጸም .................................................................................. 205

7.14. ግብይት ማስቆም ............................................................................................ 205

7.15. ገበያው በድንገተኛ ሁኔታዎች የራሱን ውሳኔዎች የማስተላለፍ ሥልጣን ያለው መሆኑ ........................................................................................................... 206

7.16. ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........................................................................ 206

**ክፍል 4 - ቀጥተኛ የኤሌክትሮኒክ ተሳትፎ ........................................................ 208**

*ምዕራፍ 8 - ለደንበኞች ቀጥታ የኤሌክትሮኒክ ተሳትፎ የበይነ መረብና የዲጂታል ግብይት መድረክ ደንቦች ........................................................................ 208*

8.1. የመሠረተ-ልማት መመዘኛዎች ........................................................................ 208

8.2. ደንበኞችን የማስተዋወቅና የደንበኛን እወቅ መመዘኛዎች ........................................ 208

8.3. የስጋት አስተዳደርና የበላይ ቁጥጥር ........................................................ 209

8.4. ለገበያው መረጃ የመስጠት ግዴታ ........................................................ 211

**ክፍል 5 - ለግብይቶች ክፍያ መፈጸም ........................................................ 212**

*ምዕራፍ 9 - ክፍያ ማጣራትና መፈጸም ........................................................ 212*

9.1. ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችንና ከግብይቱ የተገኘውን ገንዘብ ርክክብና ክፍያ መፈጸም .... 212

9.2. የማስተላለፊያ ሰነዶችን ማስረከብ ........................................................ 213

9.3. ያልተሳካን ግብይት የማሳወቅ ግዴታ ........................................................ 213

9.4. ጉድለት ያለበት ዝውውር ........................................................ 213

**ክፍል 6 - የግብይት ሥነ ምግባር ........................................................ 214**

***የየግብይት አባላት ሥነ ምግባር*** *........................................................ 214*

10.1. አጠቃላይ ሥነ ምግባር ........................................................ 214

10.2. ለገበያው ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ........................................................ 215

10.3. ወደ ግብይት ማዕከል መግባትና ቁጥጥሮች ........................................................ 215

10.4. የግብይት ማዕከል ሥነ ምግባር ........................................................ 217

10.5. በግብይት ማከናወኛ ቦታዎችና መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ጥንቃቄ ... 218

10.6. ጆሮ ጠብ እና ከደንበኞች ቀድሞ ግብይት መፈጸም ........................................ 218

10.7. የገበያ ማጭበርበር እና የሕገ ወጥ የገበያ ስምምነቶች ክልከላ ........................ 218

10.8. የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ክልከላ ........................................................ 220

10.9. አሳሳች የግብይት ልማድ ክልከላ ........................................................................ 222

10.10. መረጃ በምስጢር መያዝ ያለበት ስለመሆኑ ........................................................ 225

10.11. የትዕዛዞች ማኅደሮች ........................................................................................ 225

*ምዕራፍ 11 ግዴታዎችን አለመወጣትና ኪሳራ ......................................................................... 226*

11.1. ግዴታዎችን አለመወጣት ስለመከልከሉ ....................................................... 226

11.2. የኪሳራ ወይም ግዴታን ያለመወጣት ማስጠንቀቂያ ........................................ 226

11.3. የሙብት ጥያቄዎች የሚሸጡ፣ የሚተላለፉ ወይም በዋስትና የሚያዙ አለመሆናቸው ........................................................................................................ 227

11.4. ግዴታ ባለመወጣት ወቅት የገበያው ሥልጣን ................................................ 227

11.5. ኃላፊነትን ስለማስተባበል ...................................................................................... 229

**የአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ - የግብይት ደንቦች ..........................................230**

**ቅጽ ሠ : የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓቶችና የግጭት አፈታት ደንቦች ........................246**

**ክፍል 1 - የቅሬታ አስተዳደርና በግብይት አባላት ላይ የሚወሰዱ የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓቶች ..........................................................................................................247**

*ምዕራፍ 1 — የቅሬታ አስተዳደር........................................................................................ 247*

1.1. የቅሬታ አስተዳደር..................................................................................................... 247

*ምዕራፍ 2 —የገበያው የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓት......................................................... 247*

2.1. ለገበያው ቅሬታ ማቅረብ................................................................................ 247

2.2. የዲሲፕሊን አካላት .................................................................................................. 248

2.3. የዲሲፕሊን እርምጃዎች.......................................................................................... 248

2.4. በገበያው የጉዳይ መኮንኖች የሚወሰድ የደንብ ማስከበር እርምጃ ....................... 251

2.5. የንግድ ሥነ-ምግባር ጉባዔ ..................................................................................... 251

2.6. ማስረጃ ማቅረብና በንግድ ሥነምግባር ጉባዔ ፊት መቅረብ ................................ 252

2.7. ምርመራ እስኪጠናቀቅ መታገድ ....................................................................... 252

2.8. የመስማትና የመዳኘት ሥልጣን ........................................................................ 252

2.9. በጉባዔው ፊት በሕግ ባለሞያ መወከል ............................................................ 253

2.10. የሒደቶች መዝገብ ........................................................................................ 253

2.11. የጉባዔው ውሳኔዎች ...................................................................................... 253

2.12. የገበያው የመቅጣት ሥልጣን.......................................................................... 253

2.13. አስተዳደራዊ ቅጣቶች .................................................................................. 254

2.14. የገበያ አባልነት መቋረጥ .............................................................................. 255

2.15. የዲሲፕሊን እርምጃ ማስታወቂያ .................................................................. 255

2.16. የይግባኝ ምክንያቶች .................................................................................... 256

**ክፍል 2 - ሌሎች የቅሬታ አስተዳደር ሥነ-ሥርዓቶች..........................................256**

*ምዕራፍ 3 - በገበያው ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አቀራረብና አስተዳደር............................ 256*

3.1. የቅሬታዎች አቀራረብ ...................................................................................... 256

3.2. ኤሌክትሮኒክ የቅሬታዎች መዝገብ ................................................................ 256

3.3. የቅሬታና የጉዳይ መኮንን ምደባ .................................................................. 257

3.4. የቅሬታዎች አስተዳደር.................................................................................... 257

3.5. ቅሬታዎችን መመርመርና መፍታት ................................................................ 258

3.6. ውሳኔን ማሳወቅ.............................................................................................. 258

3.7. ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ይግባኝ...................................................................... 258

*ምዕራፍ 4 - በግብይት አባላት መካከል የሚከሰቱ የፍትሐ ብሔር አለመግባባቶችን መፍታት 258*

4.1. በግብይት አባላት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን መፍታት ........................ 258

*ምዕራፍ 5 - ገበያው የሚያስተባብረው ሽምግልና......................................................... 259*

5.1. ሽምግልና ........................................................................................................ 259

5.2. የዕርቅ ስምምነትን ወይም የመተካት ትዕዛዝን ወይም ስለመተካት የሚደነግግ የዕርቅ ስምምነትን አለማክበር ........................................................................................ 260

5.3. በየግብይት አባል ማኅደሮች ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች ................................ 261

*ምዕራፍ 6 - የግልግል ዳኝነት........................................................................................ 262*

6.1. የግልግል ዳኝነት .......................................................................................... 262

6.2. የግልግል ዳኝነት መጀመር ............................................................................ 262

6.3. የግልግል ዳኝነት ጉባዔ ................................................................................... 262

6.4. የግልግል ዳኝነት መድረክ ................................................................................ 262

6.5. የግልግል ዳኞች ጉባዔ ማቋቋም ...................................................................... 263

6.6. የሥነ-ሥርዓት ደንቦችን መወሰን ...................................................................... 263

6.7. ተከራካሪ ወገኖችን መስማት ሳያስፈልግ መወሰን ................................................ 263

6.8. ክርክር መስማት ............................................................................................. 264

6.9. ውሳኔ ........................................................................................................... 264

6.10. ገዢ ሕግና የዳኝነት ሥልጣን ......................................................................... 264

6.12. ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃዎች ..................................................................... 265

6.13. የሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ መግባት ................................................................... 265

6.14. ውሳኔዎች ................................................................................................... 265

6.15. የግልግል ዳኝነት ሒደት መቋረጥ .................................................................... 265

6.16. ምስጢር ጥበቃ ............................................................................................ 266

6.17. የግልግል ዳኝነት ወጪ ................................................................................... 266

**የአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ - የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓቶችና ግጭት አፈታት ደንቦች........................................................................................................268**

# ቅጽ ሀ፡ ጠቅላላ ደንቦች

## *ምዕራፍ 1 - ርዕስ፣ ወሰን እና ትርጓሜ*

### 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መጽሐፈ ደንብ፣ 2017 (ጠቅላላ ደንቦች)" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

1.2. ትርጓሜ

(1) በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተገለጸ ማንኛውም አገላለጽ የሴት ጾታን ይጨምራል፡፡

(2) የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፤

1. “ተባባሪ ኩባንያ” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ የተቋቋመ ማንኛውም ኩባንያ ሲሆን፣ አንድ የግብይት አባል ወይም የተመዘገበ ኩባንያና ከእሱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ኩባንያዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ድርጅቱ ካወጣው አጠቃላይ የአክሲዮን ካፒታል ቢያንስ 20 በመቶ የሚደርስ ከድርሻ የሚገኝ ጥቅምን የያዙበት ነው፡፡

2. “ባለሥልጣን”፣ “የኢካገባ” ማለት የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ነው፡፡

3. "መለኪያ ነጥብ" ማለት በፋይናንስ ዘርፍ የወለድ ምጣኔዎችና የቦንድ ገቢ ላይ የሚደረጉ ለውጦችን ለመግለጽ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውል የመለኪያ አሃድ ሲሆን፣ ይህም ከ0.01% ወይም በመቶ ከ1/100ኛ ወይም በአስርዮሽ ከ0.0001 ጋር እኩል ነው፡፡

4. “ተጠቃሚ ባለቤት” ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ አልባ ተደርገው ስለሚቀመጡበት ሁኔታ ባለስልጣኑ ባወጣው መመሪያ መሠረት የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

5. “ትልቅ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ስብስብ” ማለት በማንኛውም ኩባንያ ውስጥ የሚገኙ ማንኛውም ቁጥር ያላቸው የአክሲዮን ክፍሎች ወይም ሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሲሆኑ መጠናቸው በገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው በሚወሰነው እና በባለስልጣኑ በሚፀድቀው መጠን ልክ ድረስ ያለው ነው፡፡

6. “የዳይሬክተሮች ቦርድ” ማለት የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና/ወይም የምዝገባ ማመልከቻዎችን የማጽደቅ ኃላፊነት ከቦርዱ የተሰጠው የተሰየመ አካል ወይም ኮሚቴ ወይም ተመሳሳይ ኃላፊነት የተሰጠው ሌላ ሰው ወይም አካል ነው፡፡

7. “ቦርድ” ማለት የዋና ገበያው ቦርድ እና የአዳጊ ገበያው ቦርድ ሲሆን እንዲሁም ገበያው በየጊዜው የሚያፀድቀው ማንኛውም ሌላ ቦርድ ነው፡፡

8. “የጉርሻ አክሲዮን ማውጣት” ማለት በሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 በተደነገገው መሰረት ትርፍን በጥሬ ገንዘብ በመከፋፈል ምትክ አዳዲስ አክሲዮኖችን ማውጣት ማለት ነው፡፡

9. “የድለላ ክፍያ እና ኮሚሽን” ማለት የግብይት አባላት በገበያው ላይ የምክርና የግብይት አገልግሎቶችን ለመስጠት ደንበኞችን የሚያስከፍሉት ክፍያ ነው፡፡

10. “የሥራ ቀናት” ማለት በህግ የተደነገጉ እና በገበያው ከሚገለጹ የሕዝብ በዓላት፣ ቅዳሜና እሑድ ውጪ ያሉት ቀናት ናቸው፡፡

11. “የካላንደር ቀናት” ማለት በኢትዮጵያ የሚከበሩ የሕዝብ በዓላት፣ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ተከታታይ ቀናት ናቸው፡፡

12. “ካፒታልን መልሶ ማዋቀር” ማለት በኩባንያው የካፒታል አወቃቀር ላይ ለውጦችን ለማድረግ የሚተገበር የንግድ ሥራ ማስፈጸሚያ ስልት ነው፡፡

13. “የግብይት ገደብ ወቅት” ማለት የአውጪው ድርጅት የውስጥ አዋቂዎች በአውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ግብይት እንዳይፈጽሙ ገደብ የተደረገበት ማንኛውም ጊዜ ነው፡፡

14. “የንግድ ሕግ” ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 ሲሆን፣ በየጊዜው የሚደረግበትን ማሻሻያ ይጨምራል፡፡

15. "ዋና ኢንቨስተር" ማለት በዋና ወይም በአዳጊ ገበያ ቦርድ ላይ ከሚመዘገብ ኩባንያ ጋር በተያያዘ በኩባንያው ውስጥ ከፍተኛ የተጠቃሚነት መብት ያለው እና በኩባንያው ውጤታማነት ላይ የረጅም ጊዜ ፍላጎት ያለው ተቋማዊ ኢንቨስተር፣ የጋራ ሥራ አጋር ወይም የቴክኒክ አጋር ነው፡፡ እንደ ዋና ኢንቨስተር ለመቆጠር የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፦

- ዋናው ኢንቨስተር ኩባንያው ባወጣው የአክሲዮን ካፒታል ውስጥ ቢያንስ 10% ወይም ከዚያ በላይ የባለቤትነት ድርሻ ያለው፣ በተዛማጅ ኢንዱስትሪ ውስጥ የተረጋገጠ የሥራ ታሪክ ወይም ዝና ያለው፤ እና
- ተጽዕኖ የመፍጠር ወይም የአስተዳደር ሚና ያለው ከሆነ፡ በኩባንያው አስተዳደር ውስጥ እንደ የቦርድ አባልነት መደበኛ ውክልና በመያዝ ተጽዕኖ ወይም የአስተዳደር ሚና ያለው፣ ወይም ከአውጪው ጋር የአስተዳደር ውል ወይም ተመሳሳይ ስምምነት የገባ የቴክኒክ አጋር መሆን አለበት፡፡

16. “ተለዋጭ ሰነድ” ማለት ኢንቨስተሮቹ ሰነዱን ወደ አውጪው የአክሲዮን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ እንዲቀይሩ የሚያስገድድ ወይም የሚፈቅድ ማንኛውም የቋሚ ገቢ ሰነድ ነው፡፡

17. “ግብይት አከናዋኝ አባል ባንክ” ማለት የገበያው አባል የሆነ እና በተመዘገቡ ወይም ባልተመዘገቡ የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ገበያ እንዲከፍት በባለስልጣኑ የተፈቀደለት የንግድ ባንክ ነው፡፡

18. “በሂሳቡ ላይ እንዲወሰን ፍቃድ የሰጠ ኢንቨስተር” ማለት ኢንቨስተሩ ወይም ደንበኛው ለእያንዳንዱ ግብይት የተናጠል ፈቃድ መስጠት ሳይጠበቅበት የግብይት አባሉ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮችን እንዲገዛ እና እንዲሸጥ ሥልጣን የሚሰጥ ኢንቨስተር ወይም ደንበኛ ነው፡፡ “የምአሰ” ማለት የምስራቅ አፍሪካ ሰዓት ማለት ነው፡፡

19. “ገበያ” ማለት የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ነው፡፡

20. “ለየፈ” ማለት በገበያው ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች ነው፡፡

21. “ኤግመ” ማለት ኤሌክትሮኒክስ የግብይት መድረክ ነው፡፡

22. “ኤግመ ስርዓት” ማለት በገበያው የሚንቀሳቀሱ ወይም ለሰነደ ሙዓለ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ገበያ ለማቅረብ የሚያገለግሉ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የኮምፒዩተር ስርዓቶች እና ተያያዥ ኔትወርኮች ናቸው፡፡

23. “የግብይት ማስፈጸሚያ መስፈርቶች” ማለት ከትዕዛዝ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ዋጋ፣ ወጪዎች፣ ፍጥነት፣ የመፈጸም እና የመከፈል ዕድል፣ መጠን፣ ባህሪ፣ የአፈጻጸም መጠን፣ የዋጋ መሻሻል፣ የገበያ ተጽዕኖ ወይም ሌላ ማንኛውም ግምት ነው፡፡

24. “የውጭ ኦዲተር” በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

25. “የገንዘብ ድጋፍ” ማለት ገንዘብን ማበደር ወይም መበደር፣ ለደረሰ ዕዳ ዋስትና መስጠት ወይም ማቅረብ ወይም ዋስትና ለሰጠ ወይም ዋስትና ላቀረበ የካሳ ዋስትና መስጠት፣ ወይም ዕዳን ይቅር ማለት፣ የሌላውን ሰው የገንዘብ ግዴታ መተው ወይም ቸል ማለት፣ ወይም የሌላን የገንዘብ ግዴታዎች መውሰድ ነው፡፡

26. “የፋይናንስ ዓመት” ማለት ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ ወይም በንግድ አባል፣ በተመዘገበ ኩባንያ ወይም ሌላ አግባብነት ባለው አካል የመመሥረቻ ጽሁፍ የተወሰነው የአንድ ዓመት ጊዜ ነው፡፡

27. “የተረጋገጠ ትዕዛዝ” ማለት መጠኑንም ሆነ ዋጋውን የሚያሳይ በገበያ ላይ የቀረበ ትዕዛዝ ነው፡፡ የተረጋገጠ ትዕዛዝ በግልጽ እስከሚሰረዝ ወይም ውድቅ የሚያደርጉት አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎችን እስኪያሟላ ድረስ በሥራ ላይ ጸንቶ ይቆያል፡፡

28. "የቋሚ ገቢ ገበያ" ማለት በገበያው የተመዘገቡትን የዕዳ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና የገንዘብ ገበያ ሰነዶች ግብይት ለመፈፀም በገበያው የሚተዳደር ገበያ ነው።

29. “ያለክፍያ ማስተላለፍ” ማለት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ያለ ክፍያ ማስተላለፍ ነው።

30. "ኢጃራህ (ኪራይ)" ማለት አንድን ሀብት አከራዩ (ባለቤቱ) በተስማማበት ኪራይ ለተወሰነ ጊዜ ለተከራይ የሚያከራይበት ውል ነው።

    አግባብነት ባለው የኪራይ ውል ቃላት በሌላ መልኩ ካልተገለፀ በስተቀር የተከራየው ሀብት ባለቤትነት ሁልጊዜም የአከራዩ ሆኖ ይቆያል።

31. “ኢጅቲሃድ” ማለት በሸሪዓ ምንጮች ላይ የተሰጡ ብያኔዎችን መሰረት በማድረግ ብቁ የሆኑ ምሁራን የሚሰጡት ምክንያታዊ ትንታኔ ነው።

32. “ቅርብ የቤተሰብ አባላት” ማለት የትዳር ጓደኛ፣ ልጆች፣ ወንድሞችና እህቶች፣ ወላጆች፣ አያቶች፣ የልጅ ሚስት፣ የልጅ ባል፣ የትዳር ጓደኛ ወንድም፣ የትዳር ጓደኛ እህት፣ የትዳር ጓደኛ አባት እና የትዳር ጓደኛ እናት ሲሆን የእንጀራ እናት እና አባት እና የጉዲፈቻ ግንኙነቶችን ይጨምራል።

33. "የመመስረቻ ሰነዶች" ማለት የአንድን ኩባንያ የምስረታ እና አወቃቀር መረጃን የያዙ የህግ ሰነዶች ስብስብ ነው።

34. “ካሳ የተገባላቸው ሰዎች” ማለት ገበያው፣ ተዛማጅ ኩባንያዎቹ፣ የቁጥጥር ሥራዎችን ወይም ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን እንዲያከናውን የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል የወከለው ማንኛውም ሰው ወይም አካል ወይም ተቋም እና የእነዚሁ ዳይሬክተሮች፣ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች ወይም ወኪሎች ናቸው።

35. “የመረጃ ማስታወሻ” በሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 የተሰጠው ተመሳሳይ ትርጉም ይኖረዋል።

36. “የመጀመሪያ የህዝብ ሽያጭ” በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

37. “ውስጥ አዋቂ” በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

38. “የውስጥ አዋቂ ግብይት” በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይኖረዋል።

39. "ተቋማዊ ኢንቨስተሮች" በባለስልጣኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 እና በየጊዜው በሚደረገው ማሻሻያዎቹ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

40. "ጥቅም ያላቸው ሰዎች" በአዋጁ የተሰጠው ተመሳሳይ ትርጉም ይኖረዋል፡፡

41. "ኢንቨስተር" በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

42. "ያለፈቃድ መሰረዝ" ማለት አውጪው የገበያውን ዝቅተኛ የምዝገባ መስፈርቶች ማሟላት ባለመቻሉ ምክንያት የአውጪውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከገበያው ይፋዊ የግብይት ዝርዝር መሰረዝ ማለት ነው፡፡

43. "አአሰመ" ማለት ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚሰጥ አለም አቀፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መለያ ቁጥር ነው፡፡

44. "አውጪ" በአዋጁ አንቀጽ 2 (37) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

45. "ኬዋይሲ" ማለት "ደንበኛዎን ይወቁ" ማለት ነው፡፡

46. "የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች" በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

47. "የምዝገባ መስፈርቶች" በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

48. "የምዝገባ ማረጋገጫ ቃለ መኃላ" ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዩ በገበያው ይፋዊ መዝገብ ውስጥ ከመመዝገቡ በፊት የምዝገባ ደንቦቹን ወይም በምዝገባ ደንቦቹ መሰረት የተገባ ማንኛውንም ስምምነትን ወይም ማረጋገጫን ለማክበር አውጪው የሚፈጽመው የቃለ መኃላ ማረጋገጫ ነው፡፡

49. "የገበያ ሽፍጥ " ማለት የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ዋጋ ለመቆጣጠር የሚያስችል ጉልህ የሆነ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ይዞታ የተገኘበት ወይም ጉልህ ድርሻ የተያዘበት ሁኔታ ነው፡፡

50. "ገበያ ከፋች" በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

51. "የገበያ ዋጋ ማስተካከያ" ማለት የዕዳ ሰነደ ሙዓለ ንዋይን የገበያ ሁኔታ ወቅታዊ በሆነው የገበያ ዋጋ እንደገና መተመን ማለት ነው፡፡

52. "የዕዳ መክፈያ ቀን" ማለት እንደ ሁኔታው የሚራዘም ወይም በሌላ መልኩ ሊሻሻል የሚችል ሆኖ፣ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ እንዲከፈል የታቀደበት ቀን ነው፡፡

53. “የአባልነት ምስክር ወረቀት” ማለት ለአንድ ድርጅት በገበያው ላይ በተመዘገቡት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እንዲገበያይ የሚፈቅድ በገበያው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው።

54. “የማስታወሻ ምዝገባ” ማለት በገበያው ላይ ለግብይት ያልቀረቡ ነባር ሱኩኮች የመታየት ዕድል፣ ግልጽነት እና ለሕዝብ ተጋላጭነትን ለማሳደግ ሱኩክን ወደ ገበያው መድረክ መቀበል ነው።

55. “ውህደት እና ግዢ ” ማለት በውህደት፣ በግዢ፣ በመጠቅለል፣ በጨረታ የግዢ ሽያጮች፣ ሀብትን መግዛትንእና የአስተዳደር ግዥዎችን ጨምሮ በተለያዩ አይነት የገንዘብ ግብይቶች አማካይነት ኩባንያዎችን ወይም ሀብትን መጠቅለል ማለት ነው።

56. “አናሳ ባለአክሲዮኖች” ማለት በድርጅት እርምጃዎች ላይ ቁጥጥር ወይም ተጽዕኖ ለማሳደር የሚያስችል በቂ ድርሻ የሌላቸው የአውጪው ሁሉም ባለአክሲዮኖች ማለት ሲሆን፣ በተለይም ተቆጣጣሪ ወይም ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖችን፣ የአውጪውን አደራጆች እና ዳይሬክተሮችን አይጨምርም።

57. “አናሳ አክሲዮኖች” ማለት በአናሳ ባለአክሲዮኖች የተያዙ ሁሉም አክሲዮኖች ናቸው።

58. “ሙዳራባህ (ትርፍ መጋራት)” ማለት ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል ነው። ተዋዋይ ወገኖቹም የንግድ ሥራውን ለመደገፍ ካፒታል የሚያዋጣው ራብ አል-ማል (የካፒታል አቅራቢ) እና የንግድ ሥራውን የሚያስተዳድረው ሙድሃሪብ (ሥራ ፈጣሪ) ናቸው። የንግድ ሥራው ትርፋማ ከሆነ፣ ትርፉ ቀድመው በተስማሙበት ጥምርታ መሰረት ይከፋፈላል። የንግድ ኪሳራ በሚከሰትበት ጊዜ ኪሳራው በካፒታል አቅራቢው ብቻ ይሸፈናል።

59. “ሙሻራካህ (ትርፍ እና ኪሳራ መጋራት)” ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል ለንግድ ሥራ የሚሆን ገንዘብ ለማዋጣት የሚገባ የሽርክና ውል ሲሆን ሁሉም ወገኖች ለንግድ ሥራ የሚሆን ገንዘብን በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ካፒታል ያዋጣሉ። ከንግድ ሥራው የሚገኝ ማንኛውም ትርፍ ቀድመው በተስማሙበት የትርፍ መጋራት ስምምነት መሰረት ይከፋፈላል፣ ሆኖም ኪሳራ የካፒታል መዋጮን መሰረት በማድረግ ይጋራሉ።

60. “ኢብባ” ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው።

61. "የተጣራ የሚዳሰሱ ሀብቶች" ማለት አጠቃላይ ሀብቶች ሲቀነስ የማይዳሰሱ ሀብቶች ሲቀነስ ጠቅላላ ዕዳዎች ሲቀነስ ቁጥጥር የማያሳድሩ ከድርሻ የሚገኙ ጥቅሞች የሚገኘው ነው። ሀብቶች፣ የማይዳሰሱ ሀብቶች፣ እዳዎች እና ቁጥጥር የማያሳድሩ ከድርሻ የሚገኙ ጥቅሞች በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

62. “ኤንኤስአይኤን” ማለት በሚመለከተው ባለስልጣን ለደህንነት ሲባል የተሰጠ የብሔራዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ መለያ ቁጥር ነው።

63. “ባለዕዳ” ማለት በቋሚ የገቢ ኢንቨስትመንት ስምምነቶች መሰረት ሁሉንም ዋና ክፍያዎችን እና ሌሎች ስምምነት የተደረሰባቸው ክፍያዎችን ለመፈጸም በውል የሚገደድ ድርጅት ወይም ሰው ነው።

64. “ለግዢ ቃልኪዳን ማቅረብ” በሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 እና በማሻሻያዎቹ የተሰጠው ተመሳሳይ ትርጉም ይኖረዋል፡፡

65. “ኦፊሴላዊ መዝገብ” ማለት በገበያው የሚያዝ እና በምዝገባ ደንቦቹ መሰረት የተመዘገቡ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መዝገብ ነው ።

66. “አመንጪ” ማለት ሱኩክን ለማውጣት ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋምን ያቋቋመ እና ሱኩክን በተመለከተ የሚገደድ ሰው ሆኖ የሚሰራ እናት ኩባንያ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት (ወይም ኤጀንሲው)፣ ንዑስ ብሔራዊ አካል፣ ዓለም አቀፍ/ልዕለ-ብሔራዊ ኮርፖሬሽን ወይም ሌላ ሕጋዊ አካል ነው።

67. "አክሲዮን ላይ የሚፃፍ ዋጋ" ማለት እንደ አግባብነቱ በመመስረቻ ጽሁፍ ላይ የተገለጸው የአንድ አክሲዮን ዋጋ ወይም የአውጪው ተመጣጣኝ ዋጋ ነው።

68. "የክፍያ ቀን" ማለት በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መብቶች ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤት የሚከፈሉበት ቀን ነው። ይህ ቀን ክፍልፋዮችን (ክፍያዎችን) ከመቀበያ ቀን ጋር ሊጣመር ወይም ክፍልፋዮችን (ክፍያዎችን) ከመቀበያ ቀን በኋላ ሊከሰት ይችላል።

69. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰው ነው።

70. "ብቁ ኢንቨስተር" በአዋጁ እና በሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 ከተሰጠው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ይኖረዋል፡፡

71. “ዋጋ” ማለት በቋሚ የገቢ ገበያ ውስጥ እንደ ቃሉ አገባብ ዋጋ፣ ተመን፣ ወይም ትርፍ ነው።

72. “የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ” በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

73. “የመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ” በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

74. "ከፍተኛ ኃላፊዎች" ማለት ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ የኩባንያ ጸሐፊ፣ የውስጥ ኦዲተር፣ ዋና የፋይናንስ ኃላፊ፣ ዋና የህግ ተገዥነት መኮንን እና ዋና የአደጋ ስጋት ኃላፊን ያካትታል፡፡

75. “አዋጅ” ማለት የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና በየጊዜው የሚደረግበት ማሻሻያ ነው፡፡

76. “አደራጅ” በንግድ ሕጉ አንቀጽ 248 (1) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

77. “ደንበኛ ሳቢ መግለጫ” በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

78. “የሕዝብ ኩባንያ” በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

79. “ለግብይት የቀረበ አክሲዮን” ማለት አውጪው በገበያው ላይ ለግብይት ያወጣቸው እና በግብይት ሂደት የሚገኙ የአክሲዮን ብዛት ነው፡፡ በግብይት በሚሳተፈው ህዝብ የተያዙትን ሁሉንም አክሲዮኖች የሚያጠቃልል ሲሆን፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአውጪው አደራጆች፣ በዳይሬክተሮች እና በቅርብ ቤተሰብ አባላት፣ ትልቅ ድርሻ ባላቸው ባለአክሲዮኖች፣ የሰራተኛ ድርሻን በሚቆጣጠሩ ባለአክሲዮኖች፣ ወይም የአውጪውን አምስት በመቶ (5%) ወይም ከዚያ በላይ የካፒታል አክሲዮን በያዙ የአውጪው ተባባሪ ወይም ተቀፅላ ማህበር የተያዙ አክሲዮኖችን አያካትትም፡፡

80. “ለሕዝብ ማቅረብ” በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

81. “ሕዝብ” ማለት ከአክሲዮን ማህበር ወይም ከመንግሥት የልማት ድርጅት ጋር በተያያዘ፣ ከሚከተሉት በስተቀር ሁሉንም ግለሰቦች ወይም የሕዝብ አባላትን ያጠቃልላል፦

    i. የአውጪው እና የተቀጥላ ኩባንያዎቹ ዳይሬክተሮች፤

    ii. የሚከተሉትን ሁሉንም መስፈርቶች ካላሟሉ በስተቀር፣ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች፣ ቁጥጥር ያላቸው ባለአክሲዮኖች፣ ወይም የአውጪው ወይም ተቀጥላ ኩባንያዎቹ ተባባሪ ሰዎች፡፡ እነዚህ ባለአክሲዮኖች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ እንደ “ሕዝብ” ባለአክሲዮኖች ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ባለአክሲዮኖች፡ -

1) የሕዝብ አባላት የሆኑ አዋጮች ወይም ኢንቨስተሮች ባለቤት የሆኑባቸውን ገንዘቦችን የሚያስተዳድር በሕግ የተቋቋመ ተቋም ከሆነ፤ ወይም

2) ዝግ የሆነ ፈንድ ወይም የኢቨስትመንት ፈንድን ጨምሮ (የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ኩባንያዎችን ሳይጨምር) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሆኖ የተቋቋመ ተቋም ከሆነ፣

iii. የዳይሬክተሮች፣ የትልቅ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች፣ ቁጥጥር ያላቸው ባለአክሲዮኖች ወይም ከአውጪው ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ተባባሪዎች::

82. “የመመዝገቢያ ቀን” ማለት በአውጪው የባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ስማቸው የሚገኝ ባለአክሲዮኖች ከአውጪው ድርጅታዊ እርምጃዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት እና በአውጪው የተወሰነ ቀን ነው::

83. "ቅርበት ያለው ሰው" የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

i. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተር፣ የቁጥጥር ቦርድ አባላትና የኩባንያው ጸሐፊዎች፣

ii. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተሻሻለው የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ መሠረት በዚህ ደንብ አንቀጽ (84 (i) ከተዘረዘሩት ሰዎች ጋር በደም ወይም በሥጋ ዝምድና ግንኙነት የተሳሰሩ ሰዎች፤

iii. በዚህ ደንብ አንቀጽ 84 (2 (i እና ii)) የተዘረዘሩት ሰዎች ባለአክሲዮኖች፣ ተጠቃሚዎች ወይም የአስተዳደር ሚና የሚጫወቱበት የንግድ ድርጅት ወይም ተቋም፤

iv. የኩባንያው እናት ወይም ተቀጥላ የሆነ ኩባንያ፤

v. በመመሥረቻ ጽሁፉ ወይም በሕግ አነስተኛ የአክሲዮን ድርሻ መጠን ካልተደነገገ በስተቀር ከኩባንያው አክሲዮን ውስጥ ቢያንስ አሥር በመቶ የገዙ ሰዎች ወይም ኩባንያው ባለአክሲዮን በሆነባቸው ኩባንያዎች ወይም እርስ በርስ አንዳቸው የሌላኛውን አክሲዮን የገዙ ኩባንያዎች፤

vi. በማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፉ ወይም በሌላ ሕግ ከኩባንያው ጋር ግንኙነት ያላቸው ተብለው የተገለጹ ሌሎች ሰዎች::

84. "የተዛማጅ ወገን ግብይት" ማለት በተመዘገበው ኩባንያ እና ቅርበት ባለው ሰው መካከል የሚደረግ ግብይት ነው::

85. “የግል  ኢንቨስተር” ማለት በሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 መሠረት እንደ ተቋማዊ ወይም ብቁ ኢንቨስተር የማይቆጠር ማንኛውም ኢንቨስተር ነው፡፡

86. “ማዋመ” ማለት የማወዳደሪያ ዋጋ መጠየቂያ ነው፡፡

87. “ሁለተኛ ደረጃ ገበያ” በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይኖረዋል፡፡

88. “ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች” በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይኖረዋል፡፡

89. “የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ” ማለት እንደ አግባብነቱ የደንበኞችን መመሪያ/ትእዛዝ የማስፈጸም እና/ወይም ስፖንሰር ለሚያደርጉት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የራሳቸውን ገንዘብ በመጠቀም ግብይቶችን የመፈፀም ኃላፊነት ያለው ግለሰብ ነው፡፡

90. “ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ መኮንን“ ባለስልጣኑ ባወጣው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

91. “የአገልግሎቶች ፈቃድ” ባለስልጣኑ ባወጣው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

92. “አክሲዮን” በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይኖረዋል፡፡

93. "ጉልህ ተጽዕኖ" ባለስልጣኑ ባወጣው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

94. “ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን”  በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይኖረዋል

95. “ሱኩክ” ወይም “ህትመት” ማለት በባለስልጣኑ የጸደቁ የሸሪዓ መርሆዎችና ጽንሰ-ሀሳቦች መሰረት፣ በሚዳሰሱ ሀብቶች፣ አላባ እና አገልግሎት ላይ ያልተከፋፈለ ጥቅም/ባለቤትነትን፣ ወይም በተወሰኑ ፕሮጀክቶች ወይም ልዩ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ንብረቶች ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንትን የሚያረጋግጡ  እኩል ዋጋ ያላቸው  የኢንቨስትመንት የምስክር ወረቀቶች ወይም ሰነዶች ናቸው፡፡

96. "የሱኩክ ጨረታ" ማለት ፈላጊ ኢንቨስተሮች በጨረታ ውድድር አማካኝነት ሱኩክን ለሕዝብ የሚያቀርቡበት እና የሚሸጡበት ሂደት ነው፡፡ ይህ ዘዴ “የሕዝብ አቅርቦት” ተብሎም ይጠራል፡፡

97. "ሱኩክ ኢጃራህ" ማለት በተከራየው ሀብት እና/ወይም አላባ እና/ወይም በአገልግሎቶች ላይ እንዲሁም ከተጠቀሰው የተከራየው ሀብት እና/ወይም ጥቅም እና/ወይም አላባ እና/ወይም አገልግሎቶች ላይ የሚገኘውን የኪራይ ገቢ የመቀበል የባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጡ የኢንቨስትመንት የምስክር ወረቀቶች ወይም እኩል ዋጋ ያላቸው ሰነዶች ናቸው።

98. "ሱኩክ ሙዳራባህ" ማለት በሙዳራባህ ሥራ ውስጥ የምስክር ወረቀቶችን የያዙት አካላት ያልተከፋፈለ ባለቤትነት ያላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጡ እኩል ዋጋ ያላቸው የኢንቨስትመንት የምስክር ወረቀቶች ወይም ሰነዶች ናቸው።

99. "ሱኩክ ሙሻራካህ" ማለት በሙሻራካ (ሽርክና) ሥራ ውስጥ የምስክር ወረቀቶችን የያዙት አካላት ያልተከፋፈለ ባለቤትነት ያላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጡ እኩል ዋጋ ያላቸው የኢንቨስትመንት የምስክር ወረቀቶች ወይም ሰነዶች ናቸው።

100. "የግብይት አባል" ማለት በገበያው ላይ የተመዘገቡትን አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመገበያየት ከገበያው የአባልነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው አካል ነው።

101. "ሰልጣኝ ነጋዴ" ማለት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ለመሆን ስልጠና እየወሰደ ያለ ግለሰብ ነው።

102. "ግብይት" ማለት የገንዘብ ድጋፍ መስጠት ወይም መቀበል፣ ወይም መግዛት፣ መሸጥ ወይም ማከራየት፣ ወይም አገልግሎቶች መስጠት ወይም መቀበል፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ማውጣት ወይም መግዛት፣ የምርጫ መብት መስጠት ወይም መቀበል፣ እንዲሁም በመደበኛ የንግድ እንቅስቃሴ ቢሆንም ባይሆንም፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ (ለምሳሌ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የተጣላለፉ ድርጅቶች በኩል) የጋራ የንግድ ሥራዎች ወይም የጋራ ኢንቨስትመንቶች መመስረትን ያካትታል።

103. "በፈቃደኝነት ከምዝገባ መሰረዝ" ማለት በዚህ ረገድ በገበያው የተቀመጡትን አግባብነት ያላቸው መስፈርቶች ካሟላ በኋላ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን በያዙት በሕግ የተወሰነውን አስፈላጊ ቁጥር ያላቸው ባለቤቶችን ግልጽ ፈቃድ በማግኘት የአውጪውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ ውስጥ ማስወገድ ነው።

## 1.3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ አውጪዎች እና የግብይት አባላት ከገበያው ጋር ባላቸው ግንኙነት፣ እርስ በርስ በሚኖራቸው ግንኙነት፣ እንዲሁም በገበያው፣ አውጪዎችና የግብይት አባላት ሆነው ከሌሎች አካላትና ከሕዝቡ ጋር በሚያደርጉት የግብይት ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ 2 - የደንብ አስተዳደር እና ስምምነቶች

## 2.1. የደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የአሰራር ስርዓቶች እና ሌሎች ሰነዶች አስተዳደር እና አተገባበር

(1) በገበያው ላይ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይትን እና የግብይት አባላቱን ተግባራት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን እና ሌሎች ሰነዶችን ገበያው ያወጣል፣ ያስተዳድራል፤ እንዲሁም በዚህ ረገድ ሁሉንም ሥልጣኖች፣ ኃላፊነቶች እና ውሳኔዎችን ይተገብራል፡፡

(2) ከባለስልጣኑ አስቀድሞ ፈቃድ በማግኘት፣ የቁጥጥር ተግባራትን ወይም አስፈላጊ የሚሆኑ ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ፈቃድ ለሚሰጠው ማንኛውም አካል ወይም ተቋም ገበያው ስልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል የመወከል መብት አለው፡፡

(3) ሁሉም አውጪዎች እና የግብይት አባላት ደንቦቹን፣ መመሪያዎቹን፣ የአሰራር ስርዓቶቹን እና ሌሎች ሰነዶችን የማክበር እና በነዚህ መሰረት የመሥራት፣ እንዲሁም እነሱ ወይም ሌላ አካል የሚፈጽሙትን ማንኛውንም ጥሰት ወዲያውኑ ለገበያው የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

(4) የግብይት አባላት የሚከተሉትን መፈፀም አለባቸው፡-

ሀ) በአዋጁ እና ባለስልጣኑ ወይም ሌሎች ተዛማጅ የቁጥጥር አካላት በየጊዜው በሚያወጧቸው ማናቸውም የህግ ማዕቀፍ ድንጋጌዎች መሰረት ሥራቸውን በጥብቅ ማከናወን፤

ለ) በገበያው ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የአሰራር ስርዓቶች እና ሌሎች ሰነዶች ድንጋጌዎች መሰረት ሥራቸውን በጥብቅ ማከናወን፣

ሐ) በሚመለከተው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ፣ ክፍያ አጣሪ እና ፈፃሚ ወገን ወይም የተመሳሳዩን ወገን ደንቦች እና መመሪያዎች ድንጋጌዎች መሰረት ሥራቸውን በጥብቅ ማከናወን፣

መ) በየጊዜው በሚተገበሩ ማናቸውም ልምዶች፣ ስምምነቶች፣ አጠቃቀሞች እና ሌሎች ተዛማጅ ደንቦች መሰረት ሥራቸውን በጥብቅ ማከናወን፤ እና

ሠ) ከገበያው እንቅስቃሴዎች ጋር ምንም ግንኙነት በሌላቸው ተግባራት የገበያውን ስም ወይም የገበያውን አባልነት መብት ከመጠቀም መቆጠብ።

## 2.2. ደንብን ስለመተው ወይም ማሻሻያ ስለማድረግ

(1) በተቃራኒ ሁኔታ በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር እና የባለሥልጣኑን ፈቃድ በማግኘት፣ ገበያው ልዩ ሁኔታዎች ለማስተናገድ አንድን ደንብ ተፈፃሚ እንዳይሆን ለመተው ወይም ማሻሻያ ሊያደርግ ይችላል።

(2) ደንብን ተፈፃሚ እንዳይሆን መተው ወይም ማሻሻያ ተፈፃሚ የሚሆነው የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው።

(3) ደንብን ተፈፃሚ ላለማድረግ ሲወሰን ወይም ማሻሻያ ሲፈቀድ፣ ገበያው በተቻለ ፍጥነት ደንብ ተፈፃሚ አለመደረጉን ወይም ማሻሻያውን ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት። ሆኖም በዚህ ረገድ በገበያው የተሰጠ ውሳኔ ለሚመለከተው አካል አለማሳወቅ ደንብን ተፈፃሚ ላለማድረግ ወይም ማሻሻያ ለማድረግ በተሰጠው ውሳኔ ተፈፃሚነት ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም።

(4) የዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (1) ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ ገበያው በአዋጁ ወይም በደንቦቹ የተሰጡትን ማንኛውንም መብቶች ያልተጠቀመ ወይም ያላስፈጸመ እንደሆነ መብቶቹን እንደተወ አይቆጠርም ወይም በማንኛውም ጊዜ ለመጠቀም ወይም ለማስፈፀም በይርጋ ሊታገድ አይችልም።

(5) በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣ አንድ የግብይት አባል የደንቦቹን መጣስ ወይም አለመፈጸም ወይም በደንቦቹ መሰረት ያለውን ጥፋት ወይም ግዴታን አለመወጣት ተከትሎ የሚገኝ መብትን አለመጠቀም ወይም መብቱን ለመጠቀም መዘግየትን መብቱ እንደተተወ ለመቁጠር አይችልም።

## 2.3. በተጠቀሱ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ የሕግጋት ስብስብ፣ ሰንጠረዦች ወይም ሌሎች ሰነዶች ላይ ስለሚደረጉ ማሻሻያዎች

በእነዚህ ደንቦች የተጠቀሱ ማንኛውም የኢትዮጵያ ሕጎች ወይም የአስተዳደር ኤጀንሲዎች ያወጧቸው መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ የሕግጋት ስብስብ ወይም የአሠራር መመሪያዎች በየጊዜው

በእነዚህ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ የሕግጋት ስብስብ፣ ሰንጠረዦች ወይም ሌሎች ሰነዶች ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን ይጨምራል።

## 2.4. የደንቦች፣ የአሰራር ሂደቶች እና ሌሎች ሰነዶች አተረጓጎም

ገበያው ያወጣቸው እነዚህ ደንቦች፣ የአሰራር ሂደት እና ሌሎች ሰነዶች ላይ የትርጉም ማብራሪያን የሚሰጠው የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ቦርዱ ፈቃድ የሰጠው ማንኛውም ኮሚቴ፣ ሰው፣ አካል ወይም ተቋም ነው።

## 2.5. በመጽሐፈ ደንቡ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

እነዚህ ደንቦች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እና በቁጥጥር ማዕቀፉ ለውጦች ወይም አዳዲስ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በየጊዜው ሊሻሻሉ ይችላሉ። በእነዚህ ደንቦች ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች የባለስልጣኑ ይሁንታ ከተገኘ በኋላ እና ለአውጪዎች ወይም ለግብይት አባላት ቅድሚያ ማስታወቂያ ከተነገረ በኋላ ተግባራዊ ይደረጋሉ።

## 2.6. ለጽሑፍ እና ለግንኙነት ስለሚውል ቋንቋ

ለገበያው የሚቀርቡ ሁሉም ማመልከቻዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ ሌሎች ግንኙነቶች እና ሰነዶች በእንግሊዝኛ እና/ወይም በአማርኛ ቋንቋዎች መሆን አለባቸው። ለገበያው የሚቀርበው ማንኛውም መረጃ እና/ወይም ሰነድ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጀ ከሆነ፣ ከእንግሊዝኛ እና/ወይም አማርኛ የተረጋገጠ የተተረጎመ ቅጂው ጋር መቅረብ አለበት።

## 2.7. አጠቃላይ ስነ-ምግባር፣ አሰራር እና ይፋ የማድረግ ግዴታዎች

(1) ማንኛውም አውጪ፣ የግብይት አባል፣ ሠራተኞቹ፣ ኃላፊዎቹ፣ ዳይሬክተሮቹ ወይም ተባባሪ ሰዎች የገበያው መልካም ስም ወይም ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ማንኛውንም ድርጊት፣ ተግባር ወይም ጉዳይ መፈፀም ወይም በሌላ አካል እንዲፈጸም ማድረግ የለባቸውም።

(2) በገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ልዩ ሥልጣን ተሰጥቶት የሚሠራ የግብይት አባል ወይም አካል ካልሆነ በስተቀር፣ ማንኛውም የግብይት አባል ወይም ሌላ አካል የገበያው ወኪል ወይም እንደራሴ ወይም በማናቸውም መንገድ ለገበያው እንደሚሰራ ወይም ገበያውን ለማስገደድ የሚችል ሥልጣን ያለው አድርጎ ለየትኛውም ሰው ራሱን ማሳየት የለበትም።

(3) ሁሉም የግብይት አባላት ከገበያው ጋር በግልጽ እና በትብብር መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ገበያው በተገቢው ሁኔታ ማስታወቂያ እንዲሰጠው በሚጠብቅባቸው የገንዘብም ሆነ የገንዘብ ነክ ያልሆኑ ተግባሮቻቸው እና እንቅስቃሴዎቻቸው ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ጉዳይ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

(4) ማንኛውም የግብይት አባል በሥራው ወቅት የሚያገኘውን ማንኛውንም እውቀት ወይም መረጃ አላግባብ መጠቀም የለበትም፣ እንዲሁም ሠራተኞቹ ይህንን እንዲያከብሩ ማረጋገጥ አለበት።

## 2.8. የንግድ ሰነዶች መለያ

(1) አንድ የግብይት አባል በሁሉም የደብዳቤ ራስጌዎች፣ የውል ማስታወሻዎች፣ ብሮሸሮች፣ የገንዘብ ደረሰኞች ወይም የግብይት አባልነቱን በተመለከተ በሁሉም ለግብይት በሚጠቀምባቸው ሌሎች ሰነዶች ላይ "የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የግብይት አባል" የሚሉ ቃላት እንዲታተምባቸው ማድረግ አለበት።

(2) ድርጅት የሆነ እያንዳንዱ የግብይት አባል ቢያንስ የሚከተሉትን በሁሉም የደብዳቤ ራስጌዎች ላይ እንዲታተሙ ማድረግ አለበት ፡ -

(ሀ) የድርጅት/የንግድ ስም፤

(ለ) የዋና መሥሪያ ቤቱ አድራሻ፤

ሐ) የምዝገባ ቁጥር፤ እና

(መ) የድርጅት ኢሜይል አድራሻ እና የስልክ ቁጥርን ጨምሮ የሚሰሩ እና ትክክለኛ የመገናኛ መንገዶችን ዝርዝር።

ሠ) እንደ አስፈላጊነቱ አርማ።

(3) ሁሉም የግብይት አባላት በገበያው የተሰጣቸውን የአባልነት የምስክር ወረቀት በዋና መሥሪያ ቤቶቻቸው እና ቅርንጫፎቻቸው እና በድረ ገጻቸው በሚታይ ቦታ ላይ ማሳየት አለባቸው።

## 2.9. የተጠያቂነት ገደብ

(1) ገበያው፣ ተዛማጅ ኩባንያዎቹ፣ የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል የሚያስተላልፍለት ማንኛውም ሰው፣ አካል ወይም ተቋም፣ ወይም የእነሱ ዳይሬክተሮች፣ ባለስልጣኖች፣ ሰራተኞች ወይም ወኪሎች ምንም እንኳን እንደዚህ ዓይነት ኪሳራ ወይም ጉዳት ሊያስከትል ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊኖር እንደሚችል ቢገለፅም፣ በማንኛውም መንገድ ቢከሰትም ወይም ቢነሳም፤ ለሚደርስ ኪሳራ ወይም ጉዳት ተጠያቂ አይሆኑም። በተጨማሪም በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን ከሚከተሉት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚነሳ ወይም እነዚህን ተከትሎ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ምክንያት ለተከሰተ ማንኛውም ኪሳራ ወይም ጉዳት ለማንኛውም ሰው ተጠያቂ አይሆኑም:-

(ሀ) በአዋጁ፣ በማንኛውም ተፈጻሚነት ባለው ሕግ ወይም በእነዚህ ደንቦች መሰረት የገበያውን ግዴታዎች ወይም መብቶች ለማስፈጸም ወይም ለማስፈጸም በሚል የተደረገ (የተሰጠ መግለጫን ጨምሮ) ወይም ያልተደረገ ማንኛውም ነገር፤

ለ) በምንም ዓይነት ምክንያት የግብይት ስርዓቱ ላይ ለሚደርስ ማንኛውም መቋረጥ፣ ስህተት፣ መዘግየት ወይም ብልሽት፤

(ሐ) ወደ ግብይት ስርዓቱ መግባት ፣ መጠቀም ወይም መጠቀም አለመቻል፤

(መ) በገበያው ስር በተደራጁ ገበያዎች ላይ የሚደረግ ግብይት ወይም በምንም ዓይነት ምክንያት በእነዚህ የተደራጁ ገበያዎች ላይ የሚደረግ ግብይት መታገድ፣ መቋረጥ፣ መሰረዝ፣ መገደብ ወይም መዘጋት፤

(ሠ) ለግብይት አባል በተሰጠ መሣሪያ፣ ሶፍትዌር ወይም ሌሎች ምርቶች ላይ በምንም ዓይነት ምክንያት የሚከሰት ማንኛውም ብልሽት፣ የደህንነት ጥሰት፣ አለመሥራት ወይም ተገቢ ያልሆነ አሠራር፣ ወይም ከመጫኑ፣ ከመጠገኑ ወይም ከማስወገዱ ጋር በተያያዘ ችግር ቢፈጠር፤

(ረ) በእነዚህ ደንቦች የተሰጠ ውሳኔ የመስጠት ወይም የቁጥጥር ስልጣን ወይም ፍቃድ ስልጣን አጠቃቀም፤

(ሰ) የስህተት ግብይትን ለመሰረዝ ወይም ላለመሰረዝ በእነዚህ ደንቦች መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ፤

(ሸ) የግብይት አባል የአባልነት የምስክር ወረቀትን ለመመለስ ያቀረበውን ጥያቄ ወይም የሚመለከተው የዲሲፕሊን ወይም የፍርድ አካል ስልጣናቸውን ተጠቅመው የሚሰጡት ማንኛውም ውሳኔ ወይም ፍርድ መቀበል፤

(ቀ) ቫይረስ ወይም ማንኛውም ሌላ አጥፊ፣ መጥፎ ወይም የሚያበላሽ ፕሮግራም፣ ኮድ፣ ኤጀንት ፣ ስክሪፕት ወይም ማክሮ፤

(በ) ለማንኛውም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ውል ዋጋዎችን በማስላት፣ በመወሰን ወይም በማሰራጨት የሚከሰቱ ማንኛቸውም ስህተቶች፣ ትክክለኛ አለመሆን፣ ግድፈቶች ወይም መዘግየት፤

(ተ) የግብይት ስርዓቱ ወይም ማንኛውም ይዘቱ እውነተኝነት፣ ትክክለኛነት፣ በቂነት፣ ወቅታዊነት ወይም ምሉዕነት። በዚህ አውድ ውስጥ ይዘት ማለት ለዕይታ የቀረቡ ማንኛቸውም መረጃዎች፣ ቁሳቁሶች፣ ምስሎች፣ ድምፆች፣ ግራፊክስ፣ ቪዲዮ እና ሌሎች ቁሳቁሶች ወይም የተሰጡ ማንኛቸውም መገልገያዎች ወይም መተግበሪያዎች፣ ፕሮግራሞች ወይም አገልግሎቶች ማለት ነው።

(ቸ) በግብይት ስርዓቱ ይዘት ወይም በማንኛውም ክፍሉ ላይ የሚኖር መተማመን፤

(ነ) የግብይት ስርዓቱን በመጠቀም ጨምሮ በገበያው ወይም በግብይት አባል በኩል የሚተላለፍ ወይም እነሱ ወይም እነሱን በመወከል የሚቀበሉት ማንኛውም መረጃ፣ ወይም ባልተፈቀደላቸው ሰዎች እንዲህ ያለውን መረጃ ማግኘት ወይም መጠለፍ፤ ወይም

(ኘ) በአዋጁ እና በካሳ ፈንድ ደንቦች እና በባለስልጣኑ መመሪያዎች መሠረት ገበያው በካሳ ፈንድ በኩል ካለበት የካሳ ግዴታዎች በስተቀር፣ በገበያው ግብይት ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው።

(2) የዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ ቁጥር (1) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የሚከሰት ብልሽት አንድ የግብይት አባል ተሳታፊ በሆነባቸው ማንኛቸውም ግብይቶች ላይ ያለውን ተጠያቂነት አይቀንስም፣ አይለውጥም ወይም አይቀይርም።

(3) የዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ ቁጥር (1) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ገበያው፣ ተዛማጅ ኩባንያዎቹ፣ በደንብ 2.1. (3.) የተጠቀሰ ማንኛውም ሰው ወይም አካል ወይም የእነሱ ዳይሬክተሮች፣ ባለሥልጣኖች፣ ሠራተኞች ወይም ወኪሎች፡

(ሀ) በግልጽም ሆነ ባልተገለጸ መንገድ ማንኛውንም ዋስትና አይሰጡም፤ ወይም

(ለ) ከሚከተሉት ውስጥ ከማንኛውም ጋር በተያያዘ ለማንኛውም ሰው ተጠያቂ አይሆኑም፡-

vii. ስለገበያ ሁኔታ አመላካች ወይም ስለዋጋ እውነተኛነት፣ ትክክለኛነት፣ በቂነት፣ ወቅታዊነት ወይም ሙሉነት፤

viii. በውሎች ወይም በአማራጮችመልክ ቢሆንም ከገበያ ሁኔታ አመላካች ወይም ከዋጋው ጋር የተገናኘ ወይም የተዛመደን ማንኛውንም ሰነድ በተመለከተ የገበያ ሁኔታ አመላካችን ወይም ዋጋን በመጠቀም ስለተገኙ ውጤቶች፤

ix. የአንድ የገበያ ሁኔታ አመላካች ወይም ዋጋ ለንግድ አመቺ ስለመሆኑ እና ለአንድ የተወሰነ ዓላማ ወይም አጠቃቀም ብቁ ስለመሆኑ፤

x. እንደዚህ ዓይነት ጉዳቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ማስታወቂያ የተሰጠ ቢሆንም እንኳ፣ ለማንኛውም ቀጥተኛ፣ ልዩ፣ የቅጣት ውጤት ላለው፣ ቀጥተኛ ላልሆነ ወይም ለተከታይ ጉዳት (የጠፋ ትርፍን ጨምሮ)፤

xi. አንድን የገበያ አመላካች ወይም ዋጋን በማስላት ወይም በማሰራጨት ለሚፈጠሩ ማንኛቸውም ስህተቶች፣ ግድፈቶች ወይም መዘግየቶች፤ እና

xii. በውሎች ወይም በአማራጭ መልክ ቢሆንም ከገበያ አመላካች ወይም ከዋጋው ጋር የተገናኘ ወይም የተዛመደ ማንኛውም ሰነድ ላይ ግብይት መፈጸም፡፡

(4) ለዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ ቁጥር (3) ዓላማ፣ የገበያ አመላካች የሚለው ማጣቀሻ የገበያ አመላካቹን ማስተዳደርን፣ መፍጠርን፣ ማስላትን፣ ማሰራጨትን ወይም ማጠናቀርን፣ ወይም ከእሱ ጋር የተገናኙ ወይም ሊጠቀሱ የሚችሉ ማናኛቸውንም የውስጠ-ቀን ተኪዎች ወይም በእሱ ውስጥ የተካተቱ ወይም ሊጠቀሱ የሚችሉ ማንኛቸውንም መረጃዎችን ወይም ጥንቅሮችን ያጠቃልላል፡፡

(5) እያንዳንዱ የግብይት አባል በገበያው ሥር በሚገኙ ገበያዎች ላይ የመገበያየት መብትን በሚሰጡ ውሎች ውስጥ በማካተት ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ ደንበኞቹ በዚህ ደንብ በተደነገጉት የተጠያቂነት ገደቦች እንደሚስማሙ እና እንዲያከብሩ ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 2.10. ለገበያው ስለሚቀርብ ካሳ

(1) በግብይት አባሉ እንቅስቃሴዎች ምክንያት ካሳ በተገባላቸው አካላት ለሚደርሱ ኪሳራዎች እና/ወይም ካሳ በተገባላቸው አካላት ላይ ለሚፈጠሩ ማንኛቸውም እዳዎች እያንዳንዱ የግብይት አባል ለገበያው፣ ለተዛማጅ ኩባንያዎቹ፣ በደንብ ቁጥር 2.1.(3.) ለተጠቀሰ ማንኛውም ሰው ወይም አካል እና ለእነሱ ዳይሬክተሮች፣ ባለሥልጣኖች፣ ሠራተኞች ወይም ወኪሎች ካሳ መክፈል አለበት፡፡

(2) ለሚከተሉት ሁኔታዎች እያንዳንዱ የግብይት አባል ለእያንዳንዱ ካሳ ለተገባለት አካል ካሳ ይከፍላል፡-

(ሀ) ከግብይት አባሉ የሙያ ሥነ ምግባር ጉድለት ለሚመነጩ የህግ ተጠያቂነቶች፤

(ለ) የግብይት አባሉ በደንቦቹ ያሉበትን ግዴታዎቹን በመጣሱ ምክንያት ለሚመጣው ውጤት፤ ወይም

(ሐ) በግብይት አባሉ በፈቃደኛነት፣ በሕገወጥ፣ በግዴለሽነት ወይም በቸልተኛነት ወይም በግድፈት ለሚፈፀም ድርጊት፡፡ሙ

## ምዕራፍ 3 - የገበያው እና የግብይት ክፍያዎች

### 3.1. ክፍያዎችን እና ወጪዎችን የመወሰን እና የመከለስ ስልጣን

(1) የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖሩታል፡-

(ሀ) መጠናቸው በገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው እየተወሰነ እና የባለስልጣኑን ይሁንታ በማግኘት፣ በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ክፍያዎችን እና ወጪዎችን የመወሰን እና/ወይም የማሻሻል፤

(ለ) እነዚህ ክፍያዎች እና ወጪዎች በአውጪዎች፣ በግብይት አባላት ወይም በሌሎች ሰዎች እንዲከፈሉ መጠየቅ እና የክፍያውን ጊዜ እና የአከፋፈል ዘዴ መወሰን፡፡

(2) እያንዳንዱ አውጪ፣ የግብይት አባል ወይም ሌሎች ሰዎች ከዚህ መጽሐፈ ደንብ ጋር አባሪ በሆነው በገበያው የክፍያ ሰንጠረዥ ወይም በገበያው ማንኛውም ሌላ ሰነድ በተገለጸው መንገድ ክፍያዎቹን መፈጸም አለባቸው፡፡

### 3.2. የአባልነት ቅበላ እና የተሳትፎ ክፍያዎች

(1) የባለስልጣኑን ይሁንታ በማግኘት የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ለእያንዳንዱ የግብይት አባል መክፈል ያለባቸውን የአባልነት ቅበላ እና ተሳትፎ ክፍያዎች በየጊዜው ይወስናል፡፡

(2) ማንኛውም የግብይት አባል ለገበያው መክፈል የሚገባውን ማንኛውንም ክፍያ በወቅቱ ያልከፈለ እንደሆነ በአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ የተገለጹት ቅጣቶች ተፈፃሚ ይሆኑበታል፡፡

(3) ማንኛውንም ክፍያ/ክፍያዎች ባለመክፈሉ ምክንያት በማንኛውም የግብይት አባል ላይ የተጣለ የአባልነት እገዳ ወይም የገበያ ከፋችነት ስያሜ ላይ በጊዜያዊነት የተደረገ መቋረጥ ሊነሳ የሚችለው ከተጠራቀሙት ቅጣቶች በተጨማሪ ለገበያው የሚገባውን ክፍያ ሲከፍል ብቻ ነው፡፡

### 3.3. ለግብይት አባላት የሚከፈሉ የድለላ ክፍያዎች እና ኮሚሽኖች

(1) በማንኛውም ግብይት (ግዢ ወይም ሽያጭ) ላይ የተፈቀደው ከፍተኛው የድለላ ክፍያ እና ኮሚሽን ገበያው በየጊዜው በሚወስነው እና በባለስልጣኑ በሚጸድቀው መጠን ይሆናል፡፡

(2) የዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ ቁጥር (1) ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ በገበያው ላይ ከተመዘገቡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር የተያያዘ ተጨማሪ አገልግሎት ሲሰጥ፣ የግብይት አባል ለእነዚህ አገልግሎቶች ገበያው በየገዜው በሚወሰነው

እና በባለስልጣኑ በሚጸድቀው መጠን ብቻ ተጨማሪ ክፍያዎችን እንዲያስከፍል ይፈቀድለታል፡፡

(3) ሁሉም የድለላ ክፍያዎች እና ኮሚሽኖች በተናጠል በደንበኞች ይከፈላሉ፡፡

### 3.4. የግብይት ክፍያዎች

(1) በገበያው በተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ለሚደረግ እያንዳንዱ ግብይት በገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ የተወሰነው እና በባለስልጣኑ የጸደቀው የግብይት ክፍያ ለገበያው ይከፈላል፡፡

(2) ለገበያው የሚከፈሉ ሁሉም የግብይት ክፍያዎች በሚመለከተው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት፣ ክፍያ እና ርክክብ ፈፃሚ ወገን ወይም በተመሳሳዩ ከምንጩ ተቀንሰው ለገበያው መላክ አለባቸው፡፡

# ቅጽ ለ: የአባልነት ደንቦች

# ክፍል 1 —የግብይት አባላት

## *ምዕራፍ 1 — የግብይት አባላት ዕውቅና አሰጣጥ እና አመዳደብ*

### 1.1 አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መጽሐፈ ደንብ፣ 2017 (የአባልነት ደንቦች)" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1.2. የተፈፃሚነት ወሰን

በዚህ ቅጽ የተደነገጉት ደንቦች የግብይት አባላት ከገበያው ጋር ባላቸው ግንኙነት፣ የግብይት አባላት እርስ በርስ በሚኖራቸው ግንኙነት፣ እንዲሁም በገበያው የግብይት አባላት ሆነው ከሌሎች አካላትና ከሕዝቡ ጋር በሚያደርጉት የግብይት ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 1.3. የግብይት አባላት ምድቦች

(1) የግብይት አባልነት በሚከተሉት ምድቦች ይሰጣል፦

*ሀ)* የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ፤

*ለ)* የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አከናዋኝ፤

*ሐ)* የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ከፋቾች፤

*መ)* የኢንቨስትመንት ባንክ (የሰነደ ሙዓለንዋዮች ደላላ እና/ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አከናዋኝ ሆኖ እንዲሰራ የተፈቀደለት)፤

*ሠ)* በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንደ ባንክ የተመዘገበ፣ የመንግስት ሰነደ ሙዓለንዋዮችን በራሱ ሂሳብ ግብይት የሚያከናውን፣ እና በሌሎች ቋሚ የገቢ ገበያ ሰነዶች ላይ ለመገበያየት በባለሥልጣኑ ፈቃድ ያገኘ ግብይት አከናዋኝ አባል ባንክ፤

*ረ)* በባለሥልጣኑ መስፈርቶች መሠረት ገበያው በየጊዜው የሚለያቸው ማናቸውም ሌሎች ምድቦች፡፡

(2) ከላይ የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ገበያው የባለስልጣኑን ፈቃድ በማግኘት አስፈላጊ ናቸው ለሚላቸው የገበያው የተለያዩ ምድቦች ፍላጎት ላላቸው እና ብቁ ለሆኑ አካላት ለመስጠት እንዲችል በየጊዜው የአባልነት የምስክር ወረቀቶችን ሊመደብ ይችላል፡፡

(3) ገበያው የዲጂታል ንዑስ ደላላን በአባልነት አይቀበልም፣ እንዲሁም የገበያው የግብይት አባል ተደርጎ አይቆጠርም፡፡

(4) አንድ የግብይት አባል ገበያው ባስቀመጣቸው መለኪያዎች እና ገደቦች እና በባለስልጣኑ የፈቃድ ወይም የምዝገባ መመሪያዎች ወይም መስፈርቶች መሰረት መስራት አለበት፡፡

(5) እያንዳንዱ የግብይት አባል ገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚደነግጋቸውን ዝቅተኛ የአሠራር መስፈርቶችን እና መመዘኛዎችን ለሚከተሉት ማሟላት አለበት፦

ሀ) ሠራተኞች፤

ለ) ድርጅታዊ መዋቅር፤

ሐ) አስተዳደር፤

መ) ቴክኖሎጂ፤

ሠ) መሠረተ ልማት፤

ረ) ፖሊሲዎች እና ሂደቶች፤ እና

ሰ) ተወዳዳሪነት፡፡

## ምዕራፍ 2 ፦ የግብይት አባል ቅበላ ሂደቶች

### 2.1. አባላትን የመቀበል ስልጣን

1) በእነዚህ ደንቦች ድንጋጌዎች መሠረት አባላትን የመቀበል ብቸኛ ስልጣን ያለው ገበያው ይሆናል፡፡

2) የአባልነት ቅበላ ያገኘ አካል ፍትሃዊና ትክክለኛ የገበያ አሠራርን በሚደግፉ ግብይቶች ላይ ብቻ መሳተፍ አለበት፡፡ ገበያው አንድን የግብይት አባል በማንኛውንም ጉልህ ወይም ቀጣይነት ያለው ጥሰት ላይ ሲሳተፍ ካገኘው የግብይት አባሉን ፈቃድ ሊያግድ እና/ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

### 2.2. ለአባልነት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1) የአባልነት ማመልከቻው ገበያው በሚጠይቀው ሁኔታ መሰረት መቅረብ አለበት፡፡

2) በባለስልጣኑ ፈቃድ ያገኘ ወይም ፈቃድ ለማግኘት በሂደት ላይ ያለ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም በባለስልጣኑ ፈቃድ ያገኘ ግብይት አከናዋኝ አባል ባንክ ለአባልነት ማመልከቻ ለማቅረብ ብቁ ናቸው፡፡

3) አንድ አመልካች የአባልነት ቅበላ መስፈርቶችን ሲያሟላ፣ ገበያው የአመልካቹን ማመልከቻ በመርህ ደረጃ ያፀድቅለታል እና ይህ ለስድስት (6) ወራት ወይም በገበያው ሊወስን በሚችል አጭር ወይም ረዘም ላለ ጊዜ ብቻ የፀና ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ አመልካቹ ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን እንዲያጠናቅቅ ይጠበቃል፡፡

4) በመርህ ደረጃ የፀደቀ ወደ ሙሉ አባልነት የሚለወጠው ገበያው የብቃት ማረጋገጥ ምርመራ አካሂዶ አመልካቹ ሥራውን ለመጀመር ሁሉንም መስፈርቶች እንዳሟላ ሲያረጋግጥ ነው።

5) እንደ የግብይት አባል ሥራዎችን ለመጀመር የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከተሟሉ በኋላ የአባልነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

## 2.3. በመርህ ደረጃ የማፅደቅ መስፈርቶች

(1) ለአባልነት የሚያመለክት ማንኛውም የንግድ ድርጅት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፦

ሀ) የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ ያለው ወይም የግብይት አባል ባንክ ሆኖ እንዲሠራ ከባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ወይም ለእነዚህ ፈቃድ ለማግኘት በሂደት ላይ የሆነ ፤

ለ) አባል በሆነበት አገልግሎቶች ላይ የግብይት ሥራ ለማካሄድ ሙያዊ እና የቴክኒክ አቅም ያለው፤

ሐ) በእነዚህ ደንቦች ውስጥ የተደነገጉትን የብቃት መመዘኛዎች ሚሟላት፤ እና

መ) ማመልከቻውን የሚደግፉ አስፈላጊ ሰነዶችን ማቅረብ።

(2) አመልካቹ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፦

ሀ) አግባብነት ባለው የመንግስት አካል የተሰጠ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና/ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅጂ፤

ለ) የግብር መለያ ቁጥር ቅጂ፤

ሐ) በባለስልጣኑ የተሰጠ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ ቅጂ፤

መ) እንደ አግባብነቱ ባለአክሲዮኖችን፣ ዳይሬክተሮችን ወይም አጋሮችን እና ማመልከቻው በቀረበበት ቀን የአመልካቹን ካፒታል የሚያሳይ የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍ እና ማሻሻያዎችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን የመመስረቻ ሰነዶች፤

ሠ) አመልካቹ የንግድ ድርጅትን እንደ ኢንቨስተር ወይም እንደ ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን ያካተተ ከሆነ፣ ማመልከቻው በቀረበበት ቀን የእንደዚህ ዓይነቱ ባለአክሲዮን ባለቤትና ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰቦችን ዝርዝር የሚገልጽ አግባብነት ያለው የመመስረቻ ወይም የድርጅት ሰነድ፤

ረ) በአመልካች የንግድ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ግለሰቦች እና አካላት ዝርዝር፤

ሰ) የግብይት አባልነት ለማግኘት የተላለፈው ውሳኔ የፀደቀበት የቦርድ ቃለ ጉባኤ፤

ሸ) የዳይሬክተሮች ቦርድ አወቃቀር እና የፈቃድ ጥያቄ የቀረበባቸው ወይም ፍቃድ የተሰጣቸውን ተሿሚ እንደራሴዎች የሚያካትት የአመልካቹ የድርጅት መገለጫ፤

ቀ) እንደአግባብነቱ የአመልካቹ የቦርድ ቻርተር፤

በ) ሌሎችን ጨምሮ የንግድ ድርጅቱን የረጅም ጊዜ ዓላማዎችን እና ወደፊት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶችን የሚገልጽ የአመልካቹ የንግድ ስትራቴጂ እና ዓላማዎችን ያካተተ የንግድ እቅድ፤

ተ) የተጠሪነት እና የኃላፊነት ሰንሰለቶችን በግልጽ የሚያሳይ የአመልካቹ ድርጅታዊ መዋቅር፤

ቸ) ከፍተኛ የሥራ አስፈፃሚ መኮንኖች አስፈላጊው ሙያዊ ብቃት ያሏቸው ስለመሆኑ እና ማመልከቻው በሚቀርብበት ጊዜ ገበያው በሚገልፀው እና በሥራ ላይ በሚያውለው መሠረት የፈቃድ ጥያቄ የቀረበባቸው ወይም ፈቃድ የተሰጣቸው ተሿሚ እንደራሴዎች ለኃላፊነታቸው ወይም ለሥራቸው የብቁነት እና ተገቢነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤

ኀ) አመልካቹ ወይም ተሿሚ እንደራሴዎቹ የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለባቸው፦

i. ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማንኛውንም ገንዘብ በተሳሳተ መንገድ ያላስተዳደሩ እና ያለፈቃድ የሀብት ማጣራት ሂደት ወይም በተቆጣጣሪ አካል የኩባንያ ስረዛ ውስጥ ያላለፉ ስለመሆኑ፤

ii. ኪሳራ የታወጀበት የንግድ ሥራ ባለቤት፣ አጋር፣ ዳይሬክተር ወይም ቁልፍ ሠራተኞች አለመሆናቸውን፤

iii. ከማጭበርበር፣ ከስርቆት፣ ከእምነት ማጉደል፣ ገበያን ያለ አግባብ ከመጠቀም ወይም ከሀሰተኝነት ጋር በተያያዘ በወንጀል ያልተፈረደባቸው ወይም በሂደት ላይ ባሉ የወንጀል ክሶች ውስጥ ተሳታፊ አለመሆናቸውን፤

iv. ከማጭበርበር ወይም ሐሰተኝነት ጋር በተያያዘ እንደ ኢንቨስትመንት አማካሪ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት አከናዋኝ፣ ዳይሬክተር ወይም የፋይናንስ ተቋማት ሠራተኞች እንዳይሆኑ እና በማንኛውም የንግድ ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፉ የሚከለክል የማንኛውም ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም የቁጥጥር አካል ትዕዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ያልተላለፈባቸው ስለመሆኑ፤

v. ከማንኛውም የሙያ ማህበር፣ ድርጅት ወይም ከማንኛውም የንግድ ቡድን/ማህበር አባልነት በማናቸውም ምክንያት ያልተባረሩ ወይም ያልተሰረዙ ስለመሆኑ ወይም የሥራ ፈቃዳቸው ተሰዘርዞባቸው የማያውቅ ስለመሆኑ፤

vi. በአዕምሮ ወይም በአካላዊ ህመም ምክንያት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የሕግ ችሎታ እንዲያጣ ያልተወሰነባቸው መሆኑን፤

vii. ከማንኛውም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አለመባረራቸውን፤

viii. ማመልከቻውን በሚያቀርቡበት ቀን በሥራ ላይ በሚውሉ በገበያው የሚጠየቁ አግባብነት ያላቸውን ክፍያዎች ስለመክፈላቸው፤

ነ) ማመልከቻው በቀረበበት ቀን አመልካቹ የንግድ ስራውን ለአሥራ ሁለት (12) ወራት ወይም ከዚያ በላይ አካሂዶ ከነበረ፣ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን በፊት ላለው የበጀት አመት የፋይናንስ መግለጫዎች፣ እና ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የበጀት ዓመት ካበቃ በኋላ ሶስት (3) ወይም ከዚያ በላይ ወራት ካለፉ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን በፊት እስካለው የወር መጨረሻ ድረስ ያሉት የአስተዳደር ሂሳብ፡፡ ይህም በሕዝብ የሂሳብ አዋቂ በተገቢው ሁኔታ መፈረም አለበት፤

ኘ) ማመልከቻው በቀረበበት ቀን አመልካቹ ሥራውን ያከናወነው ከአሥራ ሁለት (12) ወራት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ማመልከቻው ካቀረበበት ቀን በፊት ባለው ወር መጨረሻ ቀን ድረስ የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ፤

አ) የአመልካቹ የተመዘገበ ጽ/ቤት አድራሻ እና አመልካቹ ሊሠራበት ያሰበውን ማንኛውም ሌላ ጽ/ቤት፤ እና

ከ) የአዋጁን ድንጋጌዎች፣ የባለስልጣኑን መመሪያዎችን፣ የገበያውን ደንቦችን እና ሕጎችን እና ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸው ህጎችን ለማክበር በግብይት አባሉ በኩል የፈቃደኝነት እና የብቃት ማረጋገጫ፡፡

(3) ገበያው የሚከተሉትን ካከናወነ በኋላ በመርህ ደረጃ ማጽደቅን ለአመልካቹ ይሰጣል፦

ሀ) ማመልከቻውን እና ማመልከቻውን ለመደገፍ የቀረቡ ሰነዶች ምርመራ፣ እና

ለ) ከኢንቨስተሮቹ፣ ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ከከፍተኛ ኃላፊዎች ጋር ቃለ ምልልስ ከተደረገ በኋላ፡፡

(4) በመርህ ደረጃ ማጽደቅ ለስድስት (6) ወራት የሚቆይ ሲሆን በዚህ ጊዜ አመልካቹ ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልጉትን ሁሉንም መስፈርቶች

ያሟላል ተብሎ ይጠበቃል በተጨማሪም ሥራውን ለመጀመር ጥያቄውን ለገበያው በጽሁፍ ያቀርባል።

(5) አንድ አመልካች በመርህ ደረጃ ማጽደቅ ከተፈቀደለት በኋላ በ6 (ስድስት) ወራት ውስጥ ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ካላሟላ፣ በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀፅ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ገበያው በራሱ ውሳኔ ከሶስት (3) ወራት ያልበለጠ የጊዜ ማራዘሚያ ይሰጣል፣ ከዚህ ጊዜ በኋላ በመርህ ደረጃ ማጽደቅ ይሰረዛል።

(6) በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀፅ (5) የተደነገጉት ቢኖሩም ጊዜውን ማራዘም ያስፈለገበት ምክንያት ከባለስልጣኑ ያልተጠናቀቁ የሚጠበቁ ሥራዎች ሲኖሩ እና ከነዚህ ሥራዎች ጋር በተያያዘ አመልካቹ ሁሉንም መስፈርቶች/ግዴታዎች እስካሟላ ድረስ፣ ገበያው በመርህ ደረጃ ማጽደቅን ከተጨማሪ ሶስት (3) ወራት በላይ ሊያራዝም ይችላል።

## 2.4. አባል ሥራ እንዲጀመር ስለሚሰጥ ማረጋገጫ

(1) አንድ አመልካች እንደ የግብይት አባል ሥራዎችን ለመጀመር ብቁ ለመሆን የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፦

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እንዲገበያይ በባለስልጣኑ የተሰጠ የፀና የካፒታል ገበያ አገልግሎት ፈቃድ፤

ለ) ተሿሚ እንደራሴ ሆነው ለሚያገለግሉ አስፈላጊ ሰራተኞች ከባለስልጣኑ የተሰጠ የፈቃድ የምስክር ወረቀት ቅጂ፤

ሐ) ማመልከቻው በሚቀርብበት ቀን በአመልካቹ እና በተሿሚ እንደራሴው የተሰጠ የቃለ መኃላ ማረጋገጫ፤

መ) እንደአስፈላጊነቱ ተፈፃሚ የሆኑ የደንበኞችን እወቅ መስፈርቶችን የሚያካትት ግን በነዚህ ያልተገደበ ደንበኞች ሂሳብ የሚከፍቱባቸው ቅፆች ናሙና፤

ሠ) በባለስልጣኑ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፈቃድ እና ቁጥጥር መመሪያ እና ገበያው በእነዚህ ደንቦች እና በሌሎች ንዑስ ሕጎች ባስቀመጠው መሠረት የቴክኖሎጂ እና የአደጋ አያያዝ መስፈርቶችን የሚሟላት ሁኔታ፤

ረ) ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም የዚህ ተመጣጣኝ ጋር ምዝገባ ስለመደረጉ ማስረጃ፤ እና

ሰ) ንግዱን በአግባቡ ለማካሄድ የተዘረጉ የንግድ ስርዓቶች እና ሂደቶች።

(2) አመልካቹ የሚከተሉትን የባንክ ሂሳቦች ስለመክፈቱ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል:-

ሀ) አመልካቹ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት አከናዋኝ በሚሆንበት ጊዜ፣ ከደንበኞች ወይም በደንበኞች ስም ለሚቀበሉት ገንዘብ እና ለደንበኞች ወይም በደንበኞች ስም ለሚከፈል ገንዘብ በግልጽ የተጠቀሰ የደንበኞች የባንክ ሂሳብ፣

ለ) ማመልከቻው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት አከናዋኝ ለመሆን በሚሆንበት ጊዜ፣ ከአመልካቹ ወይም እሱን በመወከል ለሚፈፀሙ የሰነደ ሙዓለንዋይ ግብይቶች በግልጽ የተጠቀሰ የራስ የሆነ የባንክ ሂሳብ፤ እና

ሐ) ከአመልካቹ ወይም በአመልካቹ ስም ለሚቀበሉት ገንዘብ እና ለአመልካቹ ወይም በአመልካቹ ስም ለሚከፈሉት ክፍያዎች በግልጽ የተጠቀሰ ተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሳብ።

(3) አመልካቹ ለሚከተሉት ተገዢ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) ገበያው በእነዚህ ደንቦች ውስጥ ያስቀመጣቸውን ወይም ማመልከቻው በሚቀርብበት ጊዜ ተግባራዊ የሚሆኑ ሌሎች ማናቸውም ደንቦች እና የቁጥጥር መስፈርቶች፤ እና

ለ) ገበያው በየጊዜው የሚወስናቸውን ሌሎች ማንኛቸውንም መስፈርቶች።

(4) ገበያው በአመልካቹ የንግድ እና የአሠራር ወሰን ላይ ገደቦችን ማድረግ ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ሳይገደብ ማመልከቻን ተገቢ መስሎ የሚያታየውን ሁኔታዎች ወይም ገደቦች በማስቀመጥ ሊያፀድቅ ይችላል። ገበያው ማንኛውንም የማፅደቅ ሁኔታ ሲጥል ወይም ሲያነሳ በጽሑፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት።

(5) በዚህ ደንብ ውስጥ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሲያሟላ ገበያው አመልካቹ ሥራውን ለመጀመር ሁሉንም ቅድመ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች ያሟላ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በአመልካቹ ላይ የቅድመ ማረጋገጫ ምርመራ ያካሂዳል ።

(6) የቅድመ ማረጋገጫ ፍተሻ ሁኔታዎች ሲሟሉ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኛል፣ እንዲሁም አመልካቹ ሥራውን ለመጀመር በአባልነት ተቀባይነት ያገኛል።

(7) በአባልነት ተቀባይነት ያገኘው አመልካች አባልነቱ ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን ይገለጽለታል፣ በተጨማሪም ስሙ በግብይት አባላት መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል።

## 2.5. የአባልነት ምስክር ወረቀቶች ላይ የገበያው የባለቤትነት መብት

(1) ገበያው በወጡት በማናቸውም የአባልነት የምስክር ወረቀቶች ላይ ብቸኛ የባለቤትነት መብት ያለው ሲሆን እያንዳንዱ የምስክር ወረቀት በሚከተሉት ሁኔታዎች ወዲያውኑ ለገበያው መመለስ ወይም መተው አለበት፡ -

ሀ) በተለይ የእነዚህ ደንቦች ድንጋጌዎችን አለማክበር ጋር የተያያዙ አሳማኝ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ለገበያው በቀረበ ጥያቄ፤

ለ) የአባልነት የምስክር ወረቀት ሲሻር፤

ሐ) ፈቃዱ በባለስልጣኑ ሲሰረዝ፤

መ) የግብይት አባሉ በፈቃደኝነት ምስክር ወረቀቱን አሳልፎ ሲሰጥ፤ እና

ሠ) የግብይት አባሉ ከተዘጋ፣ የሀብት ማጣራት ከተደረገበት ወይም የንግድ ሥራ በሚሰራ ሞግዚት ሲተዳደር።

(2) የገበያው አባልነት የግብይት አባሉን ዕዳ ለመክፈል የሚውሉ ሀብቶች አካል አይሆንም። ነገር ግን ወዲያውኑ ለገበያው ሊሰጥ እና በዚሁ ላይ ያለው የባለቤትነት መብት ወዲያውኑ መመለስ አለበት።

(3) የአባልነት መብቶችን ለሶስተኛ ወገኖች መሸጥ ወይም ማስተላለፍ አይቻልም።

## 2.6. የግብይት መብቶች መቋረጥ

(1) የሚከተሉት ከተፈጠሩ አንድ የግብይት አባል በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የሚተዳደሩትን ገበያዎች የማግኘት መብቱ ይቋረጣል እንዲሁም በእነዚህ ገበያዎች ላይ ማንኛውንም ትዕዛዞች ማስገባት የለበትም፡ -

ሀ) ለመዝጋት ወይም ከዚህ ጋር በተያያዘ የሕግ አስተዳዳሪ ወይም ተመሳሳይ ባለስልጣን ለመሾም በባለአክሲዮኖቹ ሲወሰን ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲሰጥ፤

ለ) ከኪሳራ ጋር በተያያዘ በማንኛውም ህግ መሠረት ከአበዳሪዎቹ ጋር የመጠባበቂያ እና መልሶ ማዋቀር ስምምነት ውስጥ ከገባ፤

ሐ) እንደ ሁኔታው በባለስልጣኑ የተሰጠ የአገልግሎት ፈቃድ ጊዜው ሲያልቅ ወይም ሲታገድ፤

መ) በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም በሌላ የክፍያ አጣሪ እና ፈፃሚ አካል ካልተመዘገበ ወይም በዚህ ረገድ ምዝገባው ከተቋረጠ፤

ሠ) ክፍያ ያቋረጠ መሆኑ በገበያው ከታወጀ፤ ወይም

ረ) በገበያው ከታገደ።

(2) በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የሚተዳደሩትን ገበያዎች የማግኘት መብቱ የታገደበት የግብይት አባል አግባብነት ያላቸውን ደንቦች ማክበሩን መቀጠል አለበት። ይህ ዓይነቱ የግብይት አባል በገበያው ላይ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ጋር በተያያዘ ላሉበት ግዴታዎች ሁሉ ተጠያቂ ሆኖ ይቆያል።

## 2.7. የግብይት አባል ሁኔታ

(1) ከቁጥጥሩ ውጭ ባሉ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር አንድ የግብይት አባል ለግብይት አባልነት ተቀባይነት ላገኘበት የንግድ ሥራ የዕለት ተዕለት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ማከናወኑን ማቆም የለበትም።

(2) አንድ የግብይት አባል በፈቃደኝነትም ይሁን ያለፍቃደኝነት ለአንድ (1) ዓመት ጊዜ የግብይት እንቅስቃሴ የሌለው ከሆነ ገበያው የግብይት አባሉን የአባልነት የምስክር ወረቀት ይሰርዛል ።

(3) አንድ የግብይት አባል በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት የግብይት እንቅስቃሴ የሌለው እንደሆነ ይቆጠራል፤

ሀ) በፍቃደኝነት አለመስራት፡ ማንኛውም የግብይት አባል በገበያው ወይም በባለስልጣኑ ሳይታገድ ማንኛውንም የግብይት እንቅስቃሴ ማሳየት ካልቻለ ።

ለ) ያለፈቃድ አለመስራት፡- ድርጅቱ በማንኛውም ጥፋት በገበያው ሲታገድ ።

## 2.8. አባልነትን ስለመተው

(1) አባልነቱን መተው የሚፈልግ ማንኛውም የግብይት አባል ለገበያው ቢያንስ የሦስት (3) ወራት የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት አለበት።

(2) የመተው ማስታወቂያው ቅጂ በሚመለከተው የገበያው ፖርታል ወይም መገናኛ ዘዴ እና በገበያው ድረ ገጽ ላይ መለጠፍ አለበት።

(3) የግብይት አባላቱ ማናቸውንም የሚተወውን የግብይት አባል የሚመለከቱ ማናቸውም ያልተከፈሉ ዕዳዎች፣ ግዴታዎች እና ቃል ኪዳኖችን እና ማንኛቸውም ያልተጠናቀቁ ግብይቶችን ለገበያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።

(4) ገበያው በራሱ ውሳኔ የሚከተሉትን ሊያደርግ ይችላል፦

ሀ) እንደዚህ ዓይነቱን የአባልነት መተው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መቀበል፤ ወይም

ለ) ለደንበኞች የተጣሉ ሁሉም ግዴታዎች መሟላታቸውን እና ሁሉም ግብይቶች መጠናቀቃቸውን ወይም በካፒታል ገበያ አገልግሎት

አቅራቢዎች ፈቃድ እና ቁጥጥር መመሪያ መሠረት ከሌላ የግብይት አባል ጋር የመተካካት ስምምነት መፈረሙን በማረጋገጥ የአባልነት መተውን መቀበል።

(5) የግብይት አባሉ የመተው ማስታወቂያውን ካስገባ በኋላ በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (4) (ለ) የተጠቀሱትን ዓላማዎችን ከማሳካት በስተቀር የግብይት ሥራ የማከናወን መብቱን ያጣል።

## ምዕራፍ 3 - ቁጥጥር፣ የባለቤትነት መዋቅር እና ጉልህ ተፅዕኖ

### 3.1 የቅድመ ማፅደቅ እና የቅድመ ማሳወቅ መስፈርቶች

(1) አንድ የግብይት አባል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ለመፈፀም ወይም ለማከናወን መደበኛ ውሳኔ የተላለፈ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ወዲያውኑ ለገበያው በጽሑፍ ማሳወቅ እና ማረጋገጫ መጠየቅ አለበት፡ -

ሀ) የግብይት አባሉ የካፒታል አክሲዮን ድርሻ ህጋዊ ወይም የጥቅም ባለቤትነት መብት ላይ በ5% ወይም ከዚያ በላይ ለውጥ የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል ማንኛውም ግብይት፤ እና

ለ) የግብይት አባሉን የቁጥጥር ስልጣን የሚቀይር ወይም ሊቀይር የሚችል ማንኛውም ለውጥ ሲከሰት።

(2) አንድ የግብይት አባል በሌላ ማንኛውም የንግድ ስራ ላይ ከመሰማራቱ ወይም በሌላ ማንኛውም የንግድ ድርጅት ውስጥ ጉልህ የሆነ የአክሲዮን ድርሻ መጠን ከመያዙ ወይም ከማግኘቱ አስር (10) የሥራ ቀናት በፊት ለገበያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

(3) አንድ የግብይት አባል የንግድ ስሙን ሲቀይር፣ ዋና መስሪያ ቤቱን ሲያዘዋውር፣ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሲከፍት፣ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱን ከማዛወሩ እና/ወይም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱን ከመዝጋቱ ቢያንስ ሠላሳ (30) የሥራ ቀናት በፊት ለገበያው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

### 3.2. የግብይት አባል ሕጋዊ ወይም የተጠቃሚ ባለቤትነት ላይ የሚደረግ ለውጥ

(1) ማንኛውም አካል በአንድ የግብይት አባል አምስት በመቶ (5%) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የአክሲዮን ድርሻን ከመያዙ አስቀድሞ የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፤

ሀ) የንግድ አባሉ የሚተላለፈውን የአክሲዮን ድርሻ ቁጥር እና መጠን በመቶኛ በመግለፅ የአክሲዮን ድርሻ መዋቅር ለውጡ እንዲፀድቅ ለገበያው እና ለባለስልጣኑ በማመልከቻ መጠየቅ አለበት፤ እና

ለ) ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉት ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፦

i. ገዢው ግለሰብ ከሆነ፣ ሊተላለፍ የታቀደውን የአክሲዮን ድርሻ ለመያዝ በግለሰቡ ወይም በግብይት አባሉ ለገበያው የሚቀርብ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ፡፡

ii. ገዢው አክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር እንደሆነ የታቀደው ግዢ የጸደቀበት የቦርድ ወይም የባለ አክሲዮኖች ቃለ ጉባኤ፤

iii. ገዢው የሽርክና ማህበር እንደሆነ የታቀደው ግዢ የፀደቀበት የሽሪኮች ቃለ ጉባኤ፤

iv. በገዢው እና በሻጩ መካከል በአግባቡ የተፈረመ የአክሲዮን ግዢ ወይም ዝውውር ስምምነት ቅጂ፤

v. በድርጅቱ ሊከናወኑ የታቀዱ የዳይሬክተሮች እና የአመራር ለውጥ ካለ፤

vi. በአዲሶቹ ዳይሬክተሮች እና በድርጅቱ ከፍተኛ የአመራር አባላት የሚፈረም ቃለ መኃላ (ለውጥ ካለ)፤

vii. አዲሶቹን ዳይሬክተሮች እና ከፍተኛ አመራሮችን በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የባለስልጣኑ ፈቃድ፤

viii. ሌሎች ገበያው እንዲቀርቡ ሊጠይቃቸው የሚችሉ ሰነዶች እና መረጃዎች፡፡

(2) ገበያው በአንድ የግብይት አባል ላይ የሚያደረገውን ሕጋዊ ወይም የጥቅም ባለቤትነት ለውጥ ሊፈቅድ የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው፦

ሀ) የአስተላላፊው ሙሉ ወይም ከፊል እንቅስቃሴ ወይም ጥቅም እና ንብረት፣ ሀብት እና እዳዎች ሙሉ በሙሉ ለሚተላለፍለት ሰው ወይም ወደ ገዢው ተቋም የተላለፉ ከሆነ፤ እና

ለ) ደንበኞችን ለመጠበቅ ሲባል የአስተላላፊውን ግዴታ ለመወጣት በቂ ዋስትና የተዘጋጀ መሆኑን ገበያው ሲያምንበት፡፡

### 3.3 የግብይት አባል በሌላ የንግድ ስራ ላይ መሰማራት

(1) አንድ የግብይት አባል በሌላ የንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት ወይም በሌላ የንግድ ድርጅት ውስጥ ትልቅ የአክሲዮን ወይም የጥቅም ድርሻ ለመያዝ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይገባዋል፡-

ሀ) በገበያው ተለይቶ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የግብይት አባሉ ለገበያው እና ለባልስጣኑ አስቀድሞ ማሳወቅ፤ እና

ለ) ሌላኛውን የንግድ ስራ በተመለከተ ከሚቀርበው ማስታወቂያ ጋር የሚከተሉት ሰነዶች ተሟልተው መቅረብ ይገባቸዋል፦

i. በነዚህ ሳይወሰን የሚከተሉትን ያካተተ የሌላኛው ንግድ መረጃ፣ የድርጅቱን መግለጫ፣ ዓላማ እና ተግባር፣ የተመዘገበ ቢሮ፣ ሌላ ማንኛውም ድርጅቱ ስራውን የሚያከናውንበት ወይም ሊያከናውን ያቀደበት ቢሮ፤

ii. በገበያው ሊጠየቁ የሚችሉ አስፈላጊ የሂሳብ መረጃዎች፤ እና

iii. ሌሎች በገበያው እንዲቀርቡ ሊጠየቁ የሚችሉ ሰነዶች እና መረጃዎች፡፡

(2) የግብይት አባሉ በሌላ የንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት ወይም በሌላ የንግድ ድርጅት ውስጥ ትልቅ የአክሲዮን ወይም የጥቅም ድርሻ የመያዝ እቅዱ አዋጁን፣ የባልስጣኑን መመሪያዎች፣ የገበያውን ደንቦች እና ተፈፃሚነት ያላቸው ሌሎች ህጎች እና ደንቦችን የማይጥስ መሆኑን ማረጋጋጥ አለበት፡፡

(3) የግብይት አባላት ለነባር ወይም ለወደፊት ደንበኞች ወይም ለገበያው ካለባቸው ግዴታ ጋር ሊጋጩ የሚችሉ ወይም ለአላማቸው መሳካት መሰናክል ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ሲኖሩ ለገበያው ሙሉ በሙሉ እና በፍትሐዊ መንገድ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

(4) ገበያው ወይም ባለስልጣኑ የግብይት አባሉ በሌላ የንግድ ስራ ላይ መሰማራቱን ወይም በሌላ የንግድ ድርጅት ውስጥ ትልቅ የአክሲዮን ወይም የጥቅም ድርሻ መያዙን ሊቃወሙ ይችላሉ፤ ይህ በሆነ ጊዜ የግብይት አባሉ ድርጊቱን ወይም የአክሲዮኑን ግዢ ማቆም አለበት፡፡

(5) የግብይት አባሉ በሌላ የንግድ ስራ ላይ መሰማራት ወይም አክሲዮን ግዢ ወይም የጥቅም ድርሻ መያዝ ላይ ገበያው ቅድመ ሁኔታዎች እና ገደቦችን ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

(6) የግብይት አባሉ በሌላ የንግድ ስራ ላይ መሰማራት ወይም በሌላ የንግድ ድርጅት ውስጥ አክሲዮን ወይም የጥቅም ድርሻ መያዙ የገበያውን ወይም የገበያዎቹን ወይም የግብይት አባሉን የፋይናንስ ተዓማኒነት፣ መልካም ስም ወይም ጥቅም በአሉታዊ መንገድ ይጎዳል ብሎ ሲያምን፣ ገበያው ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቅድመ ሁኔታዎችን ሊያስቀምጥ ወይም ሊለውጥ ወይም የግብይት አባሉ ስራውን እንዲሰርዝ፣ አክሲዮኑን እንዲሸጥ ወይም የጥቅም ድርሻውን እንዲተው ሊያደርግ ይችላል፡፡

(7) የግብይት አባሉ ተሿሚ እንደራሴ ወይም ሌሎች ግለሰቦች ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ድርጊቶችን በሚያካትቱ ሌሎች የንግድ ስራዎች ላይ እንዳይሳተፉ፣ ከፍተኛ የአክሲዮን ወይም የጥቅም ድርሻ እንዳይዙ ለመቆጣጠር እና ለማረጋጋጥ የሚያስችል የአሰራር ሂደት ሊኖረው ይገባል፦

ሀ) አዋጁን ፣ የባለስልጣኑን መመርያ ፣ የግብይቱን ደንቦችን ወይም ሌሎች ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች እና ደንቦችን የሚጥሱ፤ ወይም

ለ) የገበያውን ወይም የግብይት አባሉን የፋይናንስ ተዓማኒነት ፣ ጥቅም ወይም መልካም ስም የሚጎዱ ድርጊቶች፡፡

3.4 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ስለማቋቋም

(1) አንድ የግብይት አባል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለማቋቋም የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፤

ሀ) የታቀደውን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አድራሻ እና ቦታ፤

ለ) ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱን የሚያስተዳድሩ ባለሙያዎች ስም ዝርዝርን ጨምሮ የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ እንዲከፈት በባለስልጣኑ የተፈቀደበት ማስረጃ፤

ሐ) የግብይት አባሉ የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አስተዳዳር ፖሊሲ ቅጂ፤

መ) በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ የአካል የቅድመ ማረጋገጫ ምርምራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለቅድመ ማረጋገጫ ምርምራው አስፈላጊ የሆኑ ክፍያወች ለገበያው ስለመከፈላችው ማረጋገጫ፤ እና

ሠ) ሌሎች በገበያው እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ሰነዶች እና መረጃዎች፡፡

(2) የግብይት አባሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የግብይት አባሉ የንግድ ስራ አካል ተደርጎ ይቆጠራል፤ በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን ድንጋጌዎች ጨምሮ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆንበታል፤

ሀ) በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ውስጥ የሚኖረውን ትክክለኛ የሥራ ድርሻ ክፍፍል፤

ለ) የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ የግብይት አባሉን ስም የሚያመላክት ምልክት የያዘ መሆን፤

ሐ) ደህንነቱ የተጠበቀ መዛግብት መያዝ፤ እና

መ) ለግብይት አባሉ ማሳወቅ ሳያስፈልግ ወይም ማስታወቅያ በመስጠት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየጊዜው እና በድንገት የሚደረጉ መደበኛ እና ድንገተኛ የመስክ ምርመራዎች፡፡

(3) በእያንዳንዱ የግብይት አባል ስር የሚገኝ ጽህፈት ቤት፣ የሥራ ክፍል ወይም የንግድ ስራ በአቋቋሚው የግብይት አባል ክትትልና ቁጥጥር ስር ወይም ይህ ሃላፊነት እና ስልጣን በውክልና በተሰጠው ባለሙያ ስር መሆን አለበት፡፡

(4) የእያንድንዱ የግብይት አባል የዳይሬክተሮች ቦርድ ተገቢውን የአመራር እና ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት እና የቅርንጫፉን ውስጣዊ አሰራር እና ቁጥጥር የሚመሩ ከፍተኛ የሥራ አመራር አባሎቹን በመኮንንነት በመሾም ተፈፃሚነት ያላቸው ህግ እና ደንቦች መከበራቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ተሿሚ መኮንኖቹ፦

ሀ) አግባብነት ያለውን የቁጥጥር እና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት እያንዳንዱን ጽህፈት ቤት ወይም የሥራ ክፍል የመቆጣጠር እና የመከታተል ብቃት ላላቸው ሰራተኞች ይህን ስልጣን እና ኃላፊነት ውክልና ይሰጣሉ፤ እና

(ለ) የተሰጣቸውን ሥልጣን እና ኃላፊነት በአግባቡ እያከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ የተለየ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ይቀርባሉ፡፡

(5) በገበያው በጽሑፍ በተለየ መንገድ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የግብይት አባሉን ጽህፈት ቤት ለመምራት በገበያው ተቀባይነት የሚኖራቸው ከፍተኛ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ተገበያይ ግለሰቦች ወይም በክትትል እና በቁጥጥር እና አሰራር ሂደት ዙሪያ በቂ ልምድ እና ስልጠና ያላቸው ከፍተኛ የግብይት አባሉ ሰራተኞች ብቻ ናቸው፡፡

(6) የግብይት አባሉ የውጪ አገር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የሚቋቋመው አስቀድሞ በገበያው ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ሲሆን ቀጣይነቱም በገበያው በሚፈፀም ማንኛውም አይነት የደንብ ለውጥ ይመራል፡፡ የግብይት አባሉ የታቀደውን የንግድ ስራ ለማከናወን ከሚመለከተው የውጪ አገር ባለስልጣን የተሰጠ የፈቃድ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

(7) ለዚህ ደንብ አላማ "የወጪ አገር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት" የሚለው ቃል የሚከተሉትን የሚሰራ በውጪ አገር እራሱን ችሎ የተቋቋመ አካልን ያካትታል፡

ሀ) የግብይት አባሉ አገልግሎቶች የሚቀርቡበት፣ ወይም

ለ) የግብይት አባሉ የገንዘብ ሀብቶች ለጽህፈት ቤቱ እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የሚውሉበት፣ ወይም

ሐ) ከላይ ከተጠቀሱት ሁለቱ መካከል በቅደም ተከተል የሚገኙ ወይም ጥቅም ላይ የዋሉ ስለመሆኑ የሚገለጽበት፡፡

## 3.5 ዋና ወይም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ስለማዛወር ወይም መዝጋት

(1) የግብይት አባሉ ጽህፈት ቤቱን ወደ ሌላ ቦታ ለማዛወር ወይም ለመዝጋት ሲፈልግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይገባቸዋል፡

ሀ) ሊዛወር ወይም ሊዘጋ ስለታሰበው ጽህፈት ቤት ግልጽ እና ልዩ ልዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ቢያንስ ከ30 (ሰላሳ) የካላንደር ቀናት ላላነሰ ጊዜ ማስታወቂያ መስጠት፤

ለ) ጽህፈት ቤቱን ወደ ሌላ ቦታ ማዛወርን የሚመለከት ሲሆን የአዲሱን ጽህፈት ቤት አድራሻ እና ቦታ ዝርዝር መግለጫ፤

ሐ) የታቀደው የጽህፈት ቤት መዝጋት ወይም ወደሌላ ቦታ ማዛወርን የሚመለከት ሲሆን ደንበኞች እና ህዝቡ በባለስልጣኑ መስፈርቶች መሰረት በማስታወቂያ እንዲያውቁት ስለመደረጉ የሚቀርብ ማስረጃ፤ እና

መ) ሌሎች በገበያው እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ሰነዶች እና መረጃዎች፡፡

(2) ገበያው ተቃውሞ የሌለው ስለመሆኑ በፅሁፍ ካላሳወቀው በስተቀር የግብይት አባሉ ጽህፈት ቤቱን መዝጋት ወይም ማዛወር አይችልም፡፡

## 3.6 የንግድ ስም ስለመለወጥ

(1) የግብይት አባሉ የንግድ ስሙን ለመቀየር የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይገባቸዋል፡-

ሀ) የታሰበውን የንግድ ስም ለውጥ እና የለውጡን ምክንያት በመግለፅ ከ30 (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ላላነሰ ጊዜ ማስታወቂያ መስጠት፤

ለ) የታቀደውን አዲስ የንግድ ስም፤

ሐ) የታቀደው የንግድ ስም ለውጥ በባለስልጣኑ ስለመፅደቁ የሚቀርብ ማስረጃ፤

መ) የታቀደውን የንግድ ስም ለውጥ ለደንበኞች እና ለህዝብ በባለስልጣኑ መስፈርቶች መሰረት በማስታወቂያ እንዲያውቁት ስለመደረጉ የሚቀርብ ማስረጃ፤ እና

ሠ) በገበያው ሊጠየቅ የሚችል ማንኛውም ሌላ መረጃ ወይም ሰነድ።

(2) ገበያው የንግድ ስም ለውጡ ላይ ተቃወሞ የሌለው ስለመሆኑ በፅሁፍ ካላሳወቀ በስተቀር የግብይት አባሉ የንግድ ስሙን መለወጥ አይችልም።

## ምዕራፍ 4 - የካፒታል እና የሂሳብ ሪፖርት

### 4.1 ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርት

(1) እያንዳንዱ የግብይት አባል ሊያሟላ የሚገባው ዝቅተኛው የካፒታል መስፈርት በባለስልጣኑ በተደነገገው መሰረት መሆን ይኖርበታል።

(2) እያንዳንዱ የግብይት አባል በባለስልጣኑ እና በገበያው የተወሰነውን ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርት እና የሚፈለገውን ዝቅተኛ የገንዘብ-አከል ንብረት መጣኔ ጠብቆ ማቆየት አለበት።

(3) ገበያው የግብይት አባሉን ካፒታል በቂነት የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አለበት።

(4) የግብይት አባሉ የካፒታል በቂነት ከሚፈለገው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን በታች በሚሆንበት ጊዜ የግብይት አባሉ የሚከተሉትን ማከናወን ይኖርበታል።

ሀ) በአስቸኳይ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ የዚህን ማስታወቂያ/የመልዕክት ልውውጥ ማስረጃ በሃያ አራት (24) ሰዓት ውስጥ ለገበያበው ማቅረብ፤ እና

ለ) ከገበያው ጋር በተስማሙበት እና በባለስልጣኑ በፀደቀው ጊዜ ውስጥ የካፒታል መጠኑን ማሳደግ።

(5) ማንኛውም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ የግብይት አባል ገበያው በሚወስነው የገዜ ገደብ ከግብይት ታግዶ እንዲቆይ እና/ወይም በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ሰንጠረዥ በተመለከተው መሰረት ሌላ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል።

(6) ገበያው የዚህ ደንብ አካል በሚሆን ልዩ አባሪ ለገበያ ከፋቾች የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርት ያወጣል። በነዚህ ደንቦች ቅጽ "ለ" ምዕራፍ 9 ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን ገበያው የዚህ ደንብ አካል በሚሆን ልዩ አባሪ በማካተት ይገልፃል።

4.2 የገንዘብ አከል ንብረት መስፈርቶች

(1) እያንዳንዱ የግብይት አባል በሁሉም ጊዜ በባለስልጣኑ የተቀመጡትን እና በገበያው በየጊዜው የሚወሰኑትን የገንዘብ አከል ካፒታል መስፈርቶች ማክበር አለበት፡፡

(2) ማንኛውም ሀብት በአይነት ድልድል/የተጣራ ካፒታል እና ሌላ ማንኛውንም የገንዘብ አከል የተጣራ ንብረት መስፈርቶች ወይም ድልድል ስሌት በገበያው በተወሰነው መሰረት ይከናወናል፡፡

(3) እያንዳንዱ የግብይት አባል ሀብት በአይነት ድልድል፣የተጣራ ካፒታል እና ማንኛውንም ሌላ የገንዘብ አከል ንብረት መስፈርት በወር አንድ ጊዜ ለገበያው ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡ የሀብት በአይነት ድልድል መጠኑ ጋር በተያያዘ፣ ገንዘብ አከል ንብረት ክምችት ቅነሳ ወይም ከሌሎች የገንዘብ አከል ንብረት መስፈርቶች ጋር በተያያዘ ማንኛውንም አለመጣጣም ባወቀ ከ24 (ሃያ አራት) ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡፡

(4) የገንዘብ አከል ንብረቱ ከዝቅተኛው መስፈርት በታች ከወረደ ማንኛውም የግብይት አባል ከገበያው ጋር በተስማማበት ጊዜ ውስጥ ካፒታሉን ወደ ቦታው እንዲመልስ የሚገደድ ሲሆን እንደዚህ ዓይነቱ የገንዘብ አከል ንብረት ካለበት በተጨማሪ እንዳይቀንስ በገበያው በቅርበት ክትትል ይደረግበታል፡፡

(5) ማንኛውም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ የግብይት አባል ገበያው ለሚወስነው የጊዜ ገደብ ከግብይት ታግዶ እንዲቆይ እና/ወይም ስለቅጣት በሚደነግገው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሰረት ሌላ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡

4.3 ሪፖርት ስለማቅረብ

(1) እያንዳንዱ የግብይት አባል፡ -

ሀ) የውጭ ኦዲተሮቹ ስም ዝርዝር ላይ የሚደረግ ማንኛውንም ለውጥ በተመለከተ በአስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ ለገበያው የውጭ ኦዲተሮቹን ስም ዝርዝር ማቅረብ አለበት፡፡

ለ) የሩብ ዓመት የፋይናንስ መግለጫዎችን፣ኦዲት የተደረገ የፋይናንስ መግለጫን እና ማንኛውንም በባለስልጣኑ የሚጠየቁ ሌሎች ሪፖርቶችን በባለስልጣ እንዲቀርብ በተቀመጠበት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለገበያው እና ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ) ሌሎች በየጊዜው መቅረብ የሚገባቸውን ሪፖርቶች በተመለከተ ሪፖርቶቹ እንዲቀርቡ ባለስልጣኑ ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለገበያው ማቅረብ አለበት፡፡

መ) የፋይናንስ መግለጫዎቹ በሚሸፍኑት የጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈጻሚነት ባለው እና የኢትዮጲያ የሒሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ወይም አግባብነት ያለው ባለስልጣን ባወጣው መስፈርት መሰረት በአለም አቀፍ

የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች መሰረት ሁሉንም የፋይናንስ መግለጫዎች ያዘጋጃል።

ሠ) ከአክሲዮን ካፒታሉ ውስጥ አምስት በመቶ (5%) ወይም ከዚያ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸውን የባለአክሲዮኖች ዝርዝር በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ በማካተት ማሳወቅ አለበት።

ረ) በፋይናንስ መግለጫው ዓመት ውስጥ ስለሚኖራቸው እንቅስቃሴ በማስረጃ ላይ የተደገፉ ውሳኔዎችን ለመወሰን ጠቃሚ የሆኑ መሰረታዊ ለውጦችን ማሳወቅ አለበት።

(2) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አንድ የግብይት አባል የሩብ ዓመት የፋይናንስ መግለጫውን ወይም ዓመታዊ የተረጋገጡ የፋይናንስ መግለጫዎቹን ለማቅረብ የጊዜ ማራዘሚያ ሊጠይቅ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ የማራዘሚያ ጥያቄ ለማቅረብ የሚገባው የፋይናንስ መግለጫ ለማቅረብ ከሚያስፈልገው ቀን ቢያንስ ከአሥር (10) የሥራ ቀናት በፊት ሲሆን፣ የግብይት አባሉ የማራዘሚያውን ጥያቄ ማቅረብ ያስፈለገበትን ልዩ ልዩ ምክንያቶችን በግልፅ እና በማያሻማ መልኩ መግለጽ ይጠበቅበታል።

(3) ገበያው የግብይት አባሉን የፋይናንስ መግለጫ ወይም ሌሎች ሪፖርቶች የማቅረቢያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሙሉ ስልጣን አለው፡ ፡ በገበያው የሚሰጠው ፈቃድ በማንኛወም ሁኔታ ለሩብ አመት ሪፖርት ከማቅረቢያ ጊዜው ለአንድ (1) ወር እና ለዓመታዊ ሪፖርት ከሁለት (2) ወር በላይ ሊራዘም አይችልም።

(4) የግብይት አባሉ ሪፖርቱን በተመለከተ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወይም በተሰጠው የተራዘመ ጊዜ ሪፖርቱን ያላቀረበ እንደሆነ የግብይት አባሉን መጠየቅ ሳያስፈልግ ገበያው የግብይት አባሉን በአስቸኳይ ከግብይት ሊያግድ ይችላል።

(5) ማንኛውም የግብይት አባል ማንኛውንም ሪፖርት ባለማቅረቡ ምክንያት ከግብይት የታገደ እንደሆነ፣ እግዱ ሊነሳ የሚችለው ሌሎች በገበያው የተቀመጡ ግዴታወችን እና ቅድመ ሁኔታወችን ከማሟላት በተጨማሪ የሚፈለገው ሪፖርት ሲቀርብ ብቻ ነው።

(6) የውጭ ኦዲተሩ በፋይናንስ መግለጫው ላይ አስተያየቱን በሚሰጥበት ጊዜ የሚከተሉትን ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡

ሀ) ዝቅተኛው ካፒታል መስፈርት መሟላት አለመሟላቱን፤

ለ) የግብይት አባሉን የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ሁኔታ፤

ሐ) የፋይናንስ መግለጫዎቹ የተሳሳተ መረጃን ያካተቱ ስለመሆን አለመሆኑ፤ እና

መ) በዓመቱ ውስጥ በተፈፀሙ ጥሰቶች እና ቅጣቶች ላይ መግለጫ።

### 4.4 የፋይናንስ መግለጫን ወይም ሌሎች ሪፖርቶችን ማዛባት የተከለከለ ስለመሆኑ

(1) የግብይት አባል በማንኛወም ሁኔታ የፋይናንስ መግለጫ ወይም በገበያው እንዲቀርቡ የሚጠየቁ የሌሎች ሪፖርቶችን ይዘት ማዛባት የለበትም፡፡

(2) ማንኛውም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ የግብይት አባል ገበያው ለሚወስነው የጊዜ ገደብ ከግብይት ታግዶ እንዲቆይ እና/ወይም ስለ አስተዳደራዊ እርምጃ በሚደነግገው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሰረት ሌላ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡ ፡

## ምዕራፍ 5 - አስተዳደር፣ ክትትል እና የውስጥ የቁጥጥር ስርዓት

### 5.1 ክትትል እና የውስጥ የቁጥጥር ስርዓት

(1) ማንኛውም የግብይት አባል ገበያው በየጊዜው የሚደነግገውን ዝቅተኛ የውስጥ ቁጥጥር መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

(2) ማንኛውም የግብይት አባል የተሿሚ እንደራሴዎችን እና ሌሎች ሠራተኞቹ እንቅስቃሴ ሕግን ያከበረ ስለመሆኑ የሚከታተልበትን እና የሚያረጋግጥበትን የአሰራር ስርዓት መንደፍ እና ማዋቀር አለበት፡፡ የግብይት አባሉ በአግባቡ የመቆጣጠር የመጨረሻ ኃላፊነት አለበት፡፡

(3) የግብይት አባሉ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት የግብይት አባሉ በሚሳተፍባቸው የንግድ ዓይነቶች ላይ ቁጥጥር ለማድረግ የተዘጋጁ እና በጽሁፍ የተዘረዘሩ የአሰራር ስርዓቶች እንዲመሰረቱ፣ እንዲጠብቁ እና እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡

(4) የግብይት አባሉ የአሰራር ስርዓቶች የቁጥጥር ኃላፊዎችን እና የሕግ ተገዢነት መኮንኖችን ብቃት እና ማዕረግ ጭምር ማሳየት አለበት፡፡

(5) እያንዳንዱ የግብይት አባል የተሿሚ እንደራሴዎችን እና ሌሎች ሠራተኞቹን ብቁነት እና ተገቢነት በማጣራት የማረጋገጥ ኃላፊነት እና ግዴታ አለበት፡፡

(6) ሁሉም የግብይት አባል የተሰማራበትን የንግድ ስራ በተመለከተ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ለዚህ ተብሎ የተዘጋጁ መዛግብትን በመጠቀም ግምገማ ማከናወን አለበት፡፡ ግምገማው የተፈፀሙ ግብይቶች በትክክል መከናወናቸውን እና የደንበኞች ሂሳቦች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋጋጥ እንዲሁም የገበያውን ውስጠ ደንቦች እና እነዚህን ደንቦች ጥሰት ለመለየት እና ለመከላከል እና ተገዥነትን ለማሳካት እንዲያስችል ተደርጎ በተገቢው መንገድ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

(7) እያንዳንዱ የግብይት አባል የተደረገን መደበኛ የመስክ ምርመራ ጨምሮ የሁሉንም ጽ/ቤቶች እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንቅስቃሴ ግምገማ የሚመለከት ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

5.2 አስቀድሞ በጽሑፍ ስለሚሰጡ ፈቃዶች እና ማስታወቂያዎች

(1) እያንዳንዱ የግብይት አባል ማናቸውንም ከገበያው ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን ወይም ገበያውን ማስታወቅ የሚያስፈልጋቸው ድርጊቶች ከመፈፀሙ በፊት አስፈላጊው ፈቃድ ስለመገኘቱ ወይም ለገበያው ማስታወቂያ ስለመሰጠቱ በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሰራሮች እና ፖሊሲወች ሊኖሩት ይገባል፡፡

(2) እያንዳንዱ የግብይት አባል ላገኛቸው ፍቃዶች የጽሁፍ ወይም ሌላ ማንኛውንም አወንታዊ ማስረጃ መያዝ እና እንደዚህ ዓይነት መዛግብትን ቢያንስ ለአስር (10) ዓመታት ማስቀመጥ አለበት፡፡

5.3 የስጋት አስተዳደር

(1) እያንዳንዱ የግብይት አባል፡

ሀ) ገበያው በየጊዜው የሚደነግገውን የስጋት አስተዳደር ዝቅተኛ መስፈርቶችን እና/ወይም ደረጃዎችን ማክበር ይኖርበታል፤ እና

ለ) የስጋት አስተዳደር ቡድን ሊኖረው ይገባል፡፡

(2) እያንዳንዱ የግብይት አባል አግባብነት ያላቸውን አስፈላጊ ቀመሮች እና ዲጂታል ሲስተሞችን/ሶፍትዌሮችን በመጠቀም ተቀባይነት ያላቸውን ስጋቶችን በመቶኛ በማስቀመጥ የስጋት አስተዳደር ቡድኑን ውጤታማነት ለመቆጣጠር የሚያስችል አግባብነት ያለው የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

(3) እያንዳንዱ የግብይት አባል ለንግድ ስራው ስፋት፣ አወቃቀር እና ለደንበኞቹ አግባብነት ያለውን የግንኙነት ፖሊሲ እና ስርዓት በፅሁፍ በማዘጋጀት ያሳትማል፡፡ እነዚህ ፖሊሲዎች እና ሂደቶች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች ማካተት አለባቸው፦

ሀ) ከደንበኞች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት መገምገሚያ እና መቆጣጠሪያ፤

ለ) ድርጅታዊ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ስርዓቶች ዙሪያ ለሠራተኞች ትምህርት እና ስልጠናዎች መስጠት፤ እንዲሁም የተሰጠውን ትምህርት እና ስልጠና መመዝገብ፤ እና

ሐ) እነዚህ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ስርዓቶች መተግበራቸውን እና መከበራቸውን ለማረጋገጥ ምልከታ እና ክትትል ማድረግ፡፡

(4) የግብይት አባላት ጽህፈት ቤታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል አግባብነት ያለው ቁጥጥር እና አሰራር ስርዓት ማዘጋጀት እንዲሁም የደንበኞች መዛግብትን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና ጥሬ ገንዘብን ለማከማቸት ደህንነታቸው የተጠበቁ መገልገያዎችን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

5.4 ሕጋዊ እርምጃ

(1) የግብይት አባሉ የሚከተሉት ሲከሰቱ በአስቸኳይ እና ከ24 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፦

ሀ) በገበያው ላይ ከሚደረጉ ግብይቶች ጋር በተያያዘ ከኩባንያው የንግድ እንቅስቃሴዎች ጋር የተገናኘ ወይም የግብይት አባሉን ቀጣይነት ያለው ሥራ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የፍርድ ቤት ክሶች በግብይት አባሉ፣ በተመዘገበ ግለሰብ ወይም በሌሎች የግብይት አባሉ ሠራተኞች ላይ ከቀረቡ፤

ለ) የግብይት አባሉ እዳውን መክፈል ያቋረጠ ወይም የከሰረ እንደሆነ፤ እና

ሐ) በግብይት አባሉ ማንኛውም ባለ አክሲዮን፣ በተመዘገበ ግለሰብ ወይም ሌሎች የግብይት አባሉ ሠራተኞች ላይ የወንጀል ምርምራ ወይም ክስ ከተጀመረ።

## 5.5 በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን መከላከል

(1) ማንኛውም የግብይት አባል በኢትዮጲያ ውስጥ ተፈፃሚነት ባላቸው ህጎች መሠረት ከንግድ ስራቸው ጋር በተያያዘ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ/ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን መከላከል በተመለከተ መረጃን ይፋ የማድረግ ግዴታን ማክበር አለባቸው፤ እንዲሁም በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ/ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን መከላከል በተመለከተ ገበያው ያወጣውን ደንብ፣ የአሰራር ስርዓት እና መመሪያ ማክበር አለባቸው።

(2) ከላይ በተደነገገው መሰረት፣ እያንዳንዱ የግብይት አባል፡

ሀ) በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ/ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን መከላከል ፖሊሲ ሊኖረው እና በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ/ሽብርተኝነትን በፋይናንስ መርዳትን ስለመከላከል፣ ስለማስቆም እና ገበያው በየጊዜው የሚደነግጋቸውን ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ተግባራትን በተመለከተ ለሰራተኞቹ ስልጠና መስጠት አለበት፤

ለ) በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ወይም ከሌሎች የግብይት አባሎች ጋር በጋራ በመሆን የያዛቸውን የራስ የሆኑ ሂሳቦች በሙሉ በገበያው በሚቀመጠው መስፈርት መሰረት በየሩብ አመቱ ለገበያው ይፋ ማድረግ አለበት፤ እና

ሐ) ተሿሚ እንደራሴወች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የያዙትን የግል የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሳቦች እና በገበያው በተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ያላቸውን የጥቅም አይነት ለግብይት አባሉ ይፋ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት።

## 5.6 ድርጅታዊ አስተዳደር

(1) ሁሉም የግብይት አባላት በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ መሰረት ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ባለስልጣኑ በደነገጋቸው የድርጅታዊ አስተዳደር መመሪያዎች እና በባለስልጣኑ እና/ወይም በገበያው በየጊዜው በሚወጡ ማናቸውም ሌላ የድርጅታዊ አስተዳደር መስፈርቶች  መሰረት መመራት አለባቸው።

(2) ተፈፃሚነት ያላቸው መመሪያዎችን ወይም መስፈርቶችን አለማክበር የገበያውን ደንብ እንደመጣስ ይቆጠራል፡፡

(3) ማንኛውም የግብይት አባል ከዚህ በላይ የተደነገገው መመሪያ ወይም የድርጅታዊ አስተዳደር መስፈርት ያላከበረ እንደሆነ ገበያው ይህን ጉድለት ለግብይት አባሉ ሊያሳውቅ እና የግብይት አባሉ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ለምን እንዲህ ዓይነት ጥፋት እንደተፈጸመ እና ለምን በገበያው ሊቀጣ እንደማይገባ በጽሑፍ እንዲያብራራ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ 6 - ተሿሚ እንደራሴዎች እና ሌሎች ሠራተኞች

### 6.1 የተሿሚ እንደራሴዎች እና ሌሎች ሠራተኞች ኃላፊነት

(1) ሌሎች ተፈጻሚ ሕጎች፤ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም ውስጠ ደንቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እያንዳንዱ የግብይት አባል ለተሿሚ እንደራሴዎቹ፣ ለሰራተኞቹ እና ሌሎች ባለሙያዎቹ ድርጊቶች ሁሉ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

(2) ሁሉም የግብይት አባላት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ነጋዴዎችን እና የደንበኞችን ሂሳቦች አዘውትረው የሚይዙ ወይም የሚያካሂዱ ሰዎችን እና በእንደዚህ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ላይ በተሰማሩት ላይ የቁጥጥር ኃላፊነት ያላቸውን ሰዎች ጨምሮ በንግድ ስራቸው ውስጥ ለመሾም ወይም ለመቅጠር የሚያስቧቸውን ሰዎች የኋላ ታሪክ በጥልቀት መመርምር አለባቸው፡፡

(3) ገበያው ያወጣቸው ደንቦች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በማንኛውም ጊዜ በግብይት አባሉ የንግድ ስራ የተቀጠሩ ሰዎችን ስም፣ የሥራ ኃላፊነት፣ የሥራ ታሪክ እና አግባብነት ያላቸው መረጃዎች እንዲቀርቡለት መጠየቅ ይችላል፡፡

(4) ማንኛውም የግብይት አባል ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተገበያዮች መዝገብ ላይ ስሙ የተሰረዘን ወይም በገበያው እንዳይሳተፍ ገደብ የተጣለበትን ሰው መቅጠር ወይም በሥራ ላይ ማቆየት የለበትም፡፡

### 6.2 ተሿሚ እንደራሴዎችን የመሾም እና የማፀደቅ ግዴታ

(1) ሁሉም የግብይት አባላት የሚከተሉት ተሿሚ እንደራሴዎች ወይም ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚዎች ሊኖራቸው ይገባል ፦

ሀ) በአዋጁ እና በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ መሰረት በባለስልጣኑ የፀደቁ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፤

ለ) የግብይት አባሉ ተሿሚ እንደራሴ ሆነው በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው ዋና ስራ አስኪያጅ/ማኔጂንግ ዳይሬክተር/ዋና ስራ አስፈፃሚ መኮንን፤

ሐ) የግብይት አባሉ ተሿሚ እንደራሴ ሆኖ በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ዋና የሕግ ተገዢነት መኮንን፤

መ) ደንበኞቹን በመወከል ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመግዛት እና የመሸጥ ፈቃድ በባለስልጣኑ የተሰጠው የግብይት አባል ሲሆን የግብይት አባሉ ተሿሚ እንደራሴ በመሆን በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የደንበኞች ሰነደ ሙዓለንዋዮች ተገበያዮች፤

ሠ) የራሱ በሆነ ሂሳብ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመግዛት እና የመሸጥ ፈቃድ በባለስልጣኑ የተሰጠው የግብይት አባል ሲሆን የግብይት አባሉ ተሿሚ እንደራሴ በመሆን በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የራስ በሆነ ሂሳብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተገበያዮች፤

ረ) የገበያ ከፋች ተግባራትን እንዲፈፅም በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው የግብይት አባል ሲሆን የግብይት አባሉ ተሿሚ እንደራሴ በመሆን በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው የገበያ ከፋች ግብይት ፈፃሚ፤

ሰ) በዚህ ደንብ ወይም በባለስልጣኑ መመሪያ እና በሂደት በሚሻሻለው እንዲሁም ሌሎች በገበያው በሚወጡ ውስጠ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና አሰራር ስርዓቶች በሚመለከተው መሰረት የሚሾሙ ሌሎች እንደራሴዎች እና ከፍተኛ ባለሙያዎች።

(2) በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የግብይት አባል፦

ሀ) የደንበኞች ሰነደ ሙዓለንዋዮች ተገበያይ መደብን የራስ በሆነ ሂሳብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተገበያይ ወይም ፈቃድ ያገኘ የገበያ ከፋች ግብይት ፈፃሚ መደብ ጋር ሊያጣምር አይችልም፤ ወይም

ለ) የራስ በሆነ ሂሳብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተገበያይ መደብን ፈቃድ ካገኘ የገበያ ከፋች ግብይት ፈፃሚ መደብ ጋር ሊያጣምር አይችልም።

(3) ማናቸውም በዚህ ደንብ ውስጥ የተካተቱ ድንጋጌዎች የግብይት አባሉ ለሚፈፅማቸው ጥሰቶች ገበያውን ቅጣት ከመጣል ሊያግዱት አይችሉም፣ እንዲሁም የግብይት አባሉ ለሁሉም የተሿሚ እንደራሴዎቹ እና ሌሎች ባለሙያዎች ድርጊት ተጠያቂ ይሆናል።

(4) የግብይት አባሉ እያንዳንዱ ተሿሚ እንደራሴ ግዴታ እና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስፈልጋቸውን በቂ ትምህርት እና ስልጠና እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በገበያው የሚቀመጡ ቀጣይነት ያላቸው መሰል ትምህርት እና ስልጠናወች መውሰዱን ማረጋገጥ አለበት።

## 6.3 የግብይት አባል ተሿሚ እንደራሴዎች የስነ ምግባር ደንብ እና ግዴታዎቻቸው

(1) ማናቸውም ተሿሚ እንደራሴዎች በዚህ ደንብ መሰርት የተጣለባቸውን ግዴታ እና ኃላፊነት ከመወጣት ጋር በተገናኘ ሊፈጠር የሚችል ወይም የተፈጠረን የጥቅም ግጭት መለየት እና መቆጣጠር አለባቸው።

(2) ገበያው ማንኛውንም የተጣለበትን ኃላፊነት ችላ ያለ ወይም ሆን ብሎ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰን ተሿሚ እንደራሴ ሊያግድ ወይም ሊቀጣ ይችላል።

(3) ተሿሚ እንደራሴው የገበያው አባል ከሆነው የግብይት አባል ጋር ያለውን ቅጥር ወይም ሹመት የለቀቀ ወይም በማንኛወንም መንገድ ያለውን ግንኙነት ያቋረጠ እንደሆነ የሚከተለው ተፈፃሚ ይሆናል፡

ሀ) ማቋረጡ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ የግለሰቡ ስም ከተሿሚ እንደራሴዎች መዝገብ ላይ ይሰረዛል፤

ለ) ግለሰቡ ተመዝግቦ በነበረበት ጊዜ ከገበያው ውስጠ ደንብ ጋር በተያያዘ ወይም በተገናኘ ለተከሰቱ ጉዳቶች ለገበያው እና ለደንበኞች የሚኖርው ተጠያቂነት እንዳለ ይቀጥላል፤

ሐ) ግለሰቡ ተመዝግቦ ባለበት ጊዜ በግለሰቡ ወይም በግብይት አባሉ ለተፈፀሙ የገበያው የውስጠ ደንብ ጥሰቶችን በተመለከተ ለስነ-ምግባር ምርመራ እና ክስ ተጠያቂነቱ ይቀጥላል፤ እና

መ) ገበያው ግለሰቡ ተመዝግቦ ከገበያው እና ከግብይት አባሉ ጋር ግንኙነት በነበረው ጊዜ የፈፀማቸው እና መፈፀም ሲገባው ያልፈፀማቸውን ጉዳዮች አስመልክቶ ግለሰቡን በማስቀረብ ማብራሪያ እንዲሰጥበት የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

### 6.4 በቀድሞ ተሿሚ እንደራሴወች፣ ሰራተኞች እና ሌሎች ባለሙያዎች ላይ የሚቆይ ስልጣን

(1) ገበያው ተሿሚ እንደራሴዎች፣ ሰራተኞች እና ሌሎች ባለሙያዎች ስለ መልቀቃቸው በፅሁፍ ከተገለጸለት በኂላ በማንኛውም ጊዜ የገበያውን ውስጠ ደንብ እና መመሪያ ጥሰትን በተመለከተ አግባብ ያለው ምርመራ ለማድረግ እና ቅጣት ለመጣል ያስችለው ዘንድ በቀድሞ ተሿሚ እንደራሴዎች፣ ሰራተኞች እና ሌሎች ባለሙያዎች ላይ ያለው ስልጣን እንደተጠበቀ ይቆያል፡፡

(2) በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ በተገለጸው መሰረት ገበያው በቀድሞ ተሿሚ እንደራሴዎች፣ሰራተኞች እና ሌሎች ባለሞያዎች ላይ ስልጣኑን ከተጠቀመ እኚህ የቀድሞ ተሿሚ እንደራሴዎች፣ ሰራተኞች እና ሌሎች ባለሞያዎች በገበያው ፊት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ወይም መዝገቦችን እና ሌሎች ተጨባጭ ቁሶችን ለገበያው እንዲያቀርቡ ወይም ገበያው ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ በፅሁፍ ሲጠይቅ ምላሽ ለመስጠት ይገደዳሉ፡፡

### 6.5 የተሿሚ እንደራሴዎች መደብ ላይ ስለሚደረግ ለውጥ

(1) ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ተገበያይ የሥራ መደብ ውጪ ላሉ የሥራ መደቦች አንድ ተሿሚ እንደራሴ በባለስልጣኑ ለተመሳሳይ መደብ የተሿሚ እንደራሴነት ፈቃድ በሚያገኝበት ወቅት ለባለስልጣኑ ማሳወቅን በተመለከተ ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና የጊዜ ሰሌዳዎች ለገበያው ለሚደረገው ማስታወቂያም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

(2) አንድ ሰራተኛ ለተመሳሳይ የሥራ መደብ የተሿሚ እንደራሴነት ፈቃድ በባለስልጣኑ ያልተሰጠው እንደሆነ ወይም ባለስልጣኑ ተሿሚ እንደራሴውን በተመለከተ የማሳወቅ ግዴታን በግልፅ ያላስቀመጠ እንደሆነ ተከታዮቹ የጊዜ ሰሌዳዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፦

ሀ) የሕግ ተገዢነት መኮንን መደብን ሳይጨምር አንድ ሰራተኛ ወይም ተሿሚ እንደራሴ ከስራ ቦታ ከማዛወሩ አስቀድሞ ባሉ አምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፤

ለ) ከሁለቱ ቀድሞ የተከሰተው ላይ በመመስረት፣ አንድ ሰራተኛ ወይም ተሿሚ እንደራሴ ስራውን በፈቃደኝነት ከሚለቅበት ቀን አስቀድሞ ባሉ አምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወይም የሥራ መልቀቂያ ማስጠንቀቂያውን ከተቀበለ በአስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ፤

ሐ) የሕግ ተገዢነት መኮንን መደብን ሳይጨምር ማንኛውም ሰራተኛ ወይም ተሿሚ እንደራሴ ከስራ ከተሰናበተ ወይም ከተባረረ በኋላ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ፤ እና

መ) ማንኛውም ሰራተኛ ወይም ተሿሚ እንደራሴ መሞቱ ወይም ያለ ማስጠንቀቂያ ስራ መልቀቁ ከታወቀ በኋላ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ።

(3) የዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (2) ድንጋጌ የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚ የሥራ መደብ ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

(4) በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀፅ ቁጥር (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም የግብይት አባላት የተመዘገቡ ግለሰቦች መረጃ ዝርዝር ላይ ለውጥ በተከሰተ አንድ (1) የሥራ ቀን ውስጥ ለገበያው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

(5) ማናቸውም ተሿሚ እንደራሴዎች ወይም ሌሎች ሰራተኞችን በተመለከተ ለገበያው የሚቀርበው ማስታወቂያ ገበያው በሚያዘጋጀው ፎርም እና በተዘጋጀው መድረክ ወይም መገናኛ ዘዴ መሰረት በጽሁፍ መሆን አለበት።

## 6.6 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት

(1) በገበያው የወጡ መመሪያዎች፣ የአሰራር ስርዓቶች እና ሰነዶች ድንጋጌዎች ላለመከበራቸው የግብይት አባሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የጋራ እና የተናጠል ኃላፊነት አለባቸው።

(2) አንድ የግብይት አባል ዳይሬክተር በሌላ በገበያው በተመዘገበ ማህበር ውስጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነ እንደሆነ ዳይሬክተርነቱ ለገበያው መገለፅ አለበት።

(3) አንድ የግብይት አባል በገበያው በተመዘገበ ማህበር ውስጥ ዳይሬክተር የሆነን ግለሰብ የአስፈፃሚነት ድርሻ የሌለው ዳይሬክተር በማድረግ መሾም ይችላል ሆኖም ግን አስፈፃሚ በዳይሬክተርነት ሊሾም አይችልም።

(4) አንድ የግብይት አባል በማንኛወም ሁኔታ ቢሆን በዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ የሰብሳቢ ወይም ስራ አስፈፃሚ ያልሆነ አባልነት ሚናን ከዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ሌላ የአስፈፃሚነት ሚና ጋር ማጣምር የለበትም።

(5) አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ከአንድ (1) በላይ ለሆኑ የግብይት አባላት ውስጥ ዳይሬክተር ሆኖ ማገልገል አይችልም፡፡

(6) የሚከተሉት ሁኔታዎች ካልተሟሉ በስተቀር የአንድ የግብይት አባል ዳይሬክተር በሌላ የንግድ ስራ መሰማራት ወይም ከፍተኛ የሆነ ድርሻ ሊይዝ አይችልም፦

ሀ) የግብይት አባል ዳይሬክተር ከመሆን ጋር የጥቅም እና የኃላፊነት ግጭት የሌለ እንደሆነ፣ እና

ለ) ዳይሬክተሩ የግብይት አባሉን ፈቃድ በቅደሚያ ያገኘ ሲሆን፡፡

## 6.7 የሕግ ተገዢነት መኮንን

(1) የግብይት አባሉ የሕግ ተገዢነት መኮንን ለግብይት አባሉ፣ ለተሿሚ እንደራሴዎች እና ሌሎች ባለሙያዎች የዚህን ደንብ አፈፃፀም በተመለከተ ምክር ለመስጠት ብቃት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

(2) የሕግ ተገዢነት መኮንኑ ማናቸውም የሕግ እና የደንብ ጥሰት መፈፀሙን ባወቀ በሃያ አራት (24) ሰዓታት ውስጥ ድርጊቱ መፈፀሙን እና መወሰድ ያለበትን የመፍተሔ እርምጃ ጭምር ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡፡

(3) የሕግ ተገዢነት ቡድን ወይም ክፍል የበላይ ኃላፊ ሆኖ የተሰየመ የሕግ ተገዢነት መኮንን በግብይት አባሉ የድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ የአመራር ቡድን አባል መሆን አለበት፣ ለዳይሬክተሮች ቦርድ በቀጥታ ሪፖርት የማቅረቢያ መንገድ ሊኖረው ይገባል፣ በተጨማሪም ማንኛውም የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ለመከላከል በማናቸውም ጊዜ ነፃ እና ገለልተኛ መሆን አለበት፡፡

(4) በምንም ሁኔታ ቢሆን አንድ የግብይት አባል የሕግ ተገዢነት ቡድን/ሥራ ኃላፊ ሆኖ የተሾመ የሕግ ተገዢነት መኮንን ከሌላ ተቀራራቢነት ካለው የሥራ ኃላፊነት ጋር ማጣመር የለበትም፡፡

(5) በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (4) የተደነገገው ቢኖርም፣ ግለሰቡ ሁለቱንም ተግባራት ለማከናወን የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያሟላ እንደሆነ አንድ የግብይት አባል የሕግ ተገዢነት ቡድን ወይም ክፍል የበላይ ኃላፊ በመሆን የተመደበ የሕግ ተገዢነት መኮንን ከኩባንያ ጸሀፊ ስራ ወይም የሕግ አማካሪ ወይም ሁለገብ የሕግ አማካሪ ወይም የሕግ ክፍል ኃላፊ ወይም የስጋት መኮንን መደብ ጋር ሊጣመር ይችላል፡፡

(6) ሚና እና ኃላፊት፦

ሀ) የግብይት አባል የሕግ ተገዢነት መኮንን ለግብይት አባሉ፣ ለተሿሚ እንደራሴዎች እና ለሌሎች ባለሙያዎች በዚህ ደንብ አፈፃፀም ዙሪያ የማማከር ስራ ይሰራሉ፡፡

ለ) የሕግ ተገዢነት መኮንን አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን፣ ፖሊሲዎችን እንዲሁም ሌሎች ከካፒታል ገበያው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መስፈርቶችን የመተርጎም እና የማስፈፀም ችሎታ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህም አግባብነት ያላቸውን ተፈፃሚ ደንቦች፣ የአሠራር ሥርዓቶች እና መመሪያዎችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ክትትል ማድረግን እና ስራ ላይ ማዋል እና ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት በማዘጋጀት ለተቆጣጣሪው አካል ማቅረብ እንዲሁም በኢንዱስትሪው ውስጥ አግባብነት ያላቸው እና ጉዳት የሚቀንሱ ወይም የሚከላከሉ መልካም ልምዶችን መጠቀምን ያካትታል፡፡

ሐ) የሕግ ተገዢነት መኮንን ውስጣዊ እና ውጭዊ ደንቦችን እና ፖሊሲዎችን ለመመርመር፣ ለመለየት እና ለማስከበር የሚረዱ ድርጊቶች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፡፡

መ) የሕግ ተገዢነት መኮንኑ በየጊዜው የሚፈጠሩ የቁጥጥር ሥርዓት፣ በደንቦች፣ መመሪያዎች በአሰራር ስርዓቶች ላይ የተደረጉ ለውጦችን እና በየጊዜው የሚወጡ የደረጃ መስፈርቶችን በመከታተል ለግብይት አባሉ፣ ለተሿሚ እንደራሴዎቹ እና ለሌሎች ስራተኞች እንዲሰራጩ ያደርጋል፡፡ ሁሉንም የሥራ ክንዋኔዎችን የሚሸፍን የተገዢነት ክትትል ያካሂዳል፡፡

ሠ) የሕግ ተገዢነት መኮንኑ ሥጋትን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑትን የቁጥጥር ሥርዓቶችን በመጠቀም ሁሉም ኢንቨስትመንቶች እና ሌሎች የግብይት ስራዎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች፣ ደንቦች እና ፖሊሲዎች የሚያከብሩ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡

ረ) የሕግ ተገዢነት ቡድን ወይም የሕግ ተገዥነት መኮንኖች የበላይ ኃላፊ በመሆን የተመደበ የሕግ ተገዢነት መኮንን በግብይት አባሉ ዳይሬክተሮች ቦርድ እና ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ መኮንኖች ድጋፍ የቋተሙን መስፈርት፣ ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ በየጊዜው የሚኖረውን ለውጥ ያማከለ ጠንካራ እና ከለውጦቹ ጋር ተለዋዋጭ የሆነ የሕግ ተገዢነት ፕሮግራም በማበልፀግ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

ሰ) የሕግ ተገዢነት ቡድን ወይም የሕግ ተገዥነት መኮንኖች የበላይ ኃላፊ በመሆን የተመደበ የሕግ ተገዢነት መኮንን በፋይናንስ እና የካፒታል ገበያ አስተዳደር ላይ ያተኮረ የትምህርት እና ስልጠና ፕሮግራሞችን የማዘጋጀት፣ የማስተባበር እና የመሳተፍ እንዲሁም ሁሉም የማኔጅመንት አባላት እና ሌሎች ሰራተኞች አግባብነት ያላቸውን ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲያውቁ እና እንዲያከብሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

ሸ) የሕግ ተገዢነት ቡድን ወይም የሕግ ተገዥነት መኮንኖች የበላይ ኃላፊ በመሆን የተመደበ የሕግ ተገዢነት መኮንን ሥራ አስኪያጆች እና ሰራተኞች የተከሰቱ ወይም የተጠረጠሩ ጥሰቶችን እና የተፈጠሩ

ጥፋቶችን ጉዳት ሊደርስበኝ ይችላል ከሚል ስጋት ነፃ ሆነው እንዲጠቁሙ የሚያስችል ፖሊሲ እና ፕሮግራም የመቅረጽ ኃላፊነት አለበት፡፡

(7) ለሕግ ተገዢነት መኮንን ስለሚደረግ ጥበቃ፦

ሀ) የግብይት አባሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሕግ ተገዢነት መኮንን(ኖች) የሚጠበቅበትን ሚና እና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችለውን በቂ የጥበቃ ስርዓት ማዘጋጀት አለበት፡፡

ለ) የግብይት አባሉ የሕግ ተገዢነት መኮንን ሲሾም ለየአገልግሎት ሁኔታውን የሚገልፅ የቅጥር ወይም እንደ ሁኔታው የመደብ ለውጥ ደብዳቤ ቅጂን ለገበያው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሐ) የግብይት አባሉ አንድ የሕግ ተገዢነት መኮንን ሊያገኝ የሚገባውን ማናቸውንም ጥቅሞች፤ የሥራ እድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ ማበረታቻ፣ሥልጠና ወይም ልላ ማናቸውንም ማካካሻ እና ሽልማትን ያለ በቂ ምክንያት መከልከል የለበትም፡፡

መ) የሕግ ተገዢነት መኮንኑ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉትን ሰነዶች ለማግኘት ከማንኛውንም ሰራተኛ ጋር የመገናኘት መብት አለው፡፡

ሠ) የሕግ ተገዢነት መኮንኑ በየጊዜው አግባብነት ባለው ባለሥልጣናት የሚጠየቅ ማንኛውንም መረጃ፣ ማብራሪያ እና ሰነዶችን እንዲቀርብ ማንኛውንም የሰራተኞች አባል ሊያስገድድ ይችላል፡፡

ረ) ማናቸውም የግብይት አባል በሕግ ተገዢነት መኮንኑ ጥቆማ መሰረት የተጀመረ ምርመራ እየተከናወነ ባለበት ጊዜ የሕግ ተገዢነት መኮንኑን ከስራ ማሰናበት አይችልም፡፡

ሰ) የሕግ ተገዢነት መኮንን ሊሰናበት ወይም ከሹመቱ ሊነሳ የሚችለው ከሹመት የመነሳቱ ምክንያት በግብይት አባሉ ላይ ያቀረበው ጥቆማ እስካልሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

(8) የሕግ ተገዢነት መኮንን ዝውውር

ሀ) ማንኛውም የግብይት አባል ገበያው ተቃውሞ እንደሌለው ሳያሳውቀው አንድን የሕግ ተገዢነት መኮንን ወደ ሌላ መደብ ማዘዋወር አይችልም፡ :

ለ) የታቀደው የመደብ ዝወውር በሕግ ተገዢነት መኮንኑ ተፈፅሟል የተባለ ጥፋትን ተከትሎ ከሆነ የሕግ ተገዢነት መኮንን ከስልጣን መውረድን በተመለከተ በንዑስ ደንብ (9) የተቀመጠው ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

(9) የሕግ ተገዢነት መኮንን ስንብት ወይም ከኃላፊነት መነሳት

ሀ) የሕግ ተገዢነት መኮንኑ ሊተላለፍ የታሰበው ውሳኔ በፅሁፍ እንዲያውቀው ተደርጎ በግብይት አባሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊሰናብት ወይም ከኃላፊነት ሊነሳ ይችላል፡፡

ለ) የሚሰናበተው ወይም የሚነሳው የሕግ ተገዢነት መኮንን ጉዳዩን በፅሁፍ የማስረዳት እንዲሁም የታቀደው የስንብት ወይም ከኃላፊነት የመነሳት

ሃሳብ በሚቀርብበት የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ላይ በአካል ቀርቦ የመሰማት መብት ይኖረዋል፡፡

ሐ) የሕግ ተገዢነት መኮንን የስንበት ውሳኔ ሃሳብ ማስታወቂያው ቢያንስ ለታቀደው ስንብት ምክንያቱን የሚገልፅ መሆን እና የሕግ ተገዥነት መኮንኑ መልሱን በፅሁፍ የሚሰጥበት ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜን የሚሰጥ መሆን ይገባዋል፡፡

መ) ከላይ የተገፀው ማስታወቂያ ለሕግ ተገዢነት መኮንኑ የተላከበት እለት ሳያልፍ ለገበያው ሊላክ ይገባዋል፡፡

ሠ) የግብይት አባሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አንድ የሕግ ተገዢነት መኮንን ለማሰናበት ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት የስንብቱ መሰረት ምክንያታዊ እና ፍትሐዊ መሆኑን እንዲሁም የገበያውን አጠቃላይ ጥቅም የሚያስጠብቅ ስለመሆኑ ማረጋጋጥ አለበት፡፡

ረ) የዳይሬክተሮች ቦርድ የመጨረሻ ውሳኔ የተላለፈበት ስብሰባ በተደረገ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔው ለገበያው በፅሁፍ መገለጽ አለበት፡፡ የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ የሕግ ተገዢነቱን መኮንን ማሰናበት ከሆነ ውሳኔው ከመፈፀሙ አስቀድሞ የዳይሬክተሮች ቦርዱ ገበያው እና ከባለስልጣኑ ተቃወሞ የሌላቸውም መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሰ) በዚህ ደንብ የተደነገገው ገበያውን የሕግ ተገዢነት መኮንኑ እንዲሰናበት ከመጠየቅ ወይም አንድን የሕግ ተገዢነት መኮንን ስንብት ከመከልከል አያግደውም፡፡

## 6.8 የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች

(1) የምዝገባ መስፈርት፦

በልዩ ሁኔታ በገበያው ነፃ እስካልሆነ ድረስ የግብይት አባሉ በገበያው የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት የሚያካሂዱ ሰዎችን እንደ የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ግለሰቦች በገበያው ማስመዝገብ አለበት፡፡ ማናቸውም እንደዚህ ዓይነት ልዩ ሁኔታዎች በገበያው በፅሁፍ በግልጽ ለግብይት አባሉ ሊገለፁ ይገባል፣ ምንም አይነት ልዩ ሁኔታዎች በግምት ሊወሰዱ አይገባም ፡፡

(2) የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች መደቦች፡-

በባለስልጣኑ ለግብይት አባሉ በሚሰጠው የአገልግሎት ፈቃድ መሰረት የግብይት አባሉ የሚቀጥራቸው የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች መደቦች የሚከተሉት ናቸው፦

(ሀ) የደንበኞችን ግብይት የሚያስተዳድር የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚ (ዎች)፣

(ለ) የግብይት አባሉን የራስ የሆነ ግብይት የሚያስተዳድር የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚ (ዎች)፣ እና

(ሐ) ፈቃድ የተሰጠው ገበያ ከፋች ተገበያይ፡፡

(3) ብቁነት፦

አመልካቾች የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች ሆኖ ለመመዝገብ የሚከተሉትን ማሟለት አለባቸው፦

ሀ) አስፈላጊውን የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች ፈቃድ ከባለስልጣኑ ማግኘት፤

ለ) በገበያው ተፈፃሚነት ያላቸውን የአሰራር ስርዓቶች እና አካሄዶች በተመለከተ ገበያው የሚሰጠውን አግባብነት ያለው ስልጠና በመውሰድ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ፤

ሐ) በባለስልጣኑ የብቁነት እና ተገቢነት መስፈርት መሰረት ብቁ እና ተገቢ ሰው መሆን፤

መ) ተፈፃሚነት ሲኖረው፣ ጥሩ የሆነ የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ታሪክ መኖር፤ እና

ሠ) በየትኛወም የግዛት ስልጣን ውስጥ ባለ ገበያ ወይም ተቆጣጣሪ አካል አግባብነት ባለው ቁጥጥር የሚደረግበት እንቅስቃሴ ላይ በእንደራሴነት እንዳይሰራ ተብሎ ከዚህ ቀደም ውድቅ ያልተደረገ ሰው መሆን፡፡

(4) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች መዝገብ፤

ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች እና የቀጣሪዎቻቸው ስም በገበያው መያዝ አለበት፤ እንዲሁም ሁሉም የግብይት አባላት በማመልከቻ ሲጠይቁ ማግኘት ይችላሉ፡፡

ለ) በገበያው የተመዘገቡ እና ግብይት የሚካሄድባቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ግብይት ማድረግ የሚችሉት በገበያው የተመዘገቡ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች መዝገብ ላይ የሰፈሩት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች ብቻ ናቸው፡፡

ሐ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች እንዲመዘገቡ የተሰጠው ፈቃድ በገበያው የተሰረዘ ወይም የተሻረ እንደሆነ እንደዚህ ያለው ውሳኔ የተላለፈበት የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ከመዝገብ እንደተሰረዘ ይቆጠራል ስሙም ተሰርዘዋል በተባለበት ቀን ጀምሮ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

መ) ገበያው አንድን የተመዘገበ ግብይት ፈፃሚ የመሰረዝ ወይም የመሻር ውሳኔን በተመለከተ ለሚመለከተው ግለሰብ እና ለግብይት አባሉ ምክንያቱን መስጠት አለበት፡፡

ሰ) ማንኛውም የግብይት አባል በገበያው ስሙ ከመዝገብ የተሰረዘን ወይም የታገደን ግለሰብ መቅጠር ወይም ቅጥሩን ማስቀጠል የለበትም፡፡

(5) የመፈፀም ስልጣን፦

በገበያው እስካልተፈቀደ ድረስ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን አንድ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ሊቀጠር እና ሊሰራ የሚችለው ለአንድ (1) የግብይት አባል ብቻ ነው፡፡ምንም አይነት ልዩ ሁኔታዎች በግምት ሊወሰዱ አይገባም ሆኖም በገበያው በፅሁፍ በግልጽ ሊገለፁ ይገባል፡
:

(6) ስራ ሲለቅ/ሲተው ወይም ከመተው/ከመልቀቁ አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ

የግብይት አባሉ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፤

ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ስራ ከመልቀቁ አስቀድሞ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ። ሆኖም ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ለመልቀቅ ማስታወቂያ በደረሰው ወይም ባወቀ በሃያ አራት (24) ስዓታት ውስጥ ለገበያው ማሳወቅ አለበት።

(i) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚው ለግብይት አባሉ የ5 የሥራ ቀናት መስፈርቱን ለማሟላት የሚያስችለውን በቂ የሆነ ማስጠንቀቂያ ያልሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

(ii) መሰል ማስታወቂያ ለመስጠት በሚያስፈልገው ማንኛውም አስገዳጅ ሁኔታ።

ለ) የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚ በቂ የሥራ መልቀቅያ ማስጠንቀቂያ ላለመስጠቱ አሳማኝ የሆነ ማስተባበያ ለገበያው ካላቀረበ በስተቀር፣ ለስፖንሰር አድራጊ የግብይት አባሉ በቂ የሥራ መልቀቂያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ከስራው የለቀቀ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ጥሰት እንደፈፀመ ተደርጎ ይቆጠርበታል።

ሐ) በዚህ ንዑስ ደንብየተደነገገው ቢኖርም አንድ የግብይት አባል የገበያውን፣ የገበያዎቹን እና የተሳታፊዎችን ጠቅላላ ጥቅም ሊጎዳ የሚችል ድርጊት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ስለመፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ካወቀ በአስቸኳይ ለገበያው ማሳወቅ አለበት።

መ) መውጣት ማለት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ በገዛ ፍቃዱ ስራውን መልቀቅ፣ መሰናበትን፣ ከሥራ ቦታ መዘዋወርን፣ ከሥራ መባረር፣ ከሥራ መነሳት ወይም ሞትን የሚጨምር ሲሆን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም።

## *ምዕራፍ 7 — የሒሳብ ዶሴ እና መዝገቦች*

### 7.1. የግብይት መዝገብ እና የምርመራ መብት

(1) ማናቸውም የግብይት አባል ከሁሉም ግብይቶች ጋር በተገናኘ የሒሳብ ዶሴዎችን እና መዝገቦችን መያዝ ይኖርበታል። ገበያው እነዚህ የሂሳብ መዝገቦች እና ዶሴዎች የሚመዘገቡበትን እና የሚጠበቁበትን ቅፅ ወይም ፎርም ወመሰን እና የግብይት አባላትን መዝገቦችን በየጊዜው መመርመር ይችላል።

(2) የግብይት አባሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ተሿሚ እንደራሴዎች (ሥራ አስፈፃሚ ያልሆኑ የቦርድ አባላትን ሳይጨምር) እና የግብይት አባሉ ሁሉም የሥራ ኃላፊዎች በምርመራው ወቅት እንዲገኙ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

(3) የግብይት አባላት እና ሰራተኞቻቸው በገበያው ወይም በስልጣን በተሰጠው የመንግስት ተቆጣጣሪ በሚካሄዱ ሁሉም ምርመራዎች ላይ ሙሉ በሙሉ እና በቅልጥፍና መተባበር እና ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች በፍጥነት ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

(4) ማንኛውም የግብይት አባል የዚህን መመሪያ ማንኛውንም ድንጋጌ ከጣሰ ገበያው በአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ ውስጥ በተጠቀሰው አግባብ ቅጣት ሊጥል ይችላል።

### 7.2. የደንበኛ መዝገብን ስለማስቀመጥ

(1) ማናቸውም የግብይት አባል የሚከተሉትን መዝገቦች ከጥፋት መታደግ በሚችሉበት መንገድ በአግባቡ በማከማቸትና በመመለስ የሚመሩ ተገቢ ሂደቶች እና ስርዓቶች ሊኖሩት ይገባል፤

ሀ) ደንበኛው ለግብይት አባሉ የሰጠውን ትዕዛዞች ጨምሮ ለደንበኛ የቀረበውን አገልግሎት በተመለከተ የተደረጉ ግንኙነቶችን፤

ለ) ከደንበኞች ጋር የተያያዙ የግብይት ሰነዶች፤

ሐ) ገበያው ያስቀመጣቸውን ደንቦች ጨምሮ በግብይት አባሉ እና ደንበኞቹ መካከል የተደረጉ ውሎች፣ እና

መ) በደንቦቹ መሰረት መቅረብ ያለባቸው ወይም የደንበኞችን ሂሳቦች በብቃት ለማንቀሳቀስ አስፈላጊ የሆኑ የደንበኛ ዝርዝር መረጃዎች፤

(2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት የደንበኛ መዝገቦች በወረቀት፣ በኤሌክትሮኒክስ እና/ወይም በድምጽ ቅጂ ሊቀመጡ ይገባል፣ ነገር ግን በተደራጀ መንገድ እና ቀጣይነት ባለው አግባብ በወረቀት መልኩ እንዲዘጋጁ በሚያስችል ሁኔታ መጠበቅ አለባቸው።

(3) የገበያ አባላት በንዑስ አንቀጽ (1) ውስጥ የተጠቀሱትን መዝገቦች ራሳቸው ማስቀመጥ አይጠበቅባቸውም ነገር ግን መሰል መዝገቦች ለምርመራ ሲጠየቅ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ መቻል አለባቸው።

(4) ደንበኞች ግብይት ለማካሄድ የሰጡትን ትዕዛዞች እና ሌሎች ሁሉንም የደንበኛ መዝገቦችን ተፈጻሚነት ባላቸው ህጎች ወይም በገበያው ለተደነገገው ዝቅተኛ የማቆያ ጊዜ መጠበቅ አለባቸው።

## *ምዕራፍ 8 — የግብይት አባላት ከህዝብ ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት*

### 8.1. ከህዝብ ጋር ለሚደረግ ግንኙነት አጠቃላይ መስፈርቶች

(1) የግብይት አባላት የአክሲዮን ደላላ ንግድ ሥራቸውን ከሚያካሂዱባቸው ቢሮዎች ውጭ በቂና ሊነበብ በሚችል ፊደል በተፃፈ ሰሌዳ ላይ በግብይት ሥራቸው የተመዘገቡበትን ስም ብቻ ማሳየት ይፈቀድላቸዋል።

(2) እያንዳንዱ የግብይት አባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከገበያው፣ በገበያው ስር ባሉት ገበያዎች እና ከገበያው እንቅስቃሴዎች ጋር ሊያያዝ የሚችል ማንኛውንም ማስታወቂያ፣ ብሮሸር፣ ደብዳቤ ወይም ሌላ ማንኛውም ህትመት፤

ሀ) ትክክለኛ መረጃን የያዘ እና መሰረታዊ እና ጠቃሚ እውነታዎችን ወይም ማብራሪያዎችን መያዙን፣

ለ) አሳሳች ያልሆነ፤

ሐ) በውጪ ሊረጋገጡ የሚችሉ የይገባኛል ጥያቄዎችን ወይም ማረጋገጫዎችን ብቻ የያዘ፤

መ) ደጋፊ ማስረጃዎችን አብሮ የያዘ የኢንቨስትመንት አፈጻጸምን የሚተነብዩ ወይም የሚገምቱ ትንበያዎችን ብቻ ማካተት አለበት ፤

ሠ) በኢንቨስትመንት ላይ የተረጋገጠ ትርፍ እንደሚኖር ማረጋገጫን የሚሰጥ ተደርጎ የማይወሰድ ወይም በስህተት ሊተረጎም የማይችል፤

ረ) ስለ ድርጅቱ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ውስጥ ስላለው ችሎታ፣ ስለሚሰጠው አገልግሎት፣ ስለሚያቀርበው ምርት ወይም ስለሚያሳየው አፈጻጸም የውሸት፣ የተጋነኑ፣ ያልተረጋገጡ፣ እንዲሁም የወደፊት ቃል ኪዳን የሆኑ መግለጫዎችን፣ ይገባኛል ጥያቄዎችን ወይም ንጽጽሮችን የማያካትት መሆኑን፤

ሰ) ገበያውን፣ ተዛማጅ ድርጅቶቹን፣ ለሌሎች የግብይት አባላት መልካም ስም ላይ ጉዳት የማያደርስ፤

ቀ) የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤቱን የጽሑፍ ስምምነት ካላገኘ በስተቀር የግብይት አባሉ ያልሆነ አእምሯዊ ንብረት አያካትትም፤ ነገር ግን የባለቤቱን ያገኘ የአእምሯዊ ንብረት ሊካተት ይችላል፤

በ) የመረጃ አለመኖር ወይም እጥረት ስለግንኙነቱ የህዝቡን ግንዛቤ የሚገድብ ሲሆን መሰረታዊ ወይም ጠቃሚ መረጃዎችን በማውጫ፣ በግርጌ ማስታወሻ በማይታይ እና ድብቅ ቦታ ላይ የማያስቀምጥ፣

ተ) የግብይት አባሉን ተጠቃሚዎች ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ እና ለተጠቃሚዎች ዝርዝር ማብራሪያን የሚገልጽ መሆን፤

(3) የግብይት አባላት የሚያደርጓቸው ሁሉም ግንኙነቶች፡-

ሀ) የግብይት አባሉን በግልጽ ለመግለጽ "የኢትዮጵያ ሰነደ መዋለ ንዋይ ገበያ የግብይት አባል" የሚሉትን ቃላት በመጠቀም መዘጋጀት አለባቸው፤ እና

ለ) በገበያው የግብይት አባል ካልሆነ ሰው ወይም ከግንኙነቱ ጋር ተዛማጅነት ያለው ግለሰብ ጋር ያለውን ማንኛውንም ግንኙነት ማንፀባረቅ አለበት።

(4) በኢንቨስትመንቶች፣ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች መካከል በግንኙነቶች የሚደረገው ማንኛውም ንጽጽር የኢንቨስትመንት ዓላማዎችን፣ ወጪዎችን፣ የገንዘብ አከል መስፈርቶች፣ ዋስትናዎችን ወይም ኢንሹራንስን፣ የዋና ወይም የትርፍ ገንዘብ መለዋወጥን እና የታክስ ባህሪያትን ጨምሮ በመካከላቸው ያሉትን ሁሉንም ቁልፍ ልዩነቶች መግለጽ አለበት።

(5) እያንዳንዱ የግብይት አባል ማንኛውንም ማስታወቂያ ከመታተሙ በፊት በከፍተኛ አመራር ደረጃ ለመገምገም ጠንካራ የውስጥ አሰራር ሥርዓት ማዘጋጀት እና ማቋቋም አለበት።

(6) ገበያው የግብይት አባላት ያወጡት ማስታወቂያ ወይም ግንኙነት የእነዚህን ደንቦች ማንኛውንም ድንጋጌ እንደሚጥስ ከተገነዘበ ማቆም፣ ማሻሻል፣ መመለስ ወይም መልሶ እንዲጠራ ሊጠይቅ ይችላል ።

## 8.2. የግብይት አባል ግንኙነቶች ውስጥ የሚካተቱ ምክሮች እና ምስክርነቶች

(1) የግብይት አባሉ ግንኙነት ምክሮችን የሚያካትት ከሆነ ግንኙነቱ፡-

ሀ) ለምክሮቹ ተገቢ ምክንያትን ያካተተ እና የግብይት አባሉን፣ ተሿሚ እንደራሴዎች ፣ ተያያዥ ወይም ቅርበት ያለው ሰው እና/ወይም የግብይት አባሉን ሌሎች ሰራተኞችን የፋይናንስ ፍላጎቶችን ጨምሮ በቂ መግለጫዎችን ማካተት አለበት፤

ለ) ለነባር ደንበኞች፣ ኢንቨስት ለሚያደርገው ሕዝብ እና ገበያው በጠየቀ ጊዜ ምክሩን የሚደግፉ የኢንቨስትመንት መረጃዎችን ማቅረብ አለበት፤ እና

ሐ) የታለመ ግንኙነት በሚፈጠርበት ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ምክር በምክንያታዊ ግምገማ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የደህንነት መዋቅር እና የአደጋ - ትርፍ መግለጫ የታለመ ግንኙነት ከሚደረግላቸው አካላት ልምድ፣ እውቀት፣ የኢንቨስትመንት ዓላማዎች፣ የአደጋ ፍላጎት እና የኪሳራ አቅም ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

(2) በጉዳዩ ላይ ሙያዊ አስተያየት ለመስጠት የሚያስፈልገው ተገቢ ብቃት ባለው ሰው ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛውም የግብይት አባል በግንኙነቶች ውስጥ የምስክርነት መግለጫዎችን ማካተት የለበትም።

(3) የግብይት አባል የሚያቀርበውን ሰነድ ወይም አገልግሎት በሚመለከት ምስክርነትን የያዘ ማንኛውም ግንኙነት፡-

ሀ) ምስክርነቱ የሌሎች ደንበኞችን ተሞክሮ ሊወክል እንደማይችል መግለጽ አለበት ፤

ለ) ምስክርነቱ የወደፊት አፈጻጸም ወይም ስኬት ዋስትና አለመሆኑን፤ እና

ሐ) ክፍያ የተከፈለበት ከሆነ፣ የተከፈለበት የምስክርነት መግለጫ መሆኑን መግለጽ አለበት።

## 8.3. በህዝብ ፊት መቅረብ እና ንግግር ማድረግ

(1) የግብይት አባል በሴሚናር፣ በመድረክ፣ በሬዲዮ ወይም በቴሌቭዥን ቃለ መጠይቅ ላይ ከተሳተፈ ወይም ስፖንሰር ካደረገ ወይም በጽሑፍ ወይም ያለጽሁፍ በሕዝብ ፊት ወይም በንግግር ሥራዎች ላይ ከተሰማራ፣ የግብይት አባሉን የሚወክለው ሰው እነዚህን ደንቦች ማክበር አለበት።

(2) እያንዳንዱ የግብይት አባል ተወካዮቹ በሕዝብ ፊት ቀርበው የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚያስችል ለንግድ ሥራው፣ ለመጠኑ፣ ለመዋቅሩ እና በደንበኞቹ ተገቢ የሆኑ የጽሁፍ አሰራር ሥርዓቶችን ማዘጋጀት አለበት፤

(3) በህዝብ ፊት በሚቀርቡበት ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ ማንኛውም ጽሑፎች፣ ስላይዶች፣ እጅ ጽሑፎች ወይም ሌሎች የተጻፉ፣ የታተሙ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶች ለሁሉም ጉዳዮች እና ዓላማዎች እንደ ግንኙነት ይቆጠራሉ።

## 8.4. የሶስተኛ ወገን ግንኙነት

የግብይት አባል የሶስተኛ ወገን መድረክን በመጠቀም ማስታወቂያ ወይም ግንኙነት በሚያደርግበት ወቅት ማስታወቂያው ወይም ግንኙነቱ የዚህን ደንብ መስፈርቶች ማክበር አለበት።

## 8.5. የግንኙነት መዝገብ

(1) የግብይት አባላት ገበያው በየወቅቱ ከሚደነግገው የመረጃ ማቆያ ጊዜ ላላነሰ ጊዜ በእነሱ የሚወጡትን ሁሉንም ግንኙነቶች ትክክለኛ መዝገቦችን መያዝ አለባቸው።

## 8.6. ለደንበኞች የሚሰጥ መረጃ

(1) የግብይት አባል እና እንደራሴው ለደንበኛ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የሚያደርገው ማንኛውም አስተያየት እና የሚሰጠው መረጃ፡-

ሀ) እውነተኛ እና ትክክለኛ መሆን አለበት፤

ለ) ግልጽ በሆነ፣ ከጥርጣሬ ወይም ከግራ ማጋባት በጸዳ ቋንቋ የቀረበ መሆን አለበት፣ እንዲሁም አሳሳች መሆን የለበትም፤

ሐ) ቁልፍ እውነታዎችን ወይም አደጋዎችን የማይደብቅ መሆን አለበት፣ ለምሳሌ ተገቢ ያልሆነ ፎንት፣ ቅርጸት ወይም የቁልፍ መረጃ አቀማመጥን በመጠቀም፤

መ) ማናቸውም የተካተቱ መግለጫዎችን አሳሳች እንዳይሆኑ አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም እውነታዎች ወይም ማስጠንቀቂያዎችን ማካተት ወይም ማጣቀስ፤

ሠ) የደንበኛውን የተረጋገጠ ወይም በተገቢው መንገድ የተገመተ የእውቀት ደረጃን ግምት ውስጥ በማስገባት ማንኛውንም የተካተቱ መግለጫዎች እንደ አገልግሎቱ ሁኔታ በቂ እና ተገቢ ሆነው መቅረብ አለባቸው፤

ረ) የተጠቀሱ መጠኖች፣ ድምሮች፣ ዋጋዎች፣ ክፍያዎች፣ወይም የገንዘብ ግዴታዎች በተወሰነ የገንዘብ ቃላት መንፀባረቅ አለባቸው፣ ማንኛውም እንዲህ ዓይነት መጠን፣ ድምር፣ ዋጋ፣ ክፍያ፣ ወይም ገንዘባዊ ግዴታ በተገቢው መንገድ ሊወሰን የማይችል ከሆነ፣ የስሌቱ መሠረት በአግባቡ መገለጽ አለበት፤

ቀ) አስፈላጊ ወይም ጉልህ ለውጦች ካልተከሰቱ ወይም ተገቢው አገልግሎት አስፈላጊ ካላደረገው በስተቀር ለተመሳሳይ ደንበኛ በድጋሚ ወይም እንደገና መነገር የለበትም፣ ወይም የአገልግሎቱ አይነት ይህንን አስፈላጊ ሲያደርገው፤ አስፈላጊ በሚሆንበት ሁኔታ ለደንበኛው ስለ ለውጦቹ ያለ መዘግየት ማሳወቅ አለበት፤ እና

በ) ለአካውንት ግብይት የሚካሄድበት ሁኔታን በተመለከተ፣ እንደአስፈላጊነቱ በግብይት አባሉ እንደገና መረጋገጥ አለበት።

(2) ማንኛውም የግብይት አባል፦

ሀ) በግብይት አባሉ ወይም ተፈጻሚነት ባለው ጊዜ ንግዱ ላይ በማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ሕግ መሠረት የደንበኛው የጽሑፍ ፈቃድ ካልተገኘ ወይም መረጃውን ይፋ ማድረግ ካልተፈለገ በቀር ስለ ደንበኛ ያገኘውን ወይም የተገኘውን ማንኛውንም ሚስጥራዊ መረጃ ይፋ ማድረግ የለበትም እና

ለ) ደንበኛው ሀብቶቹን ማግኘት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ማናቸውንም ገደቦች ወይም ክልከላዎች አስቀድሞ ለደንበኛው ሳያሳውቅ መቅረት የለበትም።

# ምዕራፍ 9 — የገበያ ከፋቾች

## 9.1. የገበያ ከፋች ሆኖ ስለመሾም እና የብቃት መስፈርቶች

(1) ገበያ ከፋች የሚለውን ስያሜ ለማግኘት ብቁ ለመሆን፡ - አመልካቾች፡

ሀ) ገበያው በየጊዜው ከሚገልጻቸው መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በገበያው ተቀባይነት ባለው የድርጅት አይነት የተመሰረተ መሆን አለበት፤

ለ) በገበያው በየጊዜው የሚወስነውን ዝቅተኛውን የካፒታል መስፈርቶች ማሟላት እና ከባለስልጣኑ የተሰጠ የገበያ ከፋች አገልግሎት ፈቃድ ያለው መሆን አለበት፤

ሐ) በተገቢው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ ግብይት ለመፈፀም እና/ወይም የግብይት ቁጥጥርን ለማድረግ ገበያው የወሰነው አስፈላጊው ብቃት እና ልምድ ያላቸው የተፈቀደላቸው የገበያ ከፋች ግብይት ፈፃሚ እና ሌሎች ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ሊኖሩት ይገባል፤

መ) የገበያ ከፋችነት ንግዱን በፍጥነት እና በተደራጀ መልኩ ለመስራት የሚያስችል በቂ የሆነ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፣ መገልገያዎች እና ሰራተኞች ሊኖሩት ይገባል፤ እና

ሠ) የገበያ ከፋችነት ግብይት ሥራን በአግባቡ ለማካሄድ፣ የአደጋ አስተዳደርን በትክክል ለመወጣት፣ የጥቅም ግጭትን በአግባቡ ለማስተዳደር እና ተፈጻሚነት ያላቸውን የዚህን ደንቦች ለማክበር ተገቢ የቁጥጥር ፕሮግራም እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

(2) ገበያ ከፋች ለመሆን የሚያመለክት አመልካች በገበያው በተገለጸው ቅጽ እና በገበያው በተዘጋጀው የመገናኛ ዘዴ ወይም መድረክ አማካኝነት ማመልከቻውን በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

(3) በገበያው የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ የገበያ ከፋች ለመሆን የሚቀርብለትን ማመልከቻ ገበያው ሊያጸድቀው ወይም ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ተገቢነትን፣ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትን፣ የፋይናንስ ሁኔታን እና የአመልካቹን፣ የዋና ዋና አክስዮን ባለቤቶቹን እና የተሾሙ ተወካዮቹን ብቃት እና ተገቢነት ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ ገበያው የገበያ ከፋች ለመሆን የቀረበውን ማመልከቻ ለማጽደቅ ግምት ውስጥ የሚያስገባቸው ነገሮች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያካትታሉ ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም፡-

i. አመልካቹ ወይም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን የመፍረስ ሂደት ውስጥ ያለ ወይም እንዲፈርስ በባለአክሲዮኖች ውሳኔ የተላለፈበት ወይም የፍ/ቤት ቤት ትዕዛዝ የተሰጠበት ስለመሆኑ፤

ii. አመልካቹ ወይም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮኑ ላይ በፍርድ ቤት የተሰጠው የዕዳ ክፍያ ውሳኔ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሳይፈጸም ቀርቶ ስለመሆኑ፤

iii. አመልካቹ ወይም ማንኛውም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮኑ ከባለዕዳዎቹ ጋር ዕዳን የማደራጀት ወይም የመጠባበቂያ ስምምነት የገቡ ስለመሆኑ፤

iv. በአመልካቹ ወይም ትልቅ ድርሻ ባለው ባለአክሲዮን ማንኛውም ንብረት ላይ በሞግዚት፣ አስተዳዳሪ፣ ፍርድ ቤት የሾመው አሰተዳዳሪ ወይም ተመሳሳይ ስልጣን እና ተግባር ያለው ሌላ ሰው የተሾመ ስለመሆኑ፤

v. ገበያው የአመልካቹ ወይም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን የፋይናንስ ሁኔታን አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው፤

vi. ገበያው የአመልካቹ ወይም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮኑ ንግድ ሲካሄድበት የቆየው ወይም የሚካሄድበት ሁኔታ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው፤

vii. አመልካቹ፣ ማናቸውም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮኖቹ፣ ተሿሚ እንደራሴዎቹ ወይም ሌሎች ሰራተኞቹ በማጭበርበር ወይም በማታለል ወንጀል ከተከሰሱ ወይም በማጭበርበር ወይም በማታለል እንደሰሩ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ ፤

viii. አመልካቹ፣ ማናቸውም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮኖቹ፣ ተሿሚ እንደራሴዎቹ ወይም ሌሎች ሰራተኞቹ በአዋጁ ወይም ገበያን እና ቁጥጥር የሚደረግባቸውን አካላት ለመቆጣጠር አግባብነት ያላቸውን ሕጎች እና የቁጥጥር መስፈርቶችን በመጣስ የተከሰሱ ከሆነ፤

ix. ገበያው የአመልካቹን የቀድሞ አፈጻጸም ሪከርድ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው፤

x. አመልካቹ፣ ማናቸውም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮኖቹ፣ ተሿሚ እንደራሴዎቹ ወይም ሌሎች ሰራተኞቹ በባለስልጣኑ እና/ወይም በገበያው የሚወሰኑ የልምድ እና የብቃት መስፈርቶችን ሊያሟሉ እንደሚችሉ ገበያው አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው፤

xi. አመልካቹ፣ ማናቸውም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮኖቹ፣ ተሿሚ እንደራሴዎቹ ወይም ሌሎች ሰራተኞቹ ሥራቸውን በብቃት፣ በሐቀኝነት እና ፍትሃዊነት ሊያከናውኑ እንደማይችሉ ገበያው ለመጠርጠር ምክንያት ካለው፤

xii. አመልካቹ ለደንበኞቹ፣ ለተወሰነ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ እና/ወይም የገበያውን ገበያ(ዎች) ከፍተኛ ጥቅም ለማስጠበቅ ላይሠራ እንደሚችል ገበያው ለመጠርጠር ምክንያት ካለው፤

(4) በአመልካቹ የንግድ እና የአሠራር መስክ ላይ ገደቦችን ማስቀመጥን ጨምሮ በእነዚህ ብቻ ሳይገደብ፣ ገበያው ተገቢ እንደሆነ የሚቆጥረውን ሁኔታ ወይም ገደብ እና ጊዜ በማስቀመጥ ማመልከቻውን ማፅደቅ ይችላል።

(5) ገበያው በማንኛውም ጊዜ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ወይም ገደቦችን መቀየር ወይም ማንሳት፣ ወይም ተገቢ ናቸው ብሎ የሚያምናቸውን ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎችን ወይም ገደቦችን ማስቀመጥ ይችላል።

(6) በገበያው እንደ ገበያ ከፋች የተፈቀደለት አመልካች ስሙ በገበያ ከፋቶች መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል። የግብይት ከፋቹ ምዝገባ ተፈፃሚ ስለሚሆንበት ቀን ገበያው ሁሉንም የግብይት አባላት እና ገበያ ከፋቾችን ያሳውቃል።

(7) እንደ ገበያ ከፋች እንዲፈቀድ የቀረበው ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገ፣ ማመልከቻው ውድቅ ከተደረገ በኂላ በሚቀጥሉት ሶስት (3) ወራት ውስጥ ተመሳሳይ አመልካች ሌላ ማመልከቻን ማቅረብ አይችልም።

## 9.2. የሂሳብ እና የስርዓት መስፈርቶች

(1) ገበያ ከፋች በሚከተሉት አንድ ወይም ከዚያ በላይ መንገዶች በተወሰኑ ሰነዶች ላይ ገበያ ሊከፍት ይችላል፡

ሀ) የራሱ በሆኑ ሂሳቦች፤ እና

ለ) በተዛማጅ ወይም ተባባሪ በሆኑት ኩባንያዎች ሂሳቦች፤

(2) ውጤታማ የገበያ መረጃ ፍሰትን ለማመቻቸት እና የውሳኔ አሰጣጥ እና የግብይት ሂደቱን ለማሻሻል የገበያ ከፋቹ ውስጣዊ ስርዓቶች በገበያው ዝርዝር መግለጫዎች መሰረት ከገበያው ስርዓቶች ጋር መቀናጀት አለባቸው።

(3) የገቢያ ከፋቹ ውስጣዊ ስርዓቶች የሚከተሉትን የሚያካትቱ ባህሪያትን መደገፍ አለባቸው፡-

ሀ) በገበያው የተገለጸው የገበያ ትዕዛዝ አፈፃፀም አስተዳደር ስርዓት፤

ለ) ወቅታዊ የገበያ መረጃ መሰብሰብ፣ ማዋሃድ እና ማሰራጨት፤እና

ሐ) ደህንነቱ የተጠበቀ እና ብቃት ያለው ግንኙነት።

## 9.3. የገበያ ከፋች ቀጣይ ግዴታዎች

(1) ገበያ ከፋች፡-

ሀ) በተከታታይ ወይም በቂ የሆነ የተጣራ ገበያ እንዲኖርና ለሕዝብ ተገቢ መረጃ እንዲሰጥ ለማስቻል ገበያው በሚያዘው ሌላ መንገድ፤

ለ) ገበያው በሚወስነው ከፍተኛው እና ዝቅተኛው የዋጋ ልዩነት መጠን ውስጥ፤

ሐ) ገበያው በየጊዜው ከሚወስነው ዝቅተኛ መጠን ባላነሰ ሁኔታ፤

መ) ገበያ ከፋቹ በፈቃዱ መውጣት ለማይችልበት ዝቅተኛው የውል ግዴታ ጊዜ። ዝቅተኛው የውል ግዴታ ጊዜ በተለያየ ጊዜ በገበያው መወሰን እና መገለጽ አለበት፤ እና

ሠ) ማገድን ጨምሮ ገበያው በተለየ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ የግብይት ገደብ ከጣለ፣ ገደቦቹን በማይጥስ መንገድ፤

በግብይቱ ስርዓቱ ላይ የዋጋ ማቅረቢያ እና የዋጋ ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

(2) ገበያ ከፋች በማንኛውም ምክንያት የዋጋ ማቅረቢያ እና የዋጋ ጥያቄ ማቅረብ ሲያቆም በተቻለ ፍጥነት፦

ሀ) ማቆሙን እና ለማቆሙ ያለውን ምክንያት ለገበያው ማሳወቅ አለበት፤ እና

ለ) ማቆሙን ለህዝብ በይፋ ማሳወቅ አለበት።

(3) ገበያ ከፋች እንደገና አገልግሎት መስጠት ሲጀምር በተቻለ ፍጥነት ለገበያው እና ለህዝብ ማስታወቅ አለበት።

(4) በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም፣ ገበያ ከፋች ለተወሰነ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከዘጠና (90) ቀን በላይ የዋጋ ማቅረቢያ እና የዋጋ ጥያቄ ማቅረብ ካቆመ፣ ገበያ ከፋቹ ለተጠቀሰው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ከፋች ለመሆን የተሰጠው ፈቃድ ወዲያው እንደተሰረዘ ይቆጠራል።

(5) የገበያ ከፋቹ ሊፈጸሙ የሚችሉ ዋጋዎችን ለመጠበቅ ያለበት ግዴታ በግብይት መቋረጥ፣ መታገድ ወይም መዘጋት ወቅት እና ገበያው በየጊዜው በሚገልፃቸው ልዩ ሁኔታዎች ወቅት አይተገበርም። ምንም አይነት የግብይት መቋረጥ፣ መታገድ ወይም መዘጋት ስለመኖሩ በግምት አይወሰድም ነገር ግን ገበያው ለገበያ ከፋቹ በጽሁፍ መግለጽ አለበት።

(6) ገበያ ከፋች ሌሎች እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውን ከሆነ፣ ገበያ ከፋቹ በገበያ ከፋችነት እንቅስቃሴዎች እና በሌሎች እንቅስቃሴዎች መካከል ተገቢ የሆኑ የተለያዩ ሂደቶችን እና ስርዓቶችን ማቋቋም እና ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

(7) እያንዳንዱ ገበያ ከፋች የግብይት አባሉ እና ሰራተኞቹ በእነዚህ ደንቦች የተደነገገውን የመረጃ ገደብ መስፈርቶች ማክበራቸውን ማረጋገጥ አለበት።

(8) ገበያ ከፋች በእነዚህ ደንቦች መሠረት በሚኖረው ግዴታዎቹ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ለውጦችን በውስጣዊ ቁጥጥር ስርዓቱ ላይ ከማድረጉ በፊት ለገበያው በጽሁፍ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት።

(9) ማንኛውን ገበያ ከፋች በእነዚህ ደንቦች የተገለጹትን የብቃት መስፈርቶች በቀጣይነት ማክበር አለበት፣ እንዲሁም ከሚከተሉት ውስጥ ማንኛውም ነገር ከተከሰተ በኋላ ባለው አንድ (1) የሥራ ቀን ውስጥ ለገበያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፦

ሀ) ገበያ ከፋቹ ከዝቅተኛው የካፒታል መስፈርቶች በታች እንዲወርድ የሚያደርገው የካፒታል ለውጥ፤

ለ) የገበያ ከፋቹ ማንኛውም የአድራሻ ወይም የንግድ ሥራ ቦታ ለውጥ፤

ሐ) የገበያ ከፋቹ ስም ለውጥ፤

መ) የባለአክሲዮን ስብጥር እና የዳይሬክተሮች ቦርድን ጨምሮ ሌሎች የገበያ ከፋቹ የድርጅታዊ መዋቅር ለውጥ፤ እና

ሠ) የገበያውን ደንቦች መሠረት በማድረግ ምዝገባውን ሊጎዳ ወይም እንደ ገበያ ከፋችነት እንዳይቀጥል ሊያደርግ የሚችል ማንኛውም እንቅስቃሴ ወይም ክስተት መፈጠር።

(10) ለውጥን ወይም እንቅስቃሴን ለገበያው አስቀድሞ በማሳወቅ ይሁንታን ማግኘት የገበያ ከፋች አባልነት ሰርተፊኬትን ወይም ሌላ ምዝገባን አስጠብቆ ለማስቀጠል እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠየቅ ከሆነ፣ በዚህ ደንብ ውስጥ የተደነገገው በገበያ ከፋቹ ላይ የተጣለውን እንዲህ ያለውን ግዴታ አያስቀርም።

(11) እነዚህ ደንቦች መከበራቸውን ለመገምገም ገበያው በየጊዜው፣ በአጋጣሚ፣ ወይም በድንገት በቦታቸው ወይም ከቦታቸው ውጭ ገበያ ከፋቾች ላይ ምርመራዎችን ማድረግ ይችላል።

## 9.4. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታዎች

(1) በሂሳብ መግለጫዎቹ ማስታወሻዎች ውስጥ በቂ መግለጫዎች ማቅረብን ጨምሮ ገበያ ከፋቹ ለገበያው በሚያቀርበው ወቅታዊ ሪፖርት የግብይት መክፈት እንቅስቃሴዎቹን በተመለከተ ግልጽ፣ ተገቢና በቂ መረጃ ማቅረብ አለበት።

(2) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ የገበያ ከፋቹን የሥራ አፈጻጸም ወይም ተስማሚነት ለመገምገም እንዲያስችል ከገበያ ከፋቹ የፋይናንስ አቋም፣ ሰራተኞች እና/ወይም ውስጣዊ ቁጥጥር ሂደቶች ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን የሚያሳይ በጊዜያዊነት የተዘጋጀ እና በገለልተኛ ኦዲት የተረጋገጠ ሪፖርት እንዲያቀርብ ገበያው የገበያ ከፋቹን ሊጠይቅ ይችላል።

## 9.5. የገበያ ከፋች መውጣት

(1) የድርጅቱን፣ትልቅ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖችን እና የተሿሚ እንደራሴዎችን ተገቢነት፣ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፣ የፋይናንስ ሁኔታ እና ብቃት እና ተገቢነትን ግምት ውስጥ በማስገባት በገበያው ለተመዘገበ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ከፋችነት ምዝገባ የሰጠውን ፈቃድ ገበያው በራሱ ውሳኔ ሊሰርዝ ይችላል።

(2) ገበያው በየጊዜው የሚወስነው እና የሚያሳውቀው ዝቅተኛ የውል ግዴታ ጊዜ ሲያበቃ ብቻ ገበያ ከፋቹ ከተወሰነ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ከፋችነት ሚናው በፈቃደኝነት ለመልቀቅ ማመልከት ይችላል።

(3) በካፒታል ገበያ የአገልግሎት አቅራቢዎች ፈቃድ እና ቁጥጥር መመሪያ የተደነገጉት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ገበያ ከፋች ከተወሰነ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ከፋችነት ሚናውን ለመልቀቅ ሲፈልግ፣ ለመውጣት ከሚፈልግበት ቀን ቢያንስ ሠላሳ (30) ቀናት በፊት ማስታወቂያ ለገበያው መስጠት አለበት። እንዲህ ዓይነቱ ማስታወቂያ በገበያው በተገለጸው ቅጽ እና በገበያው በተዘጋጀው መድረክ ወይም መሳሪያ በጽሁፍ መሆን አለበት።

(4) ገበያው ለመውጣት የቀረበውን ማመልከቻ የመቀበል፣ መውጣቱ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ቀን የማራዘም እና/ወይም ገበያው ሊወስዳቸው የሚችላቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ገበያ ከፋቹ ከመውጣቱ በፊት ወይም ከወጣ በኋላ ተገቢ ናቸው ብሎ የሚያምናቸውን እርምጃዎችን ለመውሰድ ውሳኔ የመስጠት ብቸኛ ስልጣን አለው።

(5) በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (4) የተደነገገው ቢኖርም፣ ገበያው በራሱ ውሳኔ መሠረት፡-

ሀ) በእነዚህ ደንቦች መሠረት ምርመራ እያካሄደ ከሆነ፣ ቅሬታ እየመረመረ ከሆነ፣ ወይም በገበያ ከፋቹ ላይ የዲሲፕሊን ሂደት ከጀመረ፤ ወይም

ለ) ገበያ ከፋቹ ለገበያው ያለውን ሁሉንም ግዴታዎች መወጣቱን ወይም መወጣት እንደሚችል እርግጠኛ ካልሆነ፤

በገበያ ከፋቹ የቀረበውን የመውጣት ጥያቄን ውድቅ ማድረግ ይችላል።

(6) ለተወሰነ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የገበያ ከፋች ምዝገባው ሲሰረዝ ወይም ከተወሰነ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ከፋችነት ለመውጣት የቀረበው ጥያቄ በገበያው ሲጸድቅ፣ የሚከተሉት ይተገበራሉ፡-

ሀ) ተመሳሳይ ድርጅት በተጠቀሰው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ እንደ ገበያ ከፋች ዳግም ለመመዝገብ የሚያቀርበው ማንኛውም ማመልከቻ ከመሰረዙ ወይም ከመልቀቁ ቀን በኋላ ባሉት ስድስት (6) ወራት ውስጥ ተቀባይነት አያገኝም፤

ለ) የድርጅቱ ስም ከሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የገበያ ከፋቾች መዝገብ ላይ ይሰረዛል፤

ሐ) መሰረዙ ወይም መልቀቁ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ቀን ግምት ውስጥ በማስገባት፤ ድርጅቱ ለተወሰነ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በተመዘገበበት ጊዜ ውስጥ በገበያው ደንቦች መሠረት ወይም ከነዚህ ጋር በተያያዘ ለተከሰቱ ማንኛውም ክንውኖች ለገበያው እና ለደንበኞቹ እንደ አግባቡ ተጠያቂ ሆኖ ይቀጥላል፤ እና

መ) ድርጅቱ ምዝገባው ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ውስጥ ለተፈጸመ የገበያው ደንብ ጥሰት በዲሲፕሊን ሂደት እና እርምጃ ተገዢ ሆኖ ይቀጥላል።

## *ምዕራፍ 10 - ስፖንሰር አድራጊ ደላላ፣ ገበያ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ ዲጂታል ንዑስ ደላላዎች*

**10.1. ለስፖንሰር አድራጊ ደላላነት፣ ለገበያ አከናዋኝነት ወይም ለኢንቨስትመንት ባንክ ዲጂታል ንዑስ ደላላነት እውቅና ለማግኘት ቀዳሚ መስፈርቶች**

(1) እንደ ለስፖንሰር አድራጊ ደላላነት፣ ገበያ አከናዋኝነት ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ ዲጂታል ንዑስ ደላላነት እውቅና ለማግኘት የሚፈልግ አመልካች፡-

ሀ) የኢንቨስትመንት ባንክ፣ የሰነደ ሙዓለንዋዮች ገበያ አከናዋኝ ወይም የሰነደ ሙዓለንዋዮች ደላላነት የአባልነት ሰርተፊኬት ከገበያው ሊኖረው ይገባል፤

ለ) ተፈፃሚነት ባላቸው የባለስልጣኑ መመሪያዎች መሰረት ለዲጂታል ንዑስ ደላሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ለማቅረብ ሁሉም አስፈላጊ ስርዓቶች እና ሂደቶች እንዳሉት ማረጋገጥ አለበት፤ እና

ሐ) ከእሱ ጋር ግብይት ለማድረግ የሚፈልገው ዲጂታል ንዑስ ደላላ የሚያስፈልገውን የአገልግሎት ፈቃድ ከባለስልጣኑ እንዳገኘ ማረጋገጥ አለበት።

(2) የግብይት አባሉ ከዲጂታል ንዑስ ደላላ ስር ሂሳብ መክፈት ወይም የዲጂታል ንዑስ ደላላ ደንበኛ መሆን አይችልም፣ ወይም በሌላ መንገድ በዲጂታል ንዑስ ደላላ በኩል ለራሱ ማንኛውንም ግብይት ማከናወን የለበትም።

(3) ስፖንሰር አድራጊ ደላላ፣ ገበያ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ ዲጂታል ንዑስ ደላላ ሆኖ እውቅና ለማግኘት፣ የግብይት አባሉ ከዲጂታል ንዑስ ደላላ ጋር ግብይት ከመጀመሩ ቢያንስ ከአስር (10) የሥራ ቀናት በፊት በገበያው በተወሰነው ቅጽ መሠረት በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል። በዚህ መልኩ ለገበያው የሚሰጠው ማስታወቂያ በሚከተሉት የተደገፈ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ) ለዲጂታል ንዑስ ደላላው ከባለስልጣኑ የተሰጠው የአገልግሎት ፈቃድ ዋና እና ቅጂ፤

ለ) ለግብይት አባሉ ከባለስልጣኑ የተሰጠው የአገልግሎት ፈቃድ ዋና እና ቅጂ፤

ሐ) በግብይት አባሉ የተሞላ እና የተፈረመ መደበኛ የዋስትና እና የካሳ ሰነድ፤ እና

መ) ገበያው ሊጠይቀው የሚችለው ማንኛውም ሌላ መረጃ ወይም ሰነድ።

10.2. የስፖንሰር አድራጊ ደላላ፣ ገበያ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ ቀጣይ ግዴታዎች

(1) በገበያው ለዲጂታል ንዑስ ደላላ፣ እንደ ስፖንሰር አድራጊ ደላላ፣ ገበያ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ እውቅና የተሰጠው የግብይት አባል ከገበያው ጋር በተያያዘ የእንደዚህ አይነት ዲጂታል ንዑስ ዳላላ እንቅስቃሴዎች ለደንበኞች በገበያው ላይ ሰነደ ሙዓለ ንዋይዎችን ለመሸጥ እና ለመግዛት የዲጂታል መንገዶችን በማቅረብ ብቻ የተገደቡ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ይኖርበታል።

(2) የግብይት አባል ዲጂታል ንዑስ ደላላው የሚከተሉትን ያከበረ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት፦

ሀ) በየጊዜው የሚሻሻሉ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች፣ እንዲሁም ገበያው የሚያወጣቸው ሌሎች ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን እና ሰነዶችን፤ እና

ለ) ከደንበኛዎን ይወቁ ጋር የተያያዙትን ጨምሮ ሁሉንም የካፒታል ገበያ ህጎች፣ አዋጁን፣ መመሪያዎችን እና ደንቦችን።

(3) የግብይት አባላት የዲጂታል ንዑስ ደላላውን እንቅስቃሴዎች ውስጣዊ ግምገማ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፤ እንዲሁም የዲጂታል ንዑስ ደላላውን እንቅስቃሴዎች ለመከታተል የቁጥጥር ዘዴዎች እንዲኖሩ ማረጋገጥ አለባቸው።

(4) ከግብይት አባል ጋር ንግድ የሚያካሂድ ዲጂታል ንዑስ ደላላ የዚህን ደንብ ማንኛውንም ድንጋጌዎች የጣሰ እደሆነ፣ ገበያው እንደዚህ ዓይነቱን ዲጂታል ንዑስ ደላላ ስፖንሰር አድርጎ የተመዘገበውን የንግድ አባል በጥሰቱ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን ቅጣት ተፈፃሚ ሊያደርግበት ይችላል።

(5) በግብይት አባል እና በእነዚህ ደንቦች መሠረት እውቅና በተሰጠው የዲጂታል ንዑስ ደላላ መካከል ያለው ግንኙነት በማንኛውም ምክንያት ከተቋረጠ፣ የግብይት አባሉ ከመቋረጡ በኋላ ባሉት ሃያ አራት (24) ሰዓታት ውስጥ ለገበያው ግንኙነቱ መቋረጡን እና የተቋረጠበትን ምክንያት ማሳወቅ አለበት።

(6) ባለስልጣኑ ለገበያው ሲያሳውቅ ወይም ገበያው በሌላ መንገድ በዲጂታል ንዑስ ደላላው ላይ የተወሰደ የፍርድ ወይም የህግ አፈፃፀም እርምጃ መኖሩን

ሲያውቅ፣ የአፈፃፀም እርምጃው እልባት እስኪያገኝ ገበያው ለዲጂታል ንዑስ ደላላው ስፖንሰር አድራጊ ግብይት አባል የሰጠው ዕውቅና ታግዶ ይቆያል፡፡

(7) ማንኛውም የግብይት አባል የአገልግሎት ፈቃዱ በባለስልጣኑ ከታገደበት ወይም ከተሰረዘበት የዲጂታል ንዑስ ደላላ ጋር ምንም አይነት ግብይት ማካሄድ የለበትም፡፡

(8) ገበያው ዲጂታል ንዑስ ደላላው የእነዚህን ደንቦች ማንኛውንም ድንጋጌ መጣሱን ከተረዳ፣ እንደዚህ ያለውን ዲጂታል ንዑስ ደላላን ሊያግደው እና የግብይት አባላት ከዲጂታል ንዑስ ደላላው ጋር ማንኛውንም እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ መከልከል ይችላል፡፡

# *ክፍል 3 — የካሳ ፈንድ*

## *ምዕራፍ 11 — የደንበኞች ካሳ ፈንድ*

### 11.1. የደንበኞችን የካሳ ፈንድ ማቋቋም እና የፈንዱ መዋጮ

(1) ገበያው በገለልተኛ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚተዳደር የደንበኞች ካሳ ፈንድ ሊያቋቁም እና ሊያስተዳደር ይችላል፡፡

(2) እንዲህ ያለው ፈንድ በአዋጁ ክፍል አስራ ሶስት ከተደነገገው የኢንቨስተሮች ካሳ ፈንድ ተለይቶ መታየት እና መረዳት አለበት፡፡

(3) ሥራ ለመጀመር እና የአባልነት የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚያስፈልጉት ሁኔታዎች አንዱ ቅድመ ሁኔታ በመሆን፣ እያንዳንዱ የግብይት አባል፤ ገበያው በየጊዜው የሚወስነውን እና ባለስልጣኑ ያጸደቀውን ወይም ገበያው የሚወስነውን ተመላሽ የማይሆን ውስን የገንዘብ መጠን ለፈንዱ ማስጀመሪያ መዋጮ መክፈል ይኖርበታል፡፡

(4) ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ እያንዳንዱ የግብይት አባል በገበያው በሚወሰን መሰረት ዓመታዊ የፕሪሚየም ክፍያ ለፈንዱ መክፈል አለበት፡፡

### 11.2. የፈንዱ አስተዳደር እና አመራር

(1) የገበያው የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከአምስት (5) አባላት በማይበልጥ ቁጥር እንደሚከተለው ይደራጃል፡-

ሀ) ከገበያው የግብይት አባላት ተወካይ፤

ለ) ከገበያው ተወካይ፤

ሐ) ከማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ተወካይ፤

መ) ከባለስልጣኑ ተወካይ፤ እና

ሠ) የተመዘገቡ የአክስዮን ባለቤቶች ማህበር/ወይም ተመሳሳይ የኢንዱስትሪ ቡድንን፣ ገለልተኛ ባለሙያዎችን ወዘተ የሚወክል አንድ (1) ሰው።

(2) ሹመታቸው በባለስልጣኑ የሚጸድቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የደንበኞች ካሳ ፈንድ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በገበያው ይሾማሉ። ሹመቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአራት (4) ዓመታት ይሆናል።

(3) ገበያው ከወሰነ እና በባለስልጣኑ ሲጸድቅ፣ አንድ አባል ለተጨማሪ አራት (4) ዓመታት እንደገና ሊሾም ይችላል ሆኖም ከዚያ በላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል መሆን አይፈቀድም።

(4) የደንበኞች ካሳ ፈንድ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሚከተለው ከሆነ አባልነቱ ያቆማል፦

ሀ) የስልጣን ዘመኑ ካለቀ፤

ለ) ለፈንዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ወይም ፀሐፊ በተጻፈ የጽሁፍ ማስታወቂያ ከስልጣኑ ከለቀቀ።

ሐ) የስልጣን ዘመኑ ከማብቃቱ በፊት በቦርዱ ዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ ከሚወክለው ድርጅት አባልነት ከወጣ፤

መ) በዳይሬክተሮች ቦርድ ያለው አባልነቱ በቦርዱ ዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ በሚወክለው ድርጅት ከተነሳ፤

ሠ) በማንኛውም ሙያዊ አካል ወይም ማህበር በማንኛውም የማጭበርበር ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ወይም በሥነ ምግባር ጥሰት ቅጣት ከተጣለበት፤ ወይም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የማጭበርበር ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፤

ረ) ከቦርዱ አባላት ውስጥ ቢያንስ የሁለት ሶስተኛውን ድጋፍ ባገኘው የቦርዱ ዳይሬክተሮች ውሳኔ በቦርዱ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነቱ ባለው ሃላፊነት ላይ አሉታዊ ወይም የማይጣጣም እንቅስቃሴ እንደሚያደርግ ከተገመገመ፤

ሰ) በአእምሮ ወይም በአካል የቦርዱን እንቅስቃሴዎች ለመወጣት የማይችል ከሆነ። ብቁ እና ተገቢ መሆኑን ካቆመ።

(5) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የደንበኞችን የካሳ ፈንድ የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፣ እንዲሁም ፈንዱን በእነዚህ ደንቦች መሠረት መያዝ፣ ማስተዳደር እና መጠቀም አለበት።

(6) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈንዱን ለማስተዳደር በሚያስተላልፈው ውሳኔ፦

ሀ) ኃላፊነቶቹን በብቃት ለመወጣት አስፈላጊ እንደሆነ በሚቆጥረው መጠን እንደ ጠበቃ፣ የሂሳብ ባለሙያ፣ ኦዲተር ያሉ ባለሙያዎችን ሊቀጥር ይችላል፤

ለ) የቦርድ ንዑስ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፤ በተለይም፤ የካሳ መብት ለማግኘት የባለሀብቱን ተገቢነት እና ሊከፈለው የሚገባውን መጠን ለመወሰን እንዲረዳው ንዑስ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፤ እና

ሐ) ከሶስት (3) ያላነሱ እና ከአምስት (5) ያልበለጡ አባላትን የያዘ የአስተዳደር ንዑስ ኮሚቴ ሊሾም ይችላል።

(7) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያሳልፈው ውሳኔ በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀጽ (6) ለተሾመ ማንኛውም ንዑስ ኮሚቴ ሁሉንም ወይም ማንኛውንም ስልጣኑን ሊወክል ይችላል፤

(8) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለኮሚቴው በውክልና የሰጠው ማንኛውም ስልጣን፣ ኃላፊነት ወይም ፈቃድ በንዑስ ኮሚቴው አብላጫ ድምጽ ባላቸው አባላት ጥቅም ላይ ይውላል። ይህም ስልጣን፣ ኃላፊነት ወይም ፈቃድ በንዑስ ኮሚቴው አባላት አብላጫ ድምጽ ተሰጥቶት እንደነበር ይቆጠራል።

(9) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሰጠው ማንኛውም ውክልና በማንኛውም ጊዜ በተመሳሳይ መንገድ ሊሻር ወይም ሊሻሻል ይችላል።

(10) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በዚህ ክፍል መሠረት የሾመውን ማንኛውንም የንዑስ ኮሚቴ አባል በማንኛውም ጊዜ ሊያነሳው እና በማንኛውም ምክንያት በንዑስ ኮሚቴው የተፈጠረውን ማንኛውንም ክፍተት ለመሙላት ይችላል።

(11) የቦርዱ ንዑስ ኮሚቴ ውሳኔ በደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ እስኪረጋገጥ ወይም እስኪጸድቅ ድረስ አይጸናም።

## 11.3. ወደ ደንበኞች የካሳ ፈንድ የሚከፈሉ ክፍያዎች

(1) ወደ ፈንዱ የሚከፈሉት፡-

ሀ) ከገበያው የግብይት አባል የሚገኙ መዋጮዎች፣ ይህም የሚያካትተው፡-

i. የገበያው የግብይት አባል በሚሆንበት ጊዜ የሚከፈል መጠኑ በገበያው የተወሰነና ተመላሽ የማይሆን አስገዳጅ የመጀመርያ ክፍያ፤ የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው በሚወስነው፣ በገበያው በሚጸድቀው እና በካሳ ፈንድ ደንብ እና/ወይም መመሪያዎች መሰረት በባለስልጣኑ ሲጸድቅ አስገዳጅ የመጀመሪያ ክፍያ መጠኑ ሊለወጥ ይችላል፤

ii. ገበያው በሚያጸድቀው እና በባለስልጣኑ በሚፈቅደው አግባብ መሰረት መጠኑ በደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው የሚወሰን ዓመታዊ ክፍያ፤ እና

iii. ገንዘቡ ለፈንዱ ከጸደቀው ዝቅተኛ መጠን በታች ሲሆን ማንኛውንም ልዩነት ለማካካስ የሚውል መጠኑ በካፒታል ገበያ የካሳ ፈንድ ደንብ መሠረት ቦርዱ በየጊዜው የሚወስነው ጊዜያዊ ክፍያ።

ለ) ከፈንዱ ኢንቨስትመንት የሚገኙ ወለድ እና ትርፍ፤

ሐ) በአዋጁ እና/ወይም በእነዚህ ደንቦች የተሰጠውን ማንኛውንም የመክሰስ መብት በመጠቀም በደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በስሙ የተመለሱ ሁሉም ገንዘቦች፤

መ) በገበያው የግብይት አባል ወይም በተቆጣጣሪ ቦርድ በተገባ የኢንሹራንስ ወይም የካሳ ውል መሠረት በኢንሹራንስ ተቋም የተከፈሉ ሁሉም ገንዘቦች፤

ሠ) ከገበያው ወይም ከሌሎች ተቋማት እና ግለሰቦች በድጎማ፣ በልገሳ ወይም በክፍያ የተገኙ ሁሉም ገንዘቦች፤

ረ) የማንኛውም የኢንቨስትመንት ገቢ ወይም የሽያጭ ገቢ ሆነው የተገኙ ሁሉም ገንዘቦች፤ እና

ሰ) ለፈንዱ ዓላማ ቦርዱ ከገበያው የተበደራቸው ገንዘቦች።

ሸ) በአዋጁ፣ በካሳ ፈንድ መመሪያዎች እና በካፒታል ገበያ የካሳ ፈንድ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ግቦቹን እና ዓላማዎቹን ለማሳካት ፈንዱ የተቀበላቸው ሌሎች ማናቸውም ገንዘቦች።

(2) በደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ መደበኛ ውሳኔ በተሰጠው ስልጣን ወይም እንዲህ ያለውን ክፍያ የሚያፀድቅ በቦርዱ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በሙሉ በተፈረመ የጽሁፍ ውሳኔ መሰረት ካልሆነ በስተቀር የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈንዱን ለማንኛውም ክፍያ መጠቀም የለበትም።

(3) የፈንዱ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ በየጊዜው በዳይሬክተሮች ቦርድ ይወሰናል፣ ይህም በገበያው መፅደቅ ይጠበቅበታል።

## 11.4. የደንበኞችን የካሳ ፈንድ መለየት

የፈንዱ አካል የሚሆኑ ሁሉም ገንዘቦች የደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው በሚወስነው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ ተለይቶ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ይከፈላሉ ወይም ይተላለፋሉ፣ ይህም በአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት ፈንዱ ለኢንቨስትመንት ከመዋሉ ወይም ከመተግበሩ በፊት በገበያው አስቀድሞ በተፈቀደው መሰረት ይሆናል።

## 11.5. ከፈንዱ የሚከፈሉ ክፍያዎች

(1) በየጊዜው ከፈንዱ የሚከፈሉት፡-

ሀ) በእነዚህ ደንቦች መሠረት ለባለሀብቶች ካሳ ለመክፈል ለደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚያስፈልጉት ገንዘቦች፤

ለ) በየደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለፈንዱ ዓላማዎች ከገበያው ለወሰዳቸው ብድሮች ዝግጅት፣ አገልግሎት ወይም ክፍያ ለመክፈል የሚያስፈልጉ ገንዘቦች፤

ሐ) በየደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለፈንዱ ዓላማዎች በተወሰዱ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ላይ የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

መ) ፈንዱን በማቋቋም ለተገኙ የባለሙያ አገልግሎቶች የሚመነጩ ወጪዎችን፣ የፈንዱ የኦዲት ባለሙያ ክፍያዎች እና ወጪዎችን፣ የፈንዱ ሰራተኞች ወጪዎችን፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለየደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ለፈንዱ አገልግሎት ለመስጠት በደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የተሾሙ አማካሪዎች የባለሙያ ክፍያዎች እና ወጪዎችን ጨምሮ የደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአስተዳደር እና በአመራር ወቅት የተከሰቱ ሁሉም ወጪዎችን ለመሸፈን፤ እና

ሠ) በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት ከፈንዱ ሊከፈሉ የሚችሉ እንደሆነ የተጠቀሱ ሌሎች ገንዘቦች ለመክፈል።

(2) ከፈንዱ የሚፈጸሙ የካሳ ክፍያዎች በገንዘብ ብቻ የሚከፈሉ ይሆናሉ።

## 11.6. ካሳ

የተፈጸሙት ወይም መፈጸም ሲገባቸው ያልተፈጸሙት ድርጊቶች ከክፉ ልቦና የመነጩ እስካልሆኑ ድረስ፣ የየደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና ማንኛውም አባላቱ፣ ባለስልጣናቱ ወይም ሰራተኞቹ በእነዚህ ደንቦች መሠረት የደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች

ቦርድ ተግባራትን በመወጣት ላይ በተፈፀመ ወይም መፈጸም ሲገባው ባልተፈጸመ ነገር ምክንያት ከሚደርስባቸው ማንኛውም ኃላፊነት ከፈንዱ ይካሳሉ፡፡ በእነዚህ ደንቦች መሠረት ሊከፈል የሚገባው ማንኛውም መጠን በተከፈለበት የፋይናንስ ዓመት የአስተዳደር ወጪ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

## 11.7. መዝገቦች እና ሪፖርት ማቅረብ

(1) የየደንበኛ ካሳ ፈንድ ቦርድ ከካሳ ፈንድ ደንብ ጋር በሚጣጣም መልኩ በተከታታይ በእያንዳንዱ የፋይናንስ ዓመት ላይ የፈንዱን እንቅስቃሴዎች እና አስተዳደርን የሚመለከት ዓመታዊ ሪፖርት ለባለስልጣኑ እና ለገበያው ያቀርባል፣ ይህም በተመዘገበበት ዓመት ማብቂያ ላይ ባሉት ሶስት (3) ወራት ውስጥ ይዘጋጃል፡፡ ለባለስልጣኑ የሚቀርበውን ዓመታዊ ሪፖርትን በተመለከተ የተደነገገው የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በፈንዱ የመጀመሪያ የሥራ ዓመት ላይ አይተገበርም፡፡

(2) የዓመታዊ ሪፖርቱ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) በዓመቱ ውስጥ በፈንዱ ያለውን እንቅስቃሴ የሚያሳዩ እና በዓመቱ መጨረሻ ላይ የፈንዱን የንብረት እና የዕዳ ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫን የያዙ በዓለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች (IFRS) እና በኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ወይም ማንኛውም አግባብነት ያለው የኢትዮጵያ ባለስልጣን በሚያወጣው የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ ህጎች መሠረት የተዘጋጁ የፋይናንስ መግለጫዎች፣

ለ) በዓመቱ ውስጥ ወደ ፈንዱ የገቡ እና ከፈንዱ የወጡ ሁሉንም ክፍያዎች የሚያመለክት የሂሳብ መግለጫ፤

ሐ) በፋይናንስ ዓመት ውስጥ የፈንዱን እንቅስቃሴዎች የሚያሳይ የቦርዱ ሊቀመንበር መግለጫ፤ እና

መ) የፈንዱ የውጪ ገለልተኛ ኦዲተሮች ሪፖርት፡፡

(3) ቦርዱ የገበያው ኦዲተሮች የፈንዱ ኦዲተሮች ሆነው እንዳይሾሙ ማረጋገጥ አለበት፡፡

(4) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለባለስልጣኑ እና ለገበያው የቀረቡ ሁሉም የፈንዱ ዓመታዊ ሪፖርቶች በገበያው ድረ-ገጽ ወይም የደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚወስነው ሌላ ድረ-ገጽ ላይ እንዲታዩ ማረጋገጥ አለበት፡፡

(5) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣኑን እና ተግባሩን በመወጣት ላይ ዝርዝር መረጃ በየሩብ ዓመቱ ለገበያው ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

(6) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈንዱን በማስተዳደር ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ ጉልህ ክስተቶችን ለባለስልጣኑ እና ለገበያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

(7) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የፈንዱን ግብይቶች የሚያሳዩ እና የሚያብራሩ መዝገቦችን መያዝ አለበት እና፡-

ሀ) በማንኛውም ጊዜ የፈንዱን የፋይናንስ ሁኔታ ይፋ ማድረግ እና የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በእነዚህ ደንቦች የሚጠየቁትን ሪፖርቶች እንዲያቀርብ ማስቻል አለበት፤ እና

ለ) ተፈፃሚነት ባላቸው ሕጎች ወይም በገበያው በተደነገገው ዝቅተኛ ይዞ ማቆያ ጊዜ ውስጥ እንደዚህ ያሉ መዝገቦችን ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

### 11.8. የህዝብ ግንዛቤ ማስጨበጥ

የደንበኞች ካሳ ፈንድ  የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው በመረጠው የመረጃ ማሰራጫመንገድ ስለ ፈንዱ አሠራር ለህዝብ መረጃ ማሰራጨት ይችላል፡፡

## *ምዕራፍ 12 — የባለሀብቶች ካሳ*

### 12.1. የይገባኛል ጥያቄዎችን ማረጋገጥ

በካፒታል ገበያ የካሳ ፈንድ ደንብ እና/ወይም የካሳ ፈንድ መመሪያዎች መሠረት የገንዘብ ኪሳራ ደርሶብኛል በማለት የይገባኛል ጥያቄ ለገበያው የሚያቀርቡ ሰዎችን በተመለከተ፣ የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በእነዚህ ደንቦች እና በካፒታል ገበያ የካሳ ፈንድ ደንብ እና/ወይም የካሳ ፈንድ መመሪያዎች መሠረት ለተረጋገጡ የይገባኛል ጥያቄዎች የካሳ ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

### 12.2. የካሳ ክፍያ

(1) በኢንቨስተሩ ወይም በገበያው የግብይት አባል የቀረበው ማስረጃ ወይም ከሌሎች ምንጮች የተገኘው ማስረጃ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው የደንበኛ ካሳ ፈንድ ዳይሬክተሮች ቦርድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ካሳ ይከፍላል -

ሀ) የግብይት አባሉ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ላይ የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት ባለሃብቱ የይገባኛል ጥያቄ ያለው እንደሆነ፤

ለ) ባለሀብቱ ከግብይት አባሉ ያለው የይገባኛል ጥያቄን ለመፍታት በአግባቡ ያመለከተ እንደሆነ፤

ሐ) የግብይት አባሉ የይገባኛል ጥያቄውን በተገቢ ጊዜ ውስጥ መክፈል ካልቻለ፤

መ) ባለሀብቱ የገበያውን የውስጥ ቅሬታ አፈታት ሂደት ያጠናቀቀ እንደሆነ፤

ሠ) ባለሀብቱ ከፈንዱ ካሳ ለማግኘት በአግባቡ ካመለከተ፤ እና

ረ) ገበያው የይገባኛል ጥያቄውን ካረጋገጠ፡፡

(2) የይገባኛል ጥያቄ ማመልከቻው ተቀባይነት ሊያጣ የሚችለው፤

ሀ) የይገባኛል ጥያቄው ከገበያው በግብይት አባል ጋርልብይት ያ የውል ግንኙነት ስለመኖሩ፣ ባለሀብቱ በደረሰበት ኪሳራ እና የግብይት አባሉ ለእንዲህ ዓይነቱ ይገባኛል ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ አለመቻሉን ወይም ችላ ማለቱን በሚያሳይ ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ የተደገፈ ካልሆነ፤

ለ) የይገባኛል ጥያቄው ወዲያውኑ ካልቀረበ፣ ገባኛበማንኛውም ሁኔታ ባለሀብቱ ስለጉዳዩ ካወቀበት እና የግብይት አባሉ የውል ግዴታውን መወጣት እንደማይችል ከተረዳበት ቀን አንስቶ ወይም ጉዳዩ አግባብነት ባለው የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኋላ በስድስት (6) ወራት ውስጥ ካልቀረበ፤ ፤

ሐ) በህግ አሠራር ምክንያት ካልተሰረዘ፤

መ) በገበያው በሚተዳደር ሌላ የካሳ ዕቅድ ጨምሮ በሌላ የካሳበዕቅድበያው የካሳበያው ፖሊሲ መሰረት ክፍያው ከተፈፀመ፤ ወይም

ሠ) )ሲ መሰረት ክፍያው ከተፈፀመ፤ ወይም ጨምሮ በሌ የግብይት አባሉ የንግድ ሁኔታዎች ባለሀብቱ ተጠያቂ ከሆነ ወይም ከነዚህ ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ከነበረ፡፡

(3) ባለሀብቱ የደረሰበትን የገንዘብ ኪሳራ ላስከተሉት የግብይት አባሉ የንግድ ሁኔታዎች ተጠያቂ መሆኑን ወይም ከነዚህ ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ስለመሆኑ በመወሰን ረገድ የደንበኞች ካሳ ፈንድዳ ይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን ጉዳዮችን ጨምሮ ሁሉንም ተገቢ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

ሀ) ባለሀብቱ የደረሰበትን የገንዘብ ኪሳራ ላስከተሉት የግብይት አባሉ የንግድ ሁኔታዎች ተጠያቂ መሆኑን ወይም ከነዚህ ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ስለመሆኑ ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ ውሳኔ ካለ፤

ለ) ባለሀብቱ የደረሰበትን የገንዘብ ኪሳራ ላስከተሉት የግብይት አባሉ የንግድ ሁኔታዎች ተጠያቂ መሆኑን ወይም ከነዚህ ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ስለመሆኑ ካመነ፤

ሐ) ባለሀብቱ የደረሰበትን የገንዘብ ኪሳራ ላስከተሉት የግብይት አባሉ የንግድ ሁኔታዎች ተጠያቂ መሆኑን ወይም ከነዚህ ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ መሆኑን የሚያመለክት በንግድ አባል የቀረበ ወይም ከሌሎች ምንጮች ለደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚገኝ ማስረጃ ካለ፤ እና

መ) ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች ጉዳዮች።

## 12.3. በርካታ የይገባኛል ጥያቄዎች

(1) አንድ ሰው ለራሱ እንዲሁም ለሚች ባለሀብት የግል ተወካይ ሆኖ የይገባኛል ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣ በተወካይነት ያቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ እንደ ሚቹ ባለሀብት ተደርጎ ይቆጠራል። ይህም ያራሱን የግል ጥያቄ ሳይጎዳ፣ ሚቹን ባለሀብት በተመለከተ የሚችነት የምስክር ወረቀትን፣ የአስተዳደር ደብዳቤዎችን፣ ኑዛዜዎችን፣ የአስፈጻሚዎች ፈቃድን ጨምሮ የይገባኛል ጥያቄውን የሚደግፉ ሰነዶችን በማስረጃነት ማቅረብ አለበት።

(2) አንድ ሰው ለራሱ እና እንደ ጠባቂ ሆኖ የይገባኛል ጥያቄ የሚያቀርብ እንደሆነ፤ በጠባቂነት የሚያቀርበው የይገባኛል ጥያቄ የተለየ ሆኖ ይቆጠራል።

(3) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች በሽርክና የጋራ ጥቅም ያለው የይገባኛል ጥያቄ ካላቸው፣ የይገባኛል ጥያቄው የሽርክናው ይገባኛል ጥያቄ ተደርጎ ይቆጠራል፣ ይህ ካልሆነ ለካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በተቃራኒው ካልተረጋገጠ በስተቀር እያንዳንዳቸው በይገባኛል ጥያቄው ውስጥ እኩል ድርሻ እንዳላቸው ይቆጠራሉ።

(4) አንድ ወኪል ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ዋና ወኪሎች የይገባኛል ጥያቄ ካለው፣ ወኪሉን ሳይጨምር ዋናው ወካይ ወይም ተወካዮቹ የይገባኛል ጥያቄ እንዳላቸው ይቆጠራል።

(5) ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ለባለሀብቱ የሚከፈለውን አጠቃላይ የካሳ መጠን በመወሰን ረገድ የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የባለሀብቱን በርካታ የይገባኛል ጥያቄዎች ሊያጣምር ይችላል።

## 12.4. የካሳ መጠን

(1) ኪሳራ የደረሰበት ባለሀብት ሊከፈለው የሚችለው ከፍተኛው የካሳ መጠን በደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወሰነው መጠን ይሆናል። ኪሳራው በማንኛውም ጊዜ በደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከተወሰነው ከፍተኛ መጠን ያነሰ ከሆነ፣ ባለሀብቱ ኪሳራውን ለማቃለል ከፈንዱ ውጭ ካለ

ሌላ ምንጭ የተቀበለውን ወይም የሚቀበለውን ማንኛውንም ገንዘብ ወይም ሌሎች ጥቅሞችን መጠን ወይም ዋጋ በመቀነስ ሙሉው የኪሳራው መጠን ሊከፈለው ይችላል፡፡

(2) ባለሀብቱ ከአንድ የግብይት አባል ጋር በተያያዘ በደንበኛ ካሳ ፈንዱ ላይ በርካታ የይገባኛል ጥያቄዎች ቢኖሩትም ከአንድ በላይ የካሳ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡

(3) ከላይ የተጠቀሰው ቢኖርም፣ የካሳ መጠኑ በደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው ሊከለስ ይችላል፡፡ የሚከፈለውን ከፍተኛውን የካሳ መጠን በሚወሰንበት ጊዜ፣ የካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በካፒታል ገበያው ውስጥ ያሉትን ወቅታዊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

(4) አንድ ባለሀብት ከደንበኛ ካሳ ፈንድ ካሳ ከተቀበለ በኋላ ለተመሳሳይ ይገባኛል ጥያቄ ከገበያው የግብይት አባል ካሳ ከተቀበለ፣ ባለሀብቱ ከደንበኛ ካሳ ፈንድ የተከፈለውን ገንዘብ መመለስ አለበት፡፡

(5) ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መመለሻ መሰረት የካሳ ፈንድ የተመለሰለትን ማንኛውም የገንዘብ መጠን ለደንበኛ ካሳ ፈንድ ሂሳብ መከፈል አለበት፡፡

## 12.5. የተስተካከሉ ክፍያዎች

(1) በመርህ ደረጃ ካሳ ሊከፈል ይገባል ብሎ ቢያምንም ሌሎች የካሳ ክፍያ ጥያቄዎችን ከግምት በማስገባት ወዲያውኑ ሙሉ ክፍያ መፈጸም የማይቻል መሆኑን ሲወስን፣ ወይም በባለሀብቱ አጠቃላይ የተጣራ የይገባኛል ጥያቄ መጠን ላይ ማንኛውም አጠራጣሪ ጉዳይ ካለ፣ የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተገቢውን አነስተኛ መጠን እንደመጨረሻ ክፍያ ለመክፈል ወይም ከፊል ክፍያ ለመፈጸም ሊወስን ይችላል፡፡

(2) ባለሀብቱ በተመለከተው ጥያቄ ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን ወይም ለማንኛውም ሌላ ሰው ወይም ባለስልጣን የካሳ ጥያቄ በማቅረብ ካሳ ሊከፈል የሚችልበት ተስፋ ካለው፣ የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተገቢውን አነስተኛ መጠን እንደመጨረሻ ክፍያ ለመክፈል ወይም ከፊል ክፍያ ለመፈጸም ሊወስን ይችላል፡፡

(3) ባለሀብቱ በደረሰበት ኪሳራ ላይ በከፊል ተጠያቂ መሆኑን የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካረጋገጠ ለባለሀብቱ ሊከፈል የሚገባውን ካሳ ሊቀንስ ይችላል፡፡

(4) ባለሀብቱ ለደንበኛ ካሳ ፈንድ የሚከፈል ዕዳ ያለበት ከሆነ፣ የሚከፈለው የካሳ መጠን ላይ ያልተከፈለው የዕዳ መጠን ተቀንሶ ይከፈላል፡፡

## 12.6. ስለማስመለስ እና ስለ መዳረግ

(1) የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለማንኛውም ባለሀብት ክፍያ ከከፈለ በኋላ በከፈለው የካሳ ክፍያ መጠን ባለሀብቱ ባሉት ሁሉም መብቶች በመተካት

የሚመለከተውን የግብይት አባል ተጠያቂ ያደርጋል። እንዲህ ዓይነቱ ዳረጎት የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከገበያው የግብይት አባል ወይም የግብይት አባሉን ንብረቶች በመሸጥ ከከፈለው የካሳ መጠን ጋር እኩል መጠን ያለውን ገንዘብ ለማስመለስ የሚኖረውን መብት ያካትታል።

(2) በዚህ ደንብ መሠረት የደንበኛ ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ የተቀበለው ማንኛውም መጠን ወደ ፈንዱ ይከፈላል።

## 12.7. የጠቋሚ ጥበቃ

የደንበኞች ካሳ ፈንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ በካሳ ፈንድ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ጥሰቶችን በተመለከተ መረጃዎችን ለመቀበል እና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት ማቋቋም እና መጠቀም አለበት።

## 12.8. የሥነ ምግባር ደንቦች

የደንበኛ ካሳ ፈንድ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥነ ምግባር ደንብ በእነዚህ ደንቦች ውስጥ እንደተካተተ እና የዚሁ አካል እንደሆነ ይቆጠራል።

# የአስተዳደራዊ ቅጣት ሰንጠረዥ - የአባልነት ደንቦች

(1) በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መጽሐፍ ደንብ 2017 (የአባልነት ደንቦች) ድንጋጌዎች ላይ ለሚኖር ጥሰት ተፈፃሚ የሚሆኑት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በዚህ ሰንጠረዥ የተካተቱት ናቸው።

(2) የደንቡ ወይም ሌላ የስያሜ ለውጥ ሲደረግ፣ በዚህ የቅጣት ሰንጠረዥ ውስጥ ስሙ ወይም የስያሜ ለውጡ ወዲያውኑ እንደተቀየረ ይቆጠራል።

(3) ከደንቦቹ ጥሰት ጋር በተያያዘ ማንኛውም እገዳ ከተጣለ፣ እንዲህ ያለው እገዳ ሊነሳ የሚችለው ተዛማጅ ወይም ተዛማጅ ያልሆኑ ሁሉም ግዴታዎች ከተሟሉ በኋላ ብቻ ይሆናል።

| ምዕራፍ | ደንብ | ለግብይት አባል ወይም ለተሿሚ እንደራሴዎች ተፈፃሚ የሚሆን ቅጣት | ለተሿሚ እንደራሴዎች ወይም ሌሎች ሰራተኞች ተፈፃሚ የሚሆን ቅጣት | ተደጋጋሚ አካል |
|---|---|---|---|---|
| 1 የግብይት አባላት መግቢያ እና ምደባ | 1.3 የግብይት አባላት ምድቦች | ጥሰቱ እስኪስተካከል ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| 2 | 2.6. የግብይት መብት ማቆም | • የአባልነት የምስክር ወረቀት መሰረዝ | ምዝገባ መሰረዝ፣ መታገድ | ተፈጻሚነት የለውም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የግብይት አባላት የምስክር ወረቀት አሰጣት ሂደቶች | 2.7. የግብየት አባል ሁኔታ | • ከግብይት እገዳ - ስረዛ | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| 3 ቁጥጥር፣ የባለቤትነት መዋቅሮች እና ጉልህ ተጽዕኖ | በመጽሐፍ 3 ላይ (ስለቁጥጥር፣ የባለቤትነት መዋቅሮች እና ጉልህ ተጽዕኖ የተገለጹ ሁሉም ደንቦች) | ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር | ተፈጻሚነት የለውም | በአንድ (1) ዓመት ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የጥፋተኛ የሆነ አካል ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት እንቅስቃሴው እንዲታገድ ይደረጋል። |
| 4 የካፒታል እና ሂሳብ ሪፓርቶች | ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርት | • ተቋሙ ለግብይቱ ማሳወቅ በሚጠበቅበት እና ሳያሳውቅ በቀረበት እያንዳንዱ ቀን 5,000 ብር ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል። ይህ ቅጣት ለከፍተኛው 30 ቀናት ይተገበራል። እንዲሁም/ወይም<br>• ጥሰቱ እስኪስተካከል ድረስ እንቅስቃሴ እንዲታገድ ይደረጋል። | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የገንዘብ አከል ንብረት መስፈርቶች | • ተቋሙ ለግብይቱ ማሳወቅ በሚጠበቅበት እና ሳያሳውቅ በቀረበት እያንዳንዱ ቀን 5,000 ብር ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ይህ ቅጣት ለከፍተኛው 30 ቀናት ይተገበራል፡፡<br>እንዲሁም/ወይም<br>• ጥሰቱ እስኪስተካከል ድረስ እንቅስቃሴ እንዲታገድ ይደረጋል፡፡ | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| ነፓርት ማቅረብ/ማስገባት | • በየቀኑ 5,000 ብር ቅጣት ለከፍተኛው 30 ቀናት፤ እና<br>• ከ30ኛው ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኂለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፡፡ | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| 4.4 የፋይናንስ መግለጫዎችን እና ሌሎች ሪፖርቶችን የማጭበርበር ክልከላ | • ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር ቅጣት፤ እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ከሁለቱም ውስጥ የኂለኛው ጊዜ | • ለአንድ ጥሰት ከ50,000 ብር እስከ 75,000 ብር ቅጣት፤ | ተፈጻሚነት የለውም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል። | | |
| 5. አስተዳደር፣ ክትትል እና ውስጣዊ ቁጥጥሮች | 5.1 ክትትል እና ውስጣዊ ቁጥጥሮች | ለአንድ ጥሰት ከ150,000 ብር እስከ 250,000 ብር ቅጣት፤ | | በአንድ (1) ዓመት ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የጥፋተኛ የሆነ አካል ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት እንቅስቃሴው እንዲታገድ ሊደረግ ይችላል። |
| | 5.2 ቀድሞ የተሰጠ የጽሁፍ ፈቃድ እና ማስታወቂያዎች | ለአንድ ጥሰት ከ100,000 ብር እስከ 150,000 ብር | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| | 5.3 የስጋት አስተዳደር | ለአንድ ጥሰት ከ100,000 ብር እስከ 150,000 ብር | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| | 5.4 የህግ እርምጃዎች | ለአንድ ጥሰት ከ100,000 ብር እስከ 150,000 ብር | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 5.5 በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነት በገንዘብ መርዳትን መከላከል | • ለአንድ ጥሰት ከ500,000 ብር እስከ 750,000 ብር ቅጣት፤<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ካሉት ከሁለቱም ውስጥ የኋለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፣<br>• የአባልነት የምስክር ወረቀት መሰረዝ፤<br>• ማገድ ፣ እና /ወይም<br>• በወንጀል እንዲቀጡ መረጃ መስጠት | • ለአንድ ጥሰት ከ150,000 ብር እስከ 300,000 ብር ቅጣት፤<br>• ጊዜያዊ/ቋሚ ምዝገባ መሰረዝ/ማስወገድ፤<br>• በጥቁር ዝርዝር ውስጥ መመዝገብ፤ እና/ወይም<br>• ለወንጀል ክስ መምራት፡፡ | ተፈፃሚነት የለውም |
| | 5.6 የድርጅት አስተዳደር | • ለአንድ ጥሰት ከ100,000 ብር እስከ 150,000 ብር | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| 6. የተሾሙ እንደራሴዎች እና ሌሎች ሰራተኞች | 6.1 የተሾሙ እንደራሴዎች እና ሌሎች ሰራተኞች ኃላፊነት | • ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል፣ ከሁለቱም ውስጥ የኋለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፡፡ | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6.2 የተሾሙ እንደራሴዎች ለመሾም እና ፈቃድ ለማግኘት ግዴታ | ለአንድ ጥሰት ከ100,000 ብር እስከ 150,000 ብር | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| 6.3 የግብይት አባላት እና የተሾሙ እንደራሴዎች ግዴታዎች እና የሥነ ምግባር ደንብ | ተፈጻሚነት የለውም | • ለሙያዊ አካል/አካላት ወይም ማህበር/ማህበራት ማቅረብ፤<br>• በጊዜያዊነት/በቋሚነት ከምዝገባ መሰረዝ/ማስወገድ፤<br>• ማገድ፤ እና/ወይም<br>• ለወንጀል ክስ ማቅረብ። | ተፈጻሚነት የለውም |
| 6.4. የስልጣን ዘመናቸው በተጠናቀቀ ተሿሚ እንደራሴዎች፣ ሰራተኞች ወይም ሌሎች ባለሞያዎች ላይ ያለውን ሥልጣን መጠበቅ | ተፈጻሚነት የለውም | • ለሙያዊ አካል/አካላት ወይም ማህበር/ማህበራት ማቅረብ፤<br>• ጊዜያዊ/ቋሚ ምዝገባ መሰረዝ/ማስወገድ፤<br>• ማገድ፤ እና/ወይም<br>• ለወንጀል ክስ ማቅረብ። | ተፈጻሚነት የለውም |
| 6.5. የተሾሙ እንደራሴዎች ወይም ሌሎች ሰራተኞች ቦታ ላይ የሚደረጉ ለውጦች | ለአንድ ጥሰት ከ100,000 ብር እስከ 150,000 ብር | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6.6. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት | • ለአንድ ጥሰት ከ100,000 ብር እስከ 150,000 ብር፤ እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኂለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፡፡ | • ለአንድ ጥሰት ከ35,000 ብር እስከ 50,000 ብር ቅጣት፤ እና/ወይም<br>• ጊዜያዊ/ቋሚ ምዝገባ መሰረዝ/ማስወገድ፤ እና/ወይም<br>• ማገድ፡፡ | ተፈጻሚነት የለውም |
| 6.7 ዋና የሕግ ተገዢነት መኮንን | • ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር፤ እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፣ ከሁለቱም ውስጥ የኂለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ፡፡ | • ለአንድ ጥሰት ከ50,000 ብር እስከ 75,000 ብር ቅጣት፤ እና/ወይም<br>• ጊዜያዊ/ቋሚ ምዝገባ መሰረዝ/ማስወገድ፤እና/ወይም<br>• ማገድ፡፡ | ተፈፃሚነት የለውም |
| 6.8 የሰነደ ሙዓለንዋዮች ግብይት ፈፃሚ | • ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር፤ እና/ወይም | • ለአንድ ጥሰት ከ50,000 ብር እስከ 75,000 ብር ቅጣት፤ እና/ወይም | ተፈፃሚነት የለውም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኋለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል:: | • ጊዜያዊ/ቋሚ ምዝገባ መሰረዝ/ማስወገድ፤እና/ወይም<br>• ማገድ:: | |
| 7. መጽሃፍትና መዝገቦች | 7.1 የግብይት መዝገብ እና የምርመራ መብት | • ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር፤ እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኋለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል:: | • ለአንድ ጥሰት ከ 35,000 ብር እስከ 50,000 ብር ቅጣት፤ እና/ወይም<br>• ጊዜያዊ/ቋሚ ምዝገባ መሰረዝ/ማስወገድ፤እና/ወይም<br>• ማገድ፤ | ተፈፃሚነት የለውም |
| | 7.2 የደንበኛ መዝገብ መረጃ ማስቀመጥ | • ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር፤ እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኋለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል:: | ተፈጻሚነት የለውም | ጥሰቱ እስኪስተካከል ድረስ በየቀኑ ተጨማሪ 2,500 ብር ቅጣት የግብይት አባሉ ላይ ይጣላል፤ ይህም እስከ 30 ቀናት ሊተገበር ይችላል:: |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8 | የግብይት አባላት እና የተሾሙ እንደራሴዎች ከህዝቡ ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት | በምዕራፍ 8 ላይ ሁሉም ደንቦች፦ የግብይት አባላት እና የተሾሙ እንደራሴዎች ከህዝቡ ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት | • ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር፤ እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኂለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፡፡ | • ለአንድ ጥሰት ከ,35,000 ብር እስከ 50,000 ብር ቅጣት፤ እና/ወይም<br>• ጊዜያዊ/ቋሚ ምዝገባ መሰረዝ/ማስወገድ፤ እና/ወይም<br>• ማገድ፡፡ | የግብይት አባሉ ማስታወቂያ፣ መገናኛ፣ መረጃ ወዘተ እንዲያስወግድ ከተጠየቀ ጥሰቱ እስኪስተካከል ድረስ በየቀኑ ተጨማሪ 2,500 ብር ቅጣት ይጣልበታል፣ ይህም ለከፍተኛው 30 ቀናት ይተገበራል፡፡ |
| 9 | ገበያ ከፋቾች | በምዕራፍ 9 ላይ ሁሉም ደንቦች፡ ገበያ ከፋቾች | • የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ/ማሳሰቢያ<br>• ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኂለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፡፡<br>• ምዝገባን መሰረዝ | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 10. ለዲጂታል ንዑስ ደላሎች ስፓንሰር አድራጊ ደላሎች | በመጽሃፍ 10 ላይ ላሉ ደንቦች፤ የንዑስ ደላላ ስፖንሰር አድራጊ ዋና ደላሎች | • የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ/ማሳሰቢያ<br>• ለአንድ ጥሰት ከ200,000 ብር እስከ 300,000 ብር<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኋለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፤ እና/ወይም<br>• የምዝገባ መታገድ፡፡ | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |
| 11.የደንበኞች ካሳ ፈንድ | ለደንበኞች ካሳ ፈንድ ክፍያ መፈጸም | • ለአንድ ጥሰት ከ100,000 ብር እስከ 150,000 ብር፤ እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአስር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪስተካከል ባለው ከሁለቱም ውስጥ የኋለኛው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ እንቅስቃሴው ይታገዳል፡፡ | ተፈጻሚነት የለውም | ተፈጻሚነት የለውም |

# ቅፅ ሐ፡ የምዝገባ ደንቦች

# ክፍል 1 - ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## *ምዕራፍ 1 - መግቢያ*

### 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መጽሐፈ ደንብ፣ 2017 (የምዝገባ ደንቦች)" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1.2. ዓላማ

የደንቦቹ አላማ የገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ ላይ ለመመዝገብ የሚያመለክቱ ሁሉም አውጪዎች እና ሌሎች እነዚህ ደንቦች የሚመለከታቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚነት የሚኖራቸውን ቅድመ ሁኔታዎችን፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሽያጭ የሚቀርቡበትን ሥነ ሥርዓት እንዲሁም ቀጣይነት ያላቸውን የአውጪዎች ግዴታዎችን ለመደንገግ ነው፡፡

### 1.3. ጠቅላላ መርሆዎች

(1) ከዚህ በታች የተመላከቱት ጠቅላላ መርሆዎች የምዝገባ ደንቦች ዋና ክፍል ምንጪ ሲሆኑ ምዝገባ ፈልገው ወደ ገበያው ለሚመጡ ሁሉም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ ማመልከቻዎች እንዲሁም ቀደም ሲል በገበያው ላይ ለተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በሙሉ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

(2) ገበያው በእነዚህ ደንቦች ዋና ክፍል የተካተቱ ቅድም ሁኔታዎች ተፈፃሚነት እንዲቀር የማድረግ ስልጣን አለው፡፡ ተገልጋዩ በምዝገባ ደንቦች ትርጓሜ እና ተግባራዊነት ላይ ማንኛውም ጥርጣሪ ካለው ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡፡

(3) እነዚህ ደንቦች የተመሰረቱባቸው ጠቅላላ መርሆዎች፤

(ሀ) የገበያ ሥርዓቱን መሠረት ያደረገ ካፒታልን ለመሰብሰብ የሚያስችል የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመገበያየት የሚያስችል የተሳለጠ የሁለተኛ ደረጃ ገበያ እና ኢንቨስተሮች ለመጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ያለው ሥነ-ምህዳር መኖሩን ማረጋገጥ፤

(ለ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በኦፊሴላዊ መዝገብ ላይ ሊመዘገቡ የሚችሉት ገበያው እነዚህ ሰነድ ሙዓለ ንዋዮችን መመዝገብ ተገቢ መሆኑን ሲያረጋግጥ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ፤

(ሐ) ለሁሉም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች እና ለህዝቡ የአውጪውን እንቅስቃሴ በተመለከተ ትክክለኛ፣ ሙሉ፣ ሚዛናዊ፣ ወቅታዊ እና ይፋዊ መረጃ መሰጠቱን ማረጋገጥ፤

(መ) አግባብነት ያላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች አስቀድመው እንዲያስቡበት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚከተሉት ውስጥ በአንዱ ላይ ድምጽ ለመስጠት በቂ እድል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

i. በአውጭው የግብይት እንቅስቃሴ ላይ የተደረጉ ዋና ለውጦች፣ እና

ii. የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል፣ ካፒታል፣ ለባለአክሲዮኖች የሚደረግ ክፍፍልን ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች መብቶች ላይ ለውጥ የሚፈጥሩ ውሳኔዎችን ጨምሮ የአውጭውን መመስረቻ ሰነድ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶችን መብቶች የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

(ሠ) መረጃን ወደ ገበያው በቀጥታ ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶችም ሆነ ለሕዝብ በማሰራጨት የሚሳተፉ አካላት ሁሉ ከፍተኛውን የጥንቃቄ ደረጃዎች መከተላቸውን ማረጋገጥ፤

(ረ) በአንድ አውጪ የወጡ ተመሳሳይ ምድብ ያላቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የያዙ ባለቤቶች በሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸው ረገድ ተመጣጣኝና ፍትሃዊ መስተንግዶ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

(ሰ) የምዝገባ መስፈርቶች፣ እና በተለይም ቀጣይነት ያላቸው ግዴታዎች ኢንቨስተሮች በገለባ ሥርዓት እና መልካም የኩባንያ ሥራ አመራር ጉዳዮች ላይ እና በአጠቃላይ በገበያ ላይ ባለው አፈፃፀም ላይ ያላቸውን እምነት የሚያበረታቱ መሆኑን ማረጋገጥ፤ እና

(ሸ) የገበያው ሥራ የሕዝብን ጥቅም ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

## 1.4. የማክበር ግዴታ

(1) ሁሉም አውጪዎች እነዚህን ደንቦች የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

(2) ሁሉም አውጪዎች አግባብነት ባለው የገበያው ምዝገባ ቦርድ ውስጥ ተመዝግበው በሚቆዩባቸው ጊዜያት ሁሉ ተፈፃሚ በሚሆን ልክ ዝቅተኛውን የምዝገባ መስፈርት የማሟላት ግዴታ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ 2 - የገበያው ስልጣን

### 2.1. ጠቅላላ ስልጣን

(1) የአዋጁ ድንጋጌዎችና እና ባለስልጣኑ የሚያወጣቸው መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ገበያው የሚከተሉት ሥልጣኖች አሉት፤

(ሀ) ምዝገባ የሚፈልግ አውጪ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከመመዝገባቸው በፊት ሊያሟላቸው የሚገቡ የምዝገባ መስፈርቶችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ማውጣት፤

(ለ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ የተመዘገቡለት አውጪ ሊከተላቸው የሚገቡ ቀጣይነት ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ማውጣት፤

(ሐ) ተፈፃሚነት ባላቸው የምዝገባ ደንቦች መሰረት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባን መፍቀድ፣ መከልከል፣ መሰረዝ ወይም ማገድ፤

(መ) ለሁሉም ለተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች ተፈፃሚነት ያላቸው ቀጣይነት ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎችን ማስተዳደር፤

(ሠ) የምዝገባ ደንቦች ተፈፃሚነት ካላቸው የኢትዮጵያ ህጎች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደንቦች እና አለም አቀፍ ልምዶች ጋር ተስማሚነታቸውን በየጊዜው መመርመር፤

(ረ) የምዝገባ መስፈርቶችን፣ ከምዝገባ በፊት ወይም ከምዝገባ በኋላ የወጡ ቀጣይነት ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎችን መከለስ ወይም ቀሪ ማድረግ እና ተጨማሪ የምዝገባ መስፈርቶችን ወይም ቀጣይ ግዴታዎችን በየጊዜው ማውጣት፤

(ሰ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ የሚታገድበትን ወይም የሚሰረዝበትን ሁኔታዎች መወሰን፤ እና

(ሸ) ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራትን ለመፈፀም የሚያስፈልጉ ተያያዥ ጉዳዮችን ወይም እንደሁኔታው ሌሎች ተግባራትን መፈፀም።

(2) ከዚህ በላይ የተመለከቱት ስልጣኖች ሁሉንም አሟልተው የያዙ አይደሉም። የዳይሬክተሮች ቦርድ የባለስልጣኑን ፈቃድ በማግኘት እንደ አስፈላጊነቱ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል።

(3) የባለስልጣኑን ይሁንታ በማግኘት ገበያው ማናቸውም የምዝገባ መስፈርቶች የማይተገበሩባቸው በቂ እና አጥጋቢ ምክንያቶች አውጭው እንዳሉት ካረጋገጠ የሚከተሉት

ሁኔታዎች ሲሟሉ ማናቸውንም የምዝገባ መስፈርቶች ቀሪ ለማድረግ ይችላል፡፡ ይህም በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሆናል፡-

(ሀ) ቀሪ መደረጉ የህዝብን ጥቅም የማይጎዳ ከሆነ፤ እና

(ለ) የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ፤

i. አውጭው ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት የማይችል ወይም አውጭው እንዲያሟላ ማድረግ ምክንያታዊ አለመሆኑ ወይም ያልተገባ ጫና የሚያሳድር መሆኑ፤

ii. ቅድመ ሁኔታው አውጭው ላለበት ሁኔታ የማያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

iii. ቅድመ ሁኔታውን ማሟላቱ የአውጭውን የንግድ ጥቅምን ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶችን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ከተገኘ፡፡

(4) ገበያው ምዝገባውን ማፅደቁ ወይም ውድቅ ማድረጉ ለኢንቨስተሮች ጠቃሚ ነው ብሎ ባሰበ ጊዜ የምዝገባ ቅድመ ሁኔታዎችን በሙሉ ያላማሉ አውጪዎችን ሊመዘግብ ወይም የምዝገባ ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟሉ አውጪዎችን ምዝገባ ውድቅ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

(5) ማንኛውንም ማሻሻያ ጨምሮ የምዝገባ ደንቦች የሚተረጎሙት፣ የሚተዳደሩትና የሚፈፀሙት በገበያው ነው፡፡ በዚህ አግባብ የሚሰጡ የገበያው ውሳኔዎች ገበያው ላይ በተመዘገቡ ሁሉም አውጪዎች ላይ አስገዳጅነት ይኖራቸዋል፡፡

## 2.2. ስልጣን ያለው አካል

(1) የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ፤

(ሀ) በገበያው ግብይት ሊደረግባቸው የሚችሉትን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዝርዝር የማውጣት፤

(ለ) በአውጪዎች ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን የማጽደቅ እና

(ሐ.) የባለስልጣኑን ፈቃድ በማግኘት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከምዝገባ የመሰረዝ ስልጣን ያለው አካል ነው፡፡

(2) የዳይሬክተሮች ቦርድ የቅድመ ወይም የመጨረሻ ግምገማ ለማድረግ ወይም ምዝገባ ላይ ለመወሰን ወይም ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ለማከናወን ከምዝገባ ደንቡ ጋር በተገናኘ ያሉትን ሁሉንም ወይም ከፊል ስልጣኑን ለሚመለከተው ኮሚቴ በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ 3

## በገበያው የሚደረጉ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ጠቅላላ መስፈርቶች እና የምዝገባ ሥነ-ሥርዓቶች

### 3.1. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ ጠቅላላ መስፈርቶች

(1) መረጃን ይፋ ማድረግ፡-

(ሀ) ገበያው ማንኛውንም መረጃ ወይም ሰነድ በአውጪው በማናቸውም የመገናኛ ዘዴዎች እና ገበያው በሚያዘው መሠረት ይፋ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

(ለ) በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር በዚህ ደንብ መሠረት ለገበያው መረጃ እንዲሰጥ ሲጠየቅ መረጃው በጽሑፍ በኤሌክትሮኒክስ ፎርማት እና በወረቀት መቅረብ አለበት፡፡

(ሐ.) አውጪው ወይም ሌላ ማንኛውም ይህ ደንብ ተፈፃሚ የሚሆንበት ሰው ገበያው የሚጠይቀውን ማንኛውም መረጃ፣ ሰነድ ወይም ማብራሪያ መስጠት አለበት፡፡

(መ) ለገበያው የቀረቡ ወይም በገበያው የተገኙ ሰነዶች እና መረጃዎች በሙሉ የገበያው ንብረት ናቸው፡፡

(ሠ) ገበያው ሰነዱን እና መረጃውን መገልበጥ፣ መልሶ ሊገኝ በሚችልበት ሥርዓት ውስጥ ማከማቸት፣ ለሕዝብ ማስተላለፍ፣ ሁሉንም ወይም ማንኛውንም የሰነዶቹን ክፍል ማተም ወይም ለሶስተኛ ወገኖች መግለጽ እና ቅጂዎችን ለማንኛውም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ለባለስልጣኑ፣ ለሚመለከተው መንግሥት አካል፣ ባለስልጣን ወይም ለማንኛውም ገበያው ተገቢ ነው ብሎ ላሰበው ሰው ማስተላለፍ ይችላል፡፡ ገበያው መረጃውን ይፋ ሲያደርግ ሚስጢራዊነት እና የግል መረጃ ጥበቃ ጋር በተገናኘ ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎችን እና ይፋ ማድረግ ለህዝብ ያለውን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

(ረ) ገበያው በአውጭው ለገበያው የሚቀርብ ማመልከቻ አካል ሆነው የሚቀርቡ ሪፖርቶችን እና መረጃዎች ትክክለኛነትን የሚያረጋግጥ ገለልተኛ አማካሪ ወይም ባለሙያ እንዲሾም እና የዚህን ውጤት በቀጥታ ለገበያው እንዲቀርብ ትዕዛዝ ወይም አቅጣጫ ሊሰጥ ይችላል፡፡

(ሰ) አውጭው እና የአውጭው ዳይሬክተሮች ማንኛውም በእነዚህ ደንቦች መሰረት የሚቀርብ፣ ገቢ የሚደረግ ወይም የሚገለፅ ማመልከቻ፣ መግለጫ፣ መረጃ ወይም ሰነድ፦

i. ግልጽ፣ አሻሚ አለመሆኑን እና ትክክለኛ መሆኑን፤

ii. ምንም አይነት መሰረታዊ የሆነ ጉድለት የሌለበት፣ እና

ሀሰተኛ እና የማያሳስት መሆኑንማረጋገጥ አለባቸው፡፡

(ሸ) ከላይ በንዑስ አንቀፅ (1) (ረ) እና (1) (ሰ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሁሉም ለገበያው የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በአውጭው ዋና ስራ አስኪያጅ ወይም ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም ተገቢው ስልጣን ባለው ኃላፊ መፈረም አለባቸው::

(ቀ) በንዑስ አንቀፅ 1(ሰ) ላይ የተመላከተው ሰው በንዑስ አንቀፅ 1(ሰ) ላይ የተገለፀው መግለጫ፣ መረጃ ወይም ሰነድ ለገበያው ከቀረበ፣ ገቢ ከተደረገ ወይም ከተገለፀ በኋላ መግለጫው፣ መረጃው ወይም ሰነዱ የንዑስ አንቀፅ 1(ሰ) መስፈርቶችን የማያሟላ መሆኑን እንዳወቀ ወዲያውኑ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡፡

(2) ክፍያዎች፡

(ሀ) አውጭው በገበያው እንደ ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚወሰኑ ክፍያዎችን ለገበያው መክፈል አለበት፡፡ ተፈፃሚነት ያላቸው ክፍያዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው የገበያው የክፍያ ሰንጠረዥ መሰረት ይወሰናል፡፡

(ለ) ገበያው እንደሁኔታው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም ክፍያ ቀሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡

(3) ማፅደቅ

(ሀ) በእነዚህ ደንቦች መሰረት፣ ገበያው በኦፊሴላዊ መዝገቡ እንዲመዘግብ የሚቀርቡለትን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ማመልከቻዎችን ተቀብሎ የማፅደቅ ወይም ውድቅ የማድረግ ሙሉ ስልጣን አለው፡፡

(ለ) ገበያው የምዝገባ ጥያቄን ሲያፀድቅ ገበያው እንዳመነበት ምዝገባው በቅድመ ሁኔታ ወይም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በማለት ሊወስን ይችላል።

(ሐ) የምዝገባ ጥያቄን ሲያፀድቅ ገበያው የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፤

i. በእነዚህ ደንቦች መሰረት የባለአክሲዮኖች ውሳኔ የሚያስፈል መሆኑን፤

ii. የአውጭው ማመልከቻ ለግብይት የቀረበ የአውጭው አክሲዮን ላይ ያለውን ተፅዕኖ።

(መ) አውጪው ለተጨማሪ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ የሚያስፈልጉ ሁሉንም መስፈርቶች ቢያሟላም ገበያው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ማመልከቻውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

(ሰ) ገበያው በእነዚህ ደንቦች መሰረት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ውድቅ ሲያደርግ፣ ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት ማሳወቅ አለበት።

(ረ) የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ ተፈፃሚነት በአዋጁ የተጠቀሱ አስገዳጅ የምዝገባ መስፈርቶችን እና የባለስልጣኑን መመሪያዎች ተፈፃሚነት ቀሪ አያደርገውም።

(4) የምዝገባ ሥነ ሥርዓት

ገበያው በሌላ አኳኋን እስካላሳወቀ ድረስ የምዝገባ ሂደቱ እንደሚከተለው ደረጃ በደረጃ ይከናወናል።

(ሀ) አውጭው ለገበያው የምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ አለበት። የምዝገባ ማመልከቻን የሚመለከቱ የሰነድ መስፈርቶች ለአክሲዮን ምዝገባ በዚህ ቅፅ ክፍል ሁለት (2)፣ ለቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በዚሁ ቅፅ ክፍል 4፣ ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች በዚሁ ቅፅ ክፍል 5 እና የሸሪዓን መስፈርት የሚያሟሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በተመለከተ በዚሁ ቅፅ ክፍል 6 ላይ ተካተዋል። የምዝገባ ጥያቄ ጥያቄው በቀረበበት እለት ገበያው ተግባራዊ ባደረገው ክፍያ መሰረት የተከፈለ መሆኑን ከሚገልፅ ማስረጃ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት።

(ለ) ማመልከቻው ቀርቧል የሚባለው የአውጭውን ወደ ገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ የመግባት ተገቢነት ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉት ሁሉም ሰነዶች/መረጃዎች ተሟልተው ለገበያው ሲቀርቡ ብቻ ነው።

(ሐ) ገበያው ማመልከቻው የምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላት አለማሟላቱን ከተመለከተ በኋላ (በቅድመ ሁኔታ ወይም ያለቅድመ ሁኔታ) መፅደቁን ይወስናል። ገበያው ባወጣው የማፅደቂያ ደብዳቤ የተገለፁት ሁሉም ቅድመ ሁኔታዎች እስኪሟሉ ምዝገባው አይፈቀድም።

(መ) ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማውጣት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አውጭው የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን ለባለስልጣኑ አቅርቦ በማፀደቅ የፀደቀውን ኮፒ ቅጅ ከምዝገባ ሰርተፍኬቱ ጋር ለገበያው ማቅረብ አለበት።

(ሠ) የሚመዘገበው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከምዝገባ ጥያቄው አስራ ሁለት ወር በፊት በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ወይም በባለስልጣኑ መመሪያ መሰረት በሌላ የሽያጭ ሰነድ የወጣ ከሆነ ገበያው አውጪው በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ወይም ሌላ ተገቢነት ባለው የሽያጭ ሰነድ ላይ የተደረገ ጉልህ/መሠረታዊ ለውጦችን ያካተተ አባሪ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ አብሮ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።

(ረ) ገበያው ከምዝገባ በፊት አውጭው በመግለጫ ሰነዱ ላይ ካካተታቸው መረጃዎች ባሻገር ተጨማሪ መረጃዎችን እንዲያቀርብ ሊያዘው ይችላል።

(ሰ) ምዝገባው ለህዝብ ሽያጭ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ማቅረብንም በሚመሰረትበት ጊዜ፣ አውጭው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግዥ ወይም የግዥ ቃል መግቢያ ማመልከቻዎች እንዲገቡ ይጋብዛል። የሕዝብ ሽያጩ ከተዘጋ በኋላ አውጭው የሽያጩን ውጤትና እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቃል የተገባውን መጠን፣ የምደባውን መሠረትና ለሕዝብ ሽያጩ የቀረበውን የፍላጎት መግለጫ መጠን ማሳወቅ አለበት።

(ሸ) በገበያው ወጭ በተደረገው የማፅደቂያ ደብዳቤ ላይ የተገለፁት ቅድመ ሁኔታዎችን ሲያሟላ አውጭው በገበያው ፈቃድ ወደ ኦፊሴላዊ መዝገብ እንዲገባ ይደረጋል።

## 3.2. የምዝገባ ቅድመ ሁኔታዎች

ገበያው አዲስ ወይም ተጨማሪ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመመዝገብ ሲወስን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ወደ ገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ እንዲገቡ አውጭው የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች ማሟላት አለበት፤

(1) ገበያው በአውጭው ቦታ ሆኖ ወይም በአውጭው ስም መግለጫዎች፣ መረጃ ወይም ሰነዶችን በማሳተሙ፣ ይፋ በማድረጉ ወይም በማሰራጨቱ ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማንኛውም ሰው ባቀረበው ጥያቄ፣ እርምጃ ወይም ክስ ለሚደርስ ኪሳራ፣ ጉዳት ወይም ወጭ (የህግ ወጭዎችን ጨምሮ)

አውጭው ገበያውን እና ካሳ የተገባላቸውን ሰዎቹን ሙሉ በሙሉ ለመካስ እና ከተጠያቂነት ነፃ ለማድረግ ሲስማማ፣

(2) ገበያው ባዘጋጀው ቅፅ መሰረት የተዘጋጁ፣ የወጡበት ቀን የተፃፈባቸው እና በአውጭው ሁለት (2) ዳይሬክተሮች ወይም እንደሁኔታው በዳይሬክተሩና በኩባንያ ፀሀፊው የተፈረሙ የካሳ ደብዳቤ እና የተገዥነት መግለጫ ኦሪጅናል ቅጅ ገቢ ሲደረጉ፡፡

## ክፍል 2: የአክሲዮን ምዝገባ

### *ምዕራፍ 4: የገበያው የአክሲዮን የምዝገባ መስፈርቶች*

#### 4.1. ተፈፃሚነት

እነዚህ መስፈርቶች አክሲዮናቸውን ገበያው ላይ ለማስመዝገብ በሚፈልጉ የአክስዮን ኩባንያዎች ላይ በሙሉ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

#### 4.2. የገበያው የአክሲዮን ምዝገባ ቦርድ

ገበያው የተለያዩ አክሲዮን ምዝገባ ቦርዶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ እነሱም፤

(1) የዋና ገበያ ቦርድ

(2) የአዳጊ ገበያ ቦርድ፣ እና

(3) ሌላ ማንኛውም በገበያው የሚቋቋም ቦርድ

#### 4.3. የምዝገባ መንገዶች

አክሲዮኑን ገበያው ላይ ለማስመዝገብ የሚፈልግ ማንኛውም አውጪ ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ ማስመዝገብ ይችላል፤

(1) *የመጀመሪያ ምዝገባ*: የአክሲዮን የመጀመሪያ ምዝገባ ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ ሊከናወን ይችላል፡

(ሀ) የማስተዋወቅ ምዝገባ፤

(ለ) የመጀመሪያ ዙር የህዝብ ሽያጭ (ለሽያጭ ማቅረብ ወይም ለግዥ ቃል ኪዳን ማቅረብ)፤

(ሐ) የተገላቢጦሽ ውህደት፤ እና

(መ) ገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወስነው በማንኛውም መንገድ፡፡

(2) አባሪ ምዝገባ: የአክስዮኖች አባሪ ምዝገባ ከታች በደንብ 7.1 ላይ በተገለፀው መንገድ ሊፈፀም ይችላል።

## 4.4. ጠቅላላ መስፈርቶች

(1) የምዝገባ መስፈርቶች: የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባን የሚገዙ ወይም ከነዚህ ጋር የሚገናኙ የገበያው ደንቦችን ከማክበር በተጨማሪ አውጭው ፦

(ሀ) አግባብ ያላቸውን የአዋጁን፣ የንግድ ህጉን፣ የባለስልጣኑን መመሪያዎችን እና/ወይም ሌሎች ተፈፃሚነት ያላቸው የኩባንያ ሕጎችን እና ህጋዊ መስፈርቶችን ማክበር፤

(ለ) በባለስልጣኑ የፀደቀ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ወይም ለህዝብ ሽያጭ ለማቅረብ የተመዘገበ መግለጫ እና/ወይም የተመዘገበ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የምስክር ወረቀት መያዝ፤

(ሐ) በስራ ላይ ያለ ኩባንያ ወይም በስራ ላይ ያለ ኩባንያ ተተኪ መሆን፣ ማለትም በመፍረስ ላይ ያልሆነ ወይም ቦርዱ እንዲፈርስ ያልወሰነበት፣

(መ) የምዝገባ ጥያቄ የቀረበበት አክስዮን ሙሉ በሙሉ የተከፈለ እና መተላለፍ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፤

(ሠ) ምዝገባ በተጠየቀበት በእያንዳንዱ መደብ ውስጥ ያሉ አክስዮኖች ከትርፍ ክፍፍል፣ ካፒታል፣ መልሶ መግዛት፣ ያልተገደበ ማስተላለፍ፣ ስብሰባዎች ላይ ከመሳተፍ፣ በስብሰባ ድምፅ ከመስጠት፣ እኩል ከመታየት እና ከሌሎች መለኪያዎች አንፃር እኩል መብት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤

(ረ) ለመጀመሪያ ዙር ምዝገባ የሚውሉ አክስዮኖች ከሁሉም ወጭ ከተደረጉ ወይም ወደፊት ወጭ ከሚደረጉ በዚያ የአክስዮን መደብ ውስጥ ካሉ ሁሉም አክስዮኖች ጋር የሚገናኝ መሆኑን ማረጋገጥ፤

(ሰ) በምዝገባ ጥያቄ የቀረበበት ቦርድ ተፈፃሚነት ያለውን አነስተኛ ለግብይት የቀረበ አክሲዮን የድርሻ መስፈርት ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፤ እና

(ሸ) በገበያው በየጊዜው የሚወጡ ሌሎች መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ።

(2) የምዝገባ ሰነዶች: አውጭው

(ሀ) የመመስረቻ ፅሁፉ እና ማሻሻያዎቹ እንዲሁም ሌሎች ሰነዶችን ጨምሮ ተገቢነት ያላቸው የምዝገባ ሰነዶች ለገበያው የምዝገባ ጥያቄ በቀረበበት ወቅት የባለአክስዮኖችን፣ የዳይሬክተሮች እና የአውጭውን ካፒታል ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳዩ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(ለ) ማንኛውም ኩባንያ ወይም ተቋማዊ ኢንቨስተር አምስት በመቶ (5%) እና ከዚያ በላይ ድርሻውን የያዘ በሚሆንበት ጊዜ አውጭው የምዝገባ ጥያቄ በቀረበበት ወቅት የተጠቃሚ ባለሀብቶችን ማንነት የሚገልፁ የምዝገባ እና ሌሎች የድርጅቱ ሰነዶችን ማቅረብ አለበት፡፡

(3) የኩባንያ አስተዳደር: አውጭው የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፤

(ሀ) ዋና ስራ አስፈፃሚው እና ዋና የፋይናንስ መኮንንጨምሮ እያንዳንዱ ዳይሬክተር እንደ ዳይሬክተር፣ ዋና የስራ አስፈፃሚ ወይም የፋይናንስ መኮንን የየራሳቸውን ሚና በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ባህሪ፣ ልምድ፣ ታማኝነት፣ ብቃት እና ጊዜ ያላቸው ስለመሆኑ፡፡

(ለ) አግባብነት ያላቸው የኩባንያ አስተዳደር መስፈርቶች መከበራቸውን፡፡

## ምዕራፍ 5 ፡ በዋናው የገበያ ቦርድ የመጀመሪያ ዙር ምዝገባ መስፈርቶች

### 5.1. የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በዋናው የገበያ ቦርድ ምዝገባ

በምዕራፍ 3 እና አንቀጽ 4.4 ላይ የተቀመጡ ጠቅላላ መስፈርቶችን ከማሟላት በተጨማሪ ለገበያው ዋና የገበያ ቦርድ የመጀመሪያ ዙር ምዝገባ ያመለከተ አውጪ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡፡

(1) የሥራ አፈፃፀም መዝገብ፡

(ሀ) አውጭው ቢያንስ የሶስት (3) አመት የሥራ አፈፃፀም መዝገብ ሊኖረው ይገባል፡፡

(ለ) አውጭው የሶስት አመት (3) የሥራ አፈፃፀም መዝገብ ከሌለው ቢያንስ የሶስት አመት የሥራ አፈፃፀም መዝገብ ያለው እና ከፍተኛ ድርሻ ያለው ዋነኛ ኢንቨስተርን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

(ሐ) አውጭው ወይም ዋነኛ ኢንቨስተሩ (ተፈፃሚነት በሚኖረው ጊዜ) በሶስት (3) አመቱ የሥራ አፈፃፀም መዝገቡ በተያዘበት ጊዜ ሁሉ በአንድ ዋነኛ ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ እና በዋነኛ ተመሳሳይ የአስተዳደር ስር የነበረ መሆን ይኖርበታል፡፡

(መ) ገበያው እንደ ኢንዱስትሪው ዓይነት እና የቁጥጥር ማዕቀፍ የዘርፉ ተቆጣጣሪ መኖሩን ጨምሮ የዚህን ደንብ ንዑስ ደንብ 1(ሀ) እና (ለ) መስፈርቶች ሊቀንስ ወይም ቀሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ገበያው ውሳኔውን እና ቀሪ ያደረገበትን ምክንያት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

(2) ትርፋማነት፡-

አውጭው ወይም ዋናው ባለሃብቱ/የቴክኒክ አጋሩ ከማመልከቻው ቀን ቀደም ብሎ ባሉት ሦስት (3) ዓመታት ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ከታክስ በኋላ ትርፍ ማግኘቱን ያሳወቀ መሆን አለበት፡፡

(3) ለሥራ አፈፃፀም መዝገብ ጊዜ የሚቀርቡ የሂሳብ መግለጫዎች፡-

(ሀ) የእያንዳንዱ ያለፉት ሦስት (3) ዓመታት የሒሳብ መግለጫዎች በዓለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች ወይም በኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም ሌላ አግባብነት ባለው ባለስልጣን በኢትዮጵያ የሚተገበር የሂሳብ ስታንዳርድ መሰረት መዘጋጀት አለበት፡፡

(ለ) የአውጪው የሂሳብ መግለጫዎች በቁሳዊ መንገድ መገለፅ አይችሉም፡፡

(4) የገበያ ካፒታላይዜሽን፡-

(ሀ) አንድ አውጪ ሲመዘገብ ቢያንስ የአምስት መቶ ሚሊዮን ብር (500,000,000) ጠቅላላ የገበያ ካፒታላይዜሽን/በባለአክሲዮኖች የተያዙ አክሲዮኖች ሊኖረው ይገባል፡፡

(ለ) የገበያ ካፒታላይዜሽን የሚገኘው በማውጫ/መመዝገቢያ ዋጋ እና ከግብዣ በኋላ በወጣው የአክሲዮን ካፒታል መሠረት ነው፡፡

(5) ለግብይት የቀረበ አክሲዮን

(ሀ) የምዝገባ ጥያቄ ከቀረበባቸው ቢያንስ አስራ አምስት በመቶ (15%) የአውጭው አክሲዮኖች ቢያንስ በ300 የህዝብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች ወይም እንደ የውክልና ሻጭ የሚያገለግሉ የኢንቨስትመንት ባንክ ወይም በተቋማዊ ኢንቨስተር መያዝ አለበት፡፡

(ለ) በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀጽ (5) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ቢያንስ ሁለት ቢሊዮን ብር (2,000,000,000) ካፒታላይዜሽን ያለው አውጪ አሥር በመቶ (10%) ብቻ ለግብይት የቀረበ አክሲዮን እንዲኖረው ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

(ሐ.) በሕዝብ እጅ የሚያዙ አክሲዮኖች መቶኛ ስሌት ውስጥ፣ የቆዩ የህዝብ ባለአክሲዮኖች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዝውውር ገደብ ሥር ካልሆኑ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

(6) የማመልከቻ ሰነዶች

(ሀ) አውጪው በየጊዜው ገበያው በሚወስነው መሠረት አስፈላጊ ሰነዶችን ሁሉ ማቅረብ አለበት፡፡

(ለ) ገበያው የሚቀርቡ ሰነዶችን የሚያመላክት የማረጋገጫ ዝርዝር ማዘጋጀት አለበት፡፡

(ሐ.) ገበያው በየጊዜው የሚፈለጉትን ሰነዶችን ዝርዝር ሊቀይር ይችላል፡፡

(መ) በየጊዜው በገበያው የሚገለፅ ሌላ ማንኛውም መስፈርት፡፡

## 5.2. ተጨማሪ መስፈርቶች

(1) የመጀመሪያ የህዝብ አቅርቦት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዝውውር ገደብ (እንዲፈረሙ ማቅረብ/የሽያጭ አቅርቦት)፤

(ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዝውውር ገደብ ዓላማ ዳይሬክተሮች፣ ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች እና ዋና ባለሃብቶች/የቴክኒክ አጋሮች ለአውጪው ያላቸውን ግዴታዎች መፈጸም እንዲቀጥሉ እና ፍላጎቶቻቸውን ከሕዝብ ባለአክሲዮኖች ጋር ሙሉ በሙሉ ማጣጣም ነው፡፡

(ለ) በመቋቋም ላይ ያለ ኩባንያ ዋና ባለሃብቶች ጋር በተገናኘ የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከላይ የተገለጹት ወገኖች ከምዝገባው ቀን ጀምሮ በአስራ ሁለት (12) ወራት ጊዜያት ውስጥ ድርሻቸውን ከሃምሳ በመቶ (50%) በላይ መቀነስ አይችሉም፡፡ እነዚህ ሰዎች በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ አክሲዮኖችን ላለመሸጥ፣ ላለመመደብ፣ ላለማስተላለፍ፣ ላለማበደር ወይም ላለማስያዝ ቃል መግባት አለባቸው፡፡

(ሐ) ገበያው ኢንቨስት ያደረገውን ሕዝብ ጥቅም የማይጻረር ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ በላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ለመተው ወይም ለመቀነስ ይችላል፡፡

(2) አውጭው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ስለ ሥራው የተወሰነ መረጃ ወዲያውኑ ለማቅረብና አንዳንድ አስተዳደራዊ ሥርዓቶችን እንደሚከተልና የገበያው ቀጣይ የምዝገባ ግዴታዎች ሙሉ በሙሉ እንደሚፈጽም በገበያው በተዘጋጀ ፎርም መሰረት የውል ግዴታ መግባት አለበት፡፡

(3) አውጭው ከመመዝገቡ በፊት የተፈረመውንና ቀን የተሰጠውን ዋናውን የምዝገባ ሰነድ በገቢያው በተዘጋጀ ፎርማት መሰረት ማቅረብ አለበት፡፡

## *ምዕራፍ 6፡ በገበያው የአዳጊ ገበያ ቦርድ የመጀመሪያ ምዝገባ መስፈርቶች*

### 6.1. የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የአዳጊ ገበያ ቦርድ ምዝገባ

በገበያው የአዳጊ ገበያ ቦርድ ላይ ለመመዝገብ የሚፈልግ አውጪ ከዚህ በላይ በምዕራፍ 3 እና በደንብ ቁጥር 4.4 የተዘረዘሩትን አጠቃላይ መስፈርቶች ከማሟላት በተጨማሪ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

(1) የሥራ አፈፃፀም መዝገብ፡

(ሀ) አውጪው ቢያንስ የሁለት (2) አመት የሥራ አፈፃፀም መዝገብ ሊኖረው ይገባል፡፡ የሁለት (2) አመት የሥራ አፈፃፀም መዝገብ ከሌለው ቢያንስ የሁለት (2) አመት የሥራ አፈፃፀም መዝገብ ያለው እና ከፍተኛ ድርሻ ያለው ዋና ኢንቨስተርን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

(ለ) አውጭው ወይም ዋና ኢንቨስተሩ (እንደ አስፈላጊነቱ) በሁለት አመቱ የሥራ አፈፃፀም መዝገቡ በተያዘበት ጊዜ ሁሉ በአንድ ዋና ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ እና በተመሳሳይ ከፍተኛ የአስተዳደር ስር የነበረ መሆን ይኖርበታል፡፡

(2) የእድገት ተስፋ፡-

አውጭው ባለፉት ሁለት (2) ዓመታት የሥራ ክንውኖች ገቢውን በትንሹ ሃያ በመቶ (20%) ማሳደግ አለበት፡፡ አውጭው ለሁለት (2) ዓመታት የሥራ አፈፃፀም መዝገብ የማይዝ ከሆነ፣ አውጭው በዋና ኢንቬስተሩ/የቴክኒክ አጋሮቹ አማካይነት በተመሳሳይ መጠን የማደግ ተስፋ ማሳየት አለበት፡፡

(3) የገንዘብ መግለጫዎች፡-

(ሀ) የአውጪው ወይም የአውጪው ዋና ኢንቬስተር የሒሳብ መግለጫዎች በዓለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች ወይም በኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም በማንኛውም አግባብነት ባለው የኢትዮጵያ ባለሥልጣን በተቀመጠው የሒሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት ሥርዓት መሠረት መዘጋጀት አለባቸው፡፡

(ለ) የአውጪው ሒሳብ በቁሳዊ መንገድ መገለጥ የለበትም፡፡

(4) ለሕዝብ ግብይት የቀረበ አክሲዮን

(ሀ) የምዝገባ ጥያቄ ከቀረበባቸው ቢያንስ 10 በመቶ (10%) የአውጭው አክሲዮኖች ቢያንስ በሃምሳ (50) የህዝብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች ወይም እንደ የውክልና ሻጭ በሚያገለግሉ የኢንቨስትመንት ባንኮች ወይም በተቋማዊ ኢንቨስተሮች መያዝ አለበት፡፡

(ለ) በሕዝብ እጅ የሚያዙ አክሲዮኖች መቶኛ ስሌት ሲሰራ የዝውውር ገደብ ሥር ያልሆኑ የነባር ባለአክሲዮኖች የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

(5) የገበያ ካፒታላይዜሽን፡-

(ሀ) አንድ አውጪ ሲመዘገብ ቢያንስ 50,000,000.00 (ሃምሳ ሚሊዮን ብር) የሚሆን ጠቅላላ የገበያ ካፒታላይዜሽን (ማለትም የተመዘገበ እና የተከፈለ ካፒታል) ሊኖረው ይገባል፡፡

(ለ) የገበያ ካፒታላይዜሽን ዋጋ የሚወሰነው በወጣው/የተመዘገበው ዋጋ እና ከግብዣ በኋላ በሚገኘው የአክሲዮን ካፒታል መሠረት ነው፡፡

(6) የማመልከቻ ሰነዶች፡-

(ሀ) አውጪው በየጊዜው ገበያው በሚወስነው መሠረት አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ሁሉ ማቅረብ አለበት፡፡

(ለ) ገበያው የሚቀርቡትን ሰነዶች የሚያሳይ ዝርዝር ማዘጋጀት አለበት፡፡

(ሐ) ገበያው በየጊዜው የሚፈለጉትን ሰነዶች ዝርዝር ሊቀይር ይችላል፡፡

(መ) ከጊዜ ወደ ጊዜ በገበያው የሚገለፅ ሌላ ማንኛውንም መስፈርት ማሟላት አለባቸው፡፡

## 6.2. ተጨማሪ መስፈርቶች

(1) የመጀመሪያ ዙር የህዝብ ሽያጭ (እንዲፈረም/ለሽያጭ የቀረበ አቅርቦት) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዝውውር ገደብ፤

(ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዝውውር ገደብ ዓላማ፡ ዳይሬክተሮች፣ ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች እና ዋና ኢንቬስተሮች/የቴክኒክ አጋሮች ለአውጪው ያላቸውን ግዴታዎች እንዲቀጥሉ እና ፍላጎቶቻቸውን ከሕዝብ ባለአክሲዮኖች ጋር ሙሉ በሙሉ ለማጣጣም ነው።

(ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመቋቋም ላይ ያለ ኩባንያ ዋና ኢንቬስተር ጋር በተገናኘ በሕዝብ አቅርቦትና የአክስዮን ሽያጭ ከላይ የተገለጹት ሰዎች ከምዝገባው ቀን ጀምሮ በአስራ ሁለት (12) ወራት ጊዜያት ውስጥ የድርሻቸውን ከሃምሳ በመቶ (50%) በላይ መቀነስ አይችሉም። እነዚህ ሰዎች በእነዚህ ጊዚያት ውስጥ አክሲዮኖችን ላለመሸጥ፣ ለሌላ ሰው ላለመመደብ፣ ላለማስተላለፍ፣ ላለማበደር ወይም ላለማስያዝ ግዴታ መግባት አለባቸው።

(2) አውጭው ከተመዘገበበት ቀን አንሥቶ ስለ ሥራው ተፈላጊ መረጃ ወዲያውኑ ለማቅረብና አንዳንድ አስተዳደራዊ ሥርዓቶችን እንደሚከተልና የገበያው ቀጣይ የምዝገባ ግዴታዎችን ሙሉ በሙሉ እንደሚፈጽም በገበያው በተዘጋጀ ፎርም መሰረት የውል ግዴታ መግባት አለበት።

(3) ከመመዝገቡ በፊት አውጭው ቀን የተሰጠውና የተፈረመበትን ዋናውን የምዘገባ ውል በገበያው በተዘጋጅ ፎርማት መሰረት ማቅረብ አለበት።

# ምዕራፍ 7፡ አባሪ የአክሲዮን ምዝገባ መስፈርቶች

## 7.1. ተፈጻሚነት

እነዚህ መስፈርቶች የመጀመሪያ ዙር አክሲዮኖቻቸውን ወደ ገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ ውስጥ ላስመዘገቡ እና ተጨማሪ አክሲዮኖችን ለማስመዝገብ ላሰቡ አውጪዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ። አውጪዎች ተጨማሪ አክሲዮኖችን በሚከተሉት መልኩ ሊያስመዘግቡ ይችላሉ፡-

(1) ለግዢ ቃል ኪዳን ማቅረብ፤

(2) ለሽያጭ በማቅረብ፤

(3) አክሲዮኖችን የመግዛት ቅድሚያ መብት፤

(4) የጉርሻ አክሲዮን በማውጣት፤

(5) አክስዮንን መሰረት ባደረጉ ክፍያዎች፤

(6) በውህደት እና መዋጥ፤

(7) ተለዋጭ ሰነዶች እና

(8) ገበያው በየጊዜው በሚያፀድቃቸው ሌሎች ማናቸውም ዘዴዎች፡፡

## 7.2. አጠቃላይ መስፈርቶች

(1) አውጪዎች የገበያው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ ጋር የሚገናኙ እና የሚያያዙ ደንቦችን በተለይም በዚህ ደንብ ቁጥር 4.4 የተመለከቱትን የምዝገባ አጠቃላይ መስፈርቶች እና አግባብነት ያላቸው የአዋጁ፣ የንግድ ሕጉ፣ የባለስልጣኑን የመመሪያዎች እና/ወይም ሌሎች ማንኛውም አግባብነት ያላቸው የኩባንያው ህግ እና ህጋዊ መስፈርቶችን ድንጋጌዎችን ማክበር አለባቸው፡፡

(2) የአባሪ ምዝገባ ማመልከቻ እንደቀረበ የሚቆጠረው ሁሉም የተሟሉ ሰነድ(ዎች)/መረጃዎች ለገበያው ገቢ ሲደረጉ ብቻ ነው፡፡

(3) አውጪው ገበያው በየጊዜው በሚወጣው እና በገበያው ድህረ ገጽ ላይ በሚታተመው አግባብነት ባለው ዝርዝር መሰረት ሁሉንም ተገቢነት ያላቸውን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡፡

(4) አውጪዎች በገበያው በየጊዜው የሚወስነውን ሌሎች ማንኛውንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

## 7.3. ልዩ የምዝገባ መስፈርቶች

(1) አክሲዮኖችን የመግዛት ቅድሚያ መብት ተጨማሪ መስፈርቶችን በመጠቀም ተጨማሪ አክሲዮኖችን ለመዘርዘር የሚፈልግ አውጪ፡-

(ሀ) የሚወጡ መብቶች ምዝገባ ከሚከተሉት በፊት አለመወሰኑን ማረጋገጥ አለበት፡-

i. በመብቱ ጉዳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የተገኙ ባለአክሲዮኖች እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈቃድን ማግኘቱን፤

ii. በመብቱ ጉዳይ የባለስልጣኑን ፈቃድ ማግኘቱን፤

iii. የመብት ምዝገባው የገበያውን ፈቃድ ማግኘቱን፤ እና

iv. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የውክልና ሽያጭ ውል ስምምነት መኖሩን፣

(ለ) የወጡ መብቶች ዋጋ በፊት ከተዘረዘሩ በተመሳሳይ መደብ ከሚገኙ አክሲዮኖች የገበያ ዋጋ ከፍ ያላለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(ሐ) ከጊዜ ወደ ጊዜ በገበያው የሚወሰኑ ማንኛውንም ሌላ ሰነድ/መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

(2) ለጉርሻ አክሲዮን ማውጣት ተጨማሪ መስፈርቶች፡-

(ሀ) በጉርሻ ምዝገባ ተጨማሪ አክሲዮኖችን የሚያወጣ አውጪ የጉርሻ ምዝገባው የተመዘገበበት ቀን ከሚከተሉት በፊት አለመሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

i. በጉርሻ ጉዳይ የጠቅላላ ጉባኢ ስብሰባ ላይ የተገኙ ባለአክሲዮኖች እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈቃድን ማግኘቱን; እና

ii. ለጉርሻ ጉዳይ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ማግኘቱን፡፡

(ለ) ገበያው በየጊዜው ሌሎች ተጨማሪ ሰነዶችን እንዲቀርቡ ሊወስን ይችላል፡፡

(3) አክስዮንን መሰረት ያደረጉ ክፍያዎች፡ አውጭው በአክሲዮን ላይ የተመሰረተ ክፍያ ለመፈጸም ካሰበ የሚከተሉትን ተጨማሪ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፤

(ሀ) የአክሲዮን አወጣጥን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እና ሁኔታዎችን የያዘ የመጨረሻ እና የጸደቀ በአክሲዮን ላይ የተመሰረተ የክፍያ እቅድ ሰነድ ቅጂ ማስገባት፤

(ለ) በአክሲዮን ላይ ለተመሰረቱ ክፍያዎች የባለስልጣኑን ምዝገባን ማግኘት

(ሐ) ከጊዜ ወደ ጊዜ በገበያው የሚጠየቁ ሌሎች ሰነዶችን ማቅረብ አለበት፡፡

(4) ለውህደት እና በነባር ማህበር መተካት ተጨማሪ መስፈርቶች፡-

(ሀ) ውህደት እና በነባር ማህበር መተካት በተለያዩ የፋይናንሺያል ግብይቶች የኩባንያዎችን ወይም ንብረቶችን መቀላቀል ለመግለፅ የሚያገለግል አጠቃላይ ፅንሰ ሃሳብ ሲሆን ይህም ውህደት፣ በነባር ማህበር መተካት፣ መቀላቀል፣ የጨረታ አቅርቦቶች፣ የንብረት ግዢ እና የአስተዳደር ግዥዎች ያካትታል፡፡

(ለ) አውጪው ከሚከተሉት ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ምክያቶች በመነሳት አክሲዮኖችን ለማስመዝገብ ሊፈልግ ይችላል፡፡

i. በውህደትና በነባር ማህበር መተካት ውስጥ ያለ አውጪ የታለመው ኩባንያ ንብረትን ለመዋጥ ወይም ለውህደት ወይም ለመዋጥ

የተመረጠውን ኩባንያ ባለአክሲዮኖች የተያዙዋቸውን አክሲዮኖች ለመዋጥ ግምት ውስጥ በማስገባት ለታለመው ኩባንያ ባለአክሲዮኖች አክሲዮኖችን የሸጠ እንደሆነ።

ii. በውህደትና በነባር ማህበር መተካት ጊዜ ቀጣይነት ያለው ኩባንያ አስቀድሞ በገበያው የተመዘገበ ከሆነ አውጭው በመዋሃዱ ወይም በመዋጡ ምክንያት የወጡትን ተጨማሪ አክሲዮኖች እንዲመዘግብ ለገበያው ማመልከት አለበት።

iii. በተመዘገበ እና ባልተመዘገበ ኩባንያ መካከል ያለውን ውህደት እና መዋጥን በሚመለከት፣ ቀጣይነት የሚኖረው ያልተመዘገበው ኩባንያ በሚሆንበት ጊዜ የሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል።

1. ቀጣይነት የሚኖረው ኩባንያ የተመዘገበውን ኩባንያ አክሲዮን ለመያዝ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

2. የተመዘገበው ኩባንያ አክሲዮኖች መሰረዝ አለባቸው።

3. ቀጣይነት የሚኖረው ኩባንያ በገበያው መዝገብ ላይ መመዘገብ የሚችል ሲሆን በሚመለከተው የገበያው ቦርድ ውስጥ ለመመዝገብ የተቀመጡ የብቃት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት።

(5) ካፒታልን መልሶ ለማደራጀት ተጨማሪ መስፈርቶች፡-

(ሀ) አውጭው ከዚህ በታች በተገለጹት ማናቸውም ዘዴዎች ካፒታልን እንደገና ማዋቀር ይችላል።

(i) በአክሲዮን ክፍፍል: በአክሲዮን ክፍፍል አንድ ኩባንያ የአክሲዮን ብዛት በመጨመር እና የአክሲዮኖቹን ተመጣጣኝ ዋጋ በመቀነስ የካፒታል መሰረቱን ያስተካክላል። ይህ አሰራር በካፒታል ዋጋው ላይ ምንም ለውጥ አይፈጥርም።

(ii) የተገላቢጦሽ ክፍፍል፡- በአክሲዮን ውህደት ወይም በተገላቢጦሽ ክፍፍል፣ አውጪው የካፒታል መሠረቱን የተጣራ ዋጋ ሳይለውጥ የአክሲዮን ቁጥሩን በመቀነስ የአክሲዮኖቹን ተመጣጣኝ ዋጋ በተመሳሳይ መጠን ይጨምራል።

(iii) የአክሲዮን ካፒታል ቅነሳ፡ የአክሲዮን ካፒታል መቀነስ የተከፈለ ካፒታል መሰረዝን ወይም በንግድ ሕጉ ወይም በየጊዜው በሚደረጉ ማሻሻያዎች መሰረት በተቀመጠው ገደብ ልክ አክሲዮን ሊይ የሚጻፈው ዋጋን መቀነስን ያካተታል፡፡

(iv) የአክሲዮን ካፒታል መጨመር፡ ይህም የነባር አክሲዮኖችን ዋጋን በመጨመር ወይም አዲስ አክሲዮኖችን በማውጣት ሊከናወን ይችላል፡፡

(v) በገበያው በሚፈቀድ በሌላ ማንኛውም ዓይነት ግብይት፡፡

(ለ) አውጭው የካፒታል መልሶ ግንባታን ተግባራዊ ለማድረግ ባሰበ ጊዜ፡-

(i) በእዚህ ደንብ ቀጣይነት ያላችው ግዴታዎች መሠረት የቦርዱን ፈቃድ ካገኘ በኋላ የካፒታል መልሶ ግንባታውን ለገበያው ወዲያውኑ ማሳወቅ እና

(ii.) የታሰበውን የካፒታል መልሶ ግንባታን የሚመለከቱ ሁሉንም የቁጥጥር መስፈርቶች ማማላት አለበት፡፡

## ክፍል 3 - ቀጣይነት ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎች

### *ምዕራፍ 8 - ጠቅላላ ቀጣይነት ያላቸው የአውጪዎች ግዴታዎች*

#### 8.1. *መረጃን ይፋ ማድረግ*

(1) አውጪዎች ሰነደ መዋለ ንዋይን ለህዝብ ይፋ የማድረግ/የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ላይ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ የውሸት ገበያ መመስረትን ለመከላከል ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ዋጋ በወሳኝ መልኩ ሊጎዳ የሚችል ስለራሳቸው ወይም በሥራቸው ስላሉ ወይም ስለ ተባባሪ ኩባንያዎቻቸው የሚያውቁትን ወሳኝነት ያላቸው መረጃዎች ሁሉ በወቅቱ ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡

(2) የአውጪው ዳይሬክተሮች የምዝገባ ደንቦች መከበራቸውን የማረጋገጥ የነጠላና እና የአንድነት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

(3) አውጪዎች ለገበያው እንዲያሳውቁ በሚገደዱበት ጊዜ መረጃዎቹ ለገበያው በሚሰጥር ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ካልሆኑ በስተቀር በገበያው ፈቃድ ባገኙ የመገናኛ ብዙኃን አማካይነት ለሕዝብ ይፋ መሆን አለባቸው፡፡

## 8.2. ወቅታዊ መግለጫ

(1) እያንዳንዱ አውጪ ኢንቬስተሮችና እና ህዝቡ ፍላጎታቸውን ሊነካ የሚችል በተለይ በተመዘገቡ ሰነደ መዋለ ንዋዮች ንግድ እና ዋጋ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ተብለው ስለሚታሰቡ ከዋጋ ጋር የሚገናኙ ማንኛውንም አስፈላጊ መረጃዎች በፍጥነት ማካፈል እና በሚገባ እንዲያውቁ ማረጋገጥ አለበት፡፡

(2) ከዋጋ ጋር የተገናኙ መረጃዎችን ስለማሳወቅ፡ አውጪው የሚከተሉትን ከዋጋ ጋር የተገናኙ  መረጃዎች በፍጥነት ማሳወቅ አለበት፡፡

(ሀ) በአውጪው ዳይሬክቶሬት ውስጥ ያሉ ለውጦች፤

(ለ) የቁልፍ አስተዳደር ወይም የሰራተኞች ሞት፣ የስራ መልቀቅ፣ ስንብት ወይም ሹመት፤

(ሐ) እንደአስፈላጊነቱ በአውጪው የተሾመው የሸሪዓ አማካሪ ለውጥ፤

(መ) በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን ለውጥ፤

(ሠ) የገንዘብ ውጤቶች መግለጫ፤

(ረ) የትርፍ ክፍፍል መግለጫ፤

(ሰ) ከዚህ በፊት ከተገለፀው ጋር ሲነፃፀር በሚጠበቀው ትርፍ ላይ አሉታዊ ለውጥ፤

(ሸ) የታቀደ ካፒታል ማሳደግ ወይም መልሶ ማዋቀር እንቅስቃሴ ወይም በካፒታል መዋቅር ላይ የተደረጉ ለውጦች፤

(ቀ) ለመጠቅለል ወይም ለመዋሃድ፣ ለግዥ ወይም ጨረታ ማቅረብ  ወይም ሀብት ማስወገድን በተመለከተ ማስታወቂያ መስጠት ወ ይም መቀበል፤

(በ) በኩባንያው ወይም በቡድኑ የንግድ ሥራ ሞዴል ወይም አጠቃላይ ባህሪ ወይም ተፈጥሮ ላይ የተደረገ ማንኛውም ለውጥ፤

(ተ) በአውጪው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የተከሰቱ ዋና ዋና አዳዲስ ግኝቶች ማለትም ዋና ዋና አዳዲስ ምርቶችን፣ ውሎችን እና የማስፋፊያ ዕቅዶችን ጨምሮ

(ቸ) በካፒታል ገበያ አዋጅ ክፍል 9 መሠረት ጥቅም ያላቸው ሰዎች የአክሲዮን ለውጥ፤

(ነ) ያልተለመዱ ወይም ያልተደጋገመ ተፈጥሮ ያላቸው ጉዳዮች፤

(ኘ) ለሕዝብ ሽያጭ፣ በመብት ወይም በጉርሻ መልኩ የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን፤

(አ) ማንኛውም ዋና የማስፋፊያ ዕቅዶች ወይም ያሽነፈውን ጨረታ ወይም አዳዲስ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም፤

(ከ) የሥራውን አጠቃላይ ወይም ጉልህ ክፍልን ማስተላለፍ፤

(ወ) በአውጪው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ ላይ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችሉ በፖሊሲዎች፣ ዕቅዶች ወይም ሥራዎች ላይ ያሉ ማናቸውንም ለውጦች፤

(ዘ) ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የሥራ እንቅስቃሴ መስተጓጎል (ዎች)፤

(ዠ) ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ክርክር ወይም አለመግባባት፤

(የ) የመመሥረቻ ሰነዱ ላይ ሊደረግ የታቀደ ማንኛውም ለውጥ፤ እና

(ደ) በሰነደ መዋለ ነዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ መሰረት ወይም ባለአክሲዮኖች የኩባንያውን አቋም እንዲገመግሙ እና በኩባንያው አክሲዮኖች ውስጥ የውሸት ገበያ እንዳይፈጠር ለማስቻል አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መረጃዎች።

## 8.3. መረጃን ይፋ ማድረግ ተፈፃሚነት ስለማይኖርባቸው ሆኔታዎች

(1) በቁጥር 8.2 የተደነገገው ቢኖርም ሰነደ መዋለ ነዋዮችን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ የተደነገገው ቀጣይነት ባለው መልኩ ይፋ የማድረግ መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚከተሉት ውስጥ አንዳቸውም ሲከሰቱ አውጭው ይፋ ከማድረግ ግዴታ ነፃ ሊሆን ይችላል።

(ሀ) እንዲህ ዓይነቱ መግለጫ የሕግ ጥሰት የሚያስከትል ከሆነ፤ ወይም

(ለ) የሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈጻሚ የሚሆኑበት መረጃ ከሆነ፦

(i) ሁኔታ 1: ምክንያታዊ በሆነ ሰው አዕምሮ መረጃው እንዲገለጥ የማይጠብቅ ከሆነ፤

(ii) ሁኔታ 2: መረጃው ሚስጥራዊ ከሆነ፤ ወይም

(iii) ሁኔታ 3፡ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ተፈጻሚ ሲሆን፡፡

1. መረጃው ያልተሟላ ፕሮፖዛል ወይም ድርድር ከሆነ፤ ወይም

2. መረጃው ታሳቢ ጉዳዮችን የሚያካትት ወይም ይፋ ለማድረግ በቂ ካልሆነ፤

(ሐ) መረጃው የተፈጠረው ለድርጅቱ ውስጣዊ አስተዳደር ዓላማ ከሆነ; ወይም

(መ) መረጃው የንግድ ሚስጥር ከሆነ፡፡

(2) ይፋ ከማድረግ ነፃ የመሆን ፈቃዶች በገበያው የፅሁፍ ይሁንታ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡

(3) ገበያው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ለአውጪው የተሰጠውን ፈቃድ በመሻር አውጭው ወዲያውኑ ማስታወቂያውን እንዲያወጣ የማዘዝ መብት አለው፡፡

## 8.4. የሚጢራዊነት መስፈርቶች

(1) አንድ አውጪ ግብይቱን ለማስፈጸም ወይም ፋይናንስ ለማሰባሰብ በማሰብ ለአማካሪዎቹና ለሚደራደራቸው ሰዎች በጥብቅ በመተማመን መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ፣ አውጪው ለተቀባዮች መረጃው ሚስጥራዊ መረጃ እንደሆነ እና የውስጥ መረጃን እንደሚያካትት እንዲሁም መረጃው ለሕዝብ ከመቅረቡ በፊት ተቀባዮቹ በአውጭው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ምንም ዓይነት ግብይት ማድረግ እንደሌለባቸው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

(2) የእነዚህ ደንቦች ማናቸውም ድንጋጌዎች ቢኖሩም, የትኛውም የሚስጢር ስምምነት አንድ አውጪን በምዝገባ ደንቦቹ ውስጥ ያሉትን ግዴታዎች ከመወጣት አያግደውም፡፡

(3) አውጭው ያለጊዜው ይፋ ሲደረጉ አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ማናቸውንም ክስተቶች ለማሳወቅ አለመገደዱ እንደተጠበቀ ሆኖ አውጭው መረጃን ለሦስተኛ ወገን ወይም ተቆጣጣሪ እንዲገልጽ በሕግ የተገደደ እንደሆነ እና ይህ መረጃ ወደ ሕዝብ ውስጥ ከገባ እና ከዋጋ ጋር የሚገናኝ ተፈጥሮ ካለው፣ ይህ መረጃ በአንድ ጊዜ ለገበያው መውጣት አለበት፡፡

(4) ይፋ መደረግ ያለበት መረጃ በዚህ ደንብ ውስጥ ከተፈቀደው በስተቀር ለገበያው ይፋ ከመሆኑ በፊት ለሶስተኛ ወገን መሰጠት የለበትም፡፡

## 8.5. በአውጪዎች አክስዮን ላይ የሚደረጉ ግብይቶችን ይፋ ስለማድረግ

(1) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፖሊሲ፤

(ሀ) ሁሉም አውጪ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ፖሊሲ ማዘጋጀት አለበት። የግብይት ፖሊሲው ሚስጥራዊነትን በውጭ አማካሪዎች ላይ ተፈፃሚ የማድረግ አስፈላጊነትን ማካተት አለበት።

(ለ) ሁሉም አውጪዎች የሰነደ መዋለ ንዋይ ንግድ ፖሊሲያቸውን በየጊዜው በውስጥ ማስታወቂያ እና ድህረ ገፃቸው ላይ ይፋ ማድረግ አለባቸው።

(ሐ) ሁሉም የአቅራቢው የውስጥ አዋቂዎች ግብይቱ በተፈፀመበት ቀን በራሳቸው ሂሳብ ላይ የተደረጉ ግብይቶች ሁሉ በድርጅቱ ፀኃፊ በኩል ለአውጭው በፅሁፍ ማሳወቅ አለባቸው። በውስጥ አዋቂዎች ካሳወቁበት ቀን ጀምሮ አውጭው ግብይቱን በአንድ (1) የስራ ቀን ውስጥ ለገበያው ማሳወቅ አለበት።

(መ) በዳይሬክተሮች እና በዋና መኮንን የተደረጉ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይቶችን በተመለከተ አውጭው በጊዜያዊ ሪፖርቱ (ወይም በጊዜያዊ ሪፖርቱ ማጠቃለያ ካለ) እና በአመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ በሚካተት የኩባንያው አስተዳደር ሪፖርት ላይ:

(i) ኩባንያው በእነዚህ ደንቦች ውስጥ ከተካተቱት አስፈላጊ መስፈርቶች ያላነሱ መስፈርቶችን የያዘ በውስጥ አዋቂዎች የሚደረጉ የሰነደ መዋለ ንዋይ ግብይቶችን በተመለከተ ተፈፃሚ የሚሆን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ንግድ ፖሊሲ ማዘጋጀቱን፣

(ii) በውስጥ አዋቂ የሚደረጉ የሰነደ ሙዓለንዋይ ግብይቶች በሚመለከት በምዝገባ ደንቦች እና በአውጪው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ንግድ ፖሊሲ ውስጥ የተመለከተውን የሚፈለገውን መስፈርት የተከተሉ ወይም ያልተከተሉ መሆኑን፤ እና

(iii) በምዝገባ ደንቦቹ ውስጥ የተመለከቱ ማንኛውንም አስፈላጊ መስፈርት ያላሟሉ ዝርዝሮች እና እንደዚህ ያለውን አለመታዘዝ ለመፍታት አውጪው ስለወሰዳቸው የማስተካከያ እርምጃዎች ማብራሪያ።

(2) የግብይት ገደብ ወቅት፡

(ሀ) የግብይት ገደብ ወቅት

(i) በግምገማ ላይ ያለ የፋይናንስ አመት (የሩብ ወይም አመታዊ) መዝጊያ ላይ፤ ወይም

(ii) የአውጭው ቦርድ በአሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ለመዋያየት ስብሰባ ከጠራበት ወይም የአጀንዳ ወረቀቶችን ከሚበትንበት (የቀደመው ሁሉ) 15 ቀን በፊት ይጀምርና የዋጋ ተፅዕኖ የሚፈጥር መረጃዎች ለገበያው ገቢ ከተደረጉ በኋላ ለ24 ሰዓታት ይቆያል።

(ለ) ማንኛውም አውጪ የግብይት ጊዜ ገደብ ወቅት የሚጀምርበትን ጊዜ ለገበያው ቀድሞ ማሳወቅ አለበት።

(ሐ) ማንኛውም የአውጭው ውስጥ አዋቂ የንግድ መስኮቱ ዝግ በሚሆንበት ወቅት በአውጭው ሰነደ መዋለ ንዋዮች መገበያየት አይችልም።

(መ) የግብይት ጊዜ ገደብ ወቅት በደንብ ቁጥር 8.2.(2) ላይ የተዘረዘሩ መረጃዎች ሙሉበሙሉ ወይም በከፊል ይፋ የማድረጊያ ጊዜ ነው።

(ሠ) የውስጥ አዋቂዎች መዝገብ ስለመያዝ፤

(i) እያንዳንዱ አውጪ

1. የውስጥ መረጃ የሚያገኙ የራሱ ሰራተኞችን፤ እና

2. የአውጪውን ወይም የአውጪውን የፋይናንሺያል ሰነዶችን በሚመለከት የውስጥ መረጃ ማግኘት የሚችል ሌላ የማንኛውንም ሰው ዋና አድራሻ መዝገብ መያዝ አለበት።

(ii) መዝገቡ የተመዘገበውን ሰው ማንነት፣ የውስጥ መረጃ ያገኘበትን ምክንያት፣ የውስጥ መረጃውን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘበትን ቀንና ምዝገባው የተደረገበትን ቀን መግለጽ አለበት።

(iii) ይህ መዝገብ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሲፈጠር በማንኛውም ጊዜ መሻሻል አለበት፡-

1. አንድ ሰው ውስጣዊ መረጃን የሚያገኝበት ምክንያት ላይ ለውጥ ካለ፤

2. አዲስ ሰው ወደ መዝገቡ መጨመር ሲያስፈልግ፤ እና

3. በመዝገብ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው የውስጥ መረጃን ማግኘት የማይችልበት ሁኔታ ላይ ሲሆን።

(iv) እያንዳንዱ አውጪ የውስጥ አዋቂ መዝገቡን እያንዳንዱ ሩብ አመት ካለቀበት ጀምሮ ከሰላሳ (30) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በገበያው በተዘጋጀ ፎርማት መሰረት ማቅረብ አለበት።

## 8.6. የፋይናንስ መግለጫ፡ የሂሳብ አያያዝ ደረጃ

(1) ወደ ገበያው የሚላኩት የሒሳብ መግለጫዎች በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ወይም በኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም በሚመለከታቸው የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት የተደነገጉትን የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ እና ሌሎች የሒሳብ አያያዝ ሕጎችን የተከተሉ የሒሳብ ፖሊሲዎችን እና ዘዴዎችን በመጠቀም መሆን አለባቸው።

(2) ለገበያ አቅራቢው በሚቀርቡት ሁሉም የሒሳብ መግለጫዎች ውስጥ ላለው መረጃ አውጪው ኃላፊነት አለበት። ስለሆነም እነዚህን የሂሳብ መግለጫዎች በሚያዘጋጅ እና በሚያስገባበት ጊዜ አውጭው ሁሉም መረጃዎች ትክክለኛ፣ ከአሳሳች ወይም ሐሰተኛ መረጃዎች፣ እና ጉልህ ስህተቶች የፀዱ እና በመረጃው ግንዛቤ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጠቃሚ እውነታዎችን እንዳይተው ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

## 8.7. የሂሳብ መግለጫ፡ የሂሳብ መግለጫ ማስገባት

(1) አውጪው አግባብነት ያለው የሒሳብ ጊዜ ባለፈ በዘጠና (90) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ኦዲት የተደረገባቸውን የሙሉ የሒሳብ ዓመት የሂሳብ መግለጫዎች ማስታወቅ አለበት።

(2) በዋናው ቦርድ ውስጥ የተመዘገበ አውጪ የሒሳብ ጊዜው ባለቀ ከሰላሳ (30) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የስድስት ወር የሂሳብ መግለጫውን ማሳወቅ አለበት።

(3) የታዳጊ ድርጅቶች ገበያ ቦርድ ውስጥ የተመዘገበ አውጪ የሒሳብ ጊዜው ካለቀ ከሠላሳ (30) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የስድስት ወር የሂሳብ መግለጫውን ማሳወቅ አለበት።

(4) አውጪው ኦዲት የተደረገባቸውን የሂሳብ መግለጫዎች መዝገብ ከገባበት ቀን በኋላ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ሰፊ ስርጭት በሚታተሙ ጋዜጦች ላይ ማተም አለበት።

(5) አውጪው ኦዲት የተደረገባቸውን እና የሩብ ዓመቱን የሂሳብ መግለጫዎች በድረ ገጹ ላይ ማውጣት/ይፋ ማድረግ አለበት።

## 8.8. የፋይናንስ መግለጫዎችን ማስገባት አለመቻል

(1) አውጪው ኦዲት የተደረገበትን የሙሉ ዓመት (ዓመታዊ) የሂሳብ መግለጫውን ከላይ በቁጥር 8.7 መሠረት ማስታወቅ ያልቻለ እንደሆነ የሂሳብ አመቱ ካለቀ ከስልሳ (60) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማስታወቅ አለበት። የፋይናንስ ዓመቱን የሩብ ዓመት የሂሳብ መግለጫን በተመለከተ ማስታወቂያው የሚቀርበው ሩቡ አመቱ ካለቀ በኋላ በአስራ አምስት (15) ቀናት ነው።

(2) ማስታወቂያው ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

(ሀ) በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ተመስርቶ ማስታወቂያ ለመስጠት ስላለመቻሉ ሙሉ ማብራሪያ፤

(ለ) ከኦዲተሮች ጋር ስምምነት የተደረገበት የሒሳብ ዓመት የፋይናንሺያል ውጤት ይፋ ለማደረግ የሚጠበቀውን ቀን፤ እና

(ሐ) በዚህ ደንብ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት አውጭው ማስታወቂያ ሲሰጥ የፋይናንሺያል አመቱን የገንዘብ ውጤት በሚመለከት ከኦዲተሮች ጋር ስምምነት ላይ እንደደረሰ በቁጥር 8.7 የተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል።

## 8.9. የፋይናንስ መረጃን በጊዜው ይፋ ባለማድረግ መታገድ

የምዝገባ ደንቦች ጠቅላላነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ገበያው በባለስልጣኑ ይሁንታ፣ አንድ አውጪን በገበያው ምዝገባ ደንቦች መሠረት ወቅታዊ የፋይናንሺያል መረጃዎችን ይፋ ካላደረገ ከሰነድ ሙዓለ ንዋይ ንግድ ሊያግድ ይችላል። አውጪው አስፈላጊውን የፋይናንስ መረጃ ይፋ እስኪያደርግ ድረስ እገዳው ፀንቶ ይቆያል።

## 8.10. ዓመታዊ ሪፖርት

(1) አመታዊ ሪፖርቱ የአውጪውን ሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ ሁኔታ በትክክል ለመረዳት በቂ መረጃ መያዝ አለበት እንዲሁም አግባብነት ካላቸው የሂሳብ ደረጃዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እና የሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅትን በሚመለከቱ መስፈርቶች በተጨማሪ አውጪዎች በሂሳብ መግለጫዎቻቸው ውስጥ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡

(ሀ) በአውጭው ውስጥ አምስት በመቶ (5%) ወይም ከዚያ በላይ የያዙ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር፤

(ለ) የአክሲዮን ድርሻ መግለጫ፣ እና ለግብይት የቀረበው አክሲዮን ከገበያው የሽያጭ ስርጭት መስፈርት ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን የሚጠቁም መግለጫ፤

(ሐ) መግለጫው (ከተሰጠው መግለጫ ቀን ጀምሮ ዓመታዊው ጠቅላላ ጉባኤ ማስታወቂያ ወይም ማጠቃለያ የሒሳብ መግለጫ ከተሰጠበት ቀን ቀደም ብሎ ከአንድ (1) ወር ያልበለጠ ጊዜ ድረስ የተዘጋጀ ሆኖ) የሚከተሉትን የሚገልጽ ይሆናል፡-

(i.) የእያንዳንዱ የአክሲዮን መደብ ባለአክሲዮኖች ብዛት እና ከእያንዳንዱ የአክሲዮን ክፍል ጋር የተኛኘ የመምረጥ መብት፤

(ii.) የባለአክሲዮኖችን ቁጥር በድርሻ ልክ ከሚያስቀምጡ አክሲዮን ላይ ከተመሰረቱ ክፍያዎች ውጭ የእያንዳንዱ የአክሲዮን ክፍል (ተለዋዋጭ ዋስትናዎችን ጨምሮ) የማከፋፈያ መርሐግብርን የያዘ መግለጫ፡፡

(መ) በጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ አሁንም ንቁ የሆኑ ወይም ካለፈው የሒሳብ ዓመት ጀምሮ የተደረጉ የዋና ሥራ አስፈፃሚውን፣ የእያንዳንዱን ዳይሬክተር ወይም የቁጥጥር ባለአክሲዮኖችን ፍላጎት የሚያካትቱ የአውጭው እና የተቀጥላዎቹ ጠቃሚ ውሎች፡፡ ለብድር የተዘጋጀ ከሆነ፡

(i) የአበዳሪው እና የተበዳሪው ስም፤

(ii) በአበዳሪው እና በተበዳሪው መካከል ያለው ግንኙነት እና ዳይሬክተሩ ወይም ተቆጣጣሪ ባለአክሲዮን እንድ አበዳሪ ወይም ተበዳሪ የሚሳተፍ መሆን አለመሆኑን፤

(iii) የብድር መጠን፤

(iv) የወለድ መጠን፤

(v) ለወለድ እና ብድር ክፍያ የክፍያ ደንቦች፤ እና

(vi) የተሰጠው ዋስትና፡፡

(ሠ) ከአስተዳደር እና ከኩባንያ አስተዳደር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፤ እና

(ረ) በምዕራፍ 10 መሠረት እንደ አስፈላጊነቱ በበጀት ዓመቱ ስለተከናወኑ ማናቸውም የተዛማጅ ወገን ግብይቶች መረጃ ማካተተ ይኖርበታል፡፡

## 8.11. የሕግ ተገዢነት ሥራ አስኪያጅ

አውጪው እነዚህን ደንቦች የመከታተል እና የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው የውስጥ ተገዢነት ሥራ አስኪያጅ ወይም ተመጣጣኝ መኮንን መመደብ አለበት እና ማንኛውንም ጥሰት ወይም አለመታዘዝ ለገበያው ሪፖርት ያደርጋል፡፡

# *ምዕራፍ 9 - የኩባንያ ኃላፊነት*

## 9.1. ዓላማ

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ አውጪዎች ገበያው ከፍተኛ የኩባንያ አስተዳደር ደረጃዎችን ለማበረታታት ካለው ቁርጠኝነት ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ አውጪዎች ተገቢውን የኩባንያ

ኃላፊነት፣ ታማኝነት እና ተጠያቂነት ደረጃዎችን ለባለአክሲዮኖች ለማስጠበቅ ያተኮሩ አንዳንድ ልምዶችን እንዲከተሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 9.2. የዳይሬክተሮች ግዴታዎች

(1) ዳይሬክተሮች የአውጪዎች በቦርድ ስብሰባዎቻቸው እና ጠቅላላ ጉባኤ ወቅት የገበያው ደንቦችን አክብረው መንቀሳቀሳቸውን የማረጋገጥ የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

(2) ገበያው ዳይሬክተሮች የታማኝነት እና የክህሎት ግዴታቸውን በሚመለከተው ህግ ከተቀመጡት መመዘኛዎች በተመጣጠነ መልኩና እና ትጋት እንዲወጡ ይጠብቃል፡፡

(3) ዳይሬክተሮች ከዚህ በላይ የተገለጹት ተግባራት መከበራቸውን ለገበያው ወዲያውኑ የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 9.3. የቦርድ ስብሰባዎች

(1) እያንዳንዱ አውጪ ስለ የትርፍ ድርሻ፣ የጉርሻ አክሲዮን ማውጣት ወይም የመብቶች ውሳኔን በሚመለከት ለመወያየት የሚደረግ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቀንና ሰዓትን ቢያንስ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት በፊት ለገበያው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

(2) እያንዳንዱ አውጪ የሚከተሉትን ጉዳዮች በሚመለከት አግባብነት ያለው የቦርድ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ በሃያ አራት (24) ሰአታት ውስጥ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ (ዎች) አስፈላጊውን ፈቃድ ካገኘ በኋላ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፤

(ሀ) ማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መልሶ ለመግዛት የሚሰጥ ውሳኔ፣ ግዥ የሚፈፅምበትን ቀን የተመዘገበ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ መልሶ የመግዣ የዝውውር ሰነድ (ወይም ሂሳብ) የሚዘጋበትን ጊዜ ነው፡፡

(ለ) ማንኛውም መልሶ መግዛት ከተደረገ በኋላ የሚቀረውን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ መጠን፤

(ሐ) ለማንኛውም ዓመታዊ፣ የግማሽ ዓመት፣ የሩብ ዓመት እና የንጽጽር አኃዞች ከታክስ በፊት እና ከታክስ በኋላ የተገኘውን ትርፍ፣ አኃዞቹ ጊዜያዊ ወይም ኦዲት ያልተደረጉ መሆናቸውን መግለፅ አስፈላጊ የሆነባቸውን ሁኔታዎች ጨምሮ፣

(መ) የአባላት የትርፍ ክፍፍል ማፅደቅን እና የጉርሻ ጉዳይ፣ የመብት ጉዳይን ጨምሮ ማንኛውም የትርፍ ድርሻ ወይም የጉርሻ ሃሳብ፤

(ሠ) በካፒታል መዋቅሩ ላይ ለማድረግ የታቀደ ማንኛውም ለውጦች ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋይን መልሶ መግዛት፤ እና

(ረ) ለአውጭው የዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበ ማንኛውም ዋጋ-ተኮር መረጃ ::

## 9.4. የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ

(1) እያንዳንዱ አውጪ በንግድ ሕጉ፣ በአውጪው መመሥረቻ ጽሑፍና በመሳሰሉት አስፈላጊ ሰነዶች መሠረት የባለአክሲዮኖችን ወይም የሌላውን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች ጠቅላላ ጉባኤዎች ስብሰባዎች ማድረግ አለበት።

(2) እንዲሁም አውጪው ባለአክሲዮኖች ወይም የሌሎች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች መብቶቻቸውን በስብሰባዎች ላይ ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙ መፈቀዱን ማረጋገጥ አለበት።

(3) ጠቅላላ ጉባኤው ለባለአክሲዮኖች ወይም ለሌላ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች ዳይሬክተሮችንና አስተዳዳሪዎችን በሒሳብና ሪፖርቶች፣ በጉባኤው ላይ የቀረቡ ሰርኩላሮችና በአጠቃላይ አውጪውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የመጠየቅ ዕድል ይሰጣቸዋል።

(4) በስብሰባ ላይ ድምጽ መስጠት፡ በእነዚህ ደንቦች ምዕራፍ 10 እና አግባብነት ባለው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በውሳኔው ላይ ጥቅም ያላቸው ዳይሬክተሮች ለእሱ / ለሷ በሚመች የውሳኔ ሃሳቦች ላይ ድምጽ ከመስጠት እንዲቆጠቡ ይደረጋሉ። ይህ በሚመለከተው የምዝገባ ሰነድ ወይም ሰርኩላር ወይም ማስታወቂያ ለባለአክሲዮኖች መገለጽ አለበት።

(5) የአውጪዎች ስብሰባ ማስታወቂያ

(ሀ) የአውጪው የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕጉ በተደነገገው መሠረት የስብሰባ ማስታወቂያ መስጠት አለበት።

(ለ) እያንዳንዱ አውጪ በጠቅላላ ጉባኤ ጋር የተያያዙ የስብሰባ ማስታወቂያዎች፣ ሰርኩላር፣ ዓመታዊ ሪፖርቶች እና ሌሎች ሰነዶችን ወዲያውኑ በድረ-ገጹ ላይ መጫን አለበት።

(ሐ) በባለአክሲዮኖች ወይም በሌሎች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች ሲጠየቁ እና ተግባራዊ በሚሆኑበት ጊዜ አውጪዎች የጸደቁትን ሰነዶች ኤሌክትሮኒክ ቅጂዎች ለባለአክሲዮኖች ወይም ለሌላ ዋስትናዎች ባለቤቶች መስጠት አለባቸው። የእነዚህ ሰነዶች ቅጂዎች በአውጪው ድህረ ገጽ ላይ መጫን አለባቸው።

# ምዕራፍ 10፡ የተዛማጅ ወገን ግብይቶች

## 10.1. ጠቅላላ መስፈርቶች

(1) አውጪው በንግድ ሕጉ እና በባለስልጣኑ የሰነደ መዋለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ላይ በተገለጸው መስፈርት መሠረት በሒሳብ ላይ ይፋ የማደረግ እና በቀጥታ ይፋ የማድረግ ሂደት ማንኛውንም የተዛማጅ ወገን ግብይቱን ለገበያው በ 24 ሰዓት ውስጥ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት።

## 10.2. እንደ ተዛማጅ ወገን ግብይት የማይቆጠሩ ግብይቶች

አውጪው በገበያው ሁለተኛ ደረጃ ምዝገባ ላይ ያለ የውጭ ኩባንያ ከሆነ እና የመጀመሪያ ደረጃ ዋና ተቆጣጣሪው የተዛማጅ ወገን ግብይቶችን የሚቆጣጠር ከሆነ እነዚህ ደንቦች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም። ገበያው አሁንም ግብይቱ ያለችግር እንዲካሄድ ለማገዝ የተለየ መረጃ ሊጠይቅ ይችላል።

## 10.3. የተዛማጅ ወገን ግብይት ሪፖርት ይዘቶች

(1) ስለ ተዛማጅ ወገኖች ግብይት የሚገልጽ ሪፖርት ግብይቱ ከጸናበት ቀን በሃያ (20) የሥራ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን አካቶ በአውጪው መዘጋጀት አለበት።

(ሀ) ጥቅም ያለው ወገን ከአውጪው ጋር ስላደረገው ግብይት ዝርዝር፣ እና የዚያ ጥቅም ያለው ወገን በግብይቱ ላይ ያለው ጥቅም ምንነት።

(ለ) የግብይቱን ዝርዝሮች እና የግብይቱን አግባብነት ያላቸውን ደንቦች እና ስምምነቱ የተደረሰባቸው መሠረቶች።

(ሐ) ምክንያት እና ለተመዘገበው ኩባንያ ያለውን ጥቅም።

(መ) የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈቃድ፣

(ሠ) ግብይቱ በኩባንያው ከወጡ አክሲዮኖች ወይም ንብረቶች 10% ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ የውጭ ኦዲተር አስተያየት እና የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ፈቃድ ።

## 10.4. ጠቅላላ ስልጣን

(1) ከገቢ ወይም ንግድ ጋር ለተያያዙ መደበኛ ግብይቶች ወይም አስፈላጊ ለሆኑ እንደ ዕቃዎችን እና ቁሳቁሶችን መግዛት እና መሸጥ ላሉ መደበኛ ለዕለት ተዕለት ግብይቶች አውጪው ከሰነደ መዋለ ንዋይ ባለቤቶች ጠቅላላ ፈቃድ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም ይህ ፈቃድ ንብረቶችን፣ ንግዶችን ወይም ሌሎች ዋና ነገሮችን መግዛት ወይም መሸጥን አያካትትም። ይህ ፈቃድ በየአመቱ መታደስ አለበት።

(2) አውጪው፡-

(ሀ) በበጀት ዓመቱ በጠቅላላ ፈቃዱ መሠረት የተከናወኑ የግብይቶች አጠቃላይ ዋጋ በማካተት በዓመታዊው ሪፖርቱ ውስጥ የተሰጠውን አጠቃላይ ስልጣን መግለፅ፣ እና

(ለ) ሪፖርቱን ይፋ ለማድረግ በሚያስፈልገው ጊዜ ውስጥ ሪፖርት ማድረግ የሚጠበቅበትን አጠቃላይ የሒሳብ ጊዜን መሠረት በማድረግ የተከናወኑ ግብይቶችን አጠቃላይ ዋጋ ማሳወቅ አለበት፡፡

(3) ጠቅላላ ስልጣን ለመጠየቅ ለባለአክሲዮኖች የሚሰጠው ሰርኩላር የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

(ሀ) የተመዘገበው አካል አብሮት ግብይት የሚፈፅመው ተዛማጅ ሰው መደብ፤

(ለ) በተሰጠው ፈቃድ መሠረት የሚሸፈኑ ግብይቶች ዓይነት፤

(ሐ) የተመዘገበው አካል ምክንያት እና የሚያገኘው ጥቅም፤

(መ) የግብይት ዋጋ የሚወሰንበት ዘዴ ወይም ሂደት፤

(ሠ) በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀጽ (3) (መ) ውስጥ ያሉት ዘዴዎች ወይም ሂደቶች ግብይቶቹ በመደበኛ የንግድ ደንቦች መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ በቂ መሆናቸው እና የአውጪውን እና የአናሳ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶችን ጥቅም የማይጎዱ መሆኑ ላይ የገለልተኛ የፋይናንስ አማካሪ አስተያየት፤

(ረ) ከገለልተኛ የፋይናንስ አማካሪው የተለየ አመለካከት ከያዘ የኦዲት ኮሚቴ አስተያየት፤

(ሰ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (3) (መ) ውስጥ ያሉት ዘዴዎች ወይም ሂደቶች ተገቢ ካልሆኑ ከባለአክሲዮኖች አዲስ ስልጣን ማግኘት እንዳለበት የሚገልፅ በአውጪው የተሰጠ መግለጫ; እና

(ሸ) ተዛማጁ አካል እንደማይሳተፍ እና አጋሮቹ ግብይቱን ለማጽደቅ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ድምጽ እንዳይሰጡ እንደሚያደርግ የሚያረጋግጥ መገልጫ፡፡

(4) የኦዲት ኮሚቴው የከተሉትን ሁነቶች ካረጋገጠ ለጠቅላላ ስልጣን እድሳት ነፃ የሆነ የፋይናንስ አማካሪ አስተያየት አያስፈልግም

(ሀ) የግብይቱን ዋጋ የመወሰኛ ዘዴዎች ወይም ሂደቶች ከመጨረሻው የባለአክሲዮኖች ውሳኔ በኋላ አለመለወጣቸውን; እና

(ለ) ዘዴዎች ወይም ሂደቶች ግብይቶቹ በመደበኛ የንግድ ደንቦች መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ በቂ መሆናቸው እና የአውጪውን እና የአናሳ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶችን ጥቅም የማይጎዱ መሆናቸውን።

(5) ከዚህ በላይ በንኡስ ቁጥር (3) የተመለከተው መረጃ ከአውጪው ምዝገባ ጋር በተገናኘ በተዘጋጀ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ የተካተተ እንደሆነ አውጪው የድንበኛ ሳቢ መግለጫውን እንደ ጠቅላላ ሥልጣን ሊቆጥረው ይችላል። ስልጣኑ እስከ ሚከተሉት ጊዚያት ድረስ ተግባራዊ ይሆናል፦

(ሀ) ከምዝገባ በኋላ የአውጪው የመጀመሪያ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ እስኪደረግ፣ ወይም

(ለ) የምዝገባው የመጀመሪያ አመት ክብረ በዓል።

### 10.5. ስላለመተው

ገበያው ከእነዚህ ደንቦች ማናቸውም ድንጋጌዎች ነፃ የመሆን ማመልከቻን ማስተናገድ አይችልም።

## *ምዕራፍ 11፡ በአውጪዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ንግድ ላይ የሚጣል እገዳ*

### 11.1. የግብይት እገዳ

ገበያው በማንኛውም ጊዜ እና ገበያው ለሚወስነው ጊዜ በአውጪዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ላይ እገዳ የመጣል ስልጣን ያለው ሲሆን በማንኛውም ጊዜ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋይዎች ግብይትን በባለስልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ማገድ ይችላል።

(1) ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ማዋቀርን፣ እንደገና ማደራጀትን፣ዕዳን በድርድር መፍታት፣ ውህደትን ወይም በኩባንያው ምርጫ የካፒታል ቅናሽን ጨምሮ ማንኛውም ጠቃሚ የሆነ የኩባንያ ስራ ወይም የካፒታል መልሶ ማዋቀር ሲከሰት።

(2) በገበያው ውስጥ በሚገበያዩት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ሥርዓቱን የጠበቀና ፍትሐዊ ገበያ እንዲኖር ማድረግ በገበያው አስተያየት አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፤

(3) እነዚህን ደንቦች በአውጪ ወይም በዳይሬክተሮች የመጣስ ሁኔታ ሲፈጠር፤ ወይም አውጪው ወይም ዳይሬክተሮቹ የገበያውን መመሪያዎችን ሳያከብሩ ሲቀሩ፤

(4) የባለስልጣኑን የአውጪው ሰነደ መዋለ ንዋዮች ግብይትን እንዲያግድ ለገበያው ትዕዛዝ ሲሰጥ፤

(5) የተመዘገቡ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የክፍያ ጊዜ ሲደርስ፤

(6) አውጭው በገንዘብ ጠያቂዎች ወይም በፍርድ ቤት እንዲጣራ ወይም እንዲፈርስ የተደረገ እንደሆነ፤

(7) በንግድ ሕጉ መሠረት በፈቃደኝነት ወይም በግዴታ በአውጭው የታቀደ ሞግዚትነት፣ መዘጋት ወይም የመፍረስ ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ፣ ወይም

(8) በእነዚህ ደንቦች በተመለከቱት በማናቸውም ሁኔታዎችን መሠረት ባደረገ ሌላ ምክንያት ገበያው ተገቢ ነው ብሎ የገመተ እንደሆነ።

## 11.2. በፈቃደኝነት መታገድ

ገበያው በባለስልጣኑ ፈቃድ መሠረት በአውጪው ጥያቄ የተመዘገቡትን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት በማንኛውም ጊዜ ሊያቆም ይችላል። አውጪው አክሲዮኖችን ለማገድ ሲያስብ፡-

(1) የእገዳው ቀን ከመድረሱ ከአምስት (5) ቀናት በፊት አውጪው የአክሲዮን ንግዱ እንዲታገድ የሚጠይቅ ማመልከቻ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት።

(2) በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ማመልከቻ ገበያው እንደአስፈላጊነቱ በሚገልጸው መሠረት ገብያው ማመልከቻውን ለምን ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት በሚያስረዱ ምክንያቶች እና አግባብነት ባላቸው ሰነዶች አስደግፎ ማቅረብ አለበት።

(3) እገዳው የተፈጠረው በካፒታል መልሶ ማደራጀት ሥራ ምክንያት ከሆነ የአክሲዮን ግብይት እገዳው የመልሶ ማዋቀር ሥራው እስኪጠናቀቅ እና መሠራት ያለበት ነገር ሁሉ ተሰርቶ እሰኪጠናቀቅ ድረስ እንደማይነሳ አውጪው ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

(4) የአውጪው አክሲዮን ንግድ እገዳ አውጭውን እስከመጨረሻው መሰረዝን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ይህም በመጠበቂያ ስምምነት መሰረት ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሰነደ መዋለ ንዋዮች አውጭው ከገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ ሙሉ በሙሉ እሰኪሰረዝ ድረስ ታገደው እንደሚቆዩ መገንዘብ ያስፈልጋል።

## 11.3. ከእገዳዎች ጋር በተያያዘ የአውጪው ቀጣይ ግዴታዎች

የአውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በእገዳ ላይ ሲሆኑ በገበያው እና በባለስልጣኑ ፈቃድ ካልተሰጠውበስተቀር፡-

(1) በእሱ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑትን ሁሉንም የምዝገባ ግዴታዎች ማክበሩን ይቀጥላል፤ እንዲሁም

(2) የአውጪውን ወቅታዊ ሁኔታ የሚመለከቱ ወርሃዊ ሪፖርቶችን ለገበያው ያቀርባል፡፡

## *ምዕራፍ 12፡ አውጭውን እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ከገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ መሰረዝ*

### 12.1. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ምዕራፍ የሚደነግገው፤

(1) በፈቃደኝነት መሰረዝን በተመለከተ አውጪው ማማላት ያለበትን መስፈርቶች፤ እና

(2) ገበያው አውጪን ወይም የተመዘገቡ የትኛውም አይነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመሰረዝ ካለው ስልጣን ጋር የሚገናኙ ድንጋጊዎችን ነው፡፡

### 12.2. የተመዘገቡ አክሲዮኖችንማስወገድ

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣንን ፈቃድ መሰረት በማድረግ ገበያው የአውጭውን ከገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ በፈቃደኝነት የመሰረዝ ጥያቄ ሊቀበለው ይችላል፡፡

### 12.3. በፈቃደኝነት የተመሠረተ የአክስዮኖች ስረዛ

(1) አክሲዮኑ ከገበያው ኦፊሴላዊ መዝገብ ላይ እንዲሰረዝለት የሚፈልግ አውጭ፤

(ሀ) የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ጠርቶ፣ ቦርዱ ለአውጭው ባለአክሲዮኖች የሚሰጠውን በፈቃዱ መሰረዝ እንዳለበት የሚገልፅ የውሳኔ ሐሳብ ሲመረምርና ውሳኔ ሲያሳልፍ እና፤

(ለ) ለባለአክሲዮኖች አውጭው እንዲሰረዝ በቦርዱ ለባለአክሲዮኖች የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ እና የሚከተሉትን ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡

i. በዚህ ረገድ የተወሰነን የቦርዱን ውሳኔ ቅጂ፣

ii. አውጭው ገበያው በኢትዮጵያ ሰፊ ስርጭት ባለው ቢያንስ በሁለት (2) የህትመት ጋዜጦች ላይ አንዱን በአማርኛ እና ሌላው በእንግሊዘኛ ወይም በየጊዜው ገበያው በሚያዘው መሰረት ቦርዱ ያቀረበውን አውጭውን በፈቃደኝነት ማሰረዝ ሐሳብ ባለአክሲዮኖች የሚመለከቱበትን ጠቅላላ ጉባኤ ማስታወቂያ እንዲያወጣ ፈቃድ እንደሰጠው የሚጠይቅ ማመልከቻ፤

iii. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርበውንረቂቅ ማስታወቂያ ግልባጭ፤ እና

iv. በየጊዜው በገበያው የሚጠየቅ ሌላ ማንኛውም ሰነድ፡፡

ሐ. ስረዛው ከውህደት ወይም መልሶ ማቋቋም ጋር የተገናኘ በሚሆንበት ጊዜ በገበያው የተቀመጡ መሰፈርቶች መሟላት አለባቸው፡፡

(2) አውጭው ከገበያው ኦፊሳላዊ መዝገብ ውስጥ በፈቃደኝነት ለመሰረዝ ያቀረበው ማመልከቻ በገበያው ተቀባይነት የሚያገኘው የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡-

(ሀ) አውጪው አክስዮኖቹ ለመጀመሪያ ጊዜ በገበያው ላይ ከተመዘገቡበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለሦስት (3) ዓመት ተመዝግቦ የቆየ ከሆነ ነው፡፡

(ለ) የማሰረዣ ማመልከቻው በሚቀብበት ጊዜ በገበያው በተደነገገው እና በሥራ ላይ ባለው መሠረት የሚመለከተውን ክፍያ መከፈሉን የሚያሳይ ማስረጃ ጋር ተያየዞ ከቀረበ ነው፡፡ እንዲሁም በማመልከቻው መመሪያ ዝርዝር ውስጥ የተገለጹትን አስፈላጊ ደጋፊ ሰነዶች ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

(ሐ) አውጪው ከምዝገባ በኋላ ያሉትን ግዴታዎች አግባቡ መወጣቱን በጽሑፍ ሲያረጋግጥ፣ ለምሳሌ የሚመለከታቸውን ክፍያዎችን ወይም ቅጣቶችን መክፈልን እና ሂሳቦችን ማስገባት እና ሌሎችም ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸሙ በጽሑፍ ሲያረጋገጥ እና አውጪው ለባለአክሲዮኖች ያሉትን ግዴታዎች በሙሉ በአጥጋቢ ሁኔታ ሲወጣ እና በዚህም ምክንያት ለባለአክሲዮኖች እና / ወይም ለገበያው ምንም ያልተወጣቸው ግዴታዎች እንደሌሉ ሲያረጋግጥ፤

(መ) አውጭው የምዝገባ ስረዛውን ለማድረግ በተመዘገቡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይሁንታ ካገኘ፣ እና

(ሠ) አውጪው የባለስልጣኑን እና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለስልጣናትን ይሁንታ ካገኘ፡፡

(3) ከገበያው ለመሰረዝ የሚፈልግ አውጪ አግባብነት ባለው የንግድ ሕግና ሌሎች ተፈፃሚነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለአናሳ ባለአክሲዮኖች ለቁጥጥር የሚያበቃ የግዥ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ አውጪው፡-

(ሀ) ለቁጥጥር የሚያበቃ የግዥ ጥያቄው ገለልተኛ በሆነ የኢንቨስትመንት አማካሪ ምልከታ ፍትሃዊ እና ምክንያታዊ መሆኑን፡፡

(ለ) ለቁጥጥር የሚያበቃ የግዥ ጥያቄው ከሶስት (3) ወራት ላላነሰ ጊዜ ክፍት ሆኖ መቆየቱን፣ እና

(ሐ) የግዢ ጥያቄው ጊዜ መጨረሻ ምላሽ ያልሰጡ ባለአክሲዮኖች አውጪው ከተሰረዘ በኋላ የአውጪው ባለአክሲዮኖች ሆነው ለመቀጠል እንደመረጡ ይገመታል፡፡

(4) ከገበያው መዝገብ ለመሰረዝ የሚፈልግ አውጪ የሁሉንም አናሳ ባለአክሲዮኖች ድርሻ ለመግዛት የሚያስችል በቂ ገንዘብ እንዲያስቀምጥ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ገንዘብ በንግድ ሕግ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች በሚደነገገው መሠረት ፈቃድ በተሰጠው የንግድ ባንክ ውስጥ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ ስም ቢያንስ ለሦስት (3) ወራት ታገደው ይቀመጣሉ፡፡

(5) የአውጪውን ባለአክሲዮኖች ሁሉንም ድርሻ ለመግዛት የግዥ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ግዥው በአዋጁና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት መቅርብ ያለበት ሲሆን፣ አቅራቢውም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ለመግዛት በቂ ገንዘብ መመደብ አለበት፡፡ ይህ ገንዘብም በንግድ ባንክ ውስጥ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ ስም በዝግ የሂሳብ ቁጥር ታግዶ ሆነው ይቀመጣሉ፡፡

## 12.4. ለመጨረሻ ጊዜ መሰረዝ የሚያበቁ ሁኔታዎች

ገበያው የአውጪውን ከምዝገባ ስረዛ ሲያፀድቅ፣ አውጪው ከገበያው ኦፊሳላዊ ምዝገባ ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰረዙ በፊት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፣

(1) አውጪው ከገበያው ለመሰረዝ የሚያስችል ዝግጅት ማጠናቀቁንና አውጪው ከገበያው መዝገብ ከተሰረዘ በኋላ አብረው መቀጠል የማይፈልጉ አናሳ ባለአክሲዮኖች ክፍያቸውን ከማዕከላዊው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እንዲወስዱ የሚገልጽ ማስታወቂያ በኢትዮጵያ በስፋት በሚሰራጩ ቢያንስ በሁለት (2) ጋዜጦች እና በአውጪው ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ላይ ማሳተምአለበት፤

(2) ከአውጪው ጋር አብሮ ላለመቀጠል ያሰቡትን አናሳ ባለአክሲዮኖችን እ እንዲከፍል ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ ኩባንያው መመሪያ መስጠት፤ እና

(3) የተከፈሉ ባለአክሲዮኖችን ዝርዝር እንዲሁም የዚህ ደንብ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መፈፀማቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ለገበያው ያቀርባል፡፡

## 12.5. በተቆጣጣሪ አካል መሰረዝ

በገበያው አነሳሽነት መሰረዝ የገበያውን ቀጣይ የምዝገባ ግዴታዎች በተደጋጋሚ ባለማክበር ምክንያት በአውጭው ላይ ሊጣል የሚችል የመጨረሻው ቅጣት ነው፡፡ ገበያው አውጭውን ከኦፊሴላዊው መዝገብ ውስጥ ሊሰርዘው የሚችለው፦

(1) አውጪው የምዝገባ ደንቦችን ለማክበር ካልቻለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ፤

(2) በሕዝብ እጅ ውስጥ በቂ ያልሆኑ አክሲዮኖች ሲኖሩ (ማለትም ለግብይት የቀረበ አክሲዮን እጥረት)፤

(3) አንድ አውጪ ለሁለት (2) ተከታታይ ዓመታት ከሥራ ውጭ ከሆነ፤

(4) የአውጪው የሥራ ፈቃድ በመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ ሲሰረዝ፤

(5) አውጪው የሂሳብ መግለጫውን ለሁለት (2) ተከታታይ ዓመታት ካላቀረበ፤

(6) ገበያው የአውጪው መፍረስ ወይም ሂሣብ አጣርቶ መዘጋትና መጠናቀቅ አስመልክቶ ማስታወቂያ ሲደርሰው ወይም በማንኛውም መንገድ ሲያውቅ፤

(7) ገበያው የአውጪውን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከአሁን በኋላ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በገበያው ላይ መዝግቦ ማቆየት ተስማሚ አለመሆኑን ሲያረጋግጥ፤ እና

(8) ገበያው በየጊዜው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ሌላ ደንቦች እና ሁኔታዎች ሲወስን እና በባለስልጣኑ ይሁንታ ሲያገኝ።

12.6. በፈቃደኝነት ከተሰረዘ በኋላ እንደገና መመዝገብ

አንድ አውጪ ከተሰረዘበት ቀን አንሥቶ ሁለት (2) ዓመታት እስኪያበቃ ድረስ በገበያው መዝገብ ላይ እንደገና ለመመዝገብ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም።

## ክፍል 4፡ የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ

### *ምዕራፍ 13፡ በገበያው ላይ የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መመዝገቢያ መስፈርቶች*

13.1. ጠቅላላ መስፈርቶች

(1) የምዝገባ መስፈርቶች

ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባን የሚገዙና ከምዝገባው ጋር የሚገናኙ የገበያውን ደንቦች ከማክበር በተጨማሪ አውጭው፡

(ሀ) አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን፣ የንግድ ሕጉን፣ የባለስልጣኑን መመሪያዎችን እና/ወይም ሌሎች የሚመለከታቸውን የኩባንያውን ሕጎች እና ህጋዊ መስፈርቶች መከተል፤

(ለ) የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ለማቅረብ የተፈቀደለት ኩባንያ መሆን፤

(ሐ.) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባው ለገበያው ከመቅረቡ በፊት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪው ምንም ዓይነት ተቃውሞ

አለመኖሩን ማረጋገጥ። በገበያው ላይ ለመመዝገብ የሚፈለጉ ሁሉም ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በባለስልጣኑ መመዝገብ አለባቸው።

(መ) ላለፉት ሦስት (3) ተከታታይ የበጀት ዓመታት ስራ ከ50,000,000 (ሃምሳ ሚሊዮን) ብር ያላነሰ ከታክስ በፊት ትርፍ ማግኘት፤ ወይም ዋና ኢንቨስተሩ ከማመልከቻው ቀን በፊት ባሉት ሶስት (3) የፋይናንስ ዓመታት ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ከታክስ በኋላ ትርፍ ማስታወቅ አለበት።

(ሠ) በኢትዮጲያ የሰነድ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የሚመዘገበው ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከብር 10,000,000 (አሥር ሚሊዮን ብር) ያላነሰ መደበኛ የአክሲዮን ድርሻ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

(ረ) በኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ የሚመዘገበው ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ውስጥ መመዝገቡን ማረጋገጥ፤

(ሰ) ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በፕሮግራም አካል ሲወጡ፣ እያንዳንዱ ተከታታይ ወይም ሰነድ ሙዓለ ንዋይ ቡድን በእነዚህ ደንቦች መሰረት እንደ የተለየ ክፍል ይወሰዳሉ። አውጪው እነዚህን ቋሚ የገቢ ሰነድ ሙዓለ ንዋዮች ሁሉንም ወይም የተወሰኑትን በገበያው ላይ ለማስመዝገብ ይችላል።

(ሸ) ለምዝገባ የቀረቡት ቋሚ የገቢ ሰነድ ሙዓለ ንዋዮች በነፃ የሚተላለፉ እና ሙሉ ለሙሉ የተከፈሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

(2) አውጪው ወይም የአውጪው የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዋስትና ሰጪ ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና ሰጪ ኤጀንሲ አገልግሎቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

(3) ኩፖኑን እና ዋና ዕዳዎችን መክፈል ያቋረጠ አውጪ የዚህን ክፍያ እስኪፈጸም ድረስ ወይም አዲስ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማውጣት ያለመክፈል ችግርን ለማስተካከል የሚረዳ ካልሆነ በስተቀር አዲስ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በገበያው ላይ ማስመዝገብ አይችልም።

(4) ከጊዜ ወደ ጊዜ በገበያው የሚወጡ ማንኛውም ሌሎች መስፈርቶች ማክበር ይጠበቅበታል።

(2) የመመስረቻ ሰነዶች፡-

አውጪው፡-

(ሀ) ማመልከቻውን ለገበያው በሚያቀርብበት ጊዜ የወቅቱን ባለአክሲዮኖች፣ ዳይሬክተሮች እና የአውጪውን ካፒታል የሚያሳይ የማኅበሩን መመሥረቻ ጽሑፍ፣ ማሻሻያዎቹንና ማናቸውንም ሌላ የሚመለከተውን ሰነድ ጨምሮ አግባብነት ያለው የማኅበር ሰነዶችን፣

(ለ) አውጪው አምስት በመቶ (5%) ወይም ከዚያ በላይ አክሲዮኖችን የያዘ ተቋማዊ ኢንቬስተር ያለው እንደሆነ፣ ከማመልከቻው ጋር የተቋማዊ ኢንቬስተሩን፣ ተጠቃሚ ባለሀብት/ቶች ዝርዝር የሚገልጽ አግባብነት ያላቸው የማኅበር ወይም የኩባንያ ሰነዶችን መቅረባቸውን ማረጋገጥ አለበት።

(3) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደንቦችን ማሻሻል ወይም ተጨማሪ ክፍሎችን ማውጣት፡-

የእነዚህ ደንቦች ድንጋጌዎች የገበያውን ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማሻሻያ ወይም ተጨማሪ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከማውጣት ጋር በተያያዘ አውጪው ሰነዶችን እንዲያቀርብ ወይም ክፍያ እንዲከፍል የመጠየቅ መብትን አያስቀርም።

(4) የደንበኝነት ምዝገባ ሂደት፡-

ለእነዚህ ደንቦች ዓላማ፣ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የደንበኝነት ምዝገባ ሂደት በአውጪው ተወስኖ በባለስልጣኑ በሚጸድቀው አግባብ ይሆናል።

## 13.2. የምዝገባ ዘዴዎች ወይም መንገዶች

በገበያው ላይ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለማስመዝገብ የሚፈልግ አውጪ ከሚከተሉት ውስጥ በማናቸውም መንገድ በመጠቀም ማስመዝገብ ይችላል።

(1) ለህዝብ ግዥ ማቅረብ ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው ለሕዝብ ግዢ የሚያቀርበው ጥሪ ነው፣

(2) ለግል ሽያጭ ማቅረብ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ብቃት ላላቸው ባለሀብቶች ለሽያጭ የሚቀርቡበት መንገድ፣

(3) የማስተዋወቅ ምዝገባ፣

(4) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ወይም የንግድ ሕጉ በሚፈቅደው እና በገበያው በየጊዜው በሚፈቀደው ማንኛውም ሌላ መንገድ፤

## 13.3. ለባለልዩ ተልዕኮ ተቋም ተጨማሪ መስፈርቶች

አውጪው ባለልዩ ተልዕኮ ተቋም የሆነ እንደሆነ፣ መስራቹ ወይም ግዴታ ያለበት አካል የሚከተሉትን ማድረግ አለበት: ፡-

(1) ባለስልጣኑ በአውጪው ላይ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች እና እነዚህን ደንቦች፣ ቀጣይነት ያላቸው ዝርዝር ግዴታዎችን ጨምሮ፣ ልክ እንደ አውጪው ሆነው ማክበር፤ እና

(2) ገበያው በየጊዜው የሚያወጣቸውን ሌሎች መስፈርቶችን ማክበር።

(3) ባለስልጣኑ በየጊዜው በሚያስቀምጠው መሰረት፣ ባለልዩ ተልዕኮ ተቋማትን ለተጨማሪ ዓላማዎች መጠቀምን በተመለከተ ገበያው በእነዚህ ደንቦች ላይ በአንድ የተወሰነ አባሪ ላይ ይገልጻል።

### 13.4. የምዝገባ ቅድመ ሁኔታዎች

ገበያው ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወደ ኦፊሴላዊው መዘገብ ለማስገባት ከወሰነ በኋላ አውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ከመመዝገባቸው በፊት የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው።

(1) አውጪው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ስለ ሥራው የተወሰኑ መረጃ ወዲያውኑ ለማቅረብ፣ አንዳንድ አስተዳደራዊ ሥርዓቶችን ለመከተልና የገበያው ቀጣይ ምዝገባ ግደታዎችን ሙሉ በሙሉ ለማክበር በገበያው በተደነገገው ፎርም መሰረት ውል መፈረም አለበት።

(2) በግብይቱ በተደነገገው ፎርማት እና በሁለት (2) ዳይሬክተሮች ወይም ዳይሬክተር እና በአውጪው ኩባንያ ፀሐፊ የተፈረመ እና ቀን የተሰጠው ኦርጂናል የምዝገባ ውል ማቅረብ አለበት።

### 13.5. የኩባንያ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለመመዝገብ የሚፈልግ አውጪ በ 13.1 ስር የተዘረዘሩትን አጠቃላይ መስፈርቶች ከማሟላት በተጨማሪ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፤

(1) አውጪ የመሆን ፍቃድ፦

አንድ አውጪ የመመሥረቻ ፅሁፉ ድርጅቱ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እንዲያወጣ ስልጣን የሚሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።

(2) የሥራ አፈፃፀም ታሪክ

አውጪው ቢያንስ ለሦስት (3) ዓመታት የሥራ አፈፃፀም ታሪክ ሊኖረው ይገባል። አውጪው የሦስት (3) ዓመታት የሥራ አፈፃፀም ታሪክ ከሌለው ቢያንስ የሶስት (3) ዓመታት የሥራ አፈፃፀም ታሪክ ያለው የዋና ኢንቬስተር/ቴክኒካል አጋር ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

(3) የሥራ አፈፃፀም ታሪክ የሚያሳዩ የፋይናንስ መግለጫዎች፦

(ሀ) ያለፉት ሦስት (3) ዓመታት የእያንዳንዱ የፋይናንስ መግለጫ በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ወይም በኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም አግባብነት ባለው የኢትዮጵያ ባለስልጣን በተቀመጡት የሒሳብ አያያዝ ደረጃዎች መሠረት መዘጋጀት አለበት፡፡

(ለ) የአውጪው ሒሳብ መዝገብ ውሳኔን ለማስቀየር በሚያስችል መልኩ መለወጥ የለበትም፡፡

(4) የጠባቂዎች ሹመት፡-

(ሀ) ገበያው በገበያው ላይ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ፈቃድ የተሰጠው ጠባቂ እንዲሾም አውጪውን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

(ለ) ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት አውጭው ፈቃድ ያለው ጠባቂ እንዲሾም የተጠየቀ እንደሆነ አውጪው የሚመለከተውን ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጉዳይ የሚገዛ የጥበቃ ስምምነት ለገበያው ግምገማ ማቅረቡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(ሐ) የዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (4.) (ሀ.)፤

(i) በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም በማንኛውም ሕጋዊ አካል ለቀረበ፤ ወይም

(ii) በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ዋስትና ለተሰጠው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

(5) የማመልከቻ ሰነዶች፡-

(ሀ) አውጪው ገበያው በየጊዜው በሚያዘው መሠረት የሚመለከታቸውን ሰነዶች ሁሉ ማቅረብ አለበት፡፡

(ለ) ገበያው የሚቀርቡትን ሰነዶች የሚያመለክት የማረጋገጫ ዝርዝር ማቅረብ አለበት፡፡

(ሐ) ገበያው በየጊዜው የሚፈለጉትን ሰነዶች ዝርዝር ይዘት ሊቀይር ይችላል፡፡

(መ) እንደ አስፈላጊነቱ ገበያው በየጊዜው የሚያወጣው ሌላ ማንኛውም መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

13.6. የኩባንያ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ድህረ-ምዝገባ መስፈርቶች

(1) አንድ አውጪ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ዋጋ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ወይም ኢንቬስተሩ እነዚህን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ በሚወስነው ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ማንኛውንም መረጃ ለገበያው ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

(2) አውጭው የሚከተሉትን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

(ሀ) በአውጪው የወጣ አዲስ፣ተከታታይ ክፍል ወይም ፕሮግራም፤

(ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ የሚተገበሩ ደንብ እና ሁኔታ ለውጦች፤

(ሐ) የዕዳ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መልሶ መግዛት ወይም መሰረዝ፤

(መ) አምስት በመቶው (5%) እና ከዛ በላይ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጠቅላላ ዋና ገንዘብ (በመጀመሪያ ምዝገባ ጊዜ ባለው በጠቅላላው ዋና ገንዘብ መጠን መሰረት የተሰላ) መልሰው ከተገዙወይም ከተሰረዙ፤

(ሠ) የሚከፈሉ ማንኛውም የወለድ ክፍያ(ዎች) ዝርዝሮች፤

(ረ) የምትክ ሞግዚት ሹመት፤

(ሰ) እንደአስፈላጊነቱ በአውጪው የተሾመ የሸሪዓ አማካሪ ለውጥ፤ እና

(ሸ) በአሳዳሪው ስምምነት መሠረት የጥፋት ሁነት መከሰት።

(3) የፋይናንስ መግለጫ:-

(ሀ) አውጪው እና/ወይም ዋስትና ሰጪ(ዎች) ተገቢነት ባለው የሂሳብ መስፈርት መሰረት የተዘጋጀ የሒሳብ መግለጫዎቻቸውን በቁጥር 8.7 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስታወቅ አለባቸው።

(ለ) የሚከተሉት ሁሉም ሁኔታዎች ከተሟሉ አውጪው የሂሳብ መግለጫውን ማስታወቅ አይጠበቅበትም:-

(i) ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአንድ ወይም በብዙ ዋስትናዎች የተረጋገጡ ከሆነ፤

(ii) ለሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የተሰጠው ዋስትና ሙሉ እና ቅድመ ሁኔታ የሌለው ሲሆን፤ እና

(iii) አውጪው የአክሲዮን አውጪ ሲሆን እና ለገበያው የተጣመሩ የሒሳብ መግለጫዎችን እንደ አክሲዮን አውጪ ድህረ ምዝገባ ግዴታዎች አካል ይፋ ያደረገ ሲሆን።

**13.7. በኢትዮጵያ መንግስት አውጪነት የቀረቡ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮችን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች**

(1) በኢትዮጵያ መንግሥት የሚወጡ ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከዚህ በላይ ባሉት ደንቦች 13.1፣ 13.2 እና 13.3 ተገዢ ሊሆኑ አይችሉም።

(2) ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለሙዓለ ንዋዮችን በኢትዮጵያ መንግሥት የማውጣት ሂደት ለሚከተሉት መስፈርቶች ተገዢ ይሆናል፤

(ሀ) ማመልከቻው ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት ኃላፊ ወይም ወኪል ሊቀርብ ይችላል።

(ለ) ለምዝገባ የሚቀርበው ማመልከቻ የሰነደ ሙዓለሙዓለ ንዋዮች የሽያጭ ጥሪ እና ሌሎች የድርሻ እና ድልድል ዝርዝሮችን የያዙ ሰነዶችን፣ የአለም አቀፍ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መለያ ቁጥር (ISIN) እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን የንግድ ምልክቶች ማካተት አለበት።

**13.8. ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከምዝገባ መዝገብ ለመሰረዝ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች**

የተመዘገበው ቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በሚከተሉት ሁነቶች ይሰረዛል፡

(1) የቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የዕዳ መክፈያ ቀን ሲደረስ ወይም ሲያልቅ፣ ወይም

(2) አውጪው በጠየቀ ጊዜ፡ ይህም ሊሆን የሚችለው፡-

(ሀ) በቋሚ የገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ አስቀድሞ መልሶ መግዛት ከተከናወነ፤ ወይም

(ለ) ሞግዚቱ በሞግዚትነት ስምምነቱ መሰረት የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወዲያውኑ የደረሰ እና መልሶ መከፈል ያለበት መሆኑን የሚወስንበት ማንኛውም ሁኔታ ሲከሰት፤

(3) በእነዚህ ደንቦች መሰረት ከዕዳ መክፈያ ቀን በፊት ገበያው በሚሰጠው ውሳኔ፡
፡

## ክፍል 5: በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ለግብይት የሚቀርቡ ፈንዶች ምዝገባ

### *ምዕራፍ 14፡ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ላይ ለግብይት የሚቀርቡፈንዶች ምዝገባ መስፈርቶች*

#### 14.1. የማመልከቻ መስፈርቶች

በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የሚቀረቡ ፈንዶች ምዝገባ ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት:

(1) ስለአውጪው ዝርዝር መረጃዎች፤

(2) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የሚቀረቡ ፈንዶች አደረጃጀት ወይም መዋቅር አጭር መግለጫ እና አስፈላጊ ከሆነ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች ለመዋቀር መሰረት የሆኑ ንብረት(ዎች)፤

(3) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች በማመልከቻው ቀን የተጣራ የሃብት ዋጋ፤

(4) በየሳምንቱ የሚቀርብ ሆኖ ላለፉት 6 ወራት በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች/የገበያ ሁኔታ አመላካች /መሠረታዊ ንብረት (ዎች) ጥቅል ላይ የታየ የተጣራ የሃብት ዋጋ (NAV) መቶኛ ለውጥ፤

(5) የእያንዳንዳቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች/ኢንዴክስ/መሠረታዊ ንብረቶች ባለፉት ስድስት (6) ወራት ውስጥ በየሳምንቱ የነበራቸው የገንዘብ አከል መጠን ( ጠቅላላ ሽያጭ/ የገበያ ካፒታላይዜሽን) ፤

(6) የአስተዳደር ክፍያዎች ስሌት መሠረት፤

(7) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች የሚዋቀሩበት እና የሚገበያዩበት የገንዘብ አይነት፤ እና

(8) በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ለግብይት ለቀረቡ ፈንዶች የሚጠየቅ ሌላ ማንኛውም መረጃ፡፡

#### 14.2. የምዝገባ ቅድመ ሁኔታዎች

(1) በኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ለመመዝገብ፣ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች፤

(ሀ) ክፍት መሆን፣

(ለ) በኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ተቀባይነት ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ/የገበያ ሁኔታ አመላካች /መሰረታዊ ንብረት ጥቅል ላይ ተመስርቶ የወጣ መሆን፤

(ሐ) በማንኛውም ጊዜ በሚመለከታችው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች/ዕቃዎች ወይም የገንዘብ ሰነዶች አማካኝነት ሙሉ የዋስትና ሽፋን ያለው በኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ተቀባይነት ያገኘ፣ የተመዘገበ፣ በነፃነት የሚነገድ እና በቂ የገንዘብ ወይም የገንዘብ መጠን ያለው የውክልና ሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣

(መ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች የተመሰረቱበት ንብረት የተጣራ የሃብት ዋጋ (NAV) ለማወቅ የስሌት ዘዴ ያለው፣ እና

(ሠ) የሚመለከታችው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በጠባቂ እጅ ማስቀመጥ እና በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች ውስጥ ያሉትን ኢንቨስተሮች ጥቅም ለመጠበቅ ጠባቂ መሾም አለባቸው።

(2) የሚመለከተው የስር የገበያ ሁኔታ አመላካች ወይም ፖርትፎሊዮ በገበያው ላይ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮችን ያካተተ መሆን አለበት።

(3) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች አውጪ፡

(ሀ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶችን ለማውጣት በገበያው አግባብነት ያለው እውቀት እንዳለው ማረጋገጥ ወይም የእንደዚህ አይነት እውቀት የማግኘት እድል እንዳለው ማረጋገጥ አለበት።

(ለ) ገበያውን ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች ሁለተኛ ደረጃ ገበያ እንደሚኖር እና ግብይቱም ቀጣይነት እንደሚኖረውገበያውን ማሳመን፣

(ሐ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶችን የተጣራ የሃብት ዋጋ በየቀኑ ለማስላት እና በገበያው ገበያ በኩል የተጣራ ንብረት ዋጋን ለሁሉም የገበያ ተሳታፊዎች በተመሳሳይ ጊዜ በገበያው በኩል ይፋ ለማድረግ ቃል መግባት; እና

(መ) የተጣራ የሃብት ዋጋ ስሌቱ በሚመለከታቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ማንኛውንም የኮርፖሬት እርምጃ እና የአስተዳደር ክፍያዎች ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

(4) እንደ ትርፍ ክፍፍል ያለ ማንኛውም ገቢ ለባለሃብቶች ቢያንስ በየ አመቱ እና የሽያጭ ሰነዱ ላይ ከተቀመጥው ዜዝ በፊት መከፋፈል አለባቸው፡፡

### 14.3. የሽያጭ ሰነድ ይዘቶች

አንድ አውጪ አመልካች በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የሚቀረቡ ፈንዶች የሽያጭ ሰነድ ውስጥ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

(1) የአውጪውን፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሞግዚት ሙሉ ስም፣

(2) የአውጪውን፣ ሥራ አስኪያጁ እና ሞግዚቱ የተቋቋሙባቸው ሰነዶች፣

(3) የአውጪው ሥራ አስኪያጅ እና ዳይሬክተሮች ሙሉ ስም፣ ዝርዝሮች እና አድራሻዎች፤

(4) ስለ አውጪው አጠቃላይ መረጃ፡-

(ሀ) ለጉዳዩ ስፖንሰር አድራጊ ደላሎች፣ አማካሪዎች እና አስተላላፊ ወኪሎች ስም እና አድራሻ፡፡

(ለ) በተጠቃለለ መልኩ ያለፉትን 3 ዓመታት ወይም ገበያው ሊወስን ለሚችለው ጊዜ የአውጪውን የሂሳብ መግለጫዎች ;

(ሐ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የሚቀረቡ ፈንዶች ስለተመሰረቱበት ንብረት መግለጫ;

(መ) የገበያ ሁኔታ አመላካችን ወይም ኢንዴክስን መሰረት አድርጎበሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች ከሆነ፡-

i. የኢንዴክሱ መግለጫ፤

ii. የተካተቱት አክሲዮኖች መግለጫ እና የጥምርታቸው ንፅፅር፤

iii. የኢንዴክሱ አሳታሚ ስም፤

iv. የተቋቋመበት ቀን እና እንዴት እንደተጠናቀረ፤

v. ለኢንዴክሱ ድጋፍ ሚሰጠው እና/ወይም የሚያሰላው አካል ማንነት፤

vi. የኢንዴክሱ የሚሻሽልበት እና የሚታተምበት ድግግሞሽ፤

vii. የኢንዴክሱ ማሻሻያ እና መቋረጥን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤

viii. የኢንዴክሱን በሚደግፈው (ከሚቆጣጠረው) እና / ወይም ከሚያሰላው አካል የተሰጠ ኢንዴክሱን የመጠቀም ስልጣን፤ እና

(ሠ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች ገቢ ካለ ለባለሀብቶች ለማከፋፈል የሚገደድባቸው ሂደቶችና መብቶች፡፡

## 14.4. የገበያ ከፋች ሹመት

(1) አመልካች አውጪ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች ምዝገባ በፊት በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶችን በተመለከተ በየእለቱ ጨረታ የሚያውጡ እና ዋጋ የሚያሳውቁ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ገበያ ከፋቾችን ይሾማል፡፡

(2) ጨረታ ወይም የሽያጭ ጥሪ በሚኖርበት ጊዜ ገበያው ከፋቹ በእነዚያ ተመኖች ግብይቶችን ለመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

(3) አውጪው እና ገበያ ከፋቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች የገበያ ሁኔታን በሚመለከት ግልጽ የሆነ የጽሁፍ ስምምነት መፈረም አለባቸው፡፡ ገበያ ከፋቹ የገበያ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከአውጪው ጋር የተደረገውን የገበያ ስምምነት ግልባጭ ለባለስልጣኑ እና ለገበያው ማቅረብ አለበት፡፡

## 14.5. ዕለታዊ ህትመት

በእነዚህ ደንቦች ክፍል 3 ስር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በሚመለከቱ ከተገለጹት ቀጣይነት ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎች በተጨማሪ በሚመለከተው መጠን በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች ስራ አስኪያጅ በየቀኑ፤

(1) ያለፈውን ቀን በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች የተጣራ የሃብት ዋጋ ስሌት፣

(2) በመዝጊያው ቀን የእያሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የተጣራ የሃብት ዋጋ ስሌት፤

(3) የንብረቶች ፖርትፎሊዮ የተጣራ የሃብት ዋጋ ስሌት፤

(4) በመውጣት ላይ ያሉ ክፍሎች ብዛት፤

(5) ያለፈው ቀን የመረጃ/የገበያ ሁኔታ አመላካች ደረጃ ወይም የሚመለከተው ንብረት ዋጋ (እንደአስፈላጊነቱ)፤

(6) የማንኛውም የገበያ ሁኔታ አመላካች ጥቅል መተዳደሪያ፤

(7) የሚከፈሉ የአስተዳደር ክፍያዎች፤ እና

(8) የሚመለከተውን ንብረት ወይም የገበያ ሁኔታ አመላካች ጋር በተያያዘ የገበያ ማንቂያዎች (እንደአስፈላጊነቱ)፤

በየቀኑ ይፋ ማድረግ አለበት።

## ክፍል 6 - ለሸሪዓ ህግ ተገዥ የሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ

### *ምዕራፍ 15 - በገበያው ላይ የሱኩክ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች*

15.1. ለሱኩክ አውጪዎች የብቃት መስፈርት፦

(1) አውጪው በኢትዮጵያ ሕግና ደንቦች መሠረት በአግባቡ የተቋቋመ ድርጅት መሆን አለበት።

(2) አውጪው በሥራው እና በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ውስጥ የሸሪዓን መርሆዎችን ማክበር አለበት።

(3) ሱኩኩ ከታወቁ የሸሪዓ ደረጃዎች ጋር የተጣጣመና እና አወቃቀሩም በእስላማዊ ፋይናንስ መርሆዎች መሰረት መሆን አለበት።

(4) ለመመዝገብ ብቁ የሆኑ የሱኩክ ዓይነቶች ሙዳራባህ/(ትርፍን መጋራት) ሱኩክ፣ ኢጃራህ ሱኩክ፣ ሙሻራካህ (ትርፍ እና ኪሳራን መጋራት) ሱኩክ እና በሸሪዓ መመሪያ መሰረት ሌሎችንም ያካትታል።

15.2. ይፋ ማድረግ እና ግልጽነት

(1) አውጪዎች ሱኩክ የወጣበትን ዓላማ፣ ደንብ እና ሁኔታዎችን ጨምሮ አጠቃላይ እና ትክክለኛ መረጃ መስጠት አለባቸው።

(2) መደበኛ የፋይናንስ ሪፖርቶች፣ የህግ ተገዢነትን የሚመለከቱ መረጃዎች እና ማንኛውም ጠቃሚ ሁነቶች ለገበያው እና ለሕዝብ ወዲያውኑ ይፋ መደረግ አለባቸው።

15.3. የሸሪዓ መርሆዎችን ማክበር

(1) የሱኩክ መዋቅሮች እና ስራዎች ተመዝግበው በሚቆዩበት ጊዜ ሁሉ የሸሪዓን መርሆዎች ማክበር አለባቸው።

(2) ገለልተኛ የሆነ የሸሪዓ ቦርድ ወይም አማካሪ የሱኩክን ሸሪዓ ተገዢነት መቆጣጠር እና ማረጋገጥ አለበት።

15.4. የተገቢነት ጥናት እና የማጽደቅ ሂደት

(1) አውጪዎች የምዝገባ መስፈርቶችን መከበራቸውን ለማረጋገጥ በገበያው በሚካሄድ ጥልቅ የተገቢነት ጥናት ሂደት ውስጥ ማለፍ አለባቸው።

(2) ከመመዝገቡ በፊት ከባለስልጣኑ እና ከሚመለከታቸው የሸሪዓ ምሁራን ወይም አማካሪዎች ማረጋገጫ ማግኘት አለበት።

15.5. የሰነድ መስፈርቶች፦

(1) ሱኩክ ለሽያጭ ማቅረቢያ ማስታወሻ, የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ወይም ሌላ ተገቢነት ያላቸውን ሰነዶችን ማቅረብ።

(2) ከሱኩክ ጋር የተያያዙ አወቃቀሮች፣ ደንቦች እና የአደጋ ምክንያት ዝርዝሮች።

15.6. ቀጣይነት ያላቸው ግዴታዎች

(1) ቀጣይነት ያላቸው የሸሪዓ መርሆዎች እና የሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶችን ማክበር።

(2) ጉልህ ለውጦች፣ ክስተቶች ወይም ያልተከፈሉ የሱኩክ ክፍያዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በሰዓቱ ይፋ ማድረግ።

## *ምዕራፍ 16 - ለሸሪዓ ህግጋት ተገዥነት ያላቸው አክሲዮኖችን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች*

16.1. የሸሪዓን መስፈርት የሚያሟሉ አክሰዮኖችን ለመመዝገብ የብቃት መስፈርቶች፦

(1) የሸሪዓን መርሆዎችን በማክበር አክሲዮኖችን ለማስመዝገብ የሚፈልግ አውጪ፦

(ሀ) በኢትዮጵያ ህጎች እና ደንቦች መሰረት በአግባቡ የተቋቋመ ኩባንያ መሆን፤

(ለ) በአሠራሩ እና በገንዘብ ነክ ጉዳዮቹ የሸሪዓ መርሆዎችን የሚከተል መሆኑን ማረጋገጥ፤ እና

(ሐ) በባለስልጣኑ እውቅና ባለው መስፈርት አውጪ ወይም የሚመለከተው አካል በተወሰነው መሰረት የንግድ እንቅስቃሴ እና የፋይናንስ ንፅፅር መለኪያዎችን ማሟላቱን ማረጋገጥ አለበት።

(2) አውጪው በባለስልጣኑ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን ተግባራት እንዲፈጽም በባለስጣኑ ፈቃድ ያለው የሸሪዓ አማካሪ ይሾማል እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚመለከታቸውን የሸሪዓ ብያኔዎች፣ መርሆዎች እና ፅንሰ ሀሳቦች መከበራቸውን ያረጋግጣል።

16.2. የማመልከቻ ሰነድ፡

(1) አውጭው የሚመለከታቸውን ሰነዶች ሁሉ በየጊዜው ገበያው በሚያዘው መሠረት ማቅረብ አለበት፡፡

(2) ገበያው የሚቀርቡትን ሰነዶች የሚያመለክት ቼክ ሊስት ማዘጋጀት አለበት፡፡

(3) ገበያው በየጊዜው የሚፈለጉትን ሰነዶች ዝርዝር ሊለያይ ይችላል፡፡

(4) በገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚጠይቀው መሰረት ሌላ ማንኛውንም መስፈርቶችን ማቅረብ ወይም ማሟላት፡፡

16.3. የምዝገባ ሂደት፡-

በገበያው በተለየ መልኩ ካልተደነገገ በቀር በክፍል 2 የተደነገገው የአክሲዮኖች ምዝገባ ሂደት እንደአስፈላጊነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

16.4. የቀጣይነት ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎች፡-

(1) በገበያው ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር በክፍል 3 የተመለከቱት ቀጣይነተ ያላቸው የምዝገባ ግዴታዎች ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

(2) አውጪው በምዝገባው ቆይታ ወቅት በደንብ ቁጥር 16.1 የተደነገገው ያለማቋረጥ መከበሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

# ክፍል 7፡ የምዝገባ ሰንጠረዦች

## *ሰንጠረዥ 1፡ የካሳ ሽፋን ደብዳቤ ናሙና*

**(የአውጭው ደብዳቤ ራስጌ)**

**ቀን፦**

**ለኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ**

**ውድ …….**

ለ_________የ_____________አ.ማ. (አክስዮን ማህበር) አክሲዮኖች/ክፍሎች ምዝገባ ለኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የተሰጠ የካሳ ሽፋን

እኛ ድርሻችንን/ቦንዳችንን በዚህ ለሽያጭ የምናቀርብ ................አ.ማ. ("አውጭው") (የአውጭው ስም) ማናቸውንም ወኪሎችን፣ ወራሾቻቸውን፣ ተተኪዎችን፣ ጥቅም ተጋሪዎችን፣ አጋሮቻችንን፣ ተዛማጅ ወገኖችን፣ ባለስልጣናትን፣ ኃላፊዎች እና የቦርድ አባላትን በሚመለከት የምናወጣቸው በደምበኛ ሳቢ መግለጫ/የመረጃ ማስታወሻ/የመብቶች ሰርኩላር ላይ የምንሰጣቸው መግለጫዎች እና መረጃዎች በማንኛውም ሁኔታ እውነተኛ እና ትክክለኛ መሆናቸውን እና በደምበኛ ሳቢ መግለጫ/የመረጃ ማስታወሻ/የመብቶች ሰርኩላር ላይ ያልተገለፁ በድርጅቱ የሚታወቁ ወይም የማይታወቁ ማንኛውንም መግለጫ ወይም መረጃ የሚያሳስቱ እውነታዎች የሌሉ መሆናቸውን እናረጋግጣለን።

አውጭው ማንኛውም የኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን የሚመለከቱ፣ ሊጎዱ የሚችሉ፣ ተጋላጭ የሚያደርጉ፣ የተቀበላቸው ወይም የፈፀማቸው ወይም ወጭ ያወጣባቸው፤ አክሲዮን/ቦንድ ምዝገባን ከማፅደቁ የተነሳ ወይም በተያያዘ፣ እና/ወይም ሌላ ጉልህ ክስተት ወይም ከሚመለከተው ምዝገባ ጋር የተያያዘ ያለፈ ሁነትን እና/ወይም በእነዚህ አክሲዮኖች/ቦንዶች ላይ በኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ከሚካሄድ ግብይት ጋር በተገናኘ

ለሚከሰቱ ሁሉም ክሶች፣ ጥያቄዎች፣ ክፍያዎች፣ ጉዳቶች፣ ወጭዎች፣ የህግ ወጭዎች፣ ተጠያቂነቶች እና ኪሳራዎች የምንክስ፣ በዘላቂነት የካሳ ሽፋን የምንሰጥ መሆኑን እናረጋግጣለን።

አውጭው የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ከሚሳተፍባቸው ወይም ተጎጅ ከሚሆንባቸው ከአክሲዮን/ቦንድ ገዥ ወይም የግዥ ተመዝጋቢ የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ሁሉንም የአውጭውን አስፈላጊ መረጃዎች አላካተተም ወይም የተካተቱት መረጃዎች እና/ወይም መግለጫዎች ሀሰተኛ ወይም የተሳሳቱ ናቸው በሚል ለሚቀርቡ በአጠቃላይ ለማንኛውም እና ሁሉም ክሶች፣ ወጭዎች፣ ጉዳቶች፣ ክፍያዎች፣ የህግ ወጭዎች፣ ኃላፊነቶች፣ ማንኛውም አይነት ጉዳቶችን የምንክስ፣ በዘላቂነት የካሳ ሽፋን የምንሰጥ መሆኑን እናረጋግጣለን።

ይህ የካሳ ሽፋን አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕጎች የሚገዛ ይሆናል።

እኛ በአውጭው ቦታ ሁነን ይህን የካሳ ሽፋን ለመስጠት የዳይሬክተሮች ቦርድ ፈቃድ ያለን መሆኑን እናረጋግጣለን።

በቀን ………………….. በወር ………………………………… 20…..…

………………………………… ……………………………………
ዳይሬክተር/ፀሃፊ ዳይሬክተር/የኩባንያው ፀሀፊ

## ሰንጠረዥ 2— የህግ ተገዢነት ማረጋገጫ ደብዳቤ ናሙና

((የአውጪው ደብዳቤ ራስጌ))
እኛ ________ እና __________የ _________________________ ኢ.ማ እንደ ቅደም ተከተላችን( ከዚህ በኃላ "ኩባንያ") ዳይሬክተር እና የኩባንያ ፀኃፊ የሚከተሉትን እናረጋግጣለን፡፡

(1) የንግድ ህጉ በሚጠይቀው መሰረት በ____________ ቀን ________20_______ የወጡ/የቀረቡ/የተዋወቁ የሚከተሉት የኩባንያው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማለትም ( በዝርዝር ያስቀምጡ) ጋር በተያያዘ ለኩባንያዎች መዝጋቢ ተቋም እና ለባለስልጣኑ ገቢ መደረግ ያለባቸው ሁሉም ሰነዶች በተገቢ መንገድ ገቢ የተደረጉ መሆኑን እና እኛ እስከምናውቀው ድረስ ኩባንያው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከማውጣት ጋር የተያያዙ ሁሉንም ህጋዊ መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን፤

(2) ___________ መጠን ያላቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በጥሬ ገንዘብ የግዥ ጥያቄ የቀረበባቸው/የተገዙ ወይም ለግዥ ጥያቂ አቅራቢዎች/ለገዥዎች በተገቢ ሁኔታ የተላለፉ መሆኑን፤

(3) ኩባንያው ከማውጣት/አቅርቦት ጋር በተያያዘ ያሉትን ገንዘቦች በሙሉ ገቢ ያደረገ መሆኑን፤

(4) የወጡ የ ____________ ብር አክሲዮኖች/ቦንዶች በጥሬ ገንዘብ ተከፍለው ገቢ የተደረጉ እና ለባለቤቶቹ የተሰጡ/የተላለፉ መሆኑን፤

(5) በባለስልጣኑ እና/ወይም በአስቀማጭ ደንቦችና ስነ-ስርዓቶች መሰረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በኢሌክትሮኒክ ዘዴ ለባለአክሲዮኖች/የእዳ ሰነድ ባለቤቶች የአስቀማጭ ሂሳብ ገቢ የተደረገ (የተላለፈ) መሆኑን፤

(6) ሁሉም ምዝገባ የተደረገባቸው አክሲዮን/ቦንድ መጠን እያንዳንዱ ክፍል በማንኛውም አግባብ ተመሳሳይ መሆናቸውን፤ እና

(7) በእኛ ምልከታ ከኩባንያው የምዝገባ ጥያቄ ጋር በተገናኘ ለኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መገለፅ ያለባቸው ሊሎች መረጃውች የሊሉ መሆኑን፤

እኛም ይህ እውነት መሆኑን በማመን ይህን ማረጋገጫ እንሰጣለን፡፡
ተፈርሟል
.................................
.................................
**ለመፈረም ስልጣን የተሰጠው ፈራሚ ስም** **የፈቃድ ሰጪው ስም**
**ማስታወሻ፡ በዚህ አግባብ "ተመሳሳይ" ማለት**

(ሀ) በየአክሲዮኖች/ቦንዶች ክፍል አንድ አይነት የተጻፈ ዋጋ (የገበያ ዋጋ) መኖር፣

(ለ) ተመሳሳይ ጊዜ ተመሳሳይ መጠን ያለው ትርፍ/ወለድ ማግኘት መብት መኖር፣ በመሆኑም በሚቀጥለው ክፍፍል፣ በእያንዳንዱ መጠን በሚከፈለው ወለድ አንድ ዓይነት መጠን (ጠቅላላ እና የተጣራ) ድርሻ እንደሚኖራቸው ማረጋገጥ፤ እና

(ሐ) ካለገደብ ከማስተላለፍ፣ ስብሰባዎች ላይ ድምፅ ከመስጠትና ከመምረጥ እና በሌሎች ጉዳዮች በአንድ ጥላ ስር ከመታየት ጋር በተገናኘ አንድ አይነት መብት ያላቸው ማለት ነው።

## ሰንጠረዥ 3፡ የምዝገባ ውል ናሙና

(የአውጭው ደብዳቤ ራስጌ)
ቀን:
ለ የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ
ውድ …..
______________________(የ‹‹አውጪው ስም››) ለሚከተሉት እውቅና ይሰጣል፡- የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ (የሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዩ ስም/ዓይነት) በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ (‹‹ገበያው››) ላይ የመቆየት መብት በገበያው ብቸኛና ፍጹም ውሳኔ ላይ የተመሠረተ መሆኑን፤

በገበያው ላይ መቆየቱን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ አውጪው በሚከተሉት ውሳኔዎችና፣ ዋስትናዎች ይስማማል እንዲሁም ይገደዳል፦

(1) በገበያው በየጊዜው የሚወጡ ወይም የሚደነገጉትን እና በየጊዜው የሚሻሻሉ፣ የሚሟሉ ወይም የሚተኩትን (የሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ምዝገባ ቢዘገይ፣ ቢታገድ ወይም ግብይቱ ቢቆምም እንኳን) ሁሉንም መመሪያዎችን፣ ህጎች፣ ደንቦችን፣ አሰራሮችን፣ ፖሊሲዎችን እንዲሁም የሚመለከታቸው ማናቸውንም የአተገባበር እርምጃዎች እና በገበያው የሚወጡ ወይም የሚደነገጉትን የሚመለከታቸው ደንቦችን፣ ህጎች፣ አሰራሮችን፣ ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን ጨምሮ የሚከተሉትን ማክበር አለበት፤

(ሀ) የገበያው የምዝገባ ደንቦች/መስፈርቶች እና ቀጣይነት ያላቸው ግዴታዎች/ከምዝገባ በኋላ ያሉ መስፈርቶችን፤

(ለ) የተጠናቀሩ እና ያልተጠናቀሩ መረጃዎችን የሚመለከቱ ሕጎች፣ ደንቦች፣ አሰራሮች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎችን፤ እና

(ሐ) የሚመለከታቸው የኩባንያ አስተዳደር ሕጎች እና በእነሱ መሠረት የሚሰጥ የመግለጫ መስፈርቶችን።

(2) በየጊዜው የሚወጡትን የገበያው መመሪያዎችን ማክበር ይኖርበታል፣ ይህም በገበያው በተጠየቀ ጊዜ ዓመታዊ ሪፖርቱን፣ ሂሳቡን እና ሌሎች ሪፖርቶችን ወይም የኩባንያ መረጃዎችን ማስተካከልን ያካትታል።

(3) የሚመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በገበያው በየጊዜው የሚወጡ ወይም የሚደነገጉትን ህጎች፣ ደንቦች፣ አሰራሮች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ያከበሩ እና ሊመዘገቡ የማይገባበት ምንም ምክንያት የሌላቸው መሆን አለባቸው።

(4) በገበያው የተቀመጡ፣ የተቋቋሙ እና/ወይም የተጣሉትን የሚመለከታቸውን ክፍያዎች፣ ተመኖች፣ ግዴታዎች ወይም ቅጣቶች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ወዲያውኑ መክፈል አለበት።

(5) በገበያው እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ወይም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ስለ አውጪው ወይም ከአውጪው ግብይት ጋር በተያያዘ ገበያው ከ ጊዜ ወደ ጊዜ የሚፈልገውን ወይም የሚጠይቀውን መረጃ ወይም ሰነድ ወዲያውኑ ለገበያው ያቀርባል፣ ይህም መረጃ ወይም ሰነድ ትክክለኛ እና የተሟላ መሆን አለበት።

(6) በገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ የወጡ እና የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦች፣ አሰራርሮች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያውችን የማያከብርበት ማንኛውም ክስተት ቢከሰት ለገበያው ወዲያውኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

(7) በገበያው ላይ ቀጣይ የሚወጡ ወይም እንዲወጡ የተፈቀደላቸው በተመሳሳይ መደብ ያሉ ሁሉንም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማስመዝገብ አለበት።

(8) አውጪው በገበያው ላይ ካደረገው ምዝገባ ጋር በተያያዘ ለህዝብ ይፋ ማድረግ፣ ማሳወቅ እና መረጃ ማጋራት ጋር ለተገናኙ ዓላማዎች የአውጭውን ኩባንያ አርማ ፣ የድረ ገፅ አድራሻ ፣ የንግድ ስም እና የንግድ ምልክት/ የአገልግሎት ምልክት በመጠቀም የምዝገባ መረጃን ፣ ከምዝገባ ጋር የተዛመዱ የአውጭው እንቅስቃሴዎችን ፣ የግብይት ሪፖርት መረጃን እና በአውጪው በገበያው ላይ ከተደረገው ምዝገባ ጋር የተያያዙ ሌሎች መረጃዎችን እንዲጠቀም ይፈቅድለታል።

(9) በህጉ በተፈቀደው መጠን ከላይ በተገለጸው መንገድ ገበያው የደርጅቱን አርማዎች ፣ የድረ ገፅ አድራሻዎች ፣ የንግድ ስሞች እና የንግድ/ የአገልግሎት ምልክቶች በመጠቀሙ ወይም ከመጠቀም ጋር በተገናኘ ከሚመጣ ማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ ፣ ክፍያ ፣ ጥያቄ ፣ ኪሳራ ፣ ጉዳት ፣ ወጪ ፣ ተጠያቂነት ፣ ቅጣቶች ፣ ፍርዶች ፣ ክፍያዎች ፣ ክሶች ወይም ወጪዎች (ለአስማሚ እና ዳኝነት ወይም ሌሎች ወጪዎችን ፣ የጠበቃ ክፍያዎች እና የፍርድ ቤት ወጪዎችን ጨምሮ) ገበያውን፣ ኦፊሰሮቹን፣ ሠራተኞቹ እና ተዛማጅ ድርጅቶችን የመካስ ወይም በቀጣይነት የመካስ ኃላፊነት አለበት።

(10) በህጉ በተፈቀደው መጠን በዚህ የምዝገባ ውል ውስጥ የተቀመጡትን የአውጭው ግዴታዎች እና/ወይም ድንጋጌዎችን ከመጣስ ወይም ከዚህ ጋር በተገናኘ ከሚመጣ ማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ ፣ ክፍያ ፣ ጥያቄ ፣ ኪሳራ ፣ ጉዳት ፣ ወጪ ፣ ተጠያቂነት ፣ ቅጣቶች ፣ ፍርዶች ፣ ክፍያዎች ፣ ክሶች ወይም ወጪዎች (ለአስማሚ እና ዳኝነት ወይም ሌሎች ወጪዎችን ፣ የጠበቃዎችን ክፍያዎች እና የፍርድ ቤት ወጪዎችን ጨምሮ) ገበያውን፣ ኦፊሰሮቹን፣ ሠራተኞቹ እና ተዛማጅ ድርጅቶችን መካስ ወይም በቀጣይነት የመካስ ኃላፊነት አለበት።

(11) አውጪው በገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚውጡ ማንኛውም መመሪያዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ አሰራሮች፣ ፖሊሲዎች እና አሰራሮችን ሲጥስ በገበያው የሚጣሉበትን ማንኛውንም ቅጣቶች ወዲያውኑ የማክበር የማክበር ይኖርበታል።

(12) በዚህ የምዝገባ ውል ውስጥ የተካተተ ወይም ከዚህ የሚመነጭ ማንኛውም ነገር ከገበያው ጋር በገበያው ላይ የአውጭውን ሰነደ ሙዓለ  ንዋይ ምዝገባ ቀጣይነት የሚያረጋግጥ ውል ነው ተብሎ ሊተረጎም አይችልም ፣ ስለሆነም የአውጭው ሰነደ ሙዓለ  ንዋዮች የገበያው ደንቦች እና መመሪያዎችን ባለማሟላታቸው ከምዝገባ በገበያው ሊሰረዙይችላሉ ።

(13) ዳይሬክተሮቹ በዚህ የምዝገባ ውል መሰረት የተጣለባቸውን ግዴታዎች እንዲሁም ገበያው በየጊዜው በሚያወጣቸው ወይም በሚያስቀምጣቸው መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ አሰራሮች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ላይ የተመሰረተውን ግዴታ መወጣት አለባቸው፤ ይህም ገበያው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች ወይም ሰነዶች እንዲያገኝ ማድረግን ያካትታል።

(14) ገበያው አውጪው የእዚህ ምዝገባ ውል አንድ ወይም ከዛ በላይ ድንጋጌውችን ከጣሰ፣ ወይም በራሱ ውሳኔ ንግዱን ማቁረጡ ውይም ከምዝገባ መሰረዙ ለህዝብ ጠቃሚ ነው ብሎ ካመነ ውይም በሌላ መንገድ ካረጋገጠ  የተመዘገበ የአውጭው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይትን ማቋረጥ፣ ይህን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከመዝገብ መሰረዝ፣ ወይም ከገበያው ኦፊሳላዊ መዝገብ የአውጪውን ስም ለአውጭው ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ውይም ሳይሰጡ የማስወገድ መብት፣ በብቸኝነት እና ፍፁም ነፃነት እንደተጠበቀ ነው፡፡

ይህ የምዝገባ ውል የአውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በገበያው ላይ ከተመዘገቡበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል እና የአውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በገበያው ላይ ተመዝግበው በሚቆዩበት ጊዚ ሁሉ በሥራ ላይ ይቆያል፡፡

.....................................

..................................

**ዳይሬክተር**

**ዳይሬክተር/የኩባንያ ጸሐፊ**

**ቀን:** **ቀን:**

# የአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ _ የምዝገባ ደንቦች

(1) የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት መፅሐፈ ደንብ 2017 (የምዝገባ ደንቦች) ድንጋጌዎችን ሲጣሱ የሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ የተካተቱት ናቸው፡፡

(2) የአንድ ደንብ ስም ወይም ሌላ የስም አሰጣጥ ደንብ ሲቀየር ስሙ ወይም የስም አሰጣጥ ደንቡ በዚህ የቅጣት ዝርዝር ውስጥ በራሱ እንደተቀየረ ይቆጠራል፡፡

(3) ከማንኛውም ጥሰት ጋር በተያያዘ እገዳ ከተደረገ ፣ ይህ እገዳ የሚነሳው ሁሉም ተዛማጅ ወይም ተዛማጅ ያልሆኑ ግዴታዎች ከተሟሉ ብቻ ነው ፡፡

| ተ.ቁ | ክንውን | የመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ፈፃሚ | የሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ፈፃሚ<br>(በ xx ወራት ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ጥሰት መፈጸም ወይም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መመሪያዎቹን አለማክበር) | የሶስተኛ ጊዜ ጥፋት ፈፃሚ<br>(በ xx ወራት ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ጥሰት መፈጸሙ ወይም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መመሪያዎቹን አለማክበር) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መረጃን የማሳወቅ ግዴታን የሚመለከቱ ደንቦች | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ/ማሳሰቢያ | የግዴታ ህግ ተገዢነት ስልጠና | እገዳ፣ የሕዝብ ትችት እና የሕግ ተገዥነት ሁኔታ አመላካች (CSI) |
| 2 | 2 የፋይናንስ ሪፖርት ግዴታዎችን የሚመለከቱ ደንቦች | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እና የሕግ ተገዥነት ሁኔታ አመላካች (CSI) | የሕግ ተገዢነት እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ መታገድ፣ የሕዝብ ትችት እና የሕግ ተገዥነት ሁኔታ አመላካች (CSI) | |
| 3 | 3 የኮርፖሬት አስተዳደር መስፈርቶችን የሚመለከቱ ደንቦች | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ/ማሳሰቢያ | የህግ ተገዢነት ስልጠና | የሕዝብ ትችት እና የሕግ ተገዥነት ሁኔታ አመላካች (CSI) |

| የሕግ ተገዥነት ሁኔታ አመላካቾች (CSI) | | | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ. | የሕግ ተገዥነት ሁኔታ አመላካች (CSI) ኮዶች | የኮድ ስም | የኮድ ዝርዝር |
| 1. | BLS | ከምዝገባ መስፈርት በታች | ቀጣይነት ያላቸውን የገንዘብ ነክ ያልሆኑ መረጃዎችን በተመለከተ ያሉ ሁሉንም ጉድለቶች ያካትታል ። |
| 2 | MRF | የቁጥጥር ማሳወቂያ ጊዜን ያሳለፉ | የራሳቸውን የቁጥጥር ማሳወቂያ ቀነ-ገደብ ያሳለፉ የተመዘገቡ ኩባንያዎች። |
| 3. | DWL | የስረዛ ማመልከቻ ዝርዝር (መዝገብ) | እነዚህ የምዝገባ ስረዛ ማስታወቂያዎች የደረሳቸው ኩባንያዎች ናቸው ነገር ግን የምዝገባ ስረዛ ሂደቱ ቆሞ በኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮች ገበያ ለተወሰነ ጊዜ የድርጊት ማቆሚያ ተቀብለው የምዝገባ ስረዛ ማስታወቂያ እንዲወጣባቸው ያደረጓቸውን ጉዳዮች ለማስተካከል ቃል ገብተዋል። በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ወይም በተራዘመበት ጊዜ ውስጥ ችግሮችን ማስተካከል ካልቻሉ የምዝገባ ስረዛው ሂደት ይቀጥላል። |
| 4. | DIP | በሂደት ላይ ያለ የምዝገባ ሥረዛ | እነዚህ ኩባንያዎች የግዴታ ወይም በፈቃደኝነት የምዝገባ ስረዛ ሂደት ውስጥ ያሉ ኩባንያዎች ናቸው። የደንበኝነት የምዝገባ ስረዛ ሂደቱ የሚጀምረው ከኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮች ገበያ ለአውጪው (አስገዳጅ) ወይም ከአውጪው ለኢትዮጲያ ሰነደ ሙዓሙዓለ ንዋዮች ገበያ (በፈቃደኝነት) ለመሰረዝ ሃሳብን በማስታወቅ ነው ። |
| 5. | AWR | የባለስልጣን ፈቃድ በመጠበቅ ላይ ያሉ | እነዚህ የኦዲት የተደረገባቸውን የፋይናንስ መግለጫዎቻቸውን ይፋ ከማድረጋቸው በፊት ዋና የመንግስት ተቆጣጣሪውን ማረጋገጫ ወይም ተቃውሞ የለም ማረጋገጫ የሚጠብቁ ኩባንያዎች ናቸው ። |
| 6. | RST | መልሶ ማቋቋም | እነዚህ ኩባንያዎች በመልሶ ማቋቋም ሂደት ውስጥ ያሉ ኩባንያዎች ናቸው። |
| 7. | BMF | ከምዝገባ መስፈርት በታች እና የጠፉ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የቁጥጥር ማመልከቻ | |
| 8. | BAA | ከምዝገባ መስፈርት በታች እና የባለስልጣን ፈቃድ በመጠበቅ ላይ ያሉ | |
| 9. | BRS | ከምዝገባ መስፈርት በታች  እና መልሶ መቋቋም ላይ የሚገኙ | |
| 10. | MRS | የጠፋ የቁጥጥር ማመልከቻ እና መልሶ ማቋቋም ላይ የሚገኙ | |
| 11. | BMR | ከምዝገባ መስፈርት በታች፣ የጠፋ የቁጥጥር ማመልከቻ  እና መልሶ መቋቋም ላይ የሚገኙ | |

# ቅጽ መ: የግብይት ደንቦች

# ክፍል 1 - ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## *ምዕራፍ አንድ - የደንቦች አስተዳደርና ስምምነቶች*

### 1.1. አጭር ርዕስ

እነዚህ ደንቦች "የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መጽሐፈ ደንቦች፣ 2017 (የግብይት ደንቦች)" ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

### 1.2. የተፈጻሚነት ወሰን

(1.) እነዚህ ደንቦችና መመሪያዎች የግብይት አባላት ከገበያው ጋር፣ እንደ ግብይት አባላት እርስ በእርስ በሚኖራቸውና በገበያው የግብይት አባልነታቸው ከሌሎች አካላት እንዲሁም ከሰፊው ሕዝብ ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ አስገዳጅነት ይኖራቸዋል፡፡

(2.) ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሕጎች በልዩነት እንዲታዩ ካልተደነገገ በስተቀር የሁሉም የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የሚከናወነው በእነዚህ ደንቦች መሠረትና ለዚሁ በተለዩ የግብይት መድረኮች ላይ ነው፡-

(ሀ) በእነዚህ ደንቦችና በየጊዜው በሚደረግላቸው ማሻሻያዎች እንዲሁም ገበያው በሚያወጣቸው ሌሎች ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ አሠራሮችና ሰነዶች እና/ወይም

(ለ) በአዋጁና በየጊዜው በሚደረግለት ማሻሻያ፣ በአዋጁ መሠረት በሚወጡ የበታች ሕጎች እንዲሁም መመሪያዎችና እና ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው ሌሎች ከአዋጁ ጋር የተጣጣሙ ሰነዶች፡፡

### 1.3. የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ሌሎች ደንቦች ተፈፃሚነት

የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ከኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መጽሐፈ ደንብ፣ 2017 ዓ.ም (አጠቃላይ ደንቦች፣ የአባልነት ደንቦች፣ የምዝገባ ደንቦች፣ የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓትና የግጭት አፈታት ደንቦች) ጋር በጣምራ የሚነበቡ ይሆናል፡፡

# ክፍል 2 - የደንበኞች አስተዳደር

## *ምዕራፍ 2 - የደንበኛ ሒሳቦች*

### 2.1. ደንበኛን ዕወቅ እና የተገቢነት ጥናት

(1.) አንድ የግብይት አባል፣ ተፈጻሚነት ባላቸው የደንበኛን ዕወቅ ማዕቀፍና መመዘኛዎች እንዲሁም በየጊዜው በሥራ ላይ በሚውሉ ሌሎች በወንጀል የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መደገፍን ለመከላከል በሚወጡ ሕጎች መሠረት የአንድን ሰው እውነተኛ ማንነት ለማረጋገጥ ሁሉንም ምክንያታዊ የሆኑ ሒደቶች ሳይፈጽም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ መገበያያ ሒሳብ መክፈት ወይም ማንቀሳቀስ ወይም በሌላ መንገድ ማንኛውንም ሰው በመወከል መገበያየት አይችልም፡፡

(2.) እያንዳንዱ የግብይት አባል፡-

(ሀ) ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜና አስፈላጊ በሆነበት ሁኔታ የሁሉንም ደንበኞቹን ማጎደሮች ማጣራትና ማዘመን፤

(ለ) የሁሉም ደንበኞቹን ማጎደሮች ለማጣራትና ለማዘመን ስጋትን መሠረት ያደረገ አሠራር መከተል፤

(ሐ) የደንበኞቹን የጸና የዲጂታል መታወቂያ ቁጥር እና/ወይም የባንክ ሒሳብ ዝርዝሮች እና/ወይም የጸና የግል መታወቂያ ሰነዶችን መቀበል፤

(መ) የንግድ ድርጅቶችን በሚመለከት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የንግድ ምዝገባ ቁጥርና የኩባንያውን ሌሎች የተመዘገቡ ደጋፊ መረጃዎችን እንዲሁም የእያንዳንዱን ሥልጣን የተሰጠው ፈራሚ የጸና የግል መታወቂያ ሰነዶችን መቀበል፤

(ሠ) ሒሳቦች ያለአለግባብ ጥቅም ላይ አለመዋላቸውን ለማረጋገጥ ተፈፃሚነት ባላቸው የደንበኛን ዕወቅ ማዕቀፍ እና/ወይም መመዘኛና ሌሎች የደንበኛ ተገቢ ቅድመ ማጣራት መመዘኛዎች መሠረት ለሚከፈቱ ሒሳቦች በቂ የሆኑ የስጋት መከታተያ መንገዶችን መዘርጋት፤ እና

(ረ) ገበያው በየጊዜው የሚያጸድቀውን "ስጋት ይፋ የማድረጊያ ሰነድ" ለደንበኞች በመስጠትና ይዘቱን እንዲገነዘቡ በማድረግ በገበያው ላይ ግብይት መፈጸም ስለሚኖሩት መሠረታዊ ስጋቶችና ስላሏቸው መብቶች፣ ግዴታዎች ወዘተ. ለደንበኞቻቸው ማሳወቅ፡፡ የግብይት አባላት የስጋት ይፋ ማድረጊያ ሰነዱን ከየራሳቸው የንግድ ሞዴልና የደንበኞች ስጋት ጋር ማጣጣም አለባቸው

እንዲሁም እያንዳንዱ ደንበኛ በአግባቡ የፈረመበት የስጋት ይፋ ማድረጊያ ሰነድ ቅጂ በማኀደራቸው ውስጥ መዝገበው መያዝ አለባቸው፡፡

(3.) ማንኛውም የንዑስ ደንብ (1) ወይም (2) ድንጋጌዎችን የተላለፈ የግብይት አባል በቅጣቶች ‹ሰንጠረዥ› ውስጥ በተቀመጠው መሠረት የዲሲፕሊን እርምጃዎች የሚወሰድበት ይሆናል፡፡

## 2.2. የደንበኛ ሒሳቦች ቁጥጥር

(1.) የግብይት አባላት የሒሳብ አከፋፈትና አዘጋግን እንዲሁም በእነዚህ ሒሳቦች ውስጥ ለእነዚህ ባለ ሒሳቦችና በእነርሱ ስም የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ የደንበኞች ሒሳቦችን ቁጥጥር የሚመለከቱ በጽሁፍ የተቀመጡ ፖሊሲዎችና የሥነ-ሥርዓት መመሪያዎች ሊኖራቸው ይገባል፡፡

(2.) ከላይ በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (1) ውስጥ የተገለጹት ፖሊሲዎችና የሥነ-ሥርዓት መመሪያዎች የሚከተሉትን ለማረጋገጥ በምክንያታዊነት መዘጋጀት አለባቸው፡-

(ሀ) የግብይት አባሉ ከደንበኛው ሒሳብ የመክፈት ወይም የመዝጋት ጥያቄ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች እንዲያውቅ ማስቻል፤

(ለ) ደንበኛው ሒሳቡ ከመከፈቱ በፊት ስለሒሳቡ አስፈላጊ የሆኑ ይፋ ማድረጊያ ገለጻዎችን ማግኘቱን ወይም ቀርበውለት መቀበል ሳይፈልግ መቅረቱን፤

(ሐ) ደንበኛው በሒሳቡ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት የሰጣቸው መመሪያዎች በአግባቡና በተቀላጠፈ መንገድ መፈጸማቸውን፤ እና

(መ) አንድ የግብይት አባል ለደንበኞች ወይም ደንበኞችን በመወከል የሚያከናውናቸው ግብይቶችና የሚገበያይባቸው ገንዘብን የሚመለከቱ ግዴታዎች የሚከናወኑት ደንበኛው በጽሑፍ ወይም በተገቢው መንገድ በተቀዳ የድምጽ ትዕዛዝ መሠረት መከናወናቸውንና በግብይት አባሉ ወይም የግብይት አባሉን በመወከል ትዕዛዙን የሚፈጽመው ሠራተኛ ደንበኛው በሰጠው የሥልጣን ወሰን ውስጥ መሆኑን፡፡

(3.) የሒሳብ መከፈትን ማጽደቅ የሚችለው በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ተሿሚ እንደራሴ ብቻ ነው፡፡

(4.) በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (3) መሠረት የማጽደቅ ኃላፊነት ያለበት ሰው ስለ ደንበኛውና ደንበኛው ሊከፍት ስለፈለገው ሒሳብ የሚከተሉትን መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ማወቅ፣ መረዳት ወይም መገንዘብ ይኖርበታል፡-

(ሀ) የግብይት አባሉ በሒሳቡ ላይ ሥልጣን የተሰጠው ከሆነ የደንበኛው ጠቅላላ ሀብት ሊከፍት ከፈለገው ሒሳብ መጠን ጋር ያለውን ንጽጽር፤

(ለ) ደንበኛው በሒሳቡ ላይ ያሉትን የግብይት ወይም የገንዘብ ዓላማዎች፤

(ሐ) ደንበኛው በታሰበው ሒሳብ ለሚያደርገው ግብይት ስጋትን የሚታገስበት መጠን

(መ) የደንበኛው ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ልምድ፤

(ሠ) ደንበኛው ለግብይት አባሉ በሒሳቡ ላይ በሙሉ ወይም በከፊል በራሱ ውሳኔዎችን እንዲያስተላልፍ በጽሑፍ ሥልጣን የሰጠው መሆን ወይም አለመሆኑን፤ እና

(ረ) ደንበኛው ሒሳብ እንዲከፍት ድርጅቱ ቀርቦ ያግባባው ወይም በራሱ ተነሳሽነት ወደ ድርጅቱ የመጣ መሆኑን።

(5.) የግብይት አባላት የሚከተሉትን ለመፈፀም የሚያስችሉ ፖሊሲዎችንና የሥነ-ሥርዓት መመሪያዎችን መቅረጽ አለባቸው፦

(ሀ) ደንበኛውን እና/ወይም የደንበኛውን ሒሳብ የሚመለከቱ የገንዘብና ሌሎች መረጃዎችን በሙሉ መጠበቅና በምስጢር መያዝ፤

(ለ) ከደንበኛው ሒሳብ ጋር በተገናኘ የተከሰቱ ኢመደበኛ እንቅስቃሴዎችን፣ ማጭበርበሮችን ወይም ስህተቶችን በፍጥነት መለየት፤ እና

(ሐ) በምክንያታዊ ሁኔታ በተቻለ አቅም ድርጅቱ ከደንበኛው ጋር ወይም ደንበኛውን በመወከል በሚያደርጋቸው መስተጋብሮች ውስጥ በሚፈጠር ማንኛውም ኢመደበኛ እንቅስቃሴ፣ ማጭበርበር ወይም ስህተት ምክንያት በደንበኛው ላይ ሊደርስ የሚችል የኪሳራ ስጋትን መቀነስ።

(6.) የግብይት አባላት የሚከተሉትን ማድረግ አይፈቀድላቸውም፡-

(ሀ) የደንበኛን ዕወቅ አሠራሮችን ሳያከብሩ የደንበኛ ሒሳቦችን መክፈት።

(ለ) ከደንበኛው ጋር ውል ሳይፈጽሙ ወይም ከደንበኛው የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኙ የደንበኛውን ሒሳብ መጠቀም ወይም መበደር።

(ሐ) ከደንበኛው ጋር ውል ሳይፈጽሙ ወይም ከደንበኛው የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኙ የደንበኛውን ስም መጠቀም።

(መ) ማንኛውንም ግብይት ለመፈጸም ሐሰተኛ ሒሳቦችን መክፈት።

(ሠ) ለደንበኛው ያልተሟላ፣ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ መስጠት።

2.3. ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን ማረጋገጥ

(1.) አንድ የግብይት አባል በግብይት ሥርዓቱ ላይ ትዕዛዝ ከማስቀመጡ በፊት ከደንበኞቹ የተረጋገጠ ትዕዛዝ ማግኘትና ደንበኛው ትዕዛዙን ከማስቀመጡ አንስቶ ትዕዛዙ እስከሚጠናቀቅበት ወይም ደግሞ እስከሚሰረዝበት እንዲሁም በመሐል የሚከሰቱ ሁሉንም ቁልፍ ኩነቶችን ጨምሮ ሁሉንም የትዕዛዙን ገጽታዎች በሚመለከት መዝገብ መያዝ ይኖርበታል፡፡

(2.) የግብይት አባላት አንድን የመግዛት ወይም የመሸጥ ትዕዛዝ በገበያው የትዕዛዝ መዝገብ ውስጥ ወዲያውኑ ማስገባትና ትዕዛዙን በተቀመጠውና ደንበኛው ትዕዛዙን ካስተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ከአሥር (10) የሥራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ወይም ገበያው በሚያስቀምጠው ጊዜ ውስጥ ለመፈጸም በተከታታይ ሙከራ ማድረግ አለበት፡፡

(3.) ከአሥር (10) የሥራ ቀናት ተከታታይ ሙከራ ወይም ገበያው ካስቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ በገበያ ሁኔታዎች ምክንያት ትዕዛዙን መፈጸም ካልተቻለ ትዕዛዙ በደንበኛው መታደስ አለበት፡፡

(4.) በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሆነ ብሎ ትዕዛዙን ያልፈጸመ የግብይት አባል በቅጣቶች ሰንጠረዥ በተዘረዘረው መሠረት ቅጣት ይጣልበታል፡፡

(5.) አንድ የግብይት አባል በማንኛውም ሁኔታ በቅድሚያ ፊርማ ያረፈበት ባዶ የመመሪያ ሰነድ ከደንበኛው መቀበል አይፈቀድለትም፡፡

(6.) አንድ የግብይት አባል በቅድሚያ የተፈረመበትን ባዶ የትዕዛዝ ሰነድ ከተቀበለ ከግብይቱ የሚገኝን ማንኛውንም ጥቅም እንዲተው ተደርጎ በቅጣቶች ሰንጠረዥ ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት ቅጣት ይጣልበታል፡፡

(7.) እያንዳንዱ የግብይት አባል ከሚቀጥለው የግብይት ቀን መጨረሻ በፊት ለሚፈጽመው እያንዳንዱ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዢ ወይም ሽያጭ የውል ማስታወሻ መስጠት አለበት፡፡ የውል ማስታወሻው በግብይት አባሉ በአግባቡ መፈረምና የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

(ሀ) የግብይት አባሉ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላነት ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አከናዋኝነት የንግድ ሥራውን የሚያከናውንበት ስምና ዓርማ እንዲሁም የንግድ ሥራ የሚያከናውንበትን ዋና አድራሻ፤

(ለ) በውክልና ግብይቱ የተፈጸመለት ደንበኛ ስምና አድራሻ፤

(ሐ) ግብይቱ የተፈጸመበት ቀን፤

(መ) ግብይቱ የተከናወነበት መግለጫ፣ መጠንና ዋጋ፤

(ሠ) በውሉ መሠረት ለግብይቱ የሚከፈለው ክፍያ መጠን፤

(ረ) ከውሉ ጋር በተገናኘ ደንበኛው ለግብይት አባሉ የሚከፍለው የድለላ ክፍያ ወይም ኮሚሽን፤

(ሸ) የግብይት አባሉ የሚከፍላቸው በሕግ የተደነገጉ ሌሎች ክፍያዎች፡፡

## 2.4. የደንበኛ ሒሳብ አያያዝና ልየታ

(1.) እያንዳንዱ የግብይት አባል በደንበኞች ስም የሚይዘውን ገንዘብ በሙሉ ከራሱ ገንዘብ ጋር ሳይቀላቅል በተለየ የባንክ ሒሳብ ውስጥ ማስቀመጥ የሚኖርበት ሲሆን ይህም የባንክ ሒሳብ የግብይት አባሉ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ድለላ ሥራውን በሚያከናውንበት ስም ላይ "የደንበኞች ሒሳብ" የሚል ተቀጽላ ያለበት መሆን አለበት፡፡

(2.) አንድ የግብይት አባል ደንበኞቹን በመወከል የሚይዘውን ገንዘብ ከራሱ ገንዘብ በሚለይ የባንክ ሒሳብ ውስጥ ያላስቀመጠ እንደሆነ ይህንን የተለየ ሒሳብ ስለመክፈቱ የሚያሳይ ማስረጃ ለገበያው እስከሚያቀርብበት ጊዜ ድረስ ወዲያውኑ ከግብይት ታግዶ የሚቆይ ሲሆን የገንዘብ መቀጮና ሌሎች በአስተዳደራዊ ቅጣት ሰንጠረዡ ውስጥ የተቀመጡ ቅጣቶች ይጣሉበታል፡፡

(3.) የግብይት አባሉ የተፈለገውን የደንበኞች ሒሳብ ከፍቶ ይህንኑ የሚያሳይ ማስረጃ ለገበያው ቢያቀርብም በዚህ ደንብ ንዑስ-ደንብ (2) ውስጥ የተጠቀሰውን መቀጮ አለመክፈል በግብይት አባሉ ላይ የተጣለውን እግድ ላለማንሳት ምክንያት ይሆናል፡
፡

## 2.5. ለደንበኞች የሚቀርብ ወርሃዊ የሒሳብ መግለጫ

(1.) እያንዳንዱ የግብይት አባል በመደበኛነትና በፍጥነት ደንበኛውን በመወከል የተደረጉ ሁሉንም ግብይቶችን አካትቶ የደንበኛውን ሒሳብ እንቅስቃሴ ማጠቃለያ የያዘ ወርሃዊ ኤሌክትሮኒክ መግለጫ ማቅረብ አለበት፡፡

(2.) የግብይት አባላት ለደንበኞች የቀረቡትን መግለጫዎች ቅጂ መያዝ አለባቸው፡፡

(3.) ወርሃዊ ኤሌክትሮኒክ የሒሳቦች መግለጫዎቹ ደንበኞች ምንም ክፍያ ሳይከፍሉ መላክ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ 3 - የደንበኞች ሀብቶች

### 3.1. የደንበኞች ገንዘብ አጠቃቀምና ልየታ

(1.) አንድ የደንበኛውን ሀብቶች በአደራ የያዘ የግብይት አባል በዚህ ደንብ መሠረት እነዚህን ሀብቶች ለመጠበቅ ምክንያታዊ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

(2.) በግብይት አባሉ የተያዙ የደንበኛ ገንዘቦች ከግብይት አባሉ የንግድ ሥራ ሒሳብ በተለዩ አንድ (1) ወይም ከዚያ በላይ ሒሳቦች መቀመጥ አለባቸው፡፡ የደንበኞች ገንዘብ ሂሳቦች ለግብይት አባሉ ደንበኞች ጥቅም የተከፈቱ ስለመሆናቸው በግልጽ መመላከት አለባቸው፡፡

(3.) አንድ የግብይት አባል የደንበኞቹ ሒሳቦች የራስን ግዴታዎች ለማቻቻል ጥቅም ላይ እንደማይወሉ ለማረጋገጥ የደንበኞቹን ገንዘብ ከያዘው ተቋም ጋር ምክንያታዊ የሆኑ ሕጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

(4.) እያንዳንዱ የግብይት አባል እንደ ግብይት አባልነቱ ከሚያከናውነው የንግድ ሥራ ጋር በተገናኘ የሚከተሉትን ለማሳየትና ለመለየት የሚያስፈልጉ የሒሳብ መዝገቦችንና ማኅደሮችን መያዝ አለበት፦

(ሀ) ከደንበኞች ወይም ከደንበኞች ወኪሎች የተቀበላቸውን እና ለደንበኞች ወይም ለደንበኞች ወኪሎች የተከፈሉ ወይም ለደንበኛው ጥቅም በዝግ የባንክ ሒሳብ የተቀመጡ ገንዘቦችን፤ እና

(ለ) ከግብይት አባሉ ወይም ከወኪሎቹ የተቀበላቸውን ክፍያዎች እና ለግብይት አባል ወይም ለወኪሉ የተከፈሉ ክፍያዎች፡፡

(5.) ወደ ደንበኞች ሒሳቦች የሚፈጸሙ ክፍያዎች

(ሀ) ደንበኞቻቸውን በመወከል ገንዘብ የሚይዙ ወይም የሚቀበሉ የግብይት አባላት የተቀበሉትን ገንዘብ ወዲያውኑ ወደ ደንበኞቻቸው ሒሳብ ወይም ለደንበኛው ጥቅም ዝግ ወደ ሆነ የባንክ ሒሳብ ማስገባት አለባቸው፡፡

(ለ) አንድ የግብይት አባል በከፊል የደንበኛው በከፊል ደግሞ የራሱ የሆነን ገንዘብ በሚቀበልበት ጊዜ ይኸው አባል ሙሉውን ገንዘብ ወደ ደንበኛው ሒሳብ ካስገባ በኋላ የራሱን ገንዘብ ከደንበኛው ሒሳብ ወደ ራሱ ሒሳብ(ቦች) ማስተላለፍ አለበት፡፡ ይህንን በሚመለከት፡-

(i.) ይህ የገንዘብ ዝውውር ሥልጣን ባለው ተቆጣጣሪ በጽሑፍ መጽደቅና በግብይት አባላቱ የሒሳብ መዝገብ እና ማኅደሮች ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

(ii.) ገበያው ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ ለግብይት አባሉ መከፈል ያለበት የመጀመርያ ክፍያ መጠንና የግዴታውን ሁኔታ የሚያሳይ ሰነድ ወዲያውኑ መቅረብ አለበት፡፡ አንድ የግብይት አባል ይህንን ሰነድ ካልያዘ ወይም በገበያው ጥያቄ መሠረት ማቅረብ ካልቻለ የግብይት አባሉ የደንበኛውን ገንዘቦች ያለ አግባብ እንደቀላቀለ ይቆጠራል፡፡

(ሐ) ከሚከተሉት በስተቀር ወደ ደንበኛው ሒሳብ ገንዘብ መክፈል አይፈቀድም፦

(i.) ደንበኛውን በመወከል የተያዙ ወይም የተቀበሉ ገንዘቦች፤

(ii.) ከደንበኛው ሂሳብ በስህተት ወጪ የተደረገን ገንዘብ ለመተካት የሚውሉ ገንዘቦች፤ ወይም

(iii.) አንድ የግብይት አባል በከፊል ደንበኛውን በመወከል በከፊል ደግሞ ለራሱ የሚከፈሉ ገንዘቦች፡፡

(6.) ከደንበኞች ሒሳብ ወጪ ማድረግ፤

(ሀ) የግብይት አባላት ራሳቸው ለሚያደርጉት ግብይት ክፍያ ለመፈጸም ወይም የራሳቸውን የንግድ ሥራ ዕዳ ለመክፈል ከደንበኞች ሒሳቦች የደንበኞችን ገንዘቦች ማውጣት ወይም ማዘዋወር አይፈቀድላቸውም፡፡

(ለ) ከሚከተሉት በስተቀር ከደንበኞች ሒሳቦች ገንዘብ ማውጣት አይፈቀድም፦

(i.) የግብይት አባሉ ደንበኛውን በመወከል ከፈፀማቸው ግብይቶች ለሚመነጩ ኃላፊነቶች ደንበኛው ለግብይት አባሉ መክፈል ያለበትን ዕዳ ወይም ለሕዳግ ጥሪ ክፍያ ወይም ሌሎች የደንበኛው ግዴታዎችን በአግባቡ ለመወጣት ለሚያስፈልጉ ገንዘቦች፡፡

(ii.) ደንበኛው በጽሑፍ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ለደንበኛ በአግባቡ ክፍያ ለመፈጸም  የሚያስፈልጉ ገንዘቦች፤ እና

(iii.) ወደ ደንበኞች ሒሳቦች ገቢ የተደረጉና ባለቤትነታቸው የግብይት አባሉ የሆኑ ገንዘቦች፡፡

(7.) በዚህ ደንብ ውስጥ የሚገኝ ድንጋጌ አንድ የግብይት አባል በደንበኞች ሒሳብ ውስጥ በሚገኙ ገንዘቦች ላይ የሚኖረውን ሕጋዊ ዕርምጃ የመውሰድ መብትን  ማለትም ልዩ የመያዣ መብትን፣ ማቻቻልን፣ የተከሳሽ ከሳሽ ክስን ወይም ሌላ መብትን አያሳጣውም፡፡ ፡፡

(8.) ከላይ ያለው ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የግብይት አባል ዕዳውን ለማቻቻል ወይም ሌላ ግዴታውን ለመወጣት ሦስተኛ ወገኖች ከደንበኞች ሒሳብ ላይ ዕዳውን ወይም ሌላ ግዴታውን እንዲያቻችሉለት የሚፈቅድ ውል መፈጸም አይችልም፡፡

(9.) የደንበኞች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አያያዝ

(ሀ) የደንበኞች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከግብይት አባሉ የግብይት ሒሳቦች በተለዩ አንድ (1) ወይም ከዚያ በላይ ሒሳቦች መያዝ አለባቸው፡፡ የደንበኞች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሒሳቦች ለግብይት አባሉ ደንበኞች ጥቅም የተያዙ መሆናቸውን በግልጽ ማሳየት የሚኖርባቸው ሲሆን የግብይት አባሉም እነዚህ ሒሳቦች የራሱን ግዴታዎች ለማቻቻል ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ምክንያታዊ የሆኑ ሕጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

(ለ) እያንዳንዱ የግብይት አባል ከግብይት አባልነት የንግድ ሥራው ጋር በተገናኘ የሚከተሉትን ለማሳየት አስፈላጊ የሆኑ መዛግብትንና ማኅደሮችን መያዝ አለበት፡-

(i.) ለሽያጭ የተረከባቸው ወይም በገበያው ውስጥ እስኪያስረክባቸው ድረስ የያዛቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤

(ii.) ሙሉ ለሙሉ የተከፈለባቸውና ለደንበኛው ገና ያላስረከባቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤

(iii.) በደንበኛው ስም ወይም ደንበኛው በሰየመው ሰው ስም የግብይት አባሉ ለዝውውር የተረከባቸው ወይም ለዝውውር የላካቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤

(iv.) ሙሉ ለሙሉ የተከፈለባቸውና እንደ ዋስትና ወይም ሕዳግ በግብይት አባሉ ይዞታ ሥር የሚገኙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤ እና

(v.) ለሕዳግ መስፈርቶች በግብይት አባሉ ስም የተመዘገቡ ሙሉ ለሙሉ የተከፈለባቸው የደንበኛ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፡፡

3.2. የደንበኞችን ገንዘብ መመዝበር

(1.) የደንበኞቹን ገንዘብ የሚመዘብር የግብይት አባል በማንኛውም ሁኔታ ጉርሻዎችን፣ መብቶችን፣ የጥሬ ገንዘብ የትርፍ ድርሻዎችን፣ የካፒታል ጭማሪና ማንኛውንም ትርፍና ሌሎችን ጨምሮ ከመዘበረው ገንዘብ የሚገኝን ማንኛውም ጥቅም ለራሱ እንዲያስቀር አይፈቀድለትም፡፡

(2.) ማንኛውም የደንበኛውን ገንዘብ የሚመዘብር የግብይት አባል፡-

(ሀ) የገንዘቡ መጠን ገበያው ከሚወስነው ጣሪያ ጋር እኩል ሲሆን ወይም ሲያንስ የመዘበረውን ገንዘብ ከባንክ የቁጠባ ወለድ ምጣኔው በአምስት በመቶ (5%) ከሚበልጥ ወለድ ጋር መመለስ፤ ወይም

(ለ) የግብይት አባሉ ከዚህ በፊት ተመሳሳይ የገንዘብ ምዝበራ ፈጽሞ ከሆነ ወይም የተመዘበረው ገንዘብ መጠን ገበያው ካስቀመጠው ጣሪያ እኩል ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ የግብይት አባሉ የአባልነት የምስክር ወረቀቱ በገበያው ይሰረዛል፤ በተጨማሪም የመዘበረውን ገንዘብ ከወቅታዊው የባንክ የቁጠባ ወለድ ምጣኔ በአሥር በመቶ (10%) ከሚበልጥ ወለድ ጋር ይመልሳል፤

(3.) የተመዘበረው የደንበኛ ገንዘብ ለሌላ ዓላማ የግብይት አባሉ ጋር የተቀመጠ፣ ከደንበኛው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽያጭ፣ የደንበኛውን የትርፍ ድርሻ ከመቀየር ወይም ደንበኛውን በተሳሳተ ዋጋ ከማስከፈል የተገኘና በግብይት አባሉ የተያዘ ወይም ሌላ በማንኛውም መንገድ የተገኘ የደንበኛው ገንዘብ ቢሆንም የዚህ ደንብ ንዑስ-ደንብ (2) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

(4.) ማንኛውም የምርመራ ወይም የዲሲፕሊን ሒደት እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የግብይት አባሉ ከግብይት ይታገዳል፡፡

### 3.3. ያልተፈቀደ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ

(1.) ማንኛውም የግብይት አባል ከባለቤቱ ፈቃድ ሳያገኝ ማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መሸጥ ወይም ማስተላለፍ አይችልም፡፡

(2.) ያለ ባለቤቱ ፈቃድ ማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የሸጠ ወይም ያስተላለፈ የግብይት አባል ማንኛውንም ከግብይቱ የሚገኝን ጥቅም ለራሱ እንዲያስቀር አይፈቀድለትም፡፡

(3.) ማንኛውም ያለባለቤቱ ፈቃድ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የሚሸጥ ወይም የሚያስተላልፍ የግብይት አባል፡-

(ሀ) ገበያው በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹንና የተገኙ ጥቅሞችን መልሶ እንዲገዛ ይገደዳል፡፡

(ለ) የግብይቱ የገንዘብ ዋጋ ገበያው ካስቀመጠው ጣሪያ ጋር እኩል ሲሆን ወይም ሲያንስ የሚከተሉትን መቀጮ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፦

(i.) በአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ ውስጥ ከተቀመጠው መቀጮ ወይም ከሽያጩ ወይም ከማስተላለፊያ ዋጋ ሦስት (3) እጥፍ ከሆነው የገንዘብ መጠን የሚበልጠውን፤እና

(ii.) የግብይት አባሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን እንዲገዛ በገበያው ከታዘዘበት ቀን ጀምሮ የባለቤቱን አክሲዮኖችን መልሶ መግዛቱን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ ላሉት ቀናት በየቀኑ የሚታሰብ መቀጮ፡፡

(ሐ) ግብይቱ ገበያው ካስቀመጠው ጣሪያ ጋር እኩል ከሆነ ወይም ከዚያ ከበለጠ ወይም የግብይት አባሉ ከዚህ በፊት ያለ ባለቤቱ ፈቃድ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የሸጠ ወይም ያስተላለፈ ከሆነ፣ ገበያው በራሱ ምርጫ የግብይት አባሉን የአባልነት የምስክር ወረቀት ይሰርዛል በተጨማሪም የሚከተሉትን መቀጮዎች የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፦

(i.) በአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ ውስጥ ከተቀመጠው መቀጮ ወይም ከሽያጩ ወይም ከማስተላለፊያ ዋጋ ሦስት (3) ዕጥፍ ከሆነው የገንዘብ መጠን የሚበልጠውን፤ እና

(ii.) ቅጣቱ ከተጣለበት ቀን አንስቶ የግብይት ፈፃሚው አባል የአክሲዮኖቹን መልሶ መግዛት እስከሚያጠናቅቅ ድረስ በየቀኑ የሚታሰብ መቀጮ፡፡

(4.) የግብይት አባሉ የሸጣቸው ወይም ያስተላለፋቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለመኖራቸው ወይም ምክንያታዊ በሆነ ዋጋ መግዛት ካልቻለ የግብይት አባሉ ይህን እውነታ ወዲያውኑ ለገበያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤ ገበያውም በሁኔታው ለባለቤቱ መከፈል ያለበትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ይወስናል፡፡

(5.) ማንኛውም የምርመራ ወይም የዲሲፕሊን ሒደት እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የግብይት አባሉ ከግብይት ይታገዳል፡፡

## 3.4. በደንበኞች ሒሳብ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን

(1.) ማንኛውም የግብይት አባል፣ የተሾመ እንደራሴ፣ ሠራተኛ ወይም ሌላ የግብይት አባል እንደራሴ የደንበኛውን የጽሑፍ ፈቃድ አስቀድሞ ሳያገኝ በማንኛውም የደንበኛ ሒሳብ ላይ ውሳኔ የማስተላለፍ ወይም ከደንበኛው ውጪ ለአንድ ሒሳብ ትዕዛዞችን የመቀበል ሥልጣን አይኖረውም፡፡

(2.) ማንኛውም የግብይት አባል፣ የተሾመ እንደራሴ፣ ሠራተኛ ወይም ሌላ በደንበኞች ሂሳብ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ያለው የግብይት አባል እንደራሴ በደንበኛው ሒሳብ ላይ በራሱ የሚወስናቸው ውሳኔዎች ከደንበኛው ዓላማዎች ጋር ልዩነት ባላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግዢ ወይም ሽያጮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

(3.) የግብይት አባላት ደንበኞቻቸው በራሳቸው ሂሳብ ውሳኔ እንዲያስተላልፉ የሚሰጧቸው ስልጣኖችን እንዲሁም ደንበኛው የሰረዛቸው የውሳኔ ስልጣኖችን የሚያሳዩ ሰነዶችን በጽሁፍ መዝገብ መያዝ አለባቸው፡፡

### 3.5. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግዢ ወይም ሽያጭ ክፍያዎች

(1.) ሁሉም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግዢ ክፍያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ባሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን/ሽብርተኛነትን በገንዘብ መደገፍን የመከላከል ሕጎችንና መመዘኛዎችን ባከበረ መንገድ በኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ዝውውር መፈጸም አለባቸው፡፡

(2.) ሁለም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽያጭ ክፍያዎች በባንክ ሒሳቡ ባለቤት ስም በኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ዝውውር መፈጸም አለባቸው፡፡

(3.) በደንበኛው መመሪያ ካልተሰጠው በስተቀር የግብይት አባሉ ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ ገቢ ብቻ ወደ ደንበኛው ሒሳብ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በስህተት ወደ ሦስተኛ ወገን ሒሳብ ገቢ በሚደረግበት ጊዜ የግብይት አባሉ ከደንበኛው ወይም ከገበያው ጥያቄ ሲቀርብለት ወይም ስለተፈጠረው ስህተት በሚያውቅበት ጊዜ ከሁለቱ መካከል በቀደመው ወዲያውኑ ገንዘቡን ወደ ተመዘገበው ሒሳብ መመለስ ወይም ገንዘቡን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

# ክፍል 3 - ግብይት

## *ምዕራፍ 4 - የትዕዛዝ ክንውንና ምርጥ አፈጻጸም*

### 4.1. የምርጥ አፈጻጸም መርሕና መስፈርቶች

(1.) የግብይት አባላት በሁሉም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዓይነቶች ላይ የደንበኞቻቸውን ትዕዛዞች ሲፈጽሙ የሚቻለውን ምርጥ ውጤት የማስገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡

(2.) የግብይት አባላት የደንበኞቻው ትዕዛዛት ፍትሐዊነት ባለውና ተገቢ በሆነ መንገድ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ግልጽና ለመረዳት የማያዳግቱ አሠራሮችን መዘርጋት አለባቸው፡፡

(3.) እያንዳንዱ የግብይት አባል በሁሉም ጊዜ:-

(ሀ) ደንበኞቻቸውን በመወከል በግብይት መድረኩ ወይም ሥርዓቱ ላይ ትእዛዞቻቸውን ሲፈጽሙ ለደንበኞቻቸው ጥቅም በሚሻል አኳኋን መሥራት፤ እና

(ለ) የግብይት አባሉ በሁሉም ጊዜ በደንበኛው ትዕዛዝ ውስጥ የሚገኙትን ውሎችና ሁኔታዎችን በማክበር ለደንበኛው በተገቢው ጊዜ የተሻለውን

ውጤት ለማስገኘት ምክንያታዊ እርምጃዎች በመውሰድ የምርጥ አፈጻጸም መርህን መከተል አለበት፡፡

(4.) አንድ የግብይት አባል የራሱ በሆነ ሒሳብ ግብይት በሚፈጽምበትና በግብይቱ በሌላኛው ወገን ያለው የግብይት ፈፃሚው ደንበኛ በሚሆንበት ጊዜ ለምርጥ አፈጻጸም መርሕ ተገዢ መሆንን ለማረጋገጥ ግብይቱ በየግብይት አባሉ ሳይሆን በደንበኛው ትዕዛዝ እንደተፈጸመ ተደርጎ መታየት ይኖርበታል፡፡

(5.) የግብይት አባሉ የተወሰኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዓይነቶችን ትዕዛዞች በአፈፃፀም ዙሪያ ያሉትን የተለያዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የምርጥ አፈፃፀም ግዴታዎቹን መተግበር አለበት፡፡

(6.) አንድ የግብይት አባል የደንበኛን ትዕዛዝ ሲፈጽም የግብይት ማስፈጸሚያ መስፈርቶቹን አንጻራዊ ፋይዳ ለመወሰን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ከግምት ማስገባት አለበት፡-

(ሀ) በዚህ መጽሐፈ ደንብ በተሰጣቸው ትርጓሜ መሰረት መደበኛ ወይም ብቁ የሚለውን የደንበኛውን ምድብ ጨምሮ፣ የደንበኛውን ባህሪያት፣ ደንበኛውን መገለጫ

(ለ) የደንበኛውን ትዕዛዝ ልዩ ባሕርያት ማለትም እስከ ወሩ መጨረሻ ጸንቶ የሚቆይ ትዕዛዝ፣ ለአንድ ቀን ጸንቶ የሚቆይ ትዕዛዝ፣ እስከሚሰረዝ ጸንቶ የሚቆይ ትዕዛዝ፣ ወዲያውኑ ሙሉ ለሙሉ የሚፈፀም ወይም የሚሰረዝ፣ ሁሉንም ወይም ምንም እና የመሳሰሉትን ከትዕዛዝ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን አንዳንድ የአፈጻጸም ሁኔታዎችን፤ እና

(ሐ) የሚጠበቅ ትርፍ፣ ስጋት፣ ወደ ጥሬ ገንዘብ በቀላሉ መቀየር መቻልና ተለዋጭነትን ጨምሮ ትዕዛዙ የሚፈጸምባቸውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባሕርያት፡፡

## 4.2. በሒሳቡ ላይ እንዲወሰን ፈቃድ የሰጠ ኢንቨስተር

(1.) አንድ የግብይት አባል በሒሳቡ ላይ እንዲወሰን ፈቃድ የሚሰጥ ኢንቨስተርን ሒሳብ የሚይዘው በደንበኛውና ግብይት በሚፈጽመው አባል መካከል የተፈረመው የድለላ ስምምነት በግልጽ የግብይት አባሉ በዚህ መንገድ ሒሳቡን እንዲያንቀሳቅስ የሚፈቅድ አንቀጽ የተካተተበት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

(2.) የዚህ ደንብ ንዑስ-ደንብ (1) ድንጋጌ ቢኖርም አንድ የግብይት አባል የመግዛትና የመሸጥ ውሳኔ የሚወስነው በተጠቀሱት የደንበኛው የኢንቨስትመንት ግቦች መሠረት ነው፡፡

## 4.3. የዋጋ ሚና

(1.) አንድ የግብይት አባል አንድን ደንበኛ በመወከል ትዕዛዙን ሲፈጽም ሊያስገኘው የሚችለው ምርጡ ውጤት የሚወሰነው ሙሉውን ክፍያ ማለትም፦

(ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ዋጋ፤

(ለ) ደንበኛው ከትዕዛዙ መፈጸም ጋር በቀጥታ ተያይዞ የሚያወጣቸው ሁሉንም ወጪዎች ጨምሮ ትዕዛዙን ከመፈጸም ጋር የሚገናኙ ወጪዎች፤

(ሐ) የክፍያ ማጣራትና መፈጸም ክፍያዎች፤ እና

(መ) ትዕዛዙን በመፈጸም ለተሳተፉ ሦስተኛ ወገኖች የሚከፈሉ ሌሎች ክፍያዎችን ጨምሮ በማሰብ ነው።

(2.) አንድ የግብይት አባል በሒሳቡ ላይ እንዲወሰን ፈቃድ የሰጠ ኢንቨስተር ደንበኛው የሚያስተላልፈውን ትዕዛዝ በሚፈጽምበት ወቅት የሚከተሉትን የሚያካትተውንና ለደንበኛው የሚቻለውን ምርጥ ውጤት ለማስገኘት የሚያስችሉትን ሁሉንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማገባት ነው፡-

(ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ዋጋና ትዕዛዙን ከመፈጸም ጋር የሚገናኙ ወጪዎች፤

(ለ) ፍጥነት፤

(ሐ) ትዕዛዙን የመፈጸምና የክፍያ ማጠናቀቅ ዕድል መጠን፤

(መ) የትዕዛዙን መጠንና ዓይነት፤

(ሠ) የገበያ ተጽዕኖ፤ እና

(ረ) ለደንበኛው የሚቻለውን ምርጥ ውጤት በማስመዝገብ ጠቅላላ ስሌት ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወት እስከሆነ ድረስ ፊት ለፊት ከሚታየው የዋጋና ወጪ ስሌት በላይ ቦታ ሊሰጠው የሚችል ማንኛውም ሌላ በግልጽ የማይታዩ የግብይት ወጪዎች ወይም ሁኔታዎች።

## 4.4. የትዕዛዝ አፈጻጸም

(1.) የደንበኞች ትዕዛዝ አፈጻጸም ደንበኞችን ወክሎ ትዕዛዞችን መፈጸምን ያካትታል።

(2.) እያንዳንዱ የግብይት አባል የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፦

(ሀ) የሚቻለውን ምርጡን ውጤት ለማስገኘት የሚያስችሉ ውጤታማ አሠራሮችን መዘርጋትና ሥራ ላይ ማዋል፤

(ለ) በግዴታው መሠረት ለደንበኛው ትዕዛዞች ምርጡን ውጤት እንዲያስገኝ የሚያስችለውን የትዕዛዝ አፈጻጸም ፖሊሲ መዘርጋትና ሥራ ላይ ማዋል፤

(ሐ) ለደንበኞቹ በሙሉ ስለ ትዕዛዝ አፈጻጸም ፖሊሲው ተገቢ መረጃ መስጠትና የትዕዛዝ አፈጻጸም ፖሊሲውን በማንኛውም ጊዜ ድረ ገጹ ላይ እንዲታይ ማድረግ፤

(መ) አገልግሎቶቹን ከመስጠቱ በፊት በተገቢው ጊዜ ለደንበኞቹ የትዕዛዝ አፈጻጸም ፖሊሲውን መስጠት፤

(ሠ) የሚከተሉትን የሚያካትት የትዕዛዝ አፈጻጸም ፖሊሲ መዘርጋትና በሥራ ላይ ማዋል፡-

(i.) የግብይት አባሉ በአፈጻጸም መስፈርቶቹ መሠረት ለአፈጻጸም ሁኔታዎቹ ስለሚሰጠው አንጻራዊ ጥቅም ወይም የግብይት አባሉ ይህንኑ አንጻራዊ ጥቅም ስለሚወስንበት ሒደት የሚገልጽ ማብራሪያ፤ እና

(ii.) ከደንበኛው የተሰጠ ማንኛውም ዝርዝር መመሪያ የግብይት አባሉ በመደበኛው ሁኔታ የቀየሳቸውን፣ በአፈጻጸም ፖሊሲ ውስጥ የተዘረዘሩትንና ለትዕዛዞቹ የሚቻለውን ምርጥ ውጤት እንዲያመጣ ለማስቻል የተዘረዘሩትን እርምጃዎች እንዳይወስድ ሊከለክሉት እንደሚችሉ የሚጠቅስ ግልጽና በቀላሉ የሚታይ ማስጠንቀቂያ፡፡

(ረ) የአፈጻጸም ሁኔታዎቹን አንጻራዊ ጥቅም መወሰን ወይም አንጻራዊ ክብደታቸውን ለመወሰን የሚያስችለውን ሒደት መዘርጋት፤

(ሰ) የአፈጻጸም ፖሊሲውን በእያንደንዱ የደንበኛ ትዕዛዝ ላይ ተግባራዊ ማድረግ፤

(ሸ) ማንኛውንም ጉድለት ለመለየትና ተገቢ ሲሆን ለማስተካከል የትዕዛዝ አፈጻጸም ዝግጅቶችንና የፖሊሲውን ውጤታማነት በመደበኛነት መከታተል፡፡

(3.) የእያንዳንዱ የግብይት አባል የአፈጻጸም ፖሊሲ የእያንዳንዱን የአፈጻጸም ሁኔታ አንጻራዊ ጥቅም ወይም የአፈጻጸም ሁኔታዎቹን አንጻራዊ ጥቅም ለመወሰን የሚያስችል ሒደት መዘርጋት አለበት፡፡ አንድ የግብይት አባል ለአፈጻጸም ሁኔታዎቹ የሚሰጠው ጥቅም መቀረጽ ያለበት ለደንበኞቹ ትዕዛዞች የሚቻለውን ምርጥ ውጤት ማምጣት እንዲቻል መሆን አለበት፡፡

(4.) እያንዳንዱ የግብይት አባል የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፦

(ሀ) በግብይት አፈጻጸም ዝግጅቶቹ ወይም የአፈጻጸም ፖሊሲው ላይ የሚኖሩ ለውጦችን ለደንበኞቹ ማሳወቅ፤

(ለ) በየዓመቱ የትዕዛዝ አፈጻጸም ፖሊሲውንና የአፈጻጸም ዝግጅቶቹን መገምገም፡፡ ግምገማው የግብይት አባሉ ለደንበኛው ትዕዛዞች ወጥነት ባለው ሁኔታ የሚቻለውን ምርጥ ውጤት ለማስገኘት መቻሉ ላይ ተጽዕኖ የሚኖረው ዐቢይ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ መከናወን አለበት፡፡

(ሐ) ጥያቄ ሲያቀርቡለት ለደንበኞቹና ገበያው የደንበኞቹን ትዕዛዞች በአፈጻጸም ፖሊሲው መሠረት መፈጸሙን ማሳየት መቻል፡፡ የግብይት አባሉ በዚህ መጽሐፈ-ደንብ ውስጥ ለተቀመጡት የኦዲት ሰነድ ዱካ መስፈርቶች ተገዢ መሆን አለበት፡፡

(መ) ለአፈጻጸም የደንበኛውን ትዕዛዞች ሲቀበልም ሆነ ሲያስተላልፍ የደንበኛውን የላቀ ጥቅም ለማስጠበቅ መሆን አለበት፡፡

## 4.5. የደንበኞችን ዝርዝር መመሪያዎች መከተል

(1.) እያንዳንዱ የግብይት አባል የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፦

(ሀ) የደንበኛውን ዝርዝር መመሪያዎች መፈጸም፡፡

(ለ) አንድን ትዕዛዝ ወይም የአንድን ትዕዛዝ ዝርዝር ገጽታ በመፈጸም ሒደት ውስጥ የሚቻለውን ምርጥ ውጤት ለማስገኘት የሚያስፈልጉ ምክንያታዊ እርምጃዎችን በሙሉ መውሰድ፡፡

(2.) አንድ የግብይት አባል ደንበኛው የሰጠውን ዝርዝር መመሪያ በመከተል ትዕዛዙን ሲፈጽም የምርጥ አፈጻጸም ፖሊሲውን በሚያሟላ ሁኔታ ፈጽሟል የሚባለው ደንበኛው ዝርዝር መመሪያ የሰጠበትን የትዕዛዙን ክፍል ወይም ገጽታ በሚመለከት ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ተቃራኒውን የሚያመለክት ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ የደንበኛው ዝርዝር መመሪያ የግብይት ፈፃሚውን አባል ከሚመለከተው የምርጥ አፈጻጸም ፖሊሲ ግዴታ ጋር በተገናኘ በሌሎቹ የደንበኛው ትዕዛዝ ክፍሎች ወይም ገጽታዎች ላይ ተፈጻሚ እንደሆነ አይቆጠርም፡፡

(3.) ማንኛውም የግብይት አባል ደንበኛው የአንድን ትዕዛዝ አፈጻጸም በሚመለከት የሚሰጣቸው ዝርዝር መመሪያዎች ደንበኛው የሚቻለውን ምርጥ ውጤት እንዳያገኝ ሊከላከሉ እንደሚችሉ ምክንያታዊ ዕውቀት ሊኖረው ሲገባ በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ የትዕዛዙን ይዘት በምክር መልክ በማቅረብ ደንበኛው እንደዚህ ዓይነት መመሪያዎችን እንዲሰጥ ማግባባት አይችልም፡፡

(4.) ለደንበኞች የሚታዘዙ ሁሉም ትዕዛዞች የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለባቸው፡-

(ሀ) የታዘዘበት ቀንና ሰዓት፤

(ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ስምና የሚገዛውን ወይም የሚሸጠውን መጠን፤ እንዲሁም

(ሐ) የትዕዛዙን ቃሎችና ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ።

(5.) የደንበኞችን ትዕዛዝ በሚከተሉት መንገዶች መቀበል እና/ወይም ማዘዝ ይቻላል፡-

(ሀ) በግብይት አባሉ የሥራ ቦታ በግንባር በመቅረብ፤

(ለ) የግብይት አባሉና ደንበኛው ትዕዛዞችን በስልክ ለማስመዝገብ ከተስማሙና አግባነት ያላቸው አሠራሮች ከተከበሩ በስልክ (በድምጽ፣ በጽሑፍ ወይም ስካን በተደረገ ምስል)፤

(ሐ) በኤሌክትሮኒክ ሜይል፤ እና/ወይም

(መ) በአጭር የጽሑፍ መልእክት በኩል የሚላክ ትዕዛዝ በአግባቡ እስከተሰነደና ጥያቄ ሲቀርብ ማቅረብ እስከተቻለ ድረስ በየግብይት አባሉ ዘንድ ተመዝግቦ በሚገኘውና ከደንበኛው ሒሳብ ጋር ከተሳሰረው የደንበኛው ስልክ ቁጥር በተላከ የአጭር ጽሑፍ መልእክት።

(6.) ማንኛውንም ትዕዛዝ አስመልክቶ በማስረጃነት ሰነዶችን አለማቅረብ እንደ ሥነ-ምግባር ጥሰት ተወስዶ እንደ አግባብነቱ በገበያው ቅጣትን ሊያስከት ይችላል።

4.6 የደንበኛን ትዕዛዝ ማስተናገድ

(1.) የግብይት አባሉ የደንበኛው ትዕዛዝ ደርሶት መመሪያው የተሟላ መሆኑን ካረጋገጠና ተፈጻሚነት ካለው ሕግ አንጻር ከመረመረ በኋላ ትዕዛዙን ለመፈፀም ሲቀበል ትዕዛዙን በፍጥነት፣ በፍትሐዊነትና በቅልጥፍና ለመፈጸም የሚያስችሉ አሠራሮችንና ዝግጅቶችን ማከናወን አለበት።

(2.) እያንዳንዱ የግብይት አባል የደንበኛውን ትዕዛዞች ሲፈጽም፡-

(ሀ) በደንበኞች ስም የተፈጸሙ ትእዛዛች በፍጥነትና በትክክል መመዝገባቸውንና መደልደላቸውን ማረጋገጥ፤ እና

(ለ) ትዕዛዙን በተገቢው መንገድና በፍጥነት ለመፈጸም አዳጋች የሚሆኑ ዐበይት ሁኔታዎች መከሰታቸውን እንዳወቀ ወዲያውኑ ይህንኑ ለደንበኛው ማሳወቅ አለበት።

(3.) ለአዋጁ ድንጋጌዎች ተገዢ በመሆን ማንኛውም የግብይት አባል ገና ካልተፈጸሙ የደንበኞች ትዕዛዞች ጋር የሚያያዙ መረጃዎችን ያለ አግባብ መጠቀም አይችልም

በተጨማሪም እያንዳንዱ የግብይት አባል ተገቢ ያልሆነ የመረጃ አጠቃቀምን ለመከላከል ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ አለበት፡፡

## 4.7. ትዕዛዞችን በአንድ ላይ መደመርና መደልደል

(1.) የሚከለተሉት ሁኔታዎች ካልተሟሉ በስተቀር ማንኛውም የግብይት አባል የአንድን ደንበኛ ትዕዛዝ ከሌላ ደንበኛ ትዕዛዝ ጋር በመደመር ግብይት መፈጸም አይችልም፡ -

(ሀ) ትዕዛዞችንና ግብይቶችን በአንድ ላይ መደመር ተቀባይነት ያለውን ፍትሐዊ የድልድል ዘዴ የማይሸረሽሩ ወይም የማይጻረሩ ከሆነ፡፡ ተቀባይነት ያላቸው ፍትሐዊ የድልድል ዘዴዎች በየጊዜው በገበያው የሚታተሙ ይሆናል፡፡

(ለ) የትዕዛዞች ብዛት፣ ዋጋ እና/ወይም የቅበላ ጊዜ ድልድል የሚወስንበትንና ከፊል አፈጻጸሞች የሚስተናገዱበትን ሁኔታ ጨምሮ በአንድ ላይ የተደመሩ ትዕዛዞችና ግብይቶች በፍትሐዊነት ስለሚደለደሉበት አግባብ በበቂ ሁኔታ የሚደነግግ የትዕዛዝ ድልድል ፖሊሲ ተቀርጾ በውጤታማነት በሥራ ላይ የዋለ ከሆነ፡፡

(2.) አንድ የግብይት አባል የአንድ ደንበኛን ትዕዛዝ ከአንድ ወይም ከዚያ ከሚበልጡ ሌሎች ትዕዛዞች ጋር በአንድ ላይ ሲደምርና የተደመረው ትዕዛዝ በከፊል ሲፈጸም የግብይት አባሉ ግብይቶቹን በትዕዛዝ ድልድል ፖሊሲው መሠረት መደልደል አለበት፡፡

(3.) የትዕዛዝ ምደባ እና ምርጥ አፈጻጸም ፖሊሲው የትዕዛዝ አፈጻጸም ለግብይት አባሉ ደንበኞች ፍትሃዊነትን ባረጋገጠ መልኩ የሚደለደሉበትን አግባብ በግልጽ ቃላት ማስቀመጥ ያለበት ሲሆን ይህም የግብይት አባላት ውስጣዊ የፖሊሲ ሰነዶች አንዱ ይሆናል፡፡

## 4.8. የየግብይት ፈፃሚውን አባል የግል ሒሳብ ከደንበኞች ግብይት ጋር በአንድ ላይ መደመርና መደልደል የተከለከለ ስለመሆኑ

ማንኛውም የግብይት አባል የአንድን ደንበኛ ትዕዛዝ በግል ሒሳቡ ከሚያከናውነው ግብይት ጋር በአንድ ላይ መደመር አይፈቀድለትም፡፡

## 4.9. የኦዲት ዱካ መመዘኛዎች

(1.) የግብይት አባላት የትዕዛዝ መከታተያና መቆጣጠሪያ ሥርዓት መዘርጋት አለባቸው፡ ፡ ይህም የአንድን ትዕዛዝ ዑደት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚያሳይ የሰነድ ዱካ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡

(2.) በግብይት አባሉ ሥርዓት ውስጥ በተሻሻሉ፣ በተሰረዙና በተፈጸሙ ትዕዛዞች ላይ ሁሉ የኦዲት ሰነድ ዱካ ማስረጃ መኖር አለበት፡፡ ይህም በመላው የአንድ ትዕዛዝ

ዑደት ውስጥ ግልጽ ዕይታ እንዲኖር ለማስቻል የሚያስፈልግ ነው፡፡ ይህንንም ለማመቻቸት የግብይት አባላት ሰዓት አመልካቾችና ትዕዛዞች ወደ እነርሱ የደረሱበትን ሰዓት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ሌሎች አስተማማኝ መንገዶችን በሥራ ላይ ማዋላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

4.10. የቋሚ ገቢ ገበያ ትዕዛዝ የሚስተናገድበት አግባብ

(1.) የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በገበያው የኤሌክትሮኒክ ግብይት መድረክ ላይ በሚከተሉት መንገዶች መገበያየት ይቻላል፡-

(ሀ) በማወዳደሪያ ዋጋ ጥያቄ መንገድ፤ ወይም

(ለ) በግብይት መድረኩ ላይ በተቀመጠ የማይቀየር ትዕዛዝ፤ ወይም

(ሐ) በግብይት መድረኩ ወይም ለእርሱ ሪፖርት በሚደረግ የሁለትዮች/የድርድር ዘዴ (የድምጽ ወይም የውይይት መድረክ)፡፡

(2.) የማወዳደሪያ ዋጋ ጥያቄዎች በገበያው በሚወሰነው መሠረት በመደበኛ መጠኖች ወይም በመደበኛው መጠን ብዜቶች የሚቀመጡ ይሆናሉ፡፡

4.11. የቋሚ ገቢ ገበያ የተቆረጡ ዋጋዎች ወይም የትዕዛዝ ደንብ

(1.) በገበያው ላይ የሚኖሩ የዕዳ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የተቆረጡ ዋጋዎች ወይም የማይቀየሩ ትዕዛዞች በትርፍ ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፣ ነገር ግን በወለድ ክፍያዎች መካከል ያለውን ማንኛውንም የተጠራቀመ ወለድ የማያካትት ለአንድ ቦንድ ያለውን ትክክለኛ ዋጋ ማሳየት አለባቸው፡፡

(2.) የገንዘብ ገበያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ቁርጥ ዋጋዎች ወይም የማይቀየሩ ትዕዛዞች ትርፍን መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

(3.) ገበያው ግብይት አከናዋኝ ገበያ ከፋቾች ጋር ስምምነት በተደረገበት የስጋት አስተዳደር ሒደት መሠረት በቋሚ ገቢ ገበያው ውስጥ በገበያ ከፋቾች የሚኖረውን ከፍተኛውን በግዥ እና በሽያጭ ዋጋ መካከል ያለውን ልዩነት ይወስናል፤ ይለዋውጣል፡፡

(4.) ሁሉም ቁርጥ ዋጋዎች በአራት አሥርዮሽ አኃዞች መቅረብ አለባቸው፡፡

4.12. የግብይቶች የቋሚ ገቢ አፈጻጸም

(1.) ግብይቶች መፈጸም ያለባቸው በገበያው የኤሌክትሮኒክ ግብይት መድረክ በኩል ነው፡፡

(2.) በድምጽ ወይም በጽሑፍ መልእክት መድረኮች ለሚደረግና ለሚረጋገጥ የሁለትዮች/የድርድር ግብይት፣ ግብይቱ በገበያው የኤሌክትሮኒክ ግብይት መድረክ

ውስጥ በሚገኘው የግብይት ሪፖርት ማድረጊያ ሥርዓት ላይ ሪፖርት መደረግና መመዝገብ አለበት፡፡ እያንዳንዱ ግብይት አከናዋኝ አባል የገባባቸውን ግብይቶች በሚመለከት ገበያው ለወሰናቸው የሪፖርት አደራረግ መስፈርቶች ተገዢ መሆን አለበት፡፡ ግብይት አከናዋኝ አባላት የግብይት አፈጻጸምን በሚመለከት በስልክ የሚያደርጓቸው ንግግሮች መቀዳታቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 4.13. የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ቁርጥ ዋጋዎችና ትዕዛዞች የጸኑ መሆን

(1.) ቁርጥ ዋጋዎች የሚሰጡት የማወዳደሪያ ዋጋ ጥያቄ የግብይት ሞጁል፣ የማይቀየር ትዕዛዞች እና/ወይም ስልክን በመጠቀም ነው፡፡

(2.) በስልክ የተሰጡ ቁርጥ ዋጋዎች የጸኑ የሚሆኑት ለዚያ የስልክ ጥሪ ብቻ ነው፡፡

(3.) ለስክሪን ላይ ግብይቶች ቁርጥ ዋጋዎች የጸኑ የሚሆኑት የሁለት አቅጣጫ ዋጋ አቀራረብን መሠረት በማድረግ ከስልሳ ሰከንዶች ለማይበልጥ ጊዜ ነው፡፡

(4.) ከግብይት ሥርዓቱ ውጪ የተፈጸሙ ግብይቶች በተፈጸሙ በአሥር ደቂቃዎች ውስጥ በግብይት ሥርዓቱ ላይ ሪፖርት መደረግ አለባቸው፡፡

(5.) የማይቀየር ትዕዛዝ ሲሰጥ ቁርጥ ዋጋዎች እስከሚቀየሩበት ጊዜ ድረስ የጸኑ ይሆናሉ፡፡ የቁርጥ ዋጋው መጠን እና/ወይም ዋጋም እስከሚቀየሩ ድረስ የጸኑ ይሆናሉ፡፡ አንድ ቁርጥ ዋጋ ተቀባይነትን ካገኘ በኋላ ሊቀየር አይችልም፡፡

## 4.14. የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የግብይት መጠናቀቅ

(1.) አንድ ግብይት አከናዋኝ አባል ቁርጥ ዋጋ ከሰጠ በኋላ ጥያቄ አቅራቢው ግብይት አከናዋኝ አባል በተሰጠው ቁርጥ ዋጋ ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ከወሰነ ግብይቱን ለማጠናቀቅ ፈቃደኛ አለመሆን አይችልም፡፡

(2.) አንድ ግብይት አከናዋኝ አባል በዋጋና በመጠን ላይ ከስምምነት ከተደረሰ በኋላ ግብይቱን የማጠናቀቅ ግዴታ አለበት፡፡

(3.) አንድ ግብይት ተፈጸመ የሚባለው የዋጋ ማወዳደሪያ ጥያቄ ያቀረበው ግብይት አከናዋኝ አባል ቁርጥ ዋጋ ያቀረበው ግብይት አከናዋኝ አባል ባመለከተው ዋጋ መደበኛውን መጠን ወይም የተገለጸውን መጠን መግዛቱን ወይም መሸጡን ሲያረጋግጥ ነው፡፡

# *ምዕራፍ 5 - የስህተት ግብይቶችና ትዕዛዞች*

## 5.1. የትዕዛዞችን ትክክለኛነት የተመለከተ ኃላፊነት

(1.) አንድ የግብይት አባል በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ ለሚያስገባቸው ትዕዛዞች ትክክለኛነት ብቸኛ ኃላፊነት አለበት፡፡

(2.) አንድ የግብይት አባል ከደንበኛው የተረጋገጠ ትዕዛዝ ሳይሰጠው ወደ ደንበኛው የግብይት ሒሳብ መግባት አይፈቀድለትም፡፡

## 5.2. የዋና መዝገብ የስህተት ሒሳቦች

(1.) አንድ የግብይት አባል በዋና መዝገቡ ውስጥ የስህተት ሒሳብ ካልያዘ በስተቀር በገበያው የግብይት መገልገያዎች በመጠቀም ግብይቶችን መፈጸም አይፈቀድለትም፡ ፡

(2.) በገበያው የግብይት መገልገያዎች በመጠቀም ተከናውኖ የግብይት አባሉ በስህተት ምክንያት በአንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ መብት እንዲያገኝ ወይም እንዲይዝ ያስቻለ እና አንድ ግብይት አባል በስህተት የተፈጸመ ግብይትን ለማቻቻል የሚያስጀምረው ማንኛውም ግብይት ደንበኛው የስህተት ግብይቱን ካልተቀበለው በስተቀር በግብይት አባሉ የዋና ማኅደር የስህተት መለያ ሒሳብ ወይም የቡድን የዋና ማኅደር የስህተት መለያ ላይ መጣራት አለበት፡፡ የግብይት አባሉ በስህተት የተፈጸመን ግብይት ለማቻቻል በገበያው የግብይት መገልገያዎች ላይ የሚያስጀምረው ግብይት በተገቢው አኳኋን በዋና ማኅደር የስህተት መለያው ሒሳብ ላይ መቀመጥ አለበት፡፡

(3.) አንድ የግብይት አባል በስህተት የተፈጸሙ ግብይቶችን በሙሉ የሚመዘግበበት የዋና መዝገብ የስህተት ሒሳብ መክፈት አለበት፡፡ ሁሉንም ስህተቶች የሚመለከቱ ዝርዝሮች በግብይት አባሉ መያዝ የሚኖርባቸው ሲሆን የሚከተሉትን የኦዲት ሰነድ የዱካ መረጃ አካሎች ማካተት አለባቸው፡-

(ሀ) ክፍያ በሚፈጽመው አካል እንደሚያስፈልገው የሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ስም ወይም መለያ ምልክት፤

(ለ) የአክሲዮኖች ቁጥር ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ብዛት፤

(ሐ) የግብይት ዋጋ

(መ) የግብይት ሰዓት፤

(ሠ) በውሉ ውስጥ የራሱን ወገን በሚመለከት የግብይት ፈፃሚው ማንነት፤

(ረ) የተፈጸመው ስህተት ምንነት፤

(ሰ) የግብይት አባሉ ያጋጠመውና የስህተት ግብይቱ ሲመዘገብ መክፈል ያለበት አጠቃላይ የኃላፊነት መጠን፤ እና

(ሸ) ገበያው በየጊዜው የሚፈልጋቸው ሌሎች መረጃዎች፡፡

(4.) አንድ ስህተት መፍትሔ የሚያገኘው ደንበኛው የተፈመውን ስህተት ከተቀበለ ወይም የግብይት አባሉ ለደንበኛው የስህተት ግብይቱን መጠን ሲከፍል ነው፡፡

(5.) አንድ የግብይት አባል ደንበኛው ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነባቸውን የስህተት ግብይቶች በሙሉ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡፡ ይህ ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንዲሁም በገበያው ትርጓሜና ውሳኔ መሠረት የስህተቱንና የማቻቻያውን ግብይት ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

## 5.3. ግብይቶችን መሰረዝ

(1.) አንደኛው የግብይቱ ወገን በደንብ ቁጥር 5.5 መሠረት ግብይቱ እንዲሰረዝ ጥያቄ ሲያቀርብና በስህተት ግብይቱ በተቃራኒ ያሉት ወገኖች ገበያው ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በስረዛው ሲስማሙ ገበያው በራሱ ውሳኔ እነዚህን የስህተት ግብይቶች በከፊልም ሆነ በሙሉ ሊሰርዛቸው ይችላል፡፡

(2.) በግብይቶች ውስጥ ማጭበርበር እንደተፈጸመ ሲረጋገጥ ወይም ማንኛውም በገበያው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል ተብሎ በገበያው የሚታሰብ ሁኔታ ሲኖር ገበያው ግብይቶችን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

## 5.4. የግልጽ ስህተቶች አስተዳደር

(1.) ከግልጽ ስህተት የሚመነጭ አንድ (1) ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግብይቶች በሚፈጸሙበት ጊዜ ገበያው በዚህ መጽሐፈ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት እነዚህን ግብይት(ቶች) የመሰረዝ ወይም የማስተካከል ሥልጣኑን ሊጠቀም ይችላል፡፡ በተጨማሪም ከግልጽ ስህተት የመነጨና በእንጥልጥል ያሉ የግዢ ጥያቄዎችንና ተመኖችን ሊሰርዝ ወይም ሊያስተካክል ወይም ግልጹ ስህተት እስከሚፈታ ድረስ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ባሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚደረግን ግብይት ሊያስቆም ይችላል፡፡

(2.) ግልጽ ስህተት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

(ሀ) የመሸጫ ወይም የመግዣ ዋጋ መጠንን የሚመለከት ስህተት፡- ግብይቱ አንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ካለው የገበያ ዋጋ በተጋነነ መጠን ከሚጨምር የግዢ ወይም የመሸጫ ጥያቄ የመነጨ ሲሆን፤

(ለ) የግዢ ወይም የመሸጫ ዋጋን የሚመለከት ስህተት፡- ግብይቱ የተጠናቀቀው የመግዣ ዋጋው በቀረበበት ጊዜ ከገበያው ዋጋ ከፍተኛ ልዩነት ባለው ዋጋ ሲሆንና እንደዚህ ዓይነት የግብይት ዋጋን የሚያስረዳ ውጫዊ መረጃ የሌለ ሲሆን፡፡

(ሐ) ከፍተኛ የዋጋ ልዩነት ጋር የተያያዘ ስህተት፦ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ግብይት የተከናወነው ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ የገበያ ዋጋ ጋር ከፍተኛ ልዩነት ባለው ዋጋ ሲሆን፡፡

(መ) የሒሳብ ቁጥርን የሚመለከት ስህተት፡-

(i.) ከግብይት በፊት ሒሳቦችን ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን፤

(ii.) የግዢና የሽያጭ ትዕዛዞችን በማገበያየት ሒደት ለገዢውና ለሻጩ ወገኖች ተመሳሳይ የሒሳብ ቁጥር በሚገባበት ጊዜ፤

(iii.) አንድ ግብይት ያልታሰበና በአንድ ግብይት አባል ሁለት ሒሳቦች መካከል የተመሳሳይ ግዢና ሽያጭ ትዕዛዞችን ሲያገበያይና ግብይቱ የተጠቃሚ ባለቤትነት ለውጥ ሳያስከትል ሲቀር፤

(ሠ) አንድ ግብይት በፍጥነት ሲደጋገም፡- በአንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ በተመሳሳይ መጠን ተከታታይ ግብይቶች ሲፈጸሙና ሁኔታው ለአንድ ምክንያታዊ ተመልካች የመግዣው ወይም የመሸጫው ጥያቄ ከየግብይት ፈፃሚው ወይም ከደንበኞቹ ፍላጎት በተቃራኒው የየግብይት ፈፃሚው ወይም የገበያው ሥርዓት በራሱ እየደጋገማቸው ያሉ ስለመሆኑ አመላካች ሲሆን፡፡

## 5.5. የግልጽ ስህተት ማስተካከል አሠራር

(1.) የግልጽ ስህተቶችን ምርመራ ማስጀመር

(ሀ) የግብይት አባሉ አነሳሽነት፡-

(i.) በግልጽ ስህተት ምክንያት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ግብይቶች ላይ የተሳተፈ የግብይት አባል ግብይቱ (ቶቹ) በተፈጸሙ በሠላሳ (30) ደቂቃዎች ውስጥ ለገበያው ማሳወቅና ግብይቶቹ እንዲሰረዙ ወይም እንዲስተካከሉ መጠየቅ አለበት፡፡

(ii.) አንድ የግብይት ስህተት ያለበትን(ያለባቸውን) ግብይት(ቶች) በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላሳወቀ ከዚያ በኋላ ግልጽ ስህተት መሆኑን መሠረት በማድረግ ግብይቱን(ቶቹን) መሰረዝ ወይ ማስተካከል አይችልም፡፡

(iii.) ስለ ስህተቶቹ ለገበያው የሚቀርበው የማሳወቂያ ቅጽ በጽሁፍ ሲሆን ገበያው በየጊዜው በሚያዘው ቅጽ መሠረት ይሆናል፡፡

(iv.) የግልጽ ስህተት ማሳወቂያው የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን መለያ፣ የግብይት ሰዓት፣ የግብይት ዋጋ፣ የደንበኛውን/ኞቹን የሒሳብ

ቁጥሮች፣ እንዲሁም ከግልጽ ስህተት ትርጓሜው ጋር የሚጣጣም አጭር የስህተቱ መግለጫን ማካተት አለበት፡፡

(v.) ገበያውና የግብይት አባሉ የግብይቱን ስረዛ ወይም ማስተካከያ ከማከናወናቸው በፊት በግብይቱ የተሳተፈውን ሌላኛ ወገን የጽሁፍ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

(ለ) በገበያው ተነሳሽነት፡- ገበያው፣ ከግብይት አባላት ማሳወቂያ ደርሶትም ሆነ ሳይደርሰው በራሱ ተነሳሽነት ግልጽ ስህተት የሆነ(ኑ) ግብይት(ቶች)ን እንዲመረመሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የስህተት ግብይት እንደሆኑ የተጠረጠሩ ግብይቶች በተፈጸሙ በሠላሳ (30) ደቂቃ ውስጥ ወይም ገበያው ከመዘጋቱ በፊት ሊታወቁ የማይችሉ ግልጽ ስህተቶች ከሆኑ ደግሞ ገበያው ከተዘጋ በኂላ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ምርመራው መጀመር አለበት፡፡

(ሐ) ግልጽ ስህተቱ የተፈጠረው ገበያው ከተዘጋ በኂላ ባሉት ሠላሳ (30) ደቂቃዎች ውስጥ ከሆነ ገበያው በራሱ ውሳኔ ግልጽ ስህተቱ እንዲመረመር ሊያደርግ ወይም ላያደርግ ይችላል፡፡

(2.) በዚህ መጽሐፈ ደንብ መሠረት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ግብይቶች ላይ ምርመራ በሚጀመርበት ጊዜ ገበያው አንድ ግብይት ላይ ምርመራ እየተደረገበት እንደሆነ ለገበያ መረጃ የሚሰጥ ማሳወቂያ መስጠት ያለበት ሲሆን ምርመራ በሚደረግበት ግብይት ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች በተገቢው ጊዜ ውስጥ ገበያው ከሚያከናውነው ምርመራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተጨማሪ መረጃዎች እንዲያቀርቡ ግብዣ ሊያደርግላቸው ይችላል፡፡ ለገበያ የሚሰጠው ማሳወቂያ በግብይቱ ተሳታፊ ሰዎች ምላሽ የሚሰጡበትን ቀነ ገደብ ማስቀመጥ አለበት፡፡

(3.) ግልጽ ስህተት መፈጠር ወይም አለመፈጠሩን የመወሰን ኃላፊነት የገበያው ወይም የገበያው ተወካይ ብቻ ነው፡፡ ገበያው ወይም የገበያው ተወካይ ሁኔታዎቹን ከመረመረ በኂላ ግልጽ ስህተት እንደተፈጠረ ሲወስን ገበያው ከዚህ በታች በሚገኘው በንዑስ ደንብ (4) ሥር የተጠቀሰውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

(4.) የመጠንና የዋጋ ስህተቶች ሲስተካከሉ ገበያው የሚወስነው የማስተካከያ አስተዳደራዊ ክፍያ በግብይቱ ላይ ይጣላል፡፡ በምርመራ የሚጣሩ አስተዳደራዊ ክፍያዎች ወይም መቀጮዎች ቢኖሩም ገበያው አስገዳጅ ሥልጣናን ጨምሮ በገበያው የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓት ደንቦች መሠረት ለስህተት ትዕዛዝ ምዝገባው ኃላፊ በሆነው የግብይት አባል ላይ ተጨማሪ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን የመውሰድ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

(5.) ገበያው አንድ ግልጽ ስህተት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚለውን በሚመለከት የሚያሳልፈውን ውሳኔ ወዲያውኑ በግብይቱ ላይ ለተሳተፉ ወገኖችና ለገበያ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 5.6. ገበያው የስህተት ግብይቶችን አስመልክቶ የሚሰጣቸው ውሳኔዎችና ይግባኞች

ገበያው በዚህ ደንብ መሠረት መርምሮ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ በግብይቱ የተጎዳ ወገን የሚያቀርበው ይግባኝ በገበያው የቅሬታ አፈታትና ተፈጻሚነት ባላቸው የግጭት አፈታት ሥነ-ሥርዓቶች መሠረት መሆን አለበት፡፡

# *ምዕራፍ 6 - የተከለከሉ ተግባራት*

## 6.1. በዋስትና ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥራ ግንኙነት ስለ መከልከሉ

(1.) ማንኛውም የግብይት አባል፦

(ሀ) ለደንበኛው ትርፍ እንደሚያስገኝ ማረጋገጫ በመስጠት ላይ ወደ ሥራ ግንኙነት መግባት፤ ወይም

(ለ) ለደንበኛው በማንኛውም ሒሳብ ወይም የግብይት አባሉ ለደንበኛው በሚያከናውነው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ወይም ከዚህ በፊት ከደንበኛው ጋር በተስማማበት የትርፍ ሕዳግ ላይ ኪሳራ እንደማያጋጥመው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዋስትና መስጠት አይችልም፡፡

(2.) ሁሉም የግብይት አባላት ከደንበኞቻቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ለኢንቨስትመንቶች ዋስትና ያላቸው ትርፎች የተከለከሉ መሆናቸውን በግልጽ መጥቀስ አለባቸው፡፡

(3.) ሁሉም የግብይት አባላት በደንበኞች የማመልከቻ ቅጽ ላይ በዋስትና ላይ የተመሠረተ የንግድ ግንኙነትና እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ክልክል መሆናቸውን በግልጽ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

(4.) ማንኛውም የዚህን ደንብ ድንጋጌ የሚተላለፍ የግብይት አባል በአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ ሥር የሚገኙት ቅጣቶች ይጣሉበታል፡፡

## 6.2. በደንበኞች መካከል ማበላለጥ ክልክል ስለመሆኑ

(1.) የግብይት አባላት ከአፈጻጸም ቅድሚያ አሰጣጥ በሚቃረን መንገድ ለአንድ ደንበኛ ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑ ግብይቶችን መመደብን ጨምሮ የአንድ ደንበኛን ሒሳብ ከሌላኛው ማበላለጥ አይችሉም፡፡

(2.) የደንበኞች ሒሳቦችና ግብይቶች በሙሉ የሚስተናገዱት በእነዚህ ደንቦች ውስጥ የትዕዛዝ አያያዝንና የምርጥ አፈፃጸም መርሆችን በሚመለከት በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

6.3. ግዴታውን ካልፈጸመ ደንበኛ ጋር ግብይት ማድረግ ስለመከልከሉ፡፡

(1.) ማንኛውም የግብይት አባል ከሌላ የግብይት አባል ጋር ግዴታውን ካልፈጸም ደንበኛ ጋር ግብይት እንዲፈጽም አይፈቀድለትም፡፡

(2.) እያንዳንዱ የግብይት አባል እያንደንዱን ግዴታውን ያልፈጸመን ደንበኛ ስምና ተያያዥ ሁኔታዎችን ለገበያው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ እያንደንዱን ግዴታን ያለመወጣት ሁኔታ አግባብነት ላለው የገበያው አካል መቅረብ አለበት፡፡

(3.) ለገበያው የግብይት አባላት በሙሉ ለማዘዋወር ዓላማ በሚይዘው ዝርዝር ውስጥ ገበያው ዕዳ ያልከፈሉ ደንበኞችን ስም ሊያካትት ይገባል፡፡

(4.) ከላይ በንዑስ ደንብ (3) የተጠቀሰውን ዝርዝር በብቸኝነት የሚያስተዳድረው፣ የሚያዘምነውና አርትዖት የሚያደርግበት የገበያው የዲሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

6.4. የገበያው መገልገያዎችና መረጃ

(1.) ማንኛውም የግብይት አባል ከገበያው የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ እና በመደበኛው የሥራ ክንውን ሒደት ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በራሱ ወይም በተወካዮቹ በኩል የግብይት ሥርዓቱን ወይም በግብይት ሥርዓቱ የሚቀርብን መረጃ ወይም ይዘት ይፋ ማድረግ፣ ማሳየት ወይም ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ወይም መልሶ ማቀናጀት፣ መልሶ ማሰራጨት፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም አይችልም፡፡

(2.) ገበያው የመዝጊያ ዋጋዎችን ዝርዝር በየቀኑ ይፋ ያደርጋል፡፡ የግብይት አባል ማንኛውንም ዝርዝር ወይም ማንኛውም ዓይነት ተያያዥ ዝርዝርን ከገበያው አስቀድሞ ፈቃድ ሳያገኝ አትሞ መሸጥ አይችልም፡፡

## *ምዕራፍ 7 - የገበያው የግብይት ሥራዎች*

7.1. የገበያው የሥራ ቀናትና ሰዓታት

(1.) ገበያው በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ሁሉም የሥራ ቀናት በሙሉ ለግብይት ክፍት ይሆናል፡፡

(2.) ግብይት የሚከናወነው ገበያው በሚወስናቸው ጊዜዎች ውስጥ ይሆናል፡፡ ገበያው እንደ አስፈላጊነቱ ለግብይት አባላት በማሳወቅ የግብይት ሰዓቶችን ሊያራዝም፣ ሊያስቀጥል፣ ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

(3.) በገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሌላ የሥራ ሰዓት ካልተቀመጠ በስተቀር ገበያው በምስራቅ አፍሪካ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 9፡00 ሰዓት ድረስ በሚከተለው አግባብ ለግብይት ክፍት ይሆናል፡-

(ሀ) በምስራቅ አፍሪካ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30 ድረስ የቅድመ-መክፈቻ ክፍለ ጊዜ ይኖራል፤

(ለ) የመክፈቻ ሒሳቡ መውጣቱን ተከትሎ ግብይቱ ይጀመርና በምስራቅ አፍሪካ ሰዓት አቆጣጠር እስከ ቀኑ 9፡00 ሰዓት ድረስ ይቀጥላል፤

(ሐ) ግብይቱ በምስራቅ አፍሪካ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ላይ ይቆማል። ከዚህ ሰዓት በኋላ ምንም ዓይነት ግብይት አይከናወንም።

(4.) በልዩ ሁኔታዎች ገበያው በራሱ ውሳኔ ወይም በባለሥልጣኑ ጥያቄ ገበያው በቅድሚያ የባለሥልጣኑን ይሁንታ በማግኘት ለአንድ ውስን የግብይት ቀን የግብይቱን ሰዓት በምሥራቅ አፍሪካ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በኋላ ሊያራዝመው ይችላል።

(5.) ገበያው በሚቻለው ፍጥነት የግብይት ቀኑ ስለመራዘሙ የሚገልጽ ይፋዊ ማስታወቂያ መስጠት አለበት።

## 7.2. የግብይት መስፈርቶች

(1.) በአንድ ግብይት ጊዜ ከዚህ ተቃራኒው ካልተቀመጠ በስተቀር በአንድ የግብይት አባል ግብይት የሚከናወንባቸው ሁሉም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሙሉ ለሙሉ እንደተከፈለባቸውይቆጠራሉ።

(2.) የግብይት አባላት የሚገቡባቸው ሁሉም ግብይቶች በገዥና በሻጭ መካከል ባለው የተጣራ ዋጋ መሆን አለበት።

(3.) ገበያው በገበያ ክንውኖቹ ከራሱ የግብይት አባላት ውጪ የሆኑ ሌሎች ወገኖችን ተቀባይነት መስጠት የለበትም፣ እንዲሁም የግብይት አባሉ ለራሱም ሆነ ደንበኛውን በመወከል የሚያደርገው እያንዳንዱ መስተጋብር በገበያው ደንቦች፣ መመሪያዎችና ልምዶች መሠረት መሆን አለበት።

(4.) ገበያው የግብይቱን መንገድ፣ መድረኮችና ሥርዓቶች በየጊዜው ይወስናል። ማንኛውም የግብይት አባል በገበያው አውቶሜትድ የግብይት ሥርዓት በኩል ካልሆነ በቀር አንድን ግብይት መፈጸም አይችልም።

(5.) ገበያው በሚከተሉት ሳይወሰን የሚከተሉትን ከግብይት ሥርዓቱ ጋር የሚገናኙ የተለያዩ የግብይት መለኪያዎችንና መገለጫዎችን በየጊዜው ይወስናል፡-

(ሀ) የአንድ ግብይት መጠኖች፡- የአንድ ግብይት መጠን አንድ አክሲዮን ይሆናል፤

(ለ) የተቆረጡ ዋጋዎችና ትዕዛዞች ማሳያ፡- ገበያው፣ ለግብይት ሥርዓቱ የቀረቡ ግብይት ሊደረግባቸው የሚችሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የትዕዛዛት ዝርዝሮችን በየጊዜው በሚወሰን ቅርጽ ለሕዝብ ይፋ አድርጎ ያሳያል።

## 7.3. ትዕዛዞችን የማጣመር መርሆች

(1.) በገበያው አውቶሜትድ የግብይት ሥርዓት ውስጥ የተመዘገቡና የተፈጸሙ ትዕዛዞች በሚመለከተው የግብይት አባል ላይ አስገዳጅነት አላቸው።

(2.) በገበያው አውቶሜትድ የግብይት ሥርዓት ላይ የተመዘገበ ትዕዛዝ በገበያው የሚወሰኑ ዝርዝር መረጃዎችን መያዝ አለበት።

(3.) የትዕዛዞች ቅደም ተከተል የሚወሰነው በመጀመሪያ በዋጋ ከዚያም በሰዓት ይሆናል፡ :

(4.) አንድ የግብይት አባል ከራሱ የግል ትዕዛዝ በፊት ለደንበኛው ትዕዛዝ ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል።

(5.) አንድ የግብይት አባል መጠንን፣ ጊዜንና የዋጋ ወሰኖችን ጨምሮ ልዩ ልዩ መለኪያዎችን መሠረት በማድረግ በአንድ ትዕዛዝ አፈጻጸም ላይ ሁኔታዎችን ሊያስቀምጥ ይችላል።

(6.) ገበያው የግብይት አባላት በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ግብይት እንዲያከናውኑ የሚፈቀዱላቸውን የገበያ እና የግብይት ዓይነቶችን በየጊዜው ይወስናል። ይህም የትዕዛዝ አገባብ መለኪያዎችን፣ የዋጋ ከለላ ስልቶችን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አመዳደቦችን፣ በሰዓት ገደብ የተመሠረቱ ትዕዛዞችን እና ልዩ ሁኔታዎችን የያዙ ትዕዛዞችን እና ሌሎችንም ይጨምራል።

## 7.4. የግብይት ቴክኖሎጂ ሥርዓቶች አያያዝ

(1.) የግብይት አባላት፣ የደንበኞችን ትዕዛዞች ለመቀበል፣ ለማስተናገድና ለመፈጸም፣ ሪፖርቶችንና የግብይት መረጃን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ከገበያው የግብይት ሥርዓቶች ለመቀበል የሚያግዙ ተገቢ ሥርዓቶችንና ቴክኖሎጂን መዘርጋት አለባቸው።

(2.) የግብይት አባላት፣ አግባብነት ካላቸው ማእከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት፣ ከክፍያ አጣሪና ፈጻሚ አካላት ወይም ከአቻዎቻቸው ጋር በኤሌክትሮኒክ መንገድ የተሳሰሩ አስፈላጊ የኤሌክትሮኒክ መገልገያዎች ሊኖሯቸው እንዲሁም

በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ላይ የሚፈጠሩ ማናቸውንም ችግሮች ለመከላከል የሚያስችል መረጃን ለማከማቸት እና መልሶ ለማግኘት የሚያገለግል ከዋና የስራ ቦታ ውጪ የሆነ የመጠባበቂያ ሥርዓት ሊዘረጉ ይገባል፡፡

(3.) አንድ የግብይት አባል አንድን የግብይት መድረክ ሥራ ከማስጀመሩ ወይም ከማዘመኑ በፊት ቢያንስ፡-

(ሀ) የግብይት ሥርዓቱ ባልተፈለገ መንገድ ጥቅም ላይ አለመዋሉን ፤

(ለ) በሥርዓቶቹ ውስጥ እንዲኖሩ የተደረጉ የሕግ ተገዢነትና የስጋት አስተዳደር መቆጣጠሪያዎች እንደሚፈለገው እየሠሩ መሆናቸውን፤ እና

(ሐ) የግብይት ሥርዓቱ በሚያስተዳድረው የመልእክቶች ቁጥር ላይ ከፍተኛ ጭማሪ በሚኖርበት ጊዜ የግብይት ሥርዓቱ በሚገባ መሥራት መቀጠሉን፤

የሚያረጋግጡና በግልጽ የተቀመጡ የማበልጸጊያና የፍተሻ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፡፡

(4.) የግብይት አባሉ በማንኛውም ጊዜ የሚጠቀምባቸው የግብይት ቴክኖሎጂ ሥርዓቶች ለተዛባ የግብይት ሁኔታዎችን እንደማይፈጥሩ እና አስተዋጽዖ እንደማያደርጉ እንዲሁም በማንኛውም መንገድ ደንበኞቻቸውን ለመጭበርበር የማያጋልጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ማሳየት አለበት፡፡

## 7.5. የጸደቁ የግብይት መድረኮች እና ሥርዓቶች

(1.) ግብይት ማድረግ የሚፈቀደው ገበያው ባጸደቃቸው መድረኮች እና ሥርዓቶች ላይ ብቻ ነው፡፡ እነዚህም በየትኛውም የገበያው የግብይት ማዕከል፣ የአንድ የግብይት አባል የጸደቁ ቢሮዎች ላይ የሚገኙ የሥራ ቦታ ዎችን፣ የግብይት ሳጥኖችን ወይም ገበያው በየጊዜው የሚያጸድቃቸው ሌሎች የመገበያያ መንገዶችን ያካትታሉ፡፡

(2.) ወደ ግብይት ሥርዓቱ መግባት የሚቻለው ለእያንዳንዱ የግብይት አባል በሚሰጠው የተገበያይ መለያ ቁጥርና የመግቢያ ይለፍ ቃል በመጠቀም ነው፡፡

## 7.6. የግብይት አባል ኃላፊነት

አንድ የግብይት አባል በተገበያይ መለያ ቁጥርና የይለፍ ቃሉ አማካኝነት ወደ ግብይት መድረኩ በመግባቱ ለሚፈጠሩ ጉዳዮች ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ኃላፊ ይሆናል፡፡

## 7.7. የግብይት አባላት ስለሚሰይሟቸው ተጠቃሚዎች

(1.) የግብይት አባላት ባለሥልጣኑ ፈቃድ ከሰጣቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተገበያዮች መካከል የገበያውን ይሁንታ በማግኘት ወደ ግብይት ሥርዓቱ መግቢያ የሚሰጧቸውን ተሿሚ እንደራሴዎች የመሰየም መብት አላቸው።

(2.) የተጠቃሚዎች ሹመት የሚከናወነው ገበያው በየጊዜው በሚያወጣቸው ደንብና ሁኔታዎች መሠረት ነው።

(3.) በማንኛውም ጊዜ በግብይት ሰዓታት ውስጥ አንድ የግብይት አባል በግብይት ማዕከሉ ውስጥ ሊያሰማራቸው የሚችሉ የግብይት ፈፃሚዎች ቁጥር በእነዚህ ደንቦች ውስጥ በተቀመጠውና ገበያው በየጊዜው በሚወስነው መሠረት ይሆናል።

## 7.8. የግብይት ሥርዓት መግቢያ መለያዎች አጠቃቀም

(1.) ገበያው ለእያንዳንዱ የግብይት አባል ወደ ግብይት ሥርዓቱ የሚገባበትን መለያ ይሰጣል። ማንኛውም የግብይት አባል ወይም የግብይት አባሉ ተጠቃሚ የመግቢያና የይለፍ ቃሉን ለሌላ የግብይት አባል ወይም ተጠቃሚ ማጋራት አይፈቀድለትም።

(2.) ማንኛውም ከላይ የሚገኘውን የንዑስ ደንብ (1) ድንጋጌን የሚጥስ የግብይት አባል ወይም ተጠቃሚ ጥሰቱን በፈጸመበት በማንኛውም ሰዓት በገበያው የቅጣቶች ሰንጠረዥ መሠረት ቅጣት ይጣልበታል።

(3.) አንድ የግብይት አባል ገበያው በሚቀበላቸው ምክንያቶች የመግቢያ መለያዎቹን ለመለወጥ ጥያቄ ሲያቀርብ ገበያው የሚሰጠውን መመሪያዎች ወዲያውኑ መተግበር አለበት።

## 7.9. ገደቦችና ወሰኖች

(1.) አንድ የግብይት አባል ራሱም ሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው የሚከተሉትን እንዲፈጽሙ መፍቀድ የለበትም፡-

   (ሀ) በገበያው የቀረበውን ሥርዓት ገበያው ካስቀመጠውና ከሚፈቀድው ውጪ ለማንኛውም ሌላ ዓላማ መጠቀም፤

   (ለ) ገበያው የሚያቀርበውን ሥርዓት ገበያው ከሚፈቅደው ሥርዓት ውጪ በማንኛውም ሌላ መሣሪያ መጠቀም፤ እና

   (ሐ) ገበያው ያቀረበውን ሶፍትዌር እንዲቀዳ፣ እንዲለውጥ፣ እንዲቀይር ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው እንዲያገኘው ማድረግ።

(2.) በገበያው ሥርዓቶችና መገልገያዎች ላይ መገበያየት የሚቻለው ብቁ በሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዝርዝር ላይ የተካተቱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ብቻ ነው። የግብይት

አባላት ብቁ ያልሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በገበያው ሥርዓቶችና መድረኮች ላይ ለመገበያየት ብቁ እንደሆኑ አድርገው ማቅረብ የለባቸውም፡፡

(3.) ገበያው በተገለጹ ድርጅታዊ ውሳኔዎች መሠረት ጥቅም የማያስገኙ የትርፍ ድርሻ ክፍፍሎች፣ ጉርሻዎች ወይም ወለዶች በሚመለከት የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የገበያ ዋጋ የሚስተካከሉባቸውን ዘዴዎችና ቀነ ገደቦች በየጊዜው ይወስናል፡ ፡

## 7.10. ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክሲዮኖች ግብይት

(1.) ገበያው፣ አንድ የግብይት አባል ሊያከናውን የሚችለውን ከፍተኛ መጠን ያላቸውን አክሲዮኖች ግብይት የመጠን እና ዋጋ ይዘት በየጊዜው የሚወስን ሲሆን ግብይቱም የሚከናወነው ገበያው አስቀድሞ በሚሰጠው ፈቃድ ነው፡፡

(2.) ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክሲዮኖችን ማገበያየት የሚፈልጉ የግብይት አባላት ግብይት ከመፈጸማቸው በፊት ለገበያው ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ማሳወቂያውና መመዘኛዎቹ ገበያው በጊዜው በሚወስነው ቅርጽና አኳኋን መቅረብ አለባቸው፡፡

(3.) አንድ ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክሲዮኖችን ግብይት ለማከናወን ትዕዛዝ የተቀበለ የግብይት አባል ገበያው በሚያስቀምጠው ቅጽ መሠረት ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡ የግብይት አባሉ ከገበያው ፈቃድ ሳያገኝ ትዕዛዙን መፈጸም አይችልም፡፡

(4.) አንድ የግብይት አባል ግብይቱ እንደ ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክሲዮኖችን ግብይት መቆጠር ያለበት ስለመሆን ወይም አለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆነ ጥርጣሬውን ለመፍታት ከገበያው ጋር መመካከር አለበት፡፡

(5.) የግብይት አባሉ ለገበያው የሚያስገባው ማመልከቻ በጽሑፍ ሆኖ ገበያው በሚያስቀምጠው ቅርጽ መቅረብ አለበት፡፡ ማመልከቻው ከግብይቱ ትዕዛዝ ጋር አብሮ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን የትዕዛዙም ቅጽ ባለ አክሲዮኑ በአግባቡ ፈርሞበት ለግብይት አባሉ በሰጠው ቅርጽ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ገበያው በየጊዜው ለፈቃድ አብረው መቅረብ ያለባቸው የሚላቸው ሰነዶች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ሌሎች መረጃዎችም አብረው መቅረብ አለባቸው፡፡

(6.) ለትልቅ የአክሲዮኖች ስብስብ ግብይት ለገበያው የሚከፈሉ ክፍያዎች መጠን የሚወሰነው የሚሸጡት አክሲዮኖች ቁጥር ድምር ስምምነት ከተደረገበት የግብይት ዋጋ ወይም የገበያ ዋጋ መካከል ከሁለቱ ከሚበልጠው ጋር በማባዛት በሚገኘው ውጤት ላይ ገበያው በየጊዜው የሚያወጣውን ተመን ተፈጻሚ በማድረግ ነው፡፡

(7.) ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክሲዮኖችን ግብይት የሚፈጸመው ካለው የገበያ ዋጋ ውጪ ከሆነ የግብይት አባሉ ከማመልከቻው ጋር የግብይቱ ዋጋ ለማስላት እንደ መሠረት የተጠቀማቸውን ዕሳቤዎች የሚገልጽ ማብራሪያ ማካተት ይኖርበታል፡፡

(8.) ገበያው የማይመለስ የሥራ ማስኬጃ ክፍያ ስለመከፈሉ ማስረጃ ካልደረሰው ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክሲዮኖችን ግብይት ማመልከቻዎችን ማስተናገድ አይጀምርም፡፡

(9.) ገበያው በብቸኝነት የራሱ በሆነ ውሳኔ በየጊዜው አዳዲስ ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክሲዮኖችን አመዳደብ መለኪያዎች ወይም ዝቅተኛ ወለል መጠኖችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

(10.) ይህንን ደንብ መተላለፍ ገበያው በየጊዜው ለሚወስናቸው ቅጣቶች ይዳርጋል፡፡

7.11. የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከገበያው ውጪ መገበያየት ስለመከልከሉ

(1.) ማንኛውም በገበያው ተመዝግቦ የሚገኝ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከገበያው መገበያያ መድርኮች ውጪ መግዛት፣ መሸጥ ወይም ማስተላለፍ አይፈቀድም፡፡

(2.) አንድ የግብይት አባል ወይም አውጪ ይህንን ደንብ ሲጥስ ገበያው የጥሰቱን ክብደትና ድግግሞሽ ከግምት በማስገባት በየጊዜው የሚወስናቸው ቅጣቶች ይጣሉበታል፡፡

7.12. ከክፍያ ነጻ ማስተላለፍ

(1.) ማንኛውም ከክፍያ ነጻ በሆነ ማስተላለፍ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ለማስተላለፍ የሚፈልግ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለ ይዞታ በየግብይት አባሉ አማካኝነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ለማስተላለፍ እንዲፈቀድለት ለገበያው ማመልከቻ ያቀርባል፡፡ የግብይት አባሉ ተፈላጊውን የደንበኛን እወቅ የማጣራት ሥራ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለይዞታውና ሊተላለፍለት በታሰበው ሰው ላይ ያከናውናል፡፡

(2.) ገበያው በየግብይት አባሉ የቀረበውን ማመልከቻና ደጋፊ ሰነዶችን በመመርመር ለማስተላለፍ በፈለገውና ሊተላለፍለት በታሰበው ሰው መካከል ያለው ግንኙነት ግብይቱን የባለቤትነት ስም ዝውውር ተብሎ እንዲመደብ በቂ መሆን ወይም አለመሆኑን ይወስናል፡፡

(3.) ግብይቱን ከክፍያ ነጻ ማስተላለፍ ብሎ ለመመደብ ሲወስን፡-

(ሀ) በኩባንያዎች መካከል የሚደረግ ከክፍያ ነጻ ማስተላለፍን በሚመለከት አንደኛው ወገን በሌላኛው ላይ ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ ቁጥጥር ያለው መሆን ወይም አለመሆኑን ወይም ሁለቱም ወገኖች በተመሳሳይ ቁጥጥር ሥር መሆን ወይም አለመሆናቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ አንድ ወገን በሌላኛው ላይ ቁጥጥር አለው የሚባለው በሌላኛው ወገን ውስጥ

በቀጥታ ወይ በተዘዋዋሪ ከአምሳ በመቶ (50%) በላይ የሚሆኑትን ድምጽ የመስጠት መብቶችን፣ ጠቅላላ ገቢውን ወይም የወጣ የአክሲዮን ካፒታሉን ከያዘ ወይም ጥቅም በሚያስገኝ መንገድ የመያዝ መብት ካለው ነው፡፡ በኩባንያዎች መካከል ያሉ ትስስሮች በሚከተሉት ሳይወሰን የሚከትሉትን ያካትታሉ፡-

(i.) የሆልዲንግ ኩባንያዎች፣ ተቀጽላዎችና በአንድ የኩባንያዎች ቡድን ውስጥ ያሉ ተቀጽላዎች፤ እና

(ii.) የንግድ ማህበራት ጥምረት ና ለጥምረቱ ዓላማ የተፈጠረ ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም፡፡

(ለ) በግለሰቦች መካከል የሚደረግ ከክፍያ ነጻ ማስተላለፍን በሚመለከት የሚከተሉትን ግንኙነቶች ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል፡-

(i.) በአስተላላፊውና በሚተላለፍለት ሰው መካከል የትዳር አጋር፣ ወንድም፣ እህት፣ አባት፣ እናት፣ ልጅ ወይም የእንጀራ ልጅንና ሌሎችን ጨምሮ ቀጥተኛ የቤተሰብ ግንኙነት መኖር አለመኖሩን፤

(ii.) አስተላለፊው የማስተላለፍ ድርጊቱን የሚፈጽመው እንደ አስተዳደሪ፣ ጠባቂ፣ ወዘተ ወይም የማንኛውም ሟች ሰው ንብረት የሚያስተዳድር የግል ተወካይ መሆኑንና፤ አስተዳዳሪው፡-

1. የትዳር አጋርነትን፣ ወንድምነትን፣ እህትነትን፣ አባትነትን፣ እናትነትን፣ ልጅነትን ወይም የእንጀራ ልጅነትን ጨምሮ ከሟች ጋር ቤተሰባዊ ግንኙነት ያለውና ከእነዚህ ንብረቶች ጥቅም የሚያገኝ መሆን አለመሆኑን፤ ወይም

2. በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (3) (ለ)(ii.)1. መሠረት ተጠቃሚው ባለ አክሲዮን የሆነበት የሕግ ሰውነት ያለው አካል መሆኑን፤

3. የተሰየመበት ደንብ ለአስተዳዳሪው በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ 3.)(ለ)(ii.)1 መሠረት ለተጠቃሚው ጥቅም መዋል የሚችል ሥልጣን የሚሰጠው አስተዳዳሪ መሆኑን፡፡

(ሐ) በአንድ ግለሰብና በኩባንያ መካከል የሚደረግን ከክፍያ ነጻ ማስተላለፍ በሚመለከት ግለሰቡ የኩባንያው አክሲዮን ተጠቃሚ ባለይዞታ መሆን ወይም አለመሆኑን፡፡

(መ) ከግለሰብ የሚደረግ ማስተላለፍን በሚመለከት የአክሲዮኑ ባለቤት የትዳር አጋሩን ፈቃድ የሚገልጽ ሰነድ ወይም ከሲቪል ምዝገባ ባለሥልጣን የተሰጠ ያለገባ መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ ማቅረብ አለበት፡፡

የአክሲዮን ባለቤቱ የትዳር ሁኔታ ካልተቀየረ ይህ መግለጫ በየስድስት ወራቱ መታደስ አለበት፡፡

(4.) የግብይት ወገኖቹ ገበያው በየጊዜው የግብይቱን አፈጻጸም በሚመለከት የሚሰጣቸውን መመሪያዎች ማክበር አለባቸው፡፡

(5.) ገበያው ከክፍያ ነጻ ማስተላለፍ ማመልከቻ ጋር አብረው መቅረብ ያለባቸውን ሰነዶች በየጊዜው ይወስናል፡፡

(6.) ገበያው በየጊዜው የሚወስነውንና ይፋ የሚያደርገውን ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

(7.) ግብይቱ በገበያው ለመጽደቅ ብቁ በሚሆንበት ጊዜ የሚተላለፍለት ሰው ገበያው በሚወስነው ቅርጽ የካሳ ሰነድ ይፈርማል፡፡

(8.) ገበያው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እንዲተላለፉ የሚሰጠው ፈቃድ በባለሥልጣኑ መጽደቅ አለበት፡፡

## 7.13. የብድር ሽያጭ መፈጸም

(1.) ባለቤት ያልሆኑበት አክሲዮን ሽያጭ መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡ ማንኛውም ባለቤት ያልሆነበትን አክሲዮን የሸጠ የግብይት አባል በአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ ውስጥ የተቀመጡት ቅጣቶች የሚጣሉበት ይሆናል፡፡

(2.) አንድ የተመዘገበ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መጨረሻ ከተሸጠበት ዋጋ ባነሰ ዋጋ ሊሸጥ ይችላል፡፡ የብድር ሽያጭ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎችና መመዘኛዎች ባለሥልጣኑ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በገበያው የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

## 7.14. ግብይት ማስቆም

(1.) ፍትሐዊና የተረጋጋ ገበያ መኖሩን ለማረጋገጥ ወይም ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ ወይም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በተጨባጭ ወይም ሊደርስ በሚችል አካላዊ አደጋ፣ ሕዝባዊ ዐመጽ፣ ሽብር፣ የጦርነት ድርጊቶች ወይም የመገልገያዎች ዕጦት ወይም መቆራረጥ ወይም ተመሳሳይ ሁኔታዎች ውስጥ ገበያው፦

(ሀ) በገበያው ላይ ግብይት በሚደረግበት/ባቸው አንድ፣ አንዳንድ ወይም ሁሉም ሰነዶች ላይ የሚደረግን ግብይት ሊያስቆም ወይም ሊያግድ፤

(ለ) አንዳንድ ወይም ሁሉንም የገበያውን መገልገያዎች መዝጋት፤ እና/ወይም

(ሐ) ግብይቱ ቆሞ፣ ታግዶ ወይም ተዘግቶ የሚቆይበትን ጊዜ ርዝመት ሊወስን ይችላል፡፡

(2.) ገበያው እንደ አስፈላጊነቱ ወዲያውኑ ግብይት እንዲቆም ሊወስንና ይህንኑ ለባለሥልጣኑ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

(3.) ገበያው በየጊዜው በሁሉም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ግብይት የሚቆምባቸውንና መልሶ የሚከፈትባቸውን ሁኔታዎችና አሠራሮች ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡ የሚከተሉት ሁኔታዎች ግብይት እንዲቆም ሊያስገድዱ ይችላሉ፦

(ሀ) ከፍተኛ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የዋጋ መዋዠቅ::

(ለ) በእንጥልጥል ያለ ወሳኝነት ያለው ዜና ወይም መረጃ ሲኖር::

(ሐ) ኩባንያዊ የመዋቅር ሽግሽግ ወይም ያልታሰቡ ኩነቶች ሲኖሩና የገበያ ተሳታፊዎች እነዚህን ለውጦች እስከሚያውቁበት ጊዜ ድረስ::

(መ) ዐበይት አጠራጣሪ የግብይት እንቅስቃሴዎችን ያስከተሉ የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ጥርጣሬዎች::

(ሠ) የቴክኒክ ብልሽቶች::

(ረ) ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋዎችን ጨምሮ ደንገተኛ አደጋዎች::

(ሰ) የምዝገባ መስፈርቶችን አለማክበርና ሌሎች ከኩባንያዎች ጋር የሚገናኙ ክስተቶች::

(ሸ) ከዐቅም በላይ የሆኑ ክስተቶችን ተከትሎ የመንግስት ተቋም የሚሰጠው መመሪያ::

(4.) ይህ ደንብ ገበያው በማንኛውም የራሱ ደንብ ወይም ፖሊሲ መሠረት በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ውስጥ የማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ/ዮች ግብይት ለማስቆም፣ ለማገድ ወይም ለጊዜው ለማስቆም ያለውን ሥልጣን እንደሚወስን ተደርጎ መተርጎም የለበትም፡፡

## 7.15. ገበያው በድንገተኛ ሁኔታዎች የራሱን ውሳኔዎች የማስተላለፍ ሥልጣን ያለው መሆኑ

ገበያው በራሱ አስተያየት፣ እሳት ወይም ሌላ ክስተት ወይም አደጋ፣ የኃይል ብልሽት፣ የግንኙነት መሣሪያዎች ብልሽት፣ የኮምፒውተር ብልሽት ወይም ተመሳሳይ ክስተቶችን ጨምሮ የግብይት ማዕከሉ ወይም የግብይት ሥርዓቱ ተግባራት ላይ የተደቀነ ስጋት ወይም በመከሰቱ ከባድና አስከፊ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል አደጋ እንዳለ ካመነ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያስባቸውን እርምጃዎች የመውሰድ ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡

## 7.16. ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

(1.) የትርፍ ድርሻ ክፍፍልን ስለማቋረጥ፡- አንድ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪ የትርፍ ድርሻዎች ምክረ-ሐሳብ ወይም መግለጫ ስለ መሰረዙ ይፋዊ መረጃ ሲደርሰው፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ከትርፍ ክፍያ ውጭ እንደሆነ የተገለጸበት ማንኛውም ማስታወቂያ ራስ ሰር በሆነ መልኩ ይሰረዛል እንዲሁም ዋጋ ቢስ እና ምንም

ውጤት የሌለው ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በእነዚህ ዓይነት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ የሚደረጉ ግብይቶች ከትርፍ ክፍያ ውጭ እንዳልተደረጉ ሆኖ የሚጠናቀቁ ሲሆን በዚህም መሠረት የተደረገ ማንኛውም ቅናሽ ተመላሽ ይደረጋል፡፡፡

(2.) ተመሳሳይ የግዢ እና ሽያጭ ትዕዛዞችን ማገበያየት፡- አንድ የግብይት አባል አንድን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በተመሳሳይ ዋጋ ለመግዛትና ለመሸጥ ትዕዛዝ ሲኖረው የግብይት አባሉ ወይም ተገበያዩ ትዕዛዞቹን በገበያው በዚያ የግብይት ቀን ባለው ከፍተኛ የግዢ ወይም የሽያጭ ዋጋ ወይም በዚያ ውስጥ ተመሳሳዮቹን ትዕዛዞች "እርስ በእርስ" ማገበያየት ይችላል፡፡

(3.) የዝቅተኛ ዋጋ ተመንና ለውጦች፡- በገበያው እንዲገበያዩ የተፈቀደላቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የግዢና የሽያጭ ጥያቄ የዝቅተኛ ዋጋ ለውጥ ተመን ገበያው በየጊዜው በሚወስነውና ለተገበያዮች በሚያሳውቀው የለውጥ ተመን መሠረት ይቀመጣል፡፡

(4.) ከፍተኛ መጠን ያላቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት፡- ገበያው በየጊዜው ከፍተኛ መጠን ያላቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ሊመርጥ እና ሊፈቅድ ይችላል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ትዕዛዞች ዝቅተኛውን የብዛት ገደቦችን፣ ተዛማጅ የማሳወቂያ መስፈርቶችን እና ሌሎች በግብይቱ በየጊዜው የተደነገጉት ሂደቶችን ማክበር አለባቸው፡፡

(5.) የትዕዛዝ ዋጋዎች፡- በግብይት ሥርዓቱ ላይ የተመዘገቡ ትዕዛዞች በሙሉ ዋጋቸው የቁጥጥርና የድለላ ክፍያዎችን የማያካትት ይሆናል፡፡

(6.) የአክሲዮን የመዝገብ ዋጋ፡- የአንድ አክሲዮን የመዝገብ ዋጋ ቢኖርም ማንኛውም የእያንዳንዱ በገበያው የተመዘገበ አክሲዮን ዋጋ በገበያው እንቅስቃሴ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሆኖም ማንኛውም አክሲዮን ገበያው በየጊዜው ከሚወስነው የዋጋ ወለል በታች ሊገበያይ አይችልም፡፡

(7.) የግብይት አሃድ፡- የገበያው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መገበያያ አሃድ አንድ (1) ነው፡
፡

(8.) የዋጋ ወለል፡- ገበያው አንድ የአክሲዮን አሃድ ከዚያ በታች ሊገበያይ የማይችልበትን ዝቅተኛ የዋጋ መጠን ሊወስን ይችላል፡፡

(9.) የግብይት ክፍለ ጊዜዎች፡- ገበያው፣ የተለያዩ የግብይት ክፍለ ጊዜዎችንና የሚኖራቸውን የቆይታ ጊዜ፣ መመዝገብ የሚፈቀዱ የትዕዛዝ ዓይነቶችንና የየግብይት ድርጊቶችን፣ የትዕዛዞች የወረፋ ቅድሚያ፣ የዋጋ ግኝት ዘዴዎችን እና የትዕዛዝ ማጣመር/አፈጻጸም ሁኔታዎችን (ጨረታዎችን) በየጊዜው ይወስናል፡፡

# ክፍል 4 - ቀጥተኛ የኤሌክትሮኒክ ተሳትፎ

## *ምዕራፍ 8 - ለደንበኞች ቀጥታ የኤሌክትሮኒክ ተሳትፎ የበይነ መረብና የዲጂታል ግብይት መድረክ ደንቦች*

### 8.1. የመሠረተ-ልማት መመዘኛዎች

(1.) እያንዳንዱ የበይነ መረብ የግብይት መድረክ ለማቋቋም የሚፈልግ የግብይት አባል ገበያው በሚፈቅደው መሠረት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

(ሀ) ለዚሁ የተለየና ደህንነቱ የተጠበቀ የኔትወርክ ግንኙነት፤ እና

(ለ) የትዕዛዝ አስተዳደር ሥርዓት፡፡

(2.) ማንኛውም የግብይት አባል በመደበኛነትና በማንኛውም ሁኔታ በዓመት ከሁለት ጊዜያት ለማያንስ ጊዜ የደህንነትና የተገዢነት ፍተሻ ሳያስደርግ የበይነ መረብ የግብይት መድረኩን በሥራ ላይ ማዋል አይችልም፡፡

(3.) የግብይት አባሉ በበይነ መረብ የግብይት መድረኩ ላይ የተደረገውን የእያንዳንዱን ፍተሻ ሪፖርት ለገበያው ማቅረብ አለበት፡፡ ገበያው በፍተሻ የተገኙ ችግሮች በፍጥነት መስተካከላቸውን ለማረጋገጥ በመደበኛነት የዘወትር ድንገተኛ ምርመራ ማድረግ አለበት፡፡

(4.) ደንበኞች ወደ ትዕዛዝ ማስተዳደሪያ ሥርዓቱ ለመግባት የሚጠቀሟቸው መተግበሪያዎች በጠንካራ የይለፍ ቃሎችና ከኢንዱስትሪ የጥራት ደረጃዎች ጋር በተጣጣሙ ጠንካራ ማረጋገጫዎች የተጠበቁ፣ ለአሠራርና ለመደበኛ የደህንነት ፍተሻ ምቹ የሆኑ መሆን አለባቸው፡፡

### 8.2. ደንበኞችን የማስተዋወቅና የደንበኛን እወቅ መመዘኛዎች

(1.) ማንኛውም የበይነ መረብ የግብይት መድረክ በሥራ ላይ ማዋል የሚፈልግ የግብይት አባል፦

(ሀ) የተሳትፎ መብት ለማግኘት ብቁ የሆኑ ሰዎች የሚለዩባቸውን ተገቢ መስፈርቶች ማስቀመጥ፤

(ለ) እነዚህ የብቁነት መስፈርቶች፣ የኢንቨስተር ጥበቃ ግዴታዎችን ተፈጻሚ ለማድረግ ሲባል ብቁ የሆኑት ሰዎች መደበኛ ኢንቨስተሮች፣ ተቋማዊ ተሳታፊዎች ወይም ብቁ ኢንቨስተሮች መሆናቸውን ታሳቢ ማድረግ አለባቸው፤

(ሐ) የበይነ መረብ የግብይት ሒሳቡ ሥራ ከመጀመሩ በፊት እና በመድረኩ ማንኛውም ግብይት ከመፈፀሙ በፊት በበይነ መረብ የግብይት መድረኩ

በኩል በተመዘገቡ ደንበኞች ሁሉ ላይ አጠቃላይ ደንበኛን እወቅ ማጣሪያዎችን ማከናወን፡፡

(2.) የግብይት አባሉ የደንበኛ እወቅ ማህደሮችና ማናቸውንም ተዛማጅ ማህደሮች ቢያንስ ለአሥር (10) ዓመታት መያዝ አለበት፡፡

## 8.3. የስጋት አስተዳደርና የበላይ ቁጥጥር

(1.) አንድ የግብይት አባል የበይነ መረብ የግብይት መድረኩን ከማቋቋሙና ከማንቀሳቀሱ በፊት፦

(ሀ) የሚከተሉትን የሚያካትቱ ጠንካራ የስጋት አስተዳደርና የመረጃ ደህንነት ደረጃዎችን መዘርጋትና በሥራ ላይ ማዋል አለበት፡-

(i.) የተለያዩ ማረጋገጫዎች፤

(ii.) ሚስጢራዊነት፤

(iii.) ደህንነቱ የተጠበቀ ሃይፐርቴክስት ትራንስፈር ፕሮቶኮል (HTTPS)

(iv.) የተራዘመ ማረጋገጫ፤

(v.) የበይነ መረብ የግብይት መድረኮቻቸውን ከማጭበርበር፣ ከሳይበር ወንጀልና ሌሎች በድርጅታቸውና በደንበኞቻቸው ላይ ከሚደቀኑ ስጋቶች የሚከላከሉና እነዚህን የሚቀንሱ ፖሊሲዎችንና አሠራሮችን፤ እና

(vi.) ገበያው በየጊዜው የሚያስቀምጣቸው ሌሎች የደህንነት ስታንዳርዶች፡፡

(ለ) የበይነ መረብ የግብይት መድረኩንና ከእርሱ ጋር የተያያዙትን መተግበሪያዎች ጨምሮ በሁሉም ቁልፍ መተግበሪያዎቻቸው ላይ የለውጥ አስተዳደር ቁጥጥር መዘርጋት፤

(ሐ) የከፍተኛ ደረጃ የደኅንነት ቅድመ ጥንቃቄዎችን መዘርጋትና የክላውድ መፍትሔ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ጠንካራ የማረጋገጫ፣ የፈቃድና የመግቢያ ቁጥጥሮች መኖራቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ለገበያው ማቅረብ፤ እና

(መ) የበይነ መረብ የግብይት መድረክ ለማንቀሳቀስ ከገበያው የሚሰጥ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት፡፡

(2.) ደንበኛው ያስገባቸውን የገበያ ትዕዛዞች ማስጀመር፣ ማስረከብ፣ መለወጥ ወይም መቀየርን ጨምሮ የበይነ መረብ የግብይት መድረኩ የሚፈቅዳቸውን ከግብይት አባሉ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን የራሱንና ለሌሎች ተላልፎ ሊሰጥ የማይችለውን የይለፍ ቃል በመጠቀም ወደ በይነ መረቡ የግብይት መድረክ መግባት የሚችለው በበይነ መረብ የግብይት መድረኩ በኩል ለመገበያየት በየግብይት አባሉ ዘንድ በአግባቡ የተመዘገበ የግብይት አባሉ ደንበኛ ብቻ ነው፡፡

(3.) የበይነ መረብ የግብይት መድረክ የሚያንቀሳቅሱ የግብይት አባላት፡-

(ሀ) በበይነ መረብ ግብይት መድረኮቻቸው በኩል እንዲሁም በሒሳብ መክፈቻ ማመልከቻዎቻቸው ላይ የበይነ መረብ ግብይት መድረኩን ከመጠቀም ጋር የሚገናኙ ስጋቶችን መግለጽ፤

(ለ) በበይነ መረብ የግብይት መድረክ ከተፈጸሙ ግብይቶች የተገኙ ኮሚሽኖችን ከሌሎች የግብይት አባላትና ገበያው በየጊዜው ከሚወስናቸው ሌሎች የተመዘገቡ የገበያ አንቀሳቃሾች ውጪ ለሌሎች አለማጋራት፤

(ሐ) በበይነ መረብ መገበያያ መድረኩ ላይ የበይነ መረብ የግብይት መድረኩን ከመጠቀም ጋር የሚያያዙ ክፍያዎችና ወጪዎችን (ካሉ) እንዲሁም የደንበኞ አገልግሎትና የቅሬታ አፈታት ሥነ-ሥርዓት ዝርዝሮችን በበይነ መረብ የግብይት መድረኩ ላይ በግልጽ እንዲታዩ ማድረግ፤

(መ) ወደ ደንበኞች እና ከደንበኞች የሚተላለፍ የፋይናንስ መረጃ መኖሩን፣ ወጥነቱን፣ በምስጢር የሚያዝና ደኅንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ምክንያታዊ ቅድመ-ጥንቃቄዎችን በሙሉ ማድረግ፤

(ሠ) በየግብይት አባሉ በምክረ-ሐሳብነት ለሚቀርቡ ኢንቨስትመንቶች ደንበኞች ያላቸውን የፋይናንስ ዕውቀት እና ተስማሚነት ሲወስኑ ጥንቃቄ ማድረግ፤

(ረ) የግብይት አባላት ለሐሰተኛ ግብይቶች፣ በወንጀል የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ፣ ተገቢ ላልሆነ የገበያ አጠቃቀም ወይም ለማንኛውም ሕገ-ወጥ ዓላማ ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሆነ በሚያውቁበት ጊዜ የደንበኛውን ሒሳብ ማገድ ወይም መዝጋትና ይህን እርምጃ በወሰዱ በሃያ አራት (24) ሰዓታት ውስጥ ስለ ሒሳቡ መታገድ ወይም መዘጋት ለገበያው ማሳወቅ አለባቸው፡፡

(4.) የግብይት አባላት የበይነ መረብ የግብይት መድረኮቻቸውን ሲያንቀሳቅሱ ግንኙነት፣ ማስታወቂያንና ይፋ ማድረግን የሚመለከቱትን ጨምሮ ሁሉንም የገበያውን ደንብና መመሪያዎች ማክበር አለባቸው፡፡

(5.) የግብይት አባላት ቀጥተኛ ኤሌክትሮኒክ የገበያ ተሳትፎን በመጠቀም ለተፈጸሙ ትዕዛዞችና ግብይቶች ኃላፊነት አለባቸው፡፡

(6.) የግብይት አባላት ከደንበኞቻቸው ጋር ሕጋዊና አስገዳጅነት ያለው የቀጥተኛ ኤሌክትሮኒክ ተሳትፎ አቅርቦት ውል ሊኖራቸው ይገባል፡፡

(7.) አንድ የግብይት አባል ለእነዚህ ደንቦች ድንጋጌዎች ተገዢ ካልሆነ ገበያው የግብይት አባሉ የሚያቀርበውን ቀጥተኛ የኤሌክትሮኒክ ተሳትፎ ሊያግድ ወይም ሊያቋርጥበት ይችላል፡፡

(8.) በበይነ መረብ የግብይት መድረኩ ላይ የሚደረጉ የግብይት እንቅስቃሴዎች በሙሉ የግብይት አባሉ ሠራተኛ በሆነ የግብይት ፈፃሚ በአግባቡ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

(9.) በየግብይት አባሉ የበይነ መረብ የግብይት መድረክ በኩል የደህንነት ጥሰት ከተከሰተና ጥሰቱም ገበያውን ለስጋት የሚያጋልጥ ከሆነ ገበያው በብቸኝነት የራሱ በሆነ የመወሰን ሥልጣን የግብይት አባሉ የበይነ መረብ የግብይት መድረኩን እንዲዘጋ ወይም በበይነ መረብ የግብይት መድረኩና በገበያው የግብይት መገልገያዎች እና/ወይም ሌሎች መገልገያዎች መካከል ያለውን ኤሌክትሮኒክ ትስስር ማቋረጥን ጨምሮ ገበያው በራሱ የመወሰን ሥልጣን የሚወስናቸውን ሌሎች አግባብነት ያላቸው እርምጃዎችን እንዲወስድ መመሪያ ሊሰጠው ይችላል፡ ፡

## 8.4. ለገበያው መረጃ የመስጠት ግዴታ

(1.) ገበያው በማንኛውም ጊዜ ለአንድ የግብይት አባል ስለ በይነ መረብ የግብይት መድረኩና ከዚሁ ጋር ተያይዘው ስላሉ አሠራሮች መረጃ እንዲሰጠው ጥያቄ ባቀረበለት በሁለት (2) የሥራ ቀናት ውስጥ መረጃውን መስጠት አለበት፡፡

(2.) የየግብይት አባሉ የሕግ ተገዢነት መኮንን ገበያው ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ መልሶችን መስጠትን ጨምሮ ከበይነ መረብ ግብይት መድረኩ አሠራሮች ጋር ለሚገናኙ ጉዳዮች ሁሉ ኃላፊነት አለበት፡፡

# ክፍል 5 - ለግብይቶች ክፍያ መፈጸም

## ምዕራፍ 9 - ክፍያ ማጣራትና መፈጸም

### 9.1. ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችንና ከግብይቱ የተገኘውን ገንዘብ ርክክብና ክፍያ መፈጸም

(1.) ርክክብና ክፍያ መፈጸም ገበያው በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳና መሠረት ይከናወናል፡ ፡

(2.) አንድ ኢንቨስተር በአንድ አውጪ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚገበያየው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የግብይት አባሉ የኢንቨስተሩን የጋብቻ ሁኔታ፣ የባዮሜትሪክ መረጃ እና የባንክ ዝርዝሮች ጨምሮ የኢንቨስተሩን መረጃ በገበያው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም የዚሁ አቻ ላይ ገበያው በሚያስቀመጠው ጊዜ መሰረት ግብይቱን ለማረጋገጥ ያዘምነዋል፡፡

(3.) ከእያንዳንዱ ግብይት የሚገኘው ገንዘብ ከገበያው የግብይት ሥርዓት ለኢንቨስተሩ የሚከፈለው ወደ ደንበኛው ወይም ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ወይም አቻው ወዳስቀመጠው ሒሳብ በሚደረግ ቀጥተኛ ክፍያ አማካኝነት ነው፡፡

(4.) ከላይ የተደነገገው ቢኖርም፡-

(ሀ) የሒሳብ ዝርዝራቸው ለገበያው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት ወይም ለአቻው ያልቀረበ ማንኛውም ደንበኛን ወክሎ የሚከናወን የግብይት ክፍያን በተመለከተ ክፍያው የሚፈፀመው በደንበኛው የግብይት አባል ሒሳብ በኩል ይሆናል፡፡

(ለ) አንድ ደንበኛ ከሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሽያጭ በሚገኝ ገንዘብ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እንዲገዛ ለግብይት አባሉ በጽሁፍ መመሪያ ከሰጠ፤ ከሽያጩ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ክፍያ የሚፈጸመው ደንበኛው ፈቃዱን በሰጠበት ሁኔታ፣ በንግድ አባሉ ሂሳብ በኩል ይሆናል፡፡

(5.) አንድ የግብይት አባል ለደንበኛው ክፍያ የሚፈጸመው ወደዚሁ ደንበኛ ሒሳብ በሚደረግ ቀጥተኛ ክፍያ ስለመሆኑ ከደንበኛው መመሪያ በደረሰው በሦስት (3) የሥራ ቀናት ወይም ገበያው ባጸደቀው ጊዜ ውስጥ፡-

(ሀ) ለገበያው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት ወይም ለአቻው የደንበኛውን መመሪያ ማሳወቅ፤ እና

(ለ) የደንበኛውን ሒሳብ መረጃዎች መስጠት አለበት፡፡

(6.) ማንኛውም፡-

(ሀ) ከደንበኛው መመሪያ ሳይቀበል በደንበኛው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚገበያይ፤ ወይም

(ለ) ከደንበኛው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የተገኘውን ገንዘብ በሦስት (3) የሥራ ቀናት ወይም ገበያው ባጸደቀው ጊዜ ውስጥ ለደንበኛው የማይከፍል

የግብይት አባል ገበያው ከሚጥላቸው ሌሎች ቅጣቶች በተጨማሪ ያልተፈቀደ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሽያጭን በሚመለከት በዚህ ደንብ ውስጥ የተቀመጡት ቅጣቶች ይጣሉበታል፡፡

(7.) እያንዳንዱ የግብይት አባል የግብይት ክፍያ አፈጻጸም ዝርዝሮች ከደንበኛው ከራሱ የመነጩ መሆናቸውንና በዚህ ደንብ ውስጥ የሚገኙ የደንበኛን ማወቅ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ሁሉንም ምክንያታዊ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

(8.) ርክክብ ከዘገየ ገዢው ሊያገኛቸው የሚችላቸው ጥቅሞችን በተመለከተ ሻጩ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 9.2. የማስተላለፊያ ሰነዶችን ማስረከብ

የባለቤትነት ማረጋገጫዎችና ዋጋ ያላቸው የማስተላለፊያ ሰነዶች ርክክብ ገበያው በየጊዜው በሚያስቀምጠው መንገድ መከናወን አለበት፡፡

## 9.3. ያልተሳካን ግብይት የማሳወቅ ግዴታ

(1.) ገዢ የግብይት አባል በቀኑ ክፍያ ካልፈጸመ ወይም ሻጭ የግብይት አባል በቀኑ ካላስረከበ ግዴታውን የተወጣው ወገን ያኛው ወገን ግዴታውን ስላለመወጣቱ እንዳወቀ ወዲያውኑ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡፡

(2.) ማንኛውም ግብይት ሊፈጸምባቸው ከሚችሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተያያዘ እንደተፈጻሚነታቸው ለእነዚህ ደንቦች ተገዢ የማይሆን የግብይት አባል በገበያው የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## 9.4. ጉድለት ያለበት ዝውውር

(1.) ጉድለት ያለበት ዝውውር፣ አስተላላፊው ለተቀባዩ አስተላልፌለታለሁ ያላቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አግባብነት ባለው(ላቸው) የማስተላለፊያ ሰነድ(ዶች) ላይ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ የባለቤትነት ሰነዶች ላይ ያለውን ጉድለት ጨምሮ የሚተላለፍለት ሰው በራሱ ጥፋት ባልሆነ ምክንያት ትክክለኛ የባለቤትነት መብት የሌለው የሚሆንባቸውን ሁነቶችን ያካትታል፡፡

(2.) እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ሲከሰቱ ሻጩ የግብይት አባል ስለዝውውሩ ከጉድለት ተቀባዩ ወይም ከገበያው ባወቀ በአምስት (5) የግብይት ቀናት ውስጥ ጉድለት ያለበትን ዝውውር ለማስተካከል አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ

አለበት፡፡ በተጨማሪም ሻጬ የግብይት አባል ጉድለት ባለበት ዝውውር ምክንያት ተቀባዩ ያጋጠመውን ማንኛውንም ኪሳራ ጨምሮ ለማንኛውምና ለሁሉም ወጪዎችና ኪሳራዎች ኃላፊ ነው፡፡

# ክፍል 6 - የግብይት ሥነ ምግባር

## *የግብይት አባላት ሥነ ምግባር*

### 10.1. አጠቃላይ ሥነ ምግባር

(1.) እያንዳንዱ የግብይት አባል ለራሱ፣ ለሌላ የግብይት አባል ወይም ለደንበኛው የሚያናውነውን ሥራ ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ፍትሐዊና ርቱዕ በሆነ መንገድ ማከናወን አለበት፡፡

(2.) አንድ የግብይት አባል ግብይት ፈፃሚዎቹ፣ ሌሎች ተሿሚ እንደራሴዎቹ፣ ሰራተኞቹና ሌሎች ባልደረባዎቹ ለደንበኞች የላቀ ጥቅም መሥራታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(3.) ሁሉም የግብይት አባላት ቦርዱና ቦርዱ ያጸደቃቸው ሌሎች ሰዎች ወይም አካላት በእነዚህ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሥልጣናቸውን ሕጋዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም ያሳለፏቸውን ሁሉንም ውሳኔዎች፣ ትዕዛዞች እና መመሪያዎች ማክበር አለባቸው፡፡

(4.) ገበያው የተረጋጠ ሞያዊ የሥነ ምግባር ጉድለትንበፍጹም የማይታገስ ፖሊሲ ይኖረዋል፡፡፡ የግብይት አባላት የገበያውንም ሆነ የማንኛውንም የግብይት አባል መልካም ስም ሊያጎድፍ ከሚችል ድርጊት ወይም አካሄድ መቆጠብ አለባቸው፡፡

(5.) ማንኛውም የግብይት አባል የገበያውን መልካም ስም ወይም ገጽታ የሚያበላሽ ድርጊት፣ ሁኔታ ወይም ነገር መፈጸም ወይም እንዲፈጸም ማድረግ የለበትም፡፡

(6.) በገበያው ላይ የሚደረጉ ተግባራትን በሚመለከት አንድ የግብይት አባል የሽርክና፣ የውክልና ወይም የትርፍ መጋራት ስምምነት መፈጸም የሚችለው ከሌላ የግብይት አባል ከሆነ የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት ካለው ሰው እና ገበያው በየጊዜው በሚወስነው መሠረት ፈቃድ ካላቸው ሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ብቻ ነው፡፡

(7.) ማንኛውም የእነዚህን ደንቦች ድንጋጌዎች የሚተላለፍ የግብይት አባል የገንዘብ ቅጣትን ጨምሮ ገበያው ለሚጥላቸው ቅጣቶች ኃላፊ ይሆናል፡፡

### 10.2. ለገበያው ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

(1.) የግብይት አባላት ገበያው የተወሰኑ ግብይቶችን በሚመለከት በየጊዜው ለሚያወጣቸው የሪፖርት ማቅረብ እና/ወይም ሌሎች ግዴታዎች ተገዢ መሆን አለባቸው።

(2.) አንድ የግብይት አባል ራሱ ወይም እንደየሁኔታው ማንኛውም ተሿሚ እንደራሴው ወይም ሌላ ሠራተኛው የሚከተሉትን ከፈፀሙ ለገበያው ወዲያውኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፦

(ሀ) ማንኛውንም የአዋጁን፣ የእነዚህን ደንቦች፣ የማንኛውንም ሌላ ገበያ ደንቦች ወይም የየግብይት አባሉን እንቅስቃሴዎች የሚገዙ ተፈጻሚነት ያላቸው የአገር ውስጥም ሆኑ የውጪ ሕጎች ድንጋጌዎችን ከጣሰ፤

(ለ) ማንኛውንም ድንጋጌ ከጣሰ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ውጪ ማጭበርበርን ወይም ማታለልን በሚመለከት የጽሑፍ ቅሬታ ከቀረበበት ወይም ምርመራ እየተደረገበት ከሆነ፤

(ሐ) ዕገዳን፣ መሰናበትን፣ የጥቅም ማቆየትን፣ መቀጮን ወይም ማንኛውም ሌላ ከፍተኛ የእንቅስቃሴ ገደብን የሚያደርግ የዲሲፕሊን እርምጃ በየግብይት አባል ከተወሰደበት፤

(መ) አዋጁን፣ ተፈጻሚነት ያላቸውን ሌሎች ሕጎችንና የቁጥጥር መመዘኛዎችን በአቋራጭ በሚያልፍና ከመልካም የንግድ ሥራ አፈጻጸም መርሖች ጋር የማይጣጣም ተግባር ከፈጸመ፤

(ሠ) የገበያው ተአማኒነት፣ መልካም ስም ወይም ጥቅሞች የሚጎዳ ተግባር ከፈጸመ እና

(ረ) ከከሰረ ወይም በፍርድ ቤት የክስረት ወይም መዝጋት ሥነ-ሥርዓት ሥር ከሆነ

(3.) ከላይ ከተጠቀሱት ሁነቶች መካከል ማንኛቸውም ወይም ከእነዚህ ጋር የሚገናኙ ኩነቶች ሲከሰቱ ወይም የመከሰታቸው ስጋት ሲኖር በዚህ ደንብ ውስጥ የተቀመጠው የማሳወቅ ግዴታ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

### 10.3. ወደ ግብይት ማዕከል መግባትና ቁጥጥሮች

(1.) ማንኛውም የግብይት ፈፃሚ ወይም ተለማማጅ የግብይት ፈፃሚ የሚከተሉትን ካላሟላ ወደግብይት ማዕከሉ መግባት አይችልም፦

(ሀ) ገበያው በሚያስቀምጠው መመሪያ መሠረት የግብይት ማዕከል መለያ ልብስ ወይም ይፋዊ የግብይት ማዕከል አልባሳትን ካላገኘ፤ እና

(ለ) ገበያው ወደገበያው ማዕከል መግባትን የመከልከል ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ክፍያዎችን ጨምሮ ሌሎች መመዘኛዎችን በማሟላት ከገበያው የግብይት ማዕከል መታወቂያና የመግቢያ መቆጣጠሪያ ካርድ እንዲሰጠው አመልክቶ እነዚሁ ካልተሰጡት፡፡

(2.) እያንዳንዱ የግብይት ፈጻሚና ተለማማጅ የግብይት ፈጻሚ በሁሉም ጊዜ በግብይት ማዕከሉ ወይም ገበያው በሚያስቀምጣቸው ሌሎች ሥፍራዎች፡-

(ሀ) ገበያው በሚያስቀምጠው መሠረት የግብይት ማዕከል መለያ ልብስ ወይም ይፋዊ የግብይት ማዕከል አልባሳትን መልበስ፤

(ለ) ገበያው በሚያስቀምጠው ቦታ ላይ በግብይት ማዕከል መለያ ልብሱ ወይም ይፋዊ አልባሳቱ ላይ በማንኛውም ጊዜ ማንነቱን የሚገልጽ የግብይት ማዕከል መታወቂያ ማድረግ፤ እና

(ሐ) የመግቢያ መቆጣጠሪያ ካርዱንና ሌሎች የመግቢያ መሣሪያዎችን መያዝ፡፡

(3.) ማንኛውም የአለባበስ ገጽታው ከዚህ ደንብ ወይም ከሌሎች ገበያው ከሚያወጣቸው ድንጋጌዎች ተቃራኒ የሆነ የግብይት ፈፃሚ ወይም ተለማማጅ የግብይት ፈፃሚ ከገበያው ማዕከል ወይም ከሌሎች ልዩ ቦታዎች እንዲወጣ ይደረጋል፤ ገበያው የሚያስቀምጣቸው ሌሎች ቅጣቶችም ይጣሉበታል፡፡

(4.) ማንኛውም የግብይት ፈፃሚ ወይም ተለማማጅ የግብይት ፈፃሚ ተገቢው የመግቢያ መብት ሳይኖረው ወደ ገበያው የግብይት ማዕከላት ወይም ወደ ልዩ ሥፍራዎች ወይም የግብይት ሥርዓት መግባት አይፈቀድለትም፡፡

(5.) ማንኛውም የመግቢያ መቆጣጠሪያ ካርድ ሳይዝ ወይም የሌላን የግብይት ወይም ተለማማጅ የግብይት የመግቢያ መቆጣጠሪያ ካርድ በመያዝ ወደ ግብይት ማዕከሉ ለመግባት ወይም ከግብይት ማዕከሉ ለመውጣት ሲሞክር የተገኘ የግብይት ፈፃሚ ወይም ተለማማጅ የግብይት ፈፃሚ ለሁለት (2) ሳምንታት ወደ ግብይት መድረኩ እንዳይገባ ይታገዳል፤ ገበያው በሚያስቀምጠው መሠረት ሌሎች ቅጣቶችም ይጣሉበታል፡፡

(6.) ማንኛውም የሌላ የግብይት ፈፃሚ ወይም ተለማማጅ የግብይትን ፈፃሚ መታወቂያ በመልበስና ሌላ የግብይት ፈፃሚ ወይም ተለማማጅ የግብይትን ፈፃሚ መስሎ በመቅረብ ወደ ግብይት ማዕከሉ የገባ ወይም ለመግባት የሞከረ ወይም የመግቢያ መቆጣጠሪያ ካርዳቸውን ተጠቅሞ ወደ ግብይት ማዕከሉ የገባ ወይም ከማዕከሉ የወጣ ወይም ለመግባት ወይም ለመውጣት የሞከረ የግብይት ፈፃሚ ወይም ተለማማጅ የግብይት ፈፃሚ ለሁለት (2) ሳምንታት ወደ ግብይት መድረኩ እንዳይገባ ተደርጎ የገንዘብ መቀጮዎችን ጨምሮ በገበያው የሚቀመጡ ሌሎች ቅጣቶች ይጣሉበታል፡፡

(7.) ማንኛውም ከግብይት ማዕከሉ የታገደ የግብይት ፈፃሚ ወይም ተለማማጅ የግብይት ፈፃሚ የግብይት ማዕከል መታወቂያውንና የመግቢያ መቆጣጠሪያ ካርዱን ወዲያውኑ ለገበያው መመለስ አለበት፡፡ ዕገዳው እስኪነሳለት እና ወደ ግብይት ማዕከሉ ተመልሶ ተቀባይነት እስኪያገኝ ድረስ የግብይት ማዕከል መታወቂየው ይሰረዛል፣ ወደ ግብይት መድረኩ እንዳይገባ ይደረጋል፤ የመግቢያ መቆጣጠሪያ ካርዶቹም ከአገልግሎት ውጪ ይደረጋሉ፡፡

(8.) የግብይት ማዕከል መታወቂያዎችና የመግቢያ መቆጣጠሪያ ካርዶች የገበያው ንብረት በመሆናቸው ከሚከተሉት ኩነቶች መካከል ማንኛውም ሲከሰት ለገበያው መመለስ አለባቸው፦

(ሀ) መታገድ፤

(ለ) የግብይት ፈፃሚ ምዝገባ ስረዛ፤

(ሐ) ገደብ መጣል፤

(መ) የግብይት አባልነት ምስክር ወረቀት ሲመለስ፤ እና

(ሠ) የአባልነት ምስክር ወረቀት መሰረዝ፡፡

10.4. የግብይት ማዕከል ሥነ ምግባር

(1.) የግብይት ፈፃሚዎችና የተፈቀደላቸው ሰዎች በማንኛውም ጊዜ ተገቢውን ሥነ-ሥርዓት ማንጸባረቅ አለባቸው፡፡

(2.) ትምባሆ ማጤስ፣ ጨዋታዎችን መጫወት፣ ቁማር ወይም ገበያው ጥቅሞቹን እንደሚጎዳበት የሚያስበው ማንኛውንም ተግባር ማድረግ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

(3.) መጠጣትና መመገብ የሚቻለው በተለዩ ሥፍራዎች ብቻ ነው፡፡

(4.) አግባብነት ያለው የቦርዱ ኮሚቴ ወይም ቦርዱ የወከለው አካል የግብይት ፈፃሚው ይህንን ደንብ መጣሱን ሲደርስበት፦

(ሀ) የግብይት ፈፃሚው አሠሪ የሆነው የግብይት አባል በሌሎች የግብይት ፈፃሚዎች፣ የተፈቀደላቸው ሰዎች ወይም የገበያው ሠራተኞች ወይም በንብረታቸው ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳና ቦርዱ ወይም ቦርዱ የወከለው አካል በምክረ-ሐሳብነት የሚያቀርበውን የገንዘብ መቀጮ ይከፍላል፡፡

(ለ) ገበያው ጥፋቱን በፈጸመው የግብይት ፈፃሚው ወይም የተፈቀደለት ሰው ላይ ተገቢውን ቅጣት ሊጥል ይችላል፡፡

10.5. በግብይት ማከናወኛ ቦታዎችና መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ጥንቃቄ

(1.) በየግብይት አባሉ ክፍል ውስጥ በሚገኙ የግብይት ማከናወኛ ጣቢያዎች፣ የሥራ ቦታዎችና ሌሎች መሣሪያዎች ሲገለገሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የእያንዳንዱ የግብይት ፈፃሚ ግዴታ ነው።

(2.) ማንኛውም የየግብይት አባል የግብይት ፈፃሚ ወይም ሌላ የየግብይት አባሉ ሠራተኛ በመሣሪያ ወይም መገልገያ ወይም ማንኛውም ሌላ ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው የግብይት አባሉ ነው።

(3.) ጉዳቱ የደረሰው በቸልተኝነት ከሆነ ገበያው ተገቢ መስሎ የታየውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

(4.) የግብይት አባላት ለግብይት ማከናወኛ ቦታዎቻቸውና ሌሎች የግብይት ሥርዓት ደጋፊ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ለይፋዊ መሸኛ ደብዳቤዎች እና ሌሎች የምስጢርና ከፍተኛ ዋጋ ላላቸው ሰነዶቻቸው በቂ ጥበቃና ቁጥጥር ያለበት የመግቢያ ሥርዓት ማስቀመጥ አለባቸው።

(5.) ሁለት (2) ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የገበያ አባላት የሥራ ቦታ የሚጋሩ ከሆነ ወይም የገበያ አባሉ ድርጅት የሌላ ድርጅት አካል ከሆነ አሠራሮቻቸውና የቢሮዎቻቸው አቀማመጥ የሁለቱን ድርጅቶች ኃላፊነቶች በግልጽ የሚያስቀምጡና የሚያሳዩ መሆን አለባቸው።

10.6. ጆሮ ጠብ እና ከደንበኞች ቀድሞ ግብይት መፈጸም

(1.) የግብይት አባላት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የዋጋ ለውጥ ሊያስከትሉ የሚችሉ የደንበኞች ትዕዛዞችን ለራሳቸው ጥቅም ማዋል የለባቸውም፣ እንዲሁም የግብይት አባላት ደንበኞቹ ትዕዛዛቸውን ከማስፈጸማቸው በፊት በተመሳሳይ አቅጣጫ መገበያየት የለባቸውም፤ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ግብይት የግብይት አባላት ከደንበኞቻቸው ጥቅም እንዲያገኙ እና በህገ-ወጥ መንገድ በመነገድ እንዲጠቀሙ ሊያስችሏቸው ይችላሉ።

(2.) የግብይት አባላት ትዕዛዞች ከመፈጸማቸው በፊት በዚሁ አቅጣጫ ለሌሎች ግብይቶችን መፈጸም ወይም ግብይት እንዲፈጽሙ ሐሳብ መስጠት አይፈቀድላቸውም።

10.7. የገበያ ማጭበርበር እና የሕገ ወጥ የገበያ ስምምነቶች ክልከላ

(1.) ማንኛውም የግብይት አባል የሚከተሉትን መፈፀም የለበትም፦

(ሀ) ለራሱ ጥቅምም ሆነ ሌላን ሰው በመወከል በገበያው ላይ በተመዘገበ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተጭበረበረ የግብይት ልማድ

መጠቀም ወይም እያወቀ ሽፍጠኛ፣ ተገቢ ባልሆነ፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች በሆነ መንገድ የሚከተሉትን የሚያስከስት የግብይት ሥራ ውስጥ መሳተፍ፤

(i.) ከሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ጋር በተገናኘ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች የሚመስል የግብይት እንቅስቃሴ፤ ወይም

(ii.) ለሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ሰው-ሰራሽ ዋጋ እንዲፈጠር የሚያደርግ ።

(ለ) እስከሚያውቀው ድረስ ቢፈጸም በዚህ ደንብ ንዑስ-ደንብ (1) (ሀ) የታሰበው ውጤት የሚኖረውን የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዢ ወይም ሽያጭ ትዕዛዝ ማስተላለፍ።

(2.) ከላይ ከተቀመጠው በተጨማሪ የሚከተሉት የሚያጭበረብሩ፣ ተገቢ ያልሆኑ፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች የግብይት ልማዶች ሆነው ይቆጠራሉ፦

(ሀ) በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ በሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የጥቅም ባለቤትነት ላይ ምንም ለውጥ የሌለውን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግዢ ወይም ሽያጭ ትዕዛዝ ማጽደቅ ወይም ማስገባት፤

(ለ) የሚከተሉትን ለመፍጠር በማሰብ በተመሳሳይ ወይም የተለያዩ ሰዎች የተሰጠና በተመሳሳይ ጊዜ፣ በተመሳሳይ መጠንና በተመሳሳይ ዋጋ የተሰጠ ተቃራኒ ትእዛዝ ወይም ትዕዛዞች እንዳሉ እያወቀ በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ የሚገበይ ሰነደ ሙዓለ ንዋይን የግዢ ወይም የሽያጭ ትዕዛዝ ማጽደቅ ወይም ማስገባት፡-

(i.) ከሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ጋር በተገናኘ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች የሚመስል የግብይት እንቅስቃሴን፤ ወይም

(ii.) ለሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ሰው-ሰራሽ ዋጋ እንዲፈጠር የሚያደርግ።

(ሐ) በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ የሚገበይ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የገበያ ዋጋ ላይ ያለ አግባብ ተጽዕኖ ለማድረግ በማሰብ በተከታታይ እየጨመሩ በሚሄዱ ዋጋዎች ለመግዛት ወይም በተከታታይ እየቀነሱ በሚሄዱ ዋጋዎች ለመሸጥ ትዕዛዝ ማስገባት ወይም መፍቀድ፤

(መ) በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ የሚገበይ ሰነደ ሙዓለ ንዋይን የመዝጊያ ዋጋ ለመቀየር ወይም በዚያው ለማስቀጠል በማሰብ በገበያው መዝጊያ ላይ ወይም አቅራቢያ የሚሰጥን ትዕዛዝ ማጽደቅ ወይም ማስገባት፤

(ሠ) አንድን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በሚመለከት ሐሰተኛ ወይም አሳሳች ፍላጎት ወይም አቅርቦት ለመፍጠር ወይም እንዳለ ለማስመሰል በማንኛውም በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ የሚገበይ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የጨረታ ሒደት ወቅት

የግዢ ወይም የሽያጭ ትዕዛዝ ማጽደቅ ወይም ማስገባትና ከገበያው መከፈት በፊት ወዲያውኑ አስቀድሞ ትእዛዞቹን መሰረዝ፤

(ረ) የገበያ ቁጥጥርን ለመፈጸም የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ወይም ይህን ለመፍጠር እገዛ ማድረግ፤

(ሸ) በገበያው የግብይት ማዕከል የሚገበዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የግብይት ዋጋ ሰው-ሠራሽ በሆነ ደረጃ ባሉበት ማቆየት፤

(ቀ) በገበያው መገልገያዎች በኩል በተደረገ ግብይት አማካኝነት ማንኛውንም ሰው ለማታለል ማንኛውም ስልት ወይም ዘዴ መጠቀም፤

(በ) በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ ከሚገበዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተገናኘ በማጭበርበር ወይም ተመሳሳይ ውጤት ሊኖረው በሚችል ማንኛውም ድርጊት፣ ልማድ ወይም አሠራር መሰማራት

(3.) የተግባሩን ክብደትና የማቅለያ ሁኔታዎችን ጨምሮ የጉዳዩን ሁኔታዎች በሙሉ ከግምት በማስገባት ገበያው ጥሰት እንደተፈጸመ ሲወስን በቅጣቶች ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ወይም ማንኛውንም ቅጣቶች ሊጥል እንዲሁም ተገቢ ባልሆነው የገበያ ሥነ-ምግባር ተጽዕኖ የተደረገባቸውን ግብይቶች ሊሰርዝ ይችላል፡ ፡

## 10.8. የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ክልከላ

(1.) ማንኛውም የግብይት አባል በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ ከሚገበዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተገናኘ በውስጥ ዐዋቂ ግብይት መሳተፍ ወይም እያወቀ ማንኛውም ሌላ የግብይት አባል ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው በውስጥ ዐዋቂ ግብይት እንዲሳተፍ ማገዝ አይችልም፡፡

(2.) ይህ የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ክልከላ ለራሱ ጥቅም የሚደረግ የውስጥ ዐዋቂ ግብይትን ያካትታል፦

(ሀ) ማንኛውም ለራሱ ጥቅም በቀጥታም ሆነ በወኪል በኩል በተዘዋዋሪ በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ በሚገበዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው የሚችል የውስጥ መረጃ ያለው ግብይት የሚያደርግ ውስጥ ዐዋቂ ይህንን ደንብ ይተላለፋል፡፡

(ለ) አንድ ውስጥ ዐዋቂ በሚከተሉት ሁኔታዎች ጥሰት አይፈፅምም፡-

(i.) ድርጊቱን የፈጸመው ተጽዕኖ የደረሰበትን ግብይት ለማጠናቀቅ ከሆነ፤ እና

(ii.) ውስጥ ዐዋቂ የሆነው የግብይት ትዕዛዙን ለገበያው አባል ከሰጠው በኋላ ከሆነና ትዕዛዙ የውስጥ ዐዋቂ ከሆነ በኋላ በማንኛውም ረገድ ካልተለወጠ ።

(3.) ይህ የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ክልከላ ለሌላ ሰው ግብይት የሚፈጽምን ውስጥ ዐዋቂ ይጨምራል፦

(ሀ) ማንኛውም በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ በሚገበዩና ከውስጥ መረጃው ጋር ግንኙነት ባላቸው ወይም በውስጥ መረጃው ተጽዕኖ ሊደረግባቸው በሚችል ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለማንኛውም ሌላ ሰው ግብይት የሚፈጽም የውስጥ መረጃ ያለው ውስጥ ዐዋቂ ይህንን ደንብ ይተላለፋል።

(ለ) አንድ ውስጥ ዐዋቂ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይህንን ደንብ አይተላለፍም፦

(i.) የግብይት አባል ከሆነና በደንበኛው ልዩ ትዕዛዝ የሚንቀሳቀስ ከሆነ እና የውስጥ መረጃው በደንበኛው እስካልተገለፀለት ድረስ፤

(ii.) ድርጊቱን የፈጸመው ከምንዛሬ ተመን፣ የሕዝብ ዕዳን ወይም የውጪ የምንዛሬ ክምችቶችን ከማስተዳደር አኳያ የገንዘብ ፖሊሲዎችን ሥራ ላይ እያዋለ ያለ የመንግስት ዘርፍ አካልን በመወከል ያደረገው ከሆነ፤

(iii.) ተጽዕኖ የተደረገበትን ዝውውር ለማጠናቀቅ የፈጸመው ድርጊት ከሆነ፤ ወይም

(iv.) ውስጥ ዐዋቂ የሆነው የግብይት ትዕዛዙን ለገበያው አባል ከሰጠው በኋላ ከሆነና ትዕዛዙ የውስጥ ዐዋቂ ከሆነ በኋላ በማንኛውም ረገድ ካልተለወጠ።

(4.) ይህ የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ክልከላ ለሌላ ሰው የውስጥ መረጃን የሚገልጽን ሰው የውስጥ ዐዋቂ ያካትታል፦

(ሀ) አንድ የውስጥ መረጃ ያለውና ይህንኑ መረጃ ለሌላ ሰው የሚገልጽ ሰው ይህንን ደንብ ይተላለፋል፤

(ለ) ከላይ የተቀመጠው ቢኖርም አንድ ውስጥ ዐዋቂ የውስጥ መረጃውን የገለጸው በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ ከሚደረግ የማንኛውም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ ውስጥ ሥራውን፣ ኀላፊነቱን ወይም ሞያውን በአግባቡ ለመወጣት አስፈላጊ ስለነበር መሆኑን ሚዛናዊ በሆነ ደረጃ ካረጋገጠ ይህንን ደንብ የጣሰ አይሆንም።

(5.) ይህ የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ክልከላ ሌላ ሰው ግብይት እንዲፈጽም ወይም እንዳይፈጽም የሚያበረታታትን ውስጥ ዐዋቂን ያካትታል፡፡ አንድ የውስጥ መረጃ ያለውና ከዚሁ መረጃ ጋር በሚገናኙት ወይም በውስጥ አዋቂ መረጃው ተጽዕኖ ሊደረግባቸው በሚችሉት በገበያው የግብይት ማዕከል ላይ የሚገበዩት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይትን የሚያበረታታ ወይም ሌላ ሰው እንዲገበያይ የሚያደርግ ወይም ሌላ ሰው እንዳይገበያይ የሚያስቆም ውስጥ ዐዋቂ ይህንን ደንብ ይተላለፋል፡፡

(6.) ከላይ በተገለጸው ሁኔታ እያወቀ በእነዚህ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የሚፈጽም የግብይት አባል ገበያው ከሚጥልበት ማንኛውም ሌላ ቅጣት በተጨማሪ ተፈጻሚነት ባላቸው የወንጀል ሕጎች ውስጥ ለተቀመጡት ማንኛውም ቅጣቶች ኀላፊ ይሆናል፡፡

(7.) አንድ የግብይት አባል ወይም የግብይት ፈፃሚ ስለማንኛውም የገበያ ማጭበርበር፣ የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ወይም ስለ ማንኛውም የተከለከለ የግብይት ሥነ ምግባር ምክንያታዊ ጥርጣሬ ካለው ወዲያውኑ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡፡

## 10.9. አሳሳች የግብይት ልማድ ክልከላ

(1.) የደንበኛ ሒሳቦች ላይ ተደጋጋሚ ግብይት ክልከላ:- አንድ የግብይት አባል የሚከተሉትን መፈፀም የለበትም:-

(ሀ) የግብይት ክፍያዎችን፣ ኮሚሽኖችን፣ ተመላሾችን ለገበያው አባል ከማስገኘት በቀር ምክንያታዊ የኢንቨስተመንት ዓላማ በሌላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ደንበኞቹን ማበረታታት፤

(ለ) ከላይ በ (ሀ) በተገለጸው የግብይት ዓይነት እንዲሰማሩ ደንበኞቹን የሚያግባቡ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃዎችን ወይም ምክሮችን መስጠት፤

(ሐ) የገበያው አባል ትዕዛዙን በዚህ መልክ የፈጸመው ምክንያታዊ በሆነ የንግድ ዓላማ መሆኑን ማሳየት ካልቻለ በስተቀር ለራሱ ተጨማሪ የድለላ ክፍያዎችን፣ ኮሚሽኖችን፣ ተመላሾችን ወይም ሌሎች ክፍያዎችን (የገበያው አባል ትዕዛዙን በሙሉ ወይም በትላልቅ ክፍሎች ቢፈጽመው ኖሮ ከሚያገኛቸው በላይ የሆኑ) ለማስገኘት በማሰብ ትላልቅ የደንበኞችን ትዕዛዞችን በትናንሽ ትዕዛዞች ከፋፍሎ መፈጸም፡

(2.) ሌሎች የሐሰተኛ ወይም የማታለል የግብይት ልማዶች ክልከላዎች

(ሀ) አንድ የግብይት አባል ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ጋር በተገናኘ ዋነኛ አላማው የሚከተሉት የሆነ ግብይት ላይ መሳተፍ የለበትም፦

(i.) በዚያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ ሐሰተኛ፣ አሳሳች ወይም ሰው ሰራሽ መልክ ያለው የግብይት እንቅስቃሴ መፍጠር፤

(ii.) በሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የገበያ ዋጋ ላይ ያለ አግባብ ተጽዕኖ ማድረግ፤

(iii.) የገበያውን እውነተኛ ወይም በኢንቨስተሮች ዘንድ ያለውን ተጨባጭ የአቅርቦትና ፍላጎት ሁኔታ የማያሳይ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዋጋ መፍጠር፤

(iv.) ለግል ጥቅም ወይም ከግብር ለማምለጥ ወይም ግብር ለመቀነስ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዋጋ መቀየር፤ ወይም

(v.) ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎች፣ ደንቦች፣ የገበያውን ደንቦች፣ የብድር ገደቦችን፣ የሥነ-ምግባር መመሪያዎች ወይም ተመሳሳይ ገደቦችን ማስቀረት፡፡

(ለ) አንድ የግብይት አባል በንዑስ ደንብ (2) ሥር ለተጠቀሰው ቀዳሚ ዓላማ ጥሰት ፈፀመ የሚባለው፦

(i.) አንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይን በተከታታይ እየጨመሩ በሚሄዱ ዋጋዎች የመግዛት ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በተከታታይ እየቀነሱ በሚሄዱ ዋጋዎች የመሸጥ ትዕዛዝ ካስገባ፤

(ii.) ለአንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የተላለፉ ትላልቅ የደንበኞች ትዕዛዞችን ወደ ትናንሽ አፈጻጸሞች ከከፋፈለ፤

(iii.) በጥቅም ባለቤትነት ላይ ምንም ለውጥ የማያስከትል የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይትን ከፈጸመ፤

(iv.) የአንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የመዝጊያ ዋጋ ለመቀየር ወይም በዚያው ለማስቀጠል በማሰብ በገበያ መዝጊያ ሰዓት ወይም አቅራቢያ ላይ ትዕዛዝ ካስገባ፤

(v.) ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ትዕዛዝ ካስገባና ከመፈጸሙ በፊት ወዲያውኑ አስቀድሞ ትዕዛዙን ከሰረዘ፤

(vi.) የግብይት አባል ራሱ ወይም ለርሱ ቅርበት ባለው ሰው አማካኝነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ለመሸጥ ወይም ለመግዛት በማሰብና ይህንንም ለደንበኛው ሳያሳውቅ ደንበኛው አንድን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ እንዲገዛ ወይም እንዲሸጥ ከመከረ፤

(vii.) ውጤታቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ዋጋ በገበያው አባልና በሌሎች ወገኖች መካከል ከዚህ በፊት ከስምምነት ወደተደረሰበት ሰው ሰራሽ ዋጋ መለወጥ የሆኑ ትዕዛዞችን ካስገባ፤ ወይም

(viii.) ሌሎች በዚህ ሥር ባልተጠቀሱ ሆኖም በገበያው ላይ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ውጤት በሚኖራቸው ተግባራት ላይ ከተሰማራ፡፡

(3.) ማጭበርበርን ዓላማ ያደረጉ ግብይቶች ስለመከልከላቸው፡- አንድ የግብይት አባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከማንኛውም ሰው ጋር ከሚያደርገው ግብይት ጋር በተገናኘና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዢ ወይም ሽያጭ በሚመለከት ያንን ሰው ለማታለል በማሰብ ማንኛውም ስልት ወይም ዘዴ መጠቀም ወይም እንደ ማጭበርበር ወይም ማታለል መሆን የመቻል ዕድል ባለው ድርጊት፣ ልማድ ወይም የንግድ አሠራር ላይ መሰማራት የለበትም፡፡

(4.) በውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ክፍያዎችና ጉርሻዎችን መስጠት ስለመከልከሉ፡ - የገበያ አባሎች በሙሉ በማንኛውም ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ወይም ተገቢ ያልሆነ ብልጫን ለማግኘት በማሰብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጉቦ፣ ጉርሻ ወይም ማንኛውንም ዋጋ ያለውን ነገር (ግዘፍነት ያላቸውን ዕቃዎችም ሆነ ግዘፍነት የሌላቸውን አገልግሎቶች) መስጠትን፣ ቃል መግባትን፣ ማቅረብን፣ መጠየቅን፣ ለመቀበል መስማማትን ወይም መቀበልን ለሚከለከሉና ተፈጻሚ ለሆኑ የጸረ-ሙስና ሕጎችና ደንቦ በሙሉ ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡

(5.) ያልተፈቀደ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማረጋገጥ መከልከሉ፡- ማንኛውም ፈቃድ ሳይኖረው ለብቻው ወይም ከሌላ ጋር በመመሳጠር በሌላ ሰው ባለቤትነት ሥር ያሉ አክሲዮኖችን ያረጋገጠ የግብይት አባል ገበያው የሚወስናቸው ቅጣቶች ይጣሉበታል፡፡

(6.) ከታገደ የግብይት አባል ጋር የሚፈጸሙ ግብይቶች ስለመከልከል፡- ማንኛውም የግብይት አባል ገበያው ካልፈቀደለት በስተቀር የአባልነት የምስክር ወረቀቱ ከታገደ ከሌላ የግብይት አባል ጋር መገበያየት አይችልም፡፡

(7.) የውሸት ወይም የተሳሳተ መረጃ ዝውውርን መከላከል፦

(ሀ) ማንኛውም ሐሰተኛ መግለጫን ወይም መረጃን የማስፋፋት ወይም በማሰራጨት ወይም በማስፋፋት ወይም በማሰራጨት በማገዝ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ወይም የሚጨምርበት ወይም የሚቀንስበት ዕድል እንዲኖር የሚያደርግና እስከሚያውቀው ድረስ የዋጋው መጨመር ወይም መቀነስ እርሱ አሰራጭቶት ከሆነ የተሳሳተውን መረጃ መሠረት በማድረግ የሆነ የግብይት አባል ይህን ደንብ ይተላለፋል፡፡

(ለ) አንድ የግብይት አባል፣ በማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዋጋ እና/ወይም ወደ ጥሬ ገንዘብ የመቀየር ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ያላቸውን ወይም ተጽዕኖ የማድረግ አዝማሚያ ያላቸውን የገበያውን ፕሮግራሞችና

ሌሎችንም ጨምሮ የገበያን መረጃ ወይም ሁኔታ በሚመለከት ሐሰተኛ፣ አሳሳች ወይም ትክክለኛ ያልሆነን መረጃ ማስፋፋት ወይም ማሰራጨት ወይም እንዲስፋፋ ወይም እንዲሰራጭ መፍቀድ ወይም ማገዝ የለበትም።

(ሐ) አንድ እያወቀ ሐሰተኛ፣ አሳሳች ወይም ትክክል ያልሆነን መረጃ የሚያሰራጭ የግብይት አባል ገበያው ያስቀመጣቸው ቅጣቶች ይጣሉበታል።

10.10. መረጃ በምስጢር መያዝ ያለበት ስለመሆኑ

(1.) አንድ የግብይት አባል ከደንበኞቹ በአደራ የተሰጠውን መረጃ ምስጢራዊነት መጠበቅ አለበት። የገበያው አባል፦

(ሀ) ደንበኛው የአገር ክህደት፣ በወንጀል የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ፣ ሽብርተኞችን በፋይናንስ የመደገፍ ወይም የአደገኛ ዕጾች ዝውውር ወይም ሌሎች ወንጀሎችን እንደፈጸመ የሚያውቅ ወይም የሚጠረጥር ከሆነ፤ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የገበያው አባል መረጃውን የማሳወቅ ኀላፊነቱ አስገዳጅ ነው፤ ወይም

(ለ) መረጃውን የሚያሳውቀው የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ወይም የድለላ ገቢ ወይም ክፍያዎችን ለማስከፈል ለመክሰስ ወይም የቀረበበትን ክስ ለመከላከል በምክንያታዊነት አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የደንበኛውን ፈቃድ ሳያገኝ ለሦስተኛ ወገኖች ይህንን መረጃ መግለጽ የለበትም።

(2.) የገበያው አባል ገበያው በወሰነው ወለል ውስጥ ወይም ከዚያ በላይ የሆነን የአውጪውን የአክሲዮን ካፒታል ግዢ ለደንበኛው ሲፈጽም ለገበያው የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

10.11. የትዕዛዞች ማኅደሮች

(1.) አንድ የግብይት አባል ከደንበኞች የሚቀበላቸው ትዕዛዞች የዕለት ማኅደር መያዙን ማረጋጥ አለበት። የሚመዘገበው መረጃ የእያንዳንዱን ደንበኛ የግብይት ሒሳብ መለያ፣ የግብይት ፈፃሚውን መለያ፣ ዝርዝር ትዕዛዙን፣ ትዕዛዙን የተቀበለበትን፣ የተሰራጨበትን፣ የተሻሻለበትን የተፈጸመበትን ወይም የተሰረዘበትን ቀንና ሰዓት እና ሌሎችን ማካተት አለበት። ማኅደሩ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሊከማች ይችላል፡ ፡

(2.) አንድ የግብይት አባል፣ ማንኛውም ያልተፈቀደለት ሰው ወደ ግብይት ሥርዓቱ ወደገቡት ትእዛዛት ያለአዲት ዱካ እንዳይገባ እና/ወይም እንዳይበርዝ ለመከላከልና እና ሰነዶቹ እንዲጠበቁ ለማድረግ በቂ የደኅንነት አቅርቦቶችን ማዘጋጀት አለበት።

## ምዕራፍ 11 ግዴታዎችን አለመወጣትና ኪሳራ

### 11.1. ግዴታዎችን አለመወጣት ስለመከልከሉ

(1.) ማንኛውም የግብይት አባል ከሌላ የግብይት አባል፣ ደንበኛ፣ ክፍያ ፈጻሚ ባንክ ወይም ማንኛውም ሌላ የካፒታል ገበያ አንቀሳቃሽ ወይም አገልግሎት ሰጪ ጋር ባለው ግብይት መክፈል ያለበትን ክፍያዎች አለመክፈል አይችልም።

(2.) አንድ የግብይት አባል ዕዳውን እንዳልከፈለ የሚቆጠረው ለሌላ የግብይት አባል፣ ደንበኛ፣ ክፍያ ፈጻሚ ባንክ ወይም ለማንኛውም ሌላ የካፒታል ገበያ አንቀሳቃሽ ወይም አገልግሎት ሰጪ ያለበትንና ከሕጋዊ ግብይት የሚመነጭን የገንዘብ ወይም ሌላ ግዴታ መወጣት ካልቻለ ነው።

(3.) ማንኛውም ይህንን ደንብ የሚጥስ የግብይት አባል ወዲያውኑ ይታገዳል እንዲሁም ገበያው ለሚጥላቸው ሌሎች ቅጣቶችም ኀላፊ ይሆናል።

(4.) የተጣለው ዕገዳ የሚነሳው ግዴታውን ያልተወጣው አባል ለገበያው ማንኛውንም ቀሪ ክፍያዎች፣ ወይም በእነዚህ ላይ የታሰበ ወለድ ሙሉ ለሙሉ እንደተከፈለ ወይም የግብይቱ ወገኖች ጉዳዩን ለመፍታት እንደተስማሙና የግብይት አባሉም በስምምነቱ መሠረት እንደፈጸመ ወይም እየፈጸመ እንደሆነ ማስረጃ ሲያቀርብ ነው።

### 11.2. የኪሳራ ወይም ግዴታን ያለመወጣት ማስጠንቀቂያ

(1.) አንድ የግብይት አባል ግዴታውን ለመወጣት ካልቻለ ይህንኑ በጽሑፍ ለገበያው ያሳውቃል።

(2.) አንድ የግብይት አባል፡-

(ሀ) የእነዚህን ደንቦች ድንጋጌዎች ወይም በየጊዜው ከሌላ የግብይት አባል፣ ደንበኛ፣ ክፍያ ፈጻሚ ባንክ ወይም ማንኛውም ሌላ የካፒታል ገበያ አንቀሳቃሽ ወይም አገልግሎት ሰጪ ጋር በሚገባው ውል፣ መግባባት ወይም ስምምነት መሠረት ያሉበትን ግዴታዎች በአግባቡ መፈጸም ካልቻለ ወይም በገበያው አስተያየት ግዴታዎቹን ካልፈጸመ፤

(ለ) አንድ በልዩነት የማይታይ የግብይት አባል በአዋጁ መሠረት የጸና ገበያ አገልግሎቶች ፈቃድ ወይም አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ክፍሎች መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አከናዋኝነትና ደላላነት የንግድ ሥራ ለማከናወን የሚያስፈልገው ፈቃድ ሳይኖረው ሲቀር፤

(ሐ) በገበያው ደንቦች መሠረት ሲከስር ወይም እንደከሰረ ሲቆጠር፤

(መ) ገበያው፣ ፍጹም የራሱ በሆነው የውሳኔ ሥልጣን የገበያ አባሉን የፋይናንስ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታዎች በመመልከት የገበያ አባሉን ደንበኞች፣የሌሎችን አባላት ወይም ኢንቨስት የሚያደርገውን ህዝብ ጥቅም መጠበቅ አስፈላጊ ወይም ተመራጭ ሆኖ ሲያገኘው፤

(ሠ) በአንድ የግብይት አባል ምክንያት ወይም ላይ ወይም ከገበያው አባል ጋር በተገናኘ ቅያሪ፣ ስርቆት፣ የእምነት ማጉደል፣ ምዝበራ ወይም ማንኛውም ሌላ ተመሳሳይ ነገር ሲከሰት፤

(3.) ገበያው ፍጹም የራሱ በሆነው የውሳኔ ሥልጣኑ የዚያን ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ኩነቱ በገበያው አስተያየት ቀጣይነት ያለውም ሆነ የሌለው ቢሆን ግዴታን ያለመውጣት ኩነት መከሰቱን የማወጅና ይህንኑ አስመልክቶ ለገበያው አባላትና ለባለሥልጣኑ ማስጠንቀቂያ የመስጠት መብት አለው፡፡

(4.) ማንኛውም የግብይት አባል ከሌላ የግብይት አባል ጋር ባለው ግብይት ሌላኛው አባል ግዴታዎቹን ሳይወጣ ሲቀር የገበያው አባል ወዲያውኑ ይህንኑ ለገበያው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

(5.) ግዴታዎችን ያለመወጣት ማሳወቂያው ለገበያው ከደረሰው በኋላ ግዴታውን ያልተወጣው የግብይት አባል ገበያው ሳያጸድቅለት ከገበያ አባልነት እንቅስቃሴዎቹ የሚመነጩ ኀላፊነቶቹን በሚመለከት ምንም ዓይነት ስምምነት መፈጸም አይችልም፡፡

## 11.3. የመብት ጥያቄዎች የሚሸጡ፣ የሚተላለፉ ወይም በዋስትና የሚያዙ አለመሆናቸው

ማንኛውም ግዴታውን ያልተወጣው ወገን ባለ ገንዘብ የሆነ የግብይት አባል አስቀድሞ የገበያውን ፈቃድ ሳያገኝ ግዴታውን ባልተወጣው ወገን ላይ ያሉትን የመብት ጥያቄዎች የግብይት አባል ላልሆነ አካል መሸጥ፣ ማስተላለፍ ወይም በዋስትና ማስያዝ አይችልም፡፡

## 11.4. ግዴታ ባለመወጣት ወቅት የገበያው ሥልጣን

(1.) በግዴታ አለመወጣት ጉዳዮች በሙሉ ገበያው የሚከተሉት ሥልጣኖች የሚኖሩት አግባብነት ያለው ኮሚቴ ያዋቅራል፡-

(ሀ) አስፈላጊ ሆነው ሲገኝ የቴክኒክና ሞያዊ ዕገዛ መስጠት፤

(ለ) ከአክሲዮን ደለላነት ግብይቶች ጋር በተገናኘ ግዴታውን ያልፈጸመው የግብይት አባል ኦሪጅናል የሒሳብ መዛግብትና ተያያዥ ሰነዶችን እንዲሁም ለእርሱ መከፈል ያለበትንና እርሱ መክፈል ያለበትን ጠቅላላ የገንዘብ መጠን የሚያሳይ መግለጫ እንዲሰጠው ማድረግ፤

(ሐ) ባለ ገንዘብ ወይም ግዴታ ያልፈጸሙ የገበያ አባላትን ለስብሰባ መጥራት፤

(መ) ግዴታ ያልፈጸሙ ወገኖች በእነዚህ ኮሚቴዎች ስብሰባዎች ላይ እንዲቀርቡ መጥራትና በምርመራው ወቅት በኮሚቴው ፊት ራሳቸውን የሚከላከሉበትን ሙሉ መብት መስጠት፤

(ሠ) አግባብነት ባላቸው ሒሳቦች ላይ ዝርዝር ምርመራዎችን ማድረግ፤

(ረ) ወጥነት የጎደላቸው ወይም የጎደላቸው የሚመስሉ ገቢ ትዕዛዞችን፣ ግብይቶችን ወይም ሌሎች ጉዳዮችን ለገበያው ማሳወቅ፤

(ሰ) ለገበያው ባለሥልጣኑ ሲያጸድቀው ተግባራዊ የሚሆንና ግዴታውን ያልተወጣውን አባል የአክሲዮን ድለላ ሥራና ሀብቶች የሚያስተዳድር ጊዜያዊ አስተዳዳሪ ሹመትን ምክረ ሐሳብ ማቅረብ፤

(ሸ) ከምርመራው ጋር የሚገናኝ ማንኛውም ሌላ ጉዳይ።

(2.) ግዴታውን ያለመወጣቱና የኪሳራው ጉዳይ በኮሚቴው በተቃናና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲፈታ ግዴታውን ያልተወጣው የግብይት አባል በእነዚህ ደንቦች መሠረት እንዲያደርግ ሲጠየቅ፡-

(ሀ) የሥራ ቦታውን፣ ሥርዓቶቹንና መኮንኖቹን ክፍትና ተደራሽ ማድረግንና ሌሎችን ጨምሮ ኮሚቴው የሚፈልገውን ማንኛውንም ዕገዛ ማድረግ፤

(ለ) ግዴታውን ባልተወጣበት ጊዜ ከሥራው ጋር በተገናኘ ሁሉንም መረጃ፣ መዛግብት፣ ማኅደሮች እንዲሁም ያሉበትን ዕዳዎችና መክፈል ያለበትን ጠቅላላ ገንዘብ የሚያሳይ መግለጫ እንዲሁም ኮሚቴው የሚጠይቀው ማንኛውም ተዛማጅ ሰነድና መረጃ ማቅረብ፤ እና

(ሐ) ኮሚቴው ለሚስቀምጣቸው ሌሎች ተፈላጊ ሁኔታዎች ተገዢ መሆን አለበት፡ ፡

(3.) በዚህ ደንብ መሠረት የሚቋቋመው ኮሚቴ ለገበያው አባላት በሙሉና ለባለሥልጣኑ ግዴታውን ያልተወጣውን አባል ስም የሚጠቅስና ግዴታውን ባልተወጣው በዚህ አባል ላይ የመብት ጥያቄ ያላቸው በሙሉ ጥያቄዎቻቸውን በሚያስቀምጠው ቀነ ገደብ እንዲያስገቡ የሚገልጽ ማስታወቂያ እንዲላክ ያደርጋል።

(4.) የገበያው አባልና ተሿሚ እንደራሴዎቹ በገበያው በሚጠየቀው መሠረት ሲጠሩ በኮሚቴው ፊት ቀርበው በይዞታቸው ወይም በቁጥጥራቸው ሥር ያለና ከሚመረመረው ጉዳይ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን መረጃዎች፣ ሒሳቦችና ሰነዶችን ማቅረብ አለባቸው።

(5.) አንድ የግብይት አባል እና/ወይም ተሿሚ እንደራሴዎቹ ወይም ዳይክተሮቹ በኮሚቴው ሲጠየቁ ገበያው በሚያስቀምጠው ቅርጽ መሠረት የግል የገንዘብ አቋማቸውን የሚገልጽ ቃለ መሓላ ይሰጣሉ፡፡

## 11.5. ኃላፊነትን ስለማስተባበል

የእነዚህ ደንቦች አጠቃላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ ገበያው የግዴታ አለመወጣት ኩነትን ከማወጁ ወይም ካለማወጁ ለሚመነጭ ወይም ከዚሁ ጋር ለሚገናኝ (የሥራ፣ የገቢ፣ የመልካም ስም፣ የድርድር ወይም የትርፍ ወይም ሌላን ዕጦት ጨምሮ ቀጥተኛ፣ ተዘዋዋሪ፣ ልዩ ወይም ተተኪ ለሆነ) በማንኛውም የግብይት አባል ወይም ሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርስ ማንኛውም ዓይነት ጉዳት፣ ኪሳራ ወጪ ገበያው ኃላፊ አይሆንም፡፡

# የአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ - የግብይት ደንቦች

(1.) የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን መጽሐፈ ደንብ (2017 ዓ.ም) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ለሚፈጸሙ ጥፋቶች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው አስተዳደራዊ ቅጣቶች በዚህ ሰንጠረዥ ሥር የተካተቱት ናቸው፡፡

(2.) የአንድ ደንብ ወይም ሌላ የአሰያየም ልማድ ሲቀየር ስሙ ወይም የአሰያየም ልማዱም በዚህ የቅጣቶች ሰንጠረዥም በራሱ እንደተቀየረ ይቆጠራል፡፡

(3.) ከአንድ ጥሰት ጋር በተገናኘ ማንኛውም የዕገዳ እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ ዕግዱ የሚነሳው ተያያዥ ወይም ተያያዥ የሆኑ ግዴታዎች በሙሉ ተሟልተው ሲፈጸሙ ብቻ ነው፡፡

| ምዕራፍ | ደንብ | በየግብይት አባሉ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ቅጣት | በተሿሚ እንደራሴ ወይም በሌላ ሠራተኛ ላይ የሚጣል ቅጣት | ተደራራቢ ገጽታ |
|---|---|---|---|---|
| 1<br><br>የደንቦች አስተዳደርና የአሠራር ድንጋጌዎች | 1.2. የተፈጻሚነት ወሰን | | | |
| 2<br><br>የደንበኛ ሒሳቦች | 2.1. ደንበኛን ማወቅ እና ቅድመ ማጣራት | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 500,000 — 750,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 300,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም | ተፈጻሚነት የሌለው (ተ/የ) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | |
| 2.2. | የደንበኛ ሒሳቦች ቁጥጥር | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 100,000 — 150,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 35,000 — 50,000 እና/ወይም<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | (ተ/የ) |
| 2.3. | ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን ማረጋገጥ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 100,000 — 150,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ እና ወይም<br>• የምዕራፍ 20 — "ትዕዛዝ አያያዝና ምርጥ አፈጻጸም" ድንጋጌዎች ሲጣሱ ተፈጻሚነት ያላቸው ቅጣቶች | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 35,000 — 50,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• የምዕራፍ 20 — "ትዕዛዝ አያያዝና ምርጥ አፈጻጸም" ድንጋጌዎች ሲጣሱ ተፈጻሚነት ያላቸው ቅጣቶች | በአንድ (1) ዐመት ጊዜ ውስጥ ጥፋቱን ደግሞ የፈጸመ ሰው ቢያንስ ለሃያ (20) የሥራ ቀናት ይታገዳል፡፡ |
| 2.4. | የደንበኛ ሒሳብ አስተዳደርና ልየታ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 500,000 — 750,000 እና | (ተ/የ) | (ተ/የ) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪ.ታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | | |
| | 2.5. ለደንበኞች የሚሰጥ ወርሃዊ የፋይናንስ መግለጫ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 100,000 — 150,000 እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪ.ታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 35,000 — 50,000 እና/ወይም<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | (ተ/የ) |
| 3<br>የደንበኞች ሀብቶች | 3.1. የደንበኞች ገንዘብ አጠቃቀምና ልየታ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 500,000— 750,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪ.ታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 150,000 — 300,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | ለየግብይት አባል ድርጅቱ ቅጣቱ በገበያው ከተጣለበት ቀን ጀምሮ የግብይት አባሉ ክፍያውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ በየቀኑ ብር 5,000 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.2. የደንበኞችን ገንዘብ መመዝበር | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 500,000 — 750,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 300,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | ለግብይት አባል ድርጅቱ ቅጣቱ በገበያው ከተጣለበት ቀን ጀምሮ የግብይት አባሉ ክፍያውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ በየቀኑ ብር 5,000 |
| 3.3. ያልተፈቀደ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 500,000 — 750,000 ወይም ከሽያጩ ወይም ዝውውሩ ዋጋ ሦስት (3) ዕጥፍ ከሁለቱ የሚበልጠውን<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 300,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | ለየግብይት አባል ድርጅቱ ቅጣቱ በገያየው ከተጣለበት ቀን ጀምሮ የግብይት አባሉ ክፍያውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ በየቀኑ ብር 5,000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3.4. በደንበኞች ሒሳብ ላይ ውሳኔ የመስጠት ነፃነት/ሥልጣን | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 200,000 — 300,000 እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 35,000 — 50,000 እና/ወይም<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | N/A |
| | 3.5. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግዢ ወይም ሽያጭ ክፍያዎች | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 200,000 — 300,000 እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 35,000 — 50,000 እና/ወይም<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | N/A |
| 4<br>የትዕዛዝ አያያዝና ምርጥ አፈጻጸም | ከደንብ 4.9 "የኦዲት ሰነድ ዱካ መመዘኛዎች" ውጪ በምዕራፍ 4 — "የትዕዛዝ አያያዝና ምርጥ አፈጻጸም" ሥር የሚገኙ ደንቦች በሙሉ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 250,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 35,000 — 50,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | (ተ/የ) |
| | 4.9. የኦዲት ሰነድ ዱካ መመዘኛዎች | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 200,000 — 300,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም | (ተ/የ) | (ተ/የ) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ እና/ወይም<br>● ገደብ መጣል | | |
| 5<br><br>የስህተት ግብይቶችና ትዕዛዞች | በምዕራፍ 5 — "የስህተት ግብይቶችና ትዕዛዞች" ሥር የሚገኙ ደንቦች በሙሉ | ● በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 150,000 — 250,000<br>● ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ እና/ወይም<br>● ገደብ መጣል | ● በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 35,000 — 50,000<br>● ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማገሳት እና/ወይም<br>● ገደብ መጣል | (ተ/የ) |
| 6<br><br>የተከለከሉ ተግባራት | 6.1. ዋስትና በመሥጠት ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥራ ግንኙነት ስለ መከልከሉ | ● በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 1,000,000 — 1,500,000<br>● ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>● የንግድ ፈቃድ ስረዛ፤<br>● ገደብ መጣል እና/ወይም<br>● ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | ● በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 150,000 Birr — 300,000<br>● ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማገሳት<br>● ገደብ መጣል እና/ወይም<br>ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | ለየግብይት አባል ድርጅቱ ቅጣቱ በገያየው ከተጣለበት ቀን ጀምሮ የግብይት አባሉ ክፍያውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ በየቀኑ ብር 5,000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 6.2. በደንበኞች መካከል ማበላለጥ ክልክል ስለመሆኑ | የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መጽሐፈ ደንብ (2017) የምዕረፍ 4 — "የትዕዛዝ አያያዝና ምርጥ አፈጻጸም" ድንገጌዎች ሲጣሱ ተፈጻሚ የሚሆኑ ቅጣቶች | | |
| | 6.3. ዕዳ ካለበት ደንበኛ ጋር ግብይት ማድረግ ስለመከልከሉ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 200,000 — 300,000 | (ተ/የ) | በአንድ (1) ዐመት ጊዜ ውስጥ ጥፋቱን ደግሞ የፈጸመ ሰው ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ይታገዳል። |
| | 6.4. የገበያው መገልገያዎችና ዳታ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 200,000 — 300,000 | (ተ/የ) | በአንድ (1) ዐመት ጊዜ ውስጥ ጥፋቱን ደግሞ የፈጸመ ሰው ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ይታገዳል። |
| 7 የገበየው የግብይት ኦፐሬሽኖች | 7.2. የግብይት መመዘኛዎች | ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪ.ታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | (ተ/የ) | (ተ/የ) |
| | 7.3. የግብይት ሥርዓቶች አያያዝ | ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪ.ታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | (ተ/የ) | (ተ/የ) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7.7. የግብይት ሥርዓት መግቢያ ኮዶች አጠቃቀም | ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | (ተ/የ) |
| 7.8. ገደቦችና ወሰኖች | • ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• በሥርቆት/ተገቢ ያልሆነ/ያልተፈቀደ አጠቃቀም ምክንያት ላጋጠመ ጉዳት ገበያው የሚጠይቀውን የጉዳት ካሳ መክፈል | • ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• በሥርቆት/ተገቢ ያልሆነ/ያልተፈቀደ አጠቃቀም ምክንያት ላጋጠመ ጉዳት ገበያው የሚጠይቀውን የጉዳት ካሳ መክፈል | (ተ/የ) |
| 7.9. የትልቅ አክሲዮኖች ስብስብ ግብይት | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 200,000 — 300,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | (ተ/የ) | (ተ/የ) |
| 7.11. የባለቤትነት ዝውውር | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 200,000 — 300,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም | (ተ/የ) | (ተ/የ) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | | |
| 7.12. የብድር ሽያጭ መፈጸም | • ለእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 500,000 — 750,000 ወይም የጠቅላላውን ግብይት መጠን እና ከግብይቱ የተገኘ ማንኛውንም ጥቅም 5% ከሁለቱ የሚበልጠውን<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • ለእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 300,000 ወይም የጠቅላላውን ግብይት መጠን እና ከግብይቱ የተገኘ ማንኛውንም ጥቅም 5% ከሁለቱ የሚበልጠውን<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል እና<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | (ተ/የ) |
| 7.15. ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 250,000 እና<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 35,000 — 50,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም | (ተ/የ) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 8<br><br>የበይነ መረብና የዲጂታል ግብይት መድረኮችን የሚመለከቱ ደንቦች | የምዕራፉ 8 — “የበይነ መረብና ዲጂል ግብይት መድረኮች” ደንቦች በሙሉ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 150,000 — 250,000 እና<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 35,000 — 50,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | (ተ/የ) |
| 9<br><br>ክፍያ ማጣራትና መፈጸም | 9.1. ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችንና ከግብይቱ የተገኘውን ገንዘብ ርክክብና ክፍያ መፈጸም | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 100,000 Birr — 150,000 እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • (ተ/የ) | (ተ/የ) |
| | 9.2. የማስተላለፊያ ሰነዶችን ማስረከብ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 100,000 — 150,000 እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | • (ተ/የ) | (ተ/የ) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 9.3. ያልተሳኩ ግብይቶችን የማሳወቅ ግዴታ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 100,000 — 150,000 እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | (ተ/የ) | (ተ/የ) |
| | 9.4. ጉድለት ያለበት ዝውውር | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 100,000 — 150,000 እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | (ተ/የ) | (ተ/የ) |
| 10<br>የየግብይት አባላት ሥነ ምግባር | 10.1. አጠቃላይ ሥነ ምግባር | • የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ<br>• በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 200,000 — 300,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | (ተ/የ) | (ተ/የ) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | | |
| 10.2. ለገበያው ሪፖርት የማድረግ ግዴታ | ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | (ተ/የ) | (ተ/የ) |
| 10.3. ፈቃድ የተሰጣቸው የግብይትዎች የግብይት ማዕከል የአለባበስ ሥነ ሥርዓትና የመለያ መታወቂያ | • የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ<br>• በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 200,000 — 300,000<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ<br>• በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 150,000 — 300,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | (ተ/የ) |
| 10.4. የግብይት ማዕከል ሥነ ሥርዓት | • የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እና | • የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | (ተ/የ) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • ማንኛውንም ተያያዥ የጉዳት ካሳዎች መክፈል | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 300,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | |
| 10.6. ከፊት መቅደምና ከደንበኞች ቀድሞ ግብይት መፈጸም | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 500,000 — 750,000 ወይም የጠቅላላውን ግብይት መጠን እና ከግብይቱ የተገኘ ማንኛውንም ጥቅም 5% ከሁለቱ የሚበልጠውን<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • ለእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 300,000 ወይም የጠቅላላውን ግብይት መጠን እና ከግብይቱ የተገኘ ማንኛውንም ጥቅም 5% ከሁለቱ የሚበልጠውን<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>ገደብ መጣል እና<br>ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | (ተ/የ) |
| 10.7. የገበያ ሽፍጥና ሕገ ወጥ የገበያ ስምምነቶች ክልከላ | • ከግብይቱ ከተገኘው ትርፍ ወይም ጥቅም ሦስት (3) ዕጥፍ የሆነና ገበያው ቅጣቱን በጣለ | • ከግብይቱ ከተገኘው ትርፍ ወይም ጥቅም ሦስት (3) ዕጥፍ የሆነና | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በአሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ መከፈል ያለበት እንዲሁም ከዚህ ሲያልፍ ከአሥራ አንደኛው (11) የሥራ ቀን ጀምሮ ለእያንዳንዱ ለዘገየበት ቀን ሦስት በመቶ (3%) ተጨማሪ ቅጣት<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ/የምዝገባ ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | ገበያው ቅጣቱን በጣለ በአሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ መከፈል ያለበት እንዲሁም ከዚህ ሲያልፍ ከአሥራ አንደኛው (11) የሥራ ቀን ጀምሮ ለእያንዳንዱ ለዘገየበት ቀን ሦስት በመቶ (3%) ተጨማሪ ቅጣት<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | |
| 10.8. | የውስጥ ዐዋቂ ግብይት ክልከላ | • ከግብይቱ ከተገኘው ትርፍ ወይም ጥቅም ሦስት (3) ዕጥፍ የሆነና ገበያው ቅጣቱን በጣለ በአሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ መከፈል ያለበት ቅጣት<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም | • ከግብይቱ ከተገኘው ትርፍ ወይም ጥቅም ሦስት (3) ዕጥፍ የሆነና ገበያው ቅጣቱን በጣለ በአሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ መከፈል ያለበት ቅጣት | (ተ/የ) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ/የምዝገባ ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | |
| 10.9. የአሳሳች ግብይት ቅጦች ክልከላ | በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 500,000 — 750,000 ወይም የጠቅላላውን ግብይት መጠን እና ከግብይቱ የተገኘ ማንኛውንም ጥቅም 5% ከሁለቱ የሚበልጠውን<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • ለእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 150,000 — 300,000 ወይም የጠቅላላውን ግብይት መጠን እና ከግብይቱ የተገኘ ማንኛውንም ጥቅም 5% ከሁለቱ የሚበልጠውን<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | (ተ/የ) |
| 10.10. መረጃ በምስጢር መጠበቅ ያለበት መሆኑ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ክብር 100,000 — 150,000 እና/ወይም | (ተ/የ) | (ተ/የ) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | • ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | | |
| | 10.11. የትዕዛዞች ማኅደር | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 100,000 — 150,000 እና/ወይም<br>• ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት ወይም ጥሰቱ እስኪታረም ከሁለቱ መካከል መጨረሻ እስከሚሆነው ድረስ መታገድ | (ተ/የ) | (ተ/የ) |
| 11<br>ዕዳን አለመክፈልና ኪሳራ | በምዕራፍ 11 — “ዕዳን አለመክፈልና ኪሳራ” ሥር ያሉ ደንቦች በሙሉ | • ዕዳው ሳይከፈል ለሚቆይበት ወይም ድርጅቱ ለገበያው ላላሳወቀበት እያንዳንዱ ቀን (ቢበዛ ለ30 ቀናት) ብር 5,000<br>• ጥሰቱ እስኪታረም ድረስ መታገድ<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ እና/ወይም<br>• ገደብ መጣል | (ተ/የ) | (ተ/የ) |

# ቅጽ ሠ ፡ የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓቶችና የግጭት አፈታት ደንቦች

DRAFT

## ክፍል 1 - የቅሬታ አስተዳደርና በግብይት አባላት ላይ የሚወሰዱ የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓቶች

### *ምዕራፍ 1 — የቅሬታ አስተዳደር*

#### 1.1. የቅሬታ አስተዳደር

(1.) ለዚህ ደንብ ዓላማ “ቅሬታ” ማለት የግብይት አባሉ፡-

(ሀ) ደንበኛው የሰጠውን ማንኛውንም ትዕዛዝ ወይም ከደንበኛው ጋር የተደረገን ወይም የተገባን ኃላፊነት ወይም ስምምነት በመተላለፉ ወይም ባለማክበሩ፤

(ለ) የገበያውን ደንቦችና መመሪያዎች በመተላለፉ ወይም ባለማክበሩ፤

(ሐ) በማጭበርበር፣ በቸልተኝነት ወይም በግድየለሽነት ሥራውን በማከናወኑ፤ ወይም

(መ) ደንበኛውን ምክንያታዊ ወይም ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ በመያዙ፤

ደንበኛው የገንዘብ ጉዳት ደርሶብኛል በሚል የአገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት የሚያቀርበው መደበኛ ቅሬታ ነው፡፡

(2.) እያንዳንዱ የግብይት አባል፡-

(ሀ) ከደንበኞቹ ጋር የሚኖሩ አለመግባቶች የሚፈቱበት የመጀመሪያው መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ተገቢውን ውስጣዊ የቅሬታ አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት መዘርጋትና ጠብቆ ማቆየት፤

(ለ) ለነባር ደንበኞቹና ለአዳዲስ ደንበኞቹ ሒሳብ በሚከፈትበት ወቅት በእነዚህ ደንቦች ውስጥ በተደነገገው መሠረት ገበያው ስላሉት የግጭት አፈታት መንገዶች ዝርዝር መረጃ በጽሑፍ ማቅረብ፤

አለበት፡፡

DRAFT

### *ምዕራፍ 2 —የገበያው የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓት*

#### 2.1. ለገበያው ቅሬታ ማቅረብ

(1.) በአንድ የግብይት አባልና በደንበኛው መካከል ያለ አለመግባባት ቅሬታው በቀረበ በአሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ በውስጣዊው የቅሬታ አፈታት መንገድ ካልተፈታ ግብይት ፈጻሚው አባል ወይም ደንበኛው ጉዳዩን ወደ ገበያው ይመራዋል፡፡

(2.) የሚመለከተው የገበያው የሥራ ክፍል ጉዳዩን መርምሮ እንደ ቅሬታው ክብደት ሁለቱን ወገኖች ያሸማግላል፣ የራሱን የደንብ ማስከበር እርምጃ ይወስዳል ወይም ለደንብ ማስከበር እርምጃ የሚሆኑ ምክረ ሐሳቦችን ያቀርባል፡፡

## 2.2. የዲሲፕሊን አካላት

(1.) የሚከተሉት የገበያው የዲሲፕሊን አካላት የገበያውን የየዕለት የዲሲፕሊን እርምጃዎች ያስተዳድራሉ፤

(ሀ) የገበያው ሥራ አመራር፤

(ለ) የንግድ ሥነ ምግባር ጉባዔ ወይም ማንኛውም ሌላ የዳኝነት ጉባዔ፤ ወይም

(ሐ) የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የዳይሬክተሮች ቦርዱ አግባብነት ያለው የገበያ ኮሚቴ፡፡

(2.) ከዚህ በላይ የሚገኙት ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የገበያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ አንድ የግብይት አባል ከእነዚህ ደንቦች መካከል የትኛውንም የሚመለከት ከባድ የሥነ ምግባር ጉድለት ወይም ጥሰት በሚፈጽምበት ጊዜ በዚህ ደንብ ሥር የተቀመጠውን ሥልጣን የመጠቀም መብት የሚኖረው ሲሆን በሚቻለው ፍጥነትም እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን አግባብነት ወዳለው የቦርዱ ኮሚቴ መምራት አለበት፡፡

(3.) ከላይ የተጠቀሱት የዲሲፕሊን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣኖች በተናጠልም ሆነ በጣምራ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ሲሆን እነዚህን ሥልጣኖች በመጠቀም የሚወሰዱ እርምጃዎች ገበያው ከግብይት ፈጻሚው አባል ካሳ እንዲጠይቅ የሚያስችሉትን መብቶች የሚያስቀሩ መሆን የለበትም፡፡

(4.) ማንኛውም ውክልና ቢኖርም ቦርዱ ለገበያው ደንቦች ጥሰት በግብይት ፈጻሚ አባላት እና/ወይም ተሿሚ እንደራሴዎቹ ወይም ሌሎች ሰራተኞች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ የመውሰድ ሥልጠን አለው፡፡

## 2.3. የዲሲፕሊን እርምጃዎች

(1.) ገበያው አንድ የግብይት አባል፣ ተሿሚ እንደራሴው ወይም ሌሎች ሠራተኞቹ የሚከተሉትን ጥሰቶች ሲፈጽሙ በእነዚህ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የዲሲፕሊን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፡-

1.1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ደንቦች ወይም ማንኛውም መመሪያን ከጣሰ ወይም ጥሶ ከነበረ፤ እንዲሁም በእነዚህ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ውስጥ የተሰጠን ሥልጣን ካላከበረ ወይም ከተገዳደረ፤ ወይም እነዚህን ደንቦች እየጣሰ ለሚሠራ ማንኛውም ግብይት ፈፃሚ አባል ከለላ ከሰጠ፣

ከደገፈ ወይም የማሳወቅ ግዴታውን ካልተወጣ ወይም ከግብይት ፈጻሚው አባል ጋር ይህንኑ እያወቀ ስምምነት ከፈጸመ፤

1.2. እነዚህን ድንጋጌዎች ከጣሰ ወይም ጥሶ ከነበረ፤

1.3. ክፍያ የማጣራትና መፈጸም ደንቦችን ከጣሰ ወይም ጥሶ ከነበረ፤

1.4. ቦርዱ በየጊዜው ከሚወስናቸው የፈቃድ ግዴታና ሁኔታዎች መካከል ማንኛውንም ከጣሰ ወይም ጥሶ ከነበረ፤

1.5. በእነዚህ ደንቦችና መመሪያዎች የሚፈለጉትን ወቅታዊ የሪፖርት መግለጫዎች ወይም ዓመታዊ ኦዲት የተደረጉ ሒሳቦችን በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ፤

1.6. አባልነቱን ያገኘው መረጃን በመደበቅ ወይም በማጭበርበር ሲሆን፣ ይህም መረጃ ከእሱ፣ ከአቅራቢው ወይም ከደጋፊው የሚፈለግ እንደሆነ እና ቦርዱ መረጃው ወሳኝነት ያለው እንደሆነ ሲያምን፤

1.7. የማጭበርበር ወይም የሀሰተኝነት የወንጀል ክስ ከቀረበበትና ጥፋተኛ ከተባለ፤

1.8. ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ጋር የሚገናኙ የሕግ ግዴታዎችን ካልተወጣ ወይም መወጣት ካልቻለ፤

1.9. የገበያውን ተዓማኒነት በሚያጠለሽ ወይም የገበያው ዓላማዎች ላይ ጉዳት በሚያደርስ ተግባር ላይ ከተሰማራ፤

1.10. ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በሚገናኝ ያሉበትን ኃላፊነቶች ወይም ግዴታዎች የማይወጣ ስለመሆኑ በገበያው በይፋ ከተነገረ ወይም ከተገለጸ በኋላ ወይም ለግብይት አባላት በሌላ መንገድ እንዲያውቁት ከተደረገ ማንኛውም ሰው፣ አካል፣ ድርጅት፣ ኮርፖሬሽን ወይም ኩባንያ ጋር የሥራ ግንኙነት/ስምምነት ያለው ከሆነ፤

1.11. በአዋጅ፣ በደንቡ፣ በባለሥልጣኑ መመሪያዎች እና የሥነ ምግባር ደንብ እንዲሁም አግባብነት ባለው ህግ፣ መመሪያ ወይም ደንብ ውስጥ በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት በሥነ ምግባር ጉድለት ጥፋተኛ ከሆነ ወይም ከነበረ፤

1.12. ግብይት ካላሳወቀ ወይም እያወቀ ሐሰተኛ ወይም የፈጠራ ግብይት ከፈጸመ ወይም ሪፖርት ካደረገ፤

1.13. ለቦርዱ፣ ለማንኛውም የቦርዱ ኮሚቴ፣ ለዋና ሥራ አስፈጻሚው ወይም ለማንኛውም የገበያው ሠራተኛ ወሳኝነት ያለውን መረጃ አሳስቶ ካቀረበ፤

DRAFT

1.14. እያወቀ ወይም በቸልተኝነት የገበያ መረጃን ወይም ሁኔታን የሚመለከቱና የሚወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ያላቸውን ወይም ተጽዕኖ የማድረግ አዝማሚያ ያላቸውን ሐሰተኛ፣ አሳሳች፣ ወይም ትክክል ያልሆኑ ሪፖርቶችን ካሰራጨ፤

1.15. ከከሰረ በኋላ ግብይት የሚፈጽም ወይም የሚያከናውን ከሆነ፤

1.16. እንዲቀርብ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በቦርዱ፣ በማንኛውም የቦርዱ ኮሚቴ፣ በገበያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፊት ለመቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ፤

1.17. በማንኛውም የዲሲፕሊን ጉዳይ በሚሰማበት ሒደት ወይም ምርመራ ወቅት ለቀረቡለት ጥያቄዎች የተሟላ መልስ ለመስጠት ወይም ሁሉንም መዛግብትን እና ማኅደሮች ለማቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ፤

1.18. በገበያው ሥልጣን በተሰጣቸው ሰዎች ወይም አካላት በሚካሄድ ፍተሻ ወቅት ጥያቄ ሲቀርብለት መረጃዎችን፣ መዛግብትንና ማኅደሮችን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፤

1.19. በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ባለ በማንኛውም ሕግ ከዚህ በተቃራኒው ከተደነገገው በስተቀር በማንኛውም የምርመራ ወይም አሰማም ሒደት በመሳተፍ ያገኘውን ወይም በቦርዱ፣ በማንኛውም የቦርዱ ኮሚቴ፣ በዋና ሥራ አስፈጻሚው ወይም በሌላ ኃላፊ በምስጢር የተነገረውንና በምስጢር መያዝ ያለበትን መረጃ ከተጠቀመ ወይም ከገለጸ፤

DRAFT

1.20. በሚከተሉት መንገዶች አንድ ሰው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እንዲገዛ ወይም እንዲሸጥ ካግባባ ወይም ለማግባባት ከሞከረ፦

(i.) ወሳኝነት ያለውን መረጃ በሐሰተኛነት በመደበቅ፤

(ii.) ሐሰት ወይም አታላይ የሆነን መግለጫ፣ ቃል ኪዳን ወይም ትንበያ በግድየለሽነት፣ በሐሰተኛነት ወይም በሌላ ሁኔታ በመስጠት ወይም በማሳተም ወይም እንዲሰጥ ወይም እንዲታተም በማድረግ፤

(iii.) በማንኛውም ሜካኒካል፣ ኤሌክትሮኒክ ወይም ሌላ መሣሪያ ላይ ወሳኝነት ያለውንና ሐሰተኛ ወይም አሳሳች እንደሆነ የሚያውቀውን መረጃ በመቅዳት ወይም በማከማቸት።

1.21. ከአንድ ደንበኛ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ሽያጭ ወይም ግዢ ትእዛዝ ከተቀበለ በኋላ በገበያው የግብይት ማዕከላት ላይ ትእዛዙ እንዲፈጸም ካላደረገ፤

1.22. ከደንበኛው ኃላፊነት ወይም ሥልጣን ሳይሰጠው ሽያጭ ከፈጸመ፤

1.23. የአባልነት ክፍያውን ወይም የተጣለበትን መቀጮ ካልከፈለ፤

1.24. የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ቀነ ገደብ ካለፈ በኋላ የአባልነት ክፍያን ጨምሮ ለገበያው መክፈል ያለበትን ገንዘብ ሳይከፍል ከቀረ፤

1.25. እነዚህን ደንቦች እንደጣሰ ለሚያውቀው ማንኛውም ግብይት ፈጻሚ አባል ከለላ ወይም እርዳታ ከሰጠ፣ ሪፖርት ካላደረገ ወይም የሥራ ግንኙነት/ስምምነት ካደረገ፤

1.26. በንግድ ሕጉ በተቀመጠው ትርጓሜ መሠረት ኪሳራ ካጋጠመው ወይም ከአበዳሪዎቹ ጋር አግባብነት ያላቸውን በሕግ የተቀመጡ የዕዳ አከፋፈል ስምምነቶች ካደረገ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ከከሰረ፤

1.27. የግብይት አባልነት ለማግኘት ከተቀመጡት ሁኔታዎች የትኛውንም ከጣሰ፤

1.28. ፈቃድ ሳይሰጠው የደንበኛውን ሒሳብ ካዘዋወረ፤ እና/ወይም

1.29. ማንኛውንም የንግድ ሥነ ምግባር ጉባዔ፣ የዳኝነት አካል፣ የገበያውን የዳይሬክተሮች ቦርድ ኮሚቴ ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ካላከበረ፡፡

DRAFT

## 2.4. በገበያው የጉዳይ መኮንኖች የሚወሰድ የደንብ ማስከበር እርምጃ

(1.) በአንድ የግብይት አባል ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ወይም የደንብ ማስከበር እርምጃ ሲቀርብ ይህንኑ በአግባቡ መርምሮ ለገበያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የደንብ ማስከበር እርምጃዎችን በምክረ ሐሳብነት የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት የጉዳይ መኮንን ይመደባል፡፡

(2.) የሚወሰደው የደንብ ማስከበር እርምጃ ከይፋዊ ማስጠንቀቂያ፣ ከዕገዳ ወይም ከግብይት ፈጻሚው አባል የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ ወይም ከብር 100,000 ያልበለጠ የገንዘብ ቅጣት የሚያንስ በሚሆንበት ጊዜ አግባብነት ያለው ቅጣት የሚወሰነው በገበያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 2.5. የንግድ ሥነ-ምግባር ጉባዔ

(1.) የንግድ ሥነ ምግባር ፓነል ከ፡-

(ሀ) ሦስት (3) የገበያው መኮንንኖች እና

(ለ) ሁለት (2) የገበያው አባላት ተወካዮች፣ የተመዘገቡ ኩባንያዎች ተወካዮች፣ ሌሎች በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት አቅራቢዎች እና/ወይም ሌሎች ገለልተኛ ባለሞያዎች የሚውጣጣ ሲሆን ይፋዊ ማስጠንቀቂያን፣ ዕገዳን ወይም የአንድ ግብይት ፈጻሚ አባል የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛን እንዲሁም ከብር 100,000 የሚበልጥ የገንዘብ ቅጣትን ሊያስከትል የሚችል የእነዚህን ደንቦችና መመሪያዎች ድንጋጌዎችና ማንኛውም አግባብነት ያለውን የሌላ ሕግ ጥሰት በሚመለከት፡-

(ሀ) ኢንቨስተሮች በግብይት አባላት ላይ የሚያቀርቧቸውን ቅሬታዎች ይሰማል፤

(ለ) ገበያው መውሰድ ስላለበት የደንብ ማስከበር እርምጃ ምክረ-ሐሳቦችን ያቀርባል፤

## 2.6. ማስረጃ ማቅረብና በንግድ ሥነምግባር ጉባዔ ፊት መቅረብ

(1.) አንድ የግብይት አባል ለምርመራ የሚያስፈልጉ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶችና ማስረጃዎች በሙሉ ለገበያው ያቀርባል።

(2.) ገበያው የሚይዛቸው የግብይቶች የኮምፒውተር ማኅደሮች የግብይት አባላት ለፈጸሟቸው ግብይቶች በማስረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ።

(3.) አንድ የግብይት አባልና ማንኛውም ሠራተኛው ከጉባዔ መጥሪያ ሲደርሳቸው በጉባዔ ፊት ቀርበው በይዞታቸው ወይም በቁጥጥራቸው ሥር ያሉና ምርመራ እየተካሄደበት ከሚገኘው ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎች፣ መዛግብት፣ ሒሳቦችና ሰነዶች ያቀርባሉ።

(4.) ጉባዔው ማንኛውንም ምርመራ ካካሄደና ለገበያው የጽሑፍ ሪፖርት ካዘጋጀ ጉዳዩ የሚመለከተው የግብይት ፈጻሚ አባል የሪፖርቱ ቅጂ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት አለው።

## 2.7. ምርመራ እስኪጠናቀቅ መታገድ

አንድ የግብይት አባል እና/ወይም ሠራተኞቹ እነዚህን ደንቦች በመጣስ ወይም በሞያዊ ሥነ-ምግባር ጉድለት ምርመራ እየተደረገባቸው ከሆነ ገበያው  እንደ አግባብነቱ ሁኔታ አስቀምጦ ወይም ሳያስቀምጥ የግብይት አባሉን እና/ወይም ማንኛውንም የግብይት አባሉን ሌላ ሠራተኛ የማገድ ስልጣን አለው።

## 2.8. የመስማትና የመዳኘት ሥልጣን

(1.) ጉባዔው የቀረቡትን የዲሲፕሊን ጉዳዮች ለመስማትና ለመዳኘት በማንኛውም ጊዜ ጉባዔ ሊጠራ ይችላል። በእንዲህ ባለው ጉባዔ በግብይት አባል ላይ በቂ የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ክስ እንደተቋቋመ ከተረጋገጠ፣ ጉባዔው የግብይት አባሉ ወይም ማንኛውንም ተሿሚ እንደራሴው ወይም ሌላ ሠራተኛው ጉባዔ ላይ ቀርቦ ከጉዳዩ ጋር በተገናኘ ስለ ተግባሩ እንዲያስረዳ መጠየቅ አለበት።

(2.) ገበያው የጉባዔውንመጥሪያ እንዳደረሰ የሚቆጠረው፡-

(ሀ) መጥሪያው የሚመለከተው ሰው በሰጠው አድራሻ በአካል ወይም ደግሞ በኤሌክትሮኒክ ሜይል እንዲደርሰው ከተደረገ ወይም ይህ ሊሆን ካልቻለ ደግሞ፤

(ለ) መጥሪያው መጨረሻ በሚታወቀው የግብይት አባሉ አድራሻ ሲለጠፍና በገበያው መካነ ድር ላይ ይፋ ሲደረግ ወይም የግብይት አባሉ ስለ

ሒደቱ በቂ መረጃ ይደርሰዋል ተብሎ በሚታሰብ ማንኛውም ሌላ መንገድ እንዲያውቀው ሲደረግ ነው

## 2.9. በጉባዔው ፊት በሕግ ባለሞያ መወከል

አንድ የግብይት አባል በማንኛውም የዲሲፕሊን ጉዳይ(ዎች) በሚካሄድ ጉባዔ ላይ በጠበቃ ወይም በሕግ አማካሪ ወይም በሌላ የግብይት አባል የመወከል ወይም በእሱ(ሷ) ምትክ ሐሳብ የማቅረብ መብት አለው፡፡

## 2.10. የሒደቶች መዝገብ

(1.) ማንኛውም ውሳኔ በአንድ ግብይት አባል ላይ የተወሰደ የዲሲፕሊን እርምጃ በዝርዝር አሟልቶ መጥቀስ የሚኖርበት ሲሆን ይህም በጉባዔው የቃለ ጉባዔ መዝገብ ላይ ይመዘገባል፡፡

(2.) ገበያው ጥያቄ ሲቀርብለት ክፍያ በማስከፈል በግብይት አባሉ ላይ እንዲወሰዱ የተወሰኑ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን በጊዜ ቅደም ተከተል ሁሉንም ውሳኔዎች የያዘ የሂደት መዝገብ ያቀርባል፡፡ የሂደት መዝገቡ ስለውሳኔው የመጨረሻ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡

## 2.11. የጉባዔው ውሳኔዎች

(1.) አንድ የግብይት አባል የገበያውን ደንቦች ጥሶ በተገኘባቸው ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ጉባዔው መወሰድ ያለባቸውን የዲሲፕሊን እርምጃዎች በምክረ-ሐሳብነት ለዋና ሥራ አስፈጻሚው ያቀርባል፡፡

(2.) በዋና ሥራ አስፈጻሚ ውሳኔ ላይ የሚኖሩ ይግባኞች አግባብነት ላለውና በገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ለተቋቋመ ኮሚቴ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

(3.) አግባብነት ያለው የገበያ ኮሚቴ በሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ ቅር የተሰኘ ሰው ይግባኙን ወደ ባለ ሥልጣኑ ሊወስድ ይችላል፡፡

## 2.12. የገበያው የመቅጣት ሥልጣን

(1.) የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ማንኛውም በቦርዱ የተወከለ አካል፣ ተቋም ወይም ኮሚቴ በጉባዔው ላይ ወይም ጉባዔው ከተጠናቀቀ በኋላ የግብይት አባል ያቀረበውን ማብራሪያ ከግምት ውስጥ በማስገባት በግብይት አባሉ ላይ የቀረበው አቤቱታ በማስረጃ እንደተረጋገጠ ካመነ በግብይት አባሉ ወይም በተሿሚ እንደራሴዎቹ ወይም በማንኛውም ሠራተኛ ላይ ማንኛውንም የዲሲፕሊን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣኑን ሊጠቀም ይችላል፡፡

(2.) ቦርዱ ወይም ማንኛውም በቦርዱ የተወከለ ተቋም ወይም አካል የግብይት አባሉ ወይም ተሿሚ እንደራሴው ወይም ማንኛውም ሠራተኛው ቦርዱ ወይም ማንኛውም በቦርዱ የተወከለ ኮሚቴ በጠራው ጉባዔ ላይ እንዲገኝ በአግባቡ ጥሪ ከተደረገለት በኋላ ካልተገኘ በሚመለከተው የግብይት አባል ላይ ማንኛውንም የዲሲፕሊን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣኑን መጠቀም ይችላል፡፡

DRAFT

### 2.13. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

(1.) የገበያውን ደንቦች ጥሶ በተገኘ የግብይት አባል ላይ የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ቦርዱ የወከለው ማንኛውም ተቋም ወይም አካል የሚጥለው ቅጣት በቅጣቶች ሰንጠረዥ መሠረት ከዚህ በታች ከተጠቀሱት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን በማጣመር ይሆናል፡-

(ሀ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ፤

(ለ) ከገበያው አባልነት ማገድ፤

(ሐ) የአባልነት ምስክር ወረቀት መሰረዝ፤

(መ) የተሿሚ እንደራሴ ምዝገባን መሰረዝ፤

(ሠ) የግብይት አባልን ተቀጣሪ ወይም ሌላ ሠራተኛ ማሰናበት ወይም ማገድ፤

(ረ) በግብይት አባል ተሿሚ እንደራሴዎች፣ ተቀጣሪዎች ወይም ሌሎች ሠራተኞች ላይ ገደብ መጣል፤

(ሰ) የገንዘብ መቀጮ መጣል፤

(ሸ) የመተካት እና/ወይም የካሳ ትዕዛዝ መስጠት፤

(ቀ) የአስዳደራዊ ክፍያዎችን ማስከፈል፤ እና/ወይም

(በ) ገበያው በየጊዜው የሚያስቀምጠውን ማንኛውም ሌላ ቅጣት፡፡

(2.) ደንቦቹ እና/ወይም የቅጣት ሰንጠረዡ አንድ ጥሰት የሚያስከትለውን ቅጣት ካላስቀመጡ የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ቦርዱ የሚወክለው ማንኛውም ሌላ ተቋም ወይም አካል ሁኔታውን በማገናዘብ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምነውን ቅጣት ወይም እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

(3.) ማንኛውም የታገደ የግብይት አባል በዚህ ደንብ መሠረት አንድ አባል ከሚኖረው መብቶችና ልዩ ጥቅሞች ይታገዳል፡-

(4.) አንድ የግብይት አባል በማንኛውም ምክንያት ሲታገድ፡-

(ሀ) ለካሳ ፈንድ ገቢ የሚሆን፣ ለግብይት ማጣሪያ ፈንድ የሚያስፈልጉትን እንዲሁም በእነዚህ ደንቦች የተደነገጉትን ጨምሮ ለገበያው የሚከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ የግብይት አባሉ እንዳልታገደ ተቆጥሮ መከፈል ያለባቸው ናቸው፡፡

(ለ) ገበያው ላልተፈቀዱ ሽያጮች መተኪያ በሚል ካልፈቀደለት በቀር የግብይት አባሉ በዕገዳው ወቅት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግብይት መፈጸም አይችልም፡፡

DRAFT

(ሐ) ዕገዳው የግብይት አባሉ ከዕገዳው በፊት ካደረጋቸው ግብይቶች ጋር በተገናኘ የፈጸማቸውን ውሎች፣ ግብይቶች ወይም ስምምነቶች ቀሪ ለማድረግ ወይም የጸኑ በመሆናቸው ወይም በተፈጻሚነታቸው ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡

(መ) የግብይት አባሉ ከዕገዳው በፊት ከደንበኞች የተቀበላቸውን መመሪያዎች እንዲፈጽም ለሌላ ግብይት አባል መመሪያ የመስጠትና የመሰየም ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህንኑም ወዲያውኑ በጽሑፍ ለገበያው ማሳወቅ አለበት፡ ፡ የግብይት አባሉ ሲታገድና ሌላ የግብይት አባል ሲሰይም የተሰየመው ድርጅት ለሚፈጸሙት ግብይቶች ሙሉ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለበት፡ ፡

(ሠ) የግብይት አባሉ በመታገዱ ምክንያት ደንበኞቹ ምንም ዓይነት ኪሳራ ወይም ሀፍረት እንዳያጋጥማቸው የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡

(5.) የአንድ የግብይት አባል የአባልነት ምስክር ወረቀት ሲሰረዝ ወዲያውኑ በገበያው ላይ የመገበያየት መብቶቹን ያጣል፡፡

(6.) የአንድ የግብይት አባል የአባልነት ምስክር ወረቀት የሚሰረዘው በገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ላይ በአብላጫ ድምጽ እንዲሰረዝ ውሳኔ ሲተላለፍ ነው፡፡ በእንዲህ ባለው ስብሰባ ላይ ውሳኔው የሚተላለፈው በስብሰባው ከተሰጡት ድምጾች በአብላጫ ድምጽ ነው፡፡

### 2.14. የገበያ አባልነት መቋረጥ

ማንኛውም ከአባልነት የተሰረዘ የግብይት አባል ወደ አባልነት የሚመለሰው ስረዛው በባለሥልጣኑ ወይም በካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ከተቀለበሰ ብቻ ነው፡፡

### 2.15. የዲሲፕሊን እርምጃ ማስታወቂያ

(1.) ገበያው በአንድ የግብይት አባል ላይ ማንኛውንም የዲሲፕሊን እርምጃ በወሰደ በሁለት (2) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ይህ ማስታወቂያ የግብይት አባሉን ስም፣ እርምጃው የተወሰደበትን ምክንያት፣ የመቀጮ መጠንና ዓይነት እንዲሁም የዕገዳውን ጊዜ ያካትታል፡፡ ገበያው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንድ የግብይት አባል ከአባልነት መሰረዙን ለሌሎች ተቆጣጣሪ አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡

(2.) ገበያው ተገቢ ነው ብሎ ባመነው መንገድ አንድ የግብይት አባል የአባልነት ምስክር ወረቀት መሰረዙን ወይም በሌላ ምክንያት አባል መሆን ማቆሙን ወይም መታገዱን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ወይም ይፋ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡ በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ የግብይት አባሉን ስም ወይም የግብይት አባሉ መታገዱን ወይም ፈቃዱ መሰረዙን እንዲሁም የግብይት አባሉን ስም ሊያካትት ይችላል፡፡

DRAFT

## 2.16. የይግባኝ ምክንያቶች

(1.) ከሚከተሉት በማንኛውም ወይም በሁሉም ምክንያቶች ለካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡-

(ሀ) የዳኝነት ሥልጣን አለመኖር፤

(ለ) የሥነ-ሥርዓት መጓደል፤

(ሐ) የፍሬ ነገር ወይም የሕግ ስህተቶች፤

(መ) የማስረጃ አለመኖር፤ ወይም

(ሠ) ማጭበርበር፡፡

(2.) የአንድ የግብይት አባል ይግባኝ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ማግኘቱ ግብይት አባሉ በፅግዱ ምክንያት ላጋጠመው ኪሳራ (ትርፍ አለማግኘትን ጨምሮ) ወይም የመልካም ስም ጉዳት በገበያው ወይም በተወካዮቹ ላይ ክስ የመመስረት መብትን አያጎናጽፈውም፡፡

DRAFT

## ክፍል 2 - ሌሎች የቅሬታ አስተዳደር ሥነ-ሥርዓቶች

### *ምዕራፍ 3 - በገበያው ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አቀራረብና አስተዳደር*

## 3.1. የቅሬታዎች አቀራረብ

(1.) አባላትና ባለድርሻ አካላት ቅሬታዎቻቸውን በጽሁፍ በቁስ አካላዊ ሰነዶች ወይም የኤሌክትሮኒክ መንገዶችን ጨምሮ ገበያው ለዚሁ በሚያዘጋጀው የቅሬታ ማቅረቢያ መድረክ አማካኝነት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

(2.) ቅሬታዎች የቅሬታ አቅራቢውን ስም፣ የግንኙነት አድራሻ፣ ግልጽ የሆነ የቅሬታ ወይም የመረጃ ጥያቄ መግለጫ፣ ተፈጻሚነት ካለው አግባብነት ያላቸውን የግብይት ዝርዝሮችና ማንኛውንም ደጋፊ ሰነድ ማካተት አለባቸው፡፡

(3.) ገበያው ቅሬታዎች ሲደርሱት ሁሉም ተፈላጊ መረጃዎች መቅረባቸውን ለማረጋገጥ የመጀመሪያ ደረጃ ቅኝት ያደርጋል፡፡ አስፈላጊ ዝርዝሮች ያልተሟሉባቸው ቅሬታዎች ተሟልተው እንዲቀርቡ ለቅሬታ አቅራቢዎች ሊመለሱ ይችላሉ፡፡

## 3.2. ኤሌክትሮኒክ የቅሬታዎች መዝገብ

(1.) ገበያው የሚከተሉትን መረጃዎች የሚያካትት ኤሌክትሮኒክ የቅሬታዎች መዝገብ ሊኖረው ይገባል፡-

(ሀ) ጥያቄውን ወይም ቅሬታውን የተቀበለበትን ቀን፤

(ለ) የቅሬታ አቅራቢውን መረጃ (ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ የኢሜይል አድራሻን ጨምሮ)፤

(ሐ) የጥያቄውን ወይም የቅሬታውን ዓይነትና ዝርዝር፤

(መ) የተወሰደ እርምጃ/አሁናዊ ሁኔታ፤ እና

(ሠ) ቅሬታው የተፈታበትን ቀን።

## 3.3. የቅሬታና የጉዳይ መኮንን ምደባ

(1.) በገበያው ላይ የሚኖሩ ቅሬታዎች መቅረብ ወይም መመራት ያለባቸው ገበያው በየጊዜው በሚያስታውቀው መሠረት ለዚሁ ዓላማ ወደ ተመደበው የቅሬታ መኮንን ወይም አግባብነት ወዳለው የጉዳይ መኮንን ነው።

(2.) እያንዳንዱ ቅሬታ የተሟላ ምርመራ የማድረግ ኃላፊነት ላለው የጉዳይ መኮንን ይመራል።

(3.) የጉዳይ መኮንኑ ከቅሬታ አቅራቢው ጋር የመገናኘት፣ አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ መረጃ የመሰብሰብ እንዲሁም አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር የማስተባበር ኃላፊነት አለበት።

(4.) መኮንኑ ቅሬታው ወይም ጥያቄው እንደደረሰው ለክትትል፣ ለስነዳና ለሪፖርት ማጠናቀር ዓላማ ወዲያውኑ አግባብነት ላላቸው የገበያው መኮንኖች የቅሬታውን ወይም የጥያቄውን ዝርዝር ማቅረብ አለበት።

## 3.4. የቅሬታዎች አስተዳደር

ገበያው አንድ ቅሬታ ሲደርሰው የቅሬታ ወይም ጉዳይ መኮንኑ ቅሬታው እንደደረሰው የሚከተሉትን ለማረጋገጥ የሚቻለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለበት፡-

(1.) አግባብነት ያላቸው የቅሬታው ወይም የጥያቄው ዝርዝሮች ወዲያውኑ መመዝገባቸውን፤

(2.) ከዚህ በታች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በመኮንኑ መልስ መሰጠቱን፡-

(ሀ) በፖስታ ወይም በኢሜይል ለገበያው የደረሱት ቅሬታዎች በደረሱ በሁለት (2) የሥራ ቀናት ውስጥ ስለመድረሳቸው ዕውቅናና መልስ መሰጠቱን፡ ፡

(ለ) ቅሬታዎች በደረሱት በአሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ በመጀመሪያ እርከን መፈታታቸውን።

(ሐ) አንድ ቅሬታ/ወይም ጥያቄ ከላይ በተቀመጠው ቀነ ገደብ ውስጥ ሊፈታ የማይችል ከሆነ ቅሬታ አቅራቢው ጉዳዩ ምርመራ እየተደረገበት መሆኑን እንዲያውቅ መደረግ አለበት።

DRAFT

### 3.5. ቅሬታዎችን መመርመርና መፍታት

(1.) የሚቀርቡ ቅሬታዎች በሙሉ የሚመለከቷቸውን የሥራ ክፍሎችን ወደሚመሩ ከፍተኛ ሥራ መሪዎች ይቀርባሉ፡፡

(2.) ቅሬታውን ተከትሎ ምርመራ ከተደረገ በኂላ ቅሬታው ለገበያው በደረሰ በአሥር (10) ቀናት ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ግኝቶችን የያዘ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በማናቸውም ሁኔታዎች ከውሳኔ ለመድረስ ምክንያቶቹ እንዲታወቁ መደረግ አለበት፡፡

(3.) የመጀመሪያ ደረጃ ግኝቶች በሚመለከታቸው የገበያው ውስጣዊ ወገኖች ውይይት ይደረግባቸዋል፤ ቅሬታው ለገበያው በደረሰው በአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥም ለቅሬታ አቅራቢው የመፍትሔ ሐሳብ ይቀርብለታል፡፡

(4.) ቅሬታ አቅራቢው በውሳኔው ምክረ-ሐሳብና በመፍትሔ ሐሳቡ ካልረካ ቅሬታውን ወደ ገበያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሊወስደው ይችላል፡፡

(5.) ዋና ሥራ አስፈጻሚው መፍትሔውን ሊያሻሽል ወይም ሊያጸና ይችላል፡፡

(6.) ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን ወደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከወሰደው በኂላ አሁንም በውጤቱ ካልረካ ገበያው ቅሬታውን አጥጋቢ ባልሆነ መልኩ የተፈታ ቅሬታ አድርጎ ይወስደዋል፡፡

### 3.6. ውሳኔን ማሳወቅ

(1.) ገበያው የግኝቶችና የተወሰዱ እርምጃዎችን ዝርዝር የያዘ ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ይሰጣል፡፡

(2.) እንደ አግባብነቱ ወደፊት ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይከሰቱ ለመከላከል የማስተካከያ እርምጃዎች ይቀመጣሉ፡፡

### 3.7. ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ይግባኝ

ቅሬታ አቅራቢው በገበያው ቅሬታ አፈታት ካልረካ ቅሬታው እንዲፈታ ለባለሥልጣኑ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

## *ምዕራፍ 4 - በግብይት አባላት መካከል የሚከሰቱ የፍትሐ ብሔር አለመግባባቶችን መፍታት*

### 4.1. በግብይት አባላት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን መፍታት

(1) እነዚህን ደንቦች ካለማክበር በግብይት አባላት መካከል የሚከሰት ማንኛውም አለመግባባት ወዲያውኑ ለገበያው ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡

(2) ማንኛውም በዚህ ክፍል ሥር ለአለመግባባት አፈታት የተቀመጡትን ሒደቶች አሟጥጦ ያልተጠቀመ የግብይት አባል በግብይት አባልነት የግብይት

እንቅስቃሴዎቹ የሚመነጭንና በሌላ የግብይት አባል ላይ የሚኖረውን መብት ለማስከበር የሕግ እርምጃዎችን መውሰድ አይችልም፡፡

(3) ገበያው በእነዚህ ደንቦች መሠረት ራሳቸውን በራሳቸው እንደሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ከሚያከናውናቸው ተግባራት ወይም በሚወስናቸው ውሳኔዎች ላይ ወይም ውሳኔዎቹን ተግባራዊ ከማድረጉ ጋር በተያያዘ ከሚፈጽማቸው ወይም ሳይፈጽም ከሚቀራቸው ድርጊቶች በመነሳት አንድ የግብይት አባል፣ ደንበኛ ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ወገን ማንኛውንም የመብት ጥያቄ ወይም ተጠያቂነት አያነሳም ወይም ክስ አይመሠረትም፡፡

*ምዕራፍ 5 - ገበያው የሚያስተባብረው ሽምግልና*

## 5.1. ሽምግልና

(1.) በግብይት አባላት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በሙሉ በመጀመሪያ ለሽምግልና ይቀርባሉ፡፡

(2.) የንግድ ሥነ-ምግባር ጉባኤው ለአለመግባባቱ ሰላማዊ መፍትሔ ለማምጣት እንደ አሸማጋይ ሆኖ ያገለግላል፡፡

(3.) ተፈጻሚነት ሊኖረው በሚችልበት ሁኔታ ማኔጂንግ ዲሬክተር/ዋና ሥራ አስፈጻሚውና በአግባቡ የተሰየመው የግብይት አባሉ ወኪል በጉባዔው ላይ እንዲገኙ ማሳወቂያ ሲደርሳቸው "ገበያው በሚያስተባብረው ሽምግልና" ላይ በጉባዔው ላይ በመገኘት በድርጅቱ ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ያሉና ከአከራካሪው ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎች መስጠትና መዛግብት፣ ሒሳቦችና ሰነዶችን ማቅረብ አለባቸው፡፡

(4.) ዋና ዳይሬክተሩ /ዋና ሥራ አስፈጻሚው መገኘት የማይችሉበት ሁኔታዎች ሲከሰቱ፣ በጉባዔው መገኘት የማይችልበትን አሳማኝ ምክንያትና በጉባዔው ላይ የሚገኘውን የግብይት ፈጻሚውን አባል ተሿሚ እንደራሴ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ ለገበያው መስጠት አለበት፡፡

(5.) የሽምግልና ፓነሉ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በሰላም እንዲፈቱ ገለልተኛ በሆነና አድልዎ በሌለው መንገድ እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

(6.) ሰላማዊ መፍትሔ ላይ መድረስ ከተቻለ የሽምግልና ፓነሉ የተደረሰውን ስምምነት በሚያዘጋጀው ሪፖርት ውስጥ ካሰፈረ በኋላ ተከራካሪ ወገኖች እንዲፈርሙበት ይደረጋል፡፡

(7.) ተከራካሪ ወገኖች አለመግበባቱን መፍታት ካልቻሉና ቢያንስ የአሥር (10) ቀናት የማሰላሰያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ከመካከላቸው አንደኛው የግልግል ዳኝነት ሒደትን ሊያስጀምር ይችላል፡፡

DRAFT

## 5.2. የዕርቅ ስምምነትን ወይም የመተካት ትዕዛዝን ወይም ስለመተካት የሚደነግግ የዕርቅ ስምምነትን አለማክበር

(1.) *የዕገዳ ወይም የስንብት ማስጠንቀቂያ*

(ሀ) አንድ የግብይት አባል ወይም በአግባቡ የተሾመ እንደራሴው ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ በገበያው ሥልጣን ሥር ያለ ሰው በእነዚህ ወይም በሌሎች የገበያው ደንቦች መሠረት ከተፈጸመ ሽምግልና ጋር የሚያያዝን የዕርቅ ስምምነት ካላከበረ ገበያው ለግብይት ፈጻሚው አባል ወይም በአግባቡ ለተሾመው እንደራሴው ማስጠንቀቂያው በደረሳቸው በሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ውስጥ ስምምነቱን አለማክበር የሚከተሉት ውጤቶች እንደሚኖሩት የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይችላል፡-

(i.) ጉዳዩ የግብይት አባልን የሚመለከት ከሆነ የግብይት አባሉ በተፋጠነ ሁኔታ እንደሚታገድ ወይም የአባልነት የምስክር ወረቀቱ እንደሚሰረዝ፤ ወይም

(ii.) ማንኛውንም ሌላ ሕጋዊ ሰው የሚመለከት ከሆነ የዕርቅ ስምምነቱ በተሟላ ሁኔታ እስኪፈጸም ድረስ ከማንኛውም የግብይት አባል ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ማገድ፡፡

(ለ) አንድ የግብይት አባል ወይም የግብይት አባሉ ተሿሚ እንደራሴ በገበያው ደንቦች መሠረት የሚደረግ የዕርቅ ውሳኔን ወይም ከሽምግልናው ጋር የሚገናኝን ስምምነት ካላከበረ መክፈል አለመቻልን እንደመከላከያ ማቅረብ አይችልም፡፡

(2.) *የዕገዳ ወይም የስንብት ማስጠንቀቂያ ማድረስ*

በዚህ ደንብ ንዑስ ደንብ (1) ሥር ከተገለጸው ሽምግልና ጋር የሚያያዘውን የዕርቅ ስምምነት ያለማክበር ማስጠንቀቂያ ለግብይት ፈጻሚው አባል፣ ከግብይት ፈጻሚው አባል ጋር ግንኙነት ሳለው ሰው ወይም በሌላ ሁኔታ በገበያው ሥልጣን ሥር ላለ ሰው እንዲደርስ የሚደረገው በእነዚህ ደንቦች ውስጥ ስለ ማስጠንቀቂያዎች አሰጣጥ ከተደነገገው ጋር በተጣጣመ መንገድ ነው፡፡

(3.) *የማስጠንቀቂያው ይዘት፡-*

(ሀ) በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ገበያው የሚወስደው እርምጃ ከዕገዳ ወይም ከስንብት የትኛውን እንደሆነና እና ለዚህም መሠረት የሆኑትን ምክንያቶችና የፍሬ ነገር ዝርዝሮች ማካተት እንዲሁም የእርምጃው ተፈጻሚ የሚሆንበትን ጊዜና መልስ ሰጪው እርምጃውን ለማስቀረት ማድረግ ያለበትን ነገሮች ማብራራት አለበት፡፡

DRAFT

(4.) (ለ) ማስጠንቀቂያው መልስ ሰጪው የመሰማት ዕድል እንዲሰጠው በጽሑፍ ለገበያው ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችል የሚገልጽ መሆን አለበት፣ እንዲሁም ይህ ጥያቄው መቅረብ ያለበትንን የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ የሚኖርበት ሲሆን፣ የጊዜ ገደቡም ማስጠንቀቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ያነሰ መሆን የለበትም፡፡ዕገዳው ወይም ስንብቱ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ግብይት ፈጻሚው አባል ወይም ማስጠንቀቂያው የደረሰው ሰው ባቀረበው ጥያቄ መሠረት በገበያው ካልተራዘመ በስተቀር በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣውና ለመልስ ሰጪው እንዲደርሰው በሚደረገው ማስጠንቀቂያ ውስጥ የሚጠቀሰው ዕገዳ ወይም ስንብት ማስጠንቀቂያው ለመልስ ሰጪው ከደረሰው ከሃያ አንድ (21) ቀናት በኂላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

(5.) የመሰማት ጥያቄ

(ሀ) አንድ የግብይት አባል ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ማስጠንቀቂያ የደረሰው ሰው ለሽምግልናው የዕርቅ ስምምነት ተገዢ አለመሆኑን በሚመለከት የመሰማት ጥያቄውን ለገበያው ማቅረብ ይችላል፡፡

(ለ) የመሰማት ጥያቄ በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከተው መሠረት ማስጠንቀቂያው ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን በፊት መቅረብ አለበት፡፡ የመሰማት ጥያቄው ገበያው ለሚወስደው እርምጃ የሚያቀርብ(ቡ) መከላከያ (ዎች)ን በሙሉ በዝርዝር መጥቀስ አለበት፡፡

(6.) የመሰማት ጥያቄ አለማቅረብ

አንድ የግብይት አባል በጊዜ ገደቡ ውስጥ የመሰማት ጥያቄ ካላቀረበ ማስጠንቀቂያው ለመልስ ሰጪው ከደረሰው ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት በኂላ የተጠቀሰው ዕገዳ ወይም ስንብት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ማስጠንቀቂያውም የመጨረሻው የገበያው እርምጃ ይሆናል፡፡

(7.) ዕገዳ እንዲነሳ የሚቀርብ ጥያቄ

በዚህ ደንብ መሠረት የታገደ አንድ የግብይት አባል ወይም ሰው፣ ማስጠንቀቂያውን ወይም ውሳኔውን በተሟላ ሁኔታ ማክበሩን መሠረት በማድረግ ዕገዳው እንዲነሳለት ጥያቄውን በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ለገበያው መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ገበያውም በበቂ ምክንያት የቀረበውን እፎይታ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5.3. በየግብይት አባል ማኅደሮች ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች

(1.) በግብይት አባል የግብይት ማኅደር ላይ ማንኛውንም ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው አንድ አለመግባባት ሪፖርት ከተደረገና ገበያው ውሳኔ ከሰጠበት በኂላ ነው፡፡ ይህ ውሳኔ የመጨረሻ፣ የጸና እና በሚመለከታቸው ወገኖች ላይ አስገዳጅነት የሚኖረው ነው፡፡

DRAFT

(2.) አንድ ቅሬታ የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛን ሊያስከትል የሚችል የገበያ ደንብ ጥሰትን የሚመለከት ከሆነ ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ገበያው የንግድ ሥነ ምግባር ፓነል ይመራል፡፡

*ምዕራፍ 6 - የግልግል ዳኝነት*

### 6.1. የግልግል ዳኝነት

በግብይት ፈጻሚ አባላት መካከል እንዲሁም በግብይት ፈጻሚ አባላትና በገበያው መካከል የሚፈጠሩና ምክንያታዊ በሆነና በማንኛውም ሁኔታ ደግሞ ከ30 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በሽምግልና ሊፈቱ የማይችሉ የፍትሐ ብሔር አለመግባባቶች በሙሉ የሚፈቱት በግልግል ዳኝነት ነው፡፡

### 6.2. የግልግል ዳኝነት መጀመር

(1.) የግልግል ዳኝነት ሒደቱን የሚያስጀምረው ወገን ("አመልካች") የአለመግባባቱን ሁኔታ፣ የሚጠይቀውን ዳኝነት እንዲሁም ስለ ግልግል ዳኞች አሰያየም ያለውን ምክረ-ሐሳብ የያዘ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለሌላኛው ወገን ("መልስ ሰጭ") መስጠት አለበት፡፡

(2.) ክሱ የቀረበው በአንድ የግብይት አባል ላይ ሲሆን ገበያው ማመልከቻው ሲደርሰው የክስ አቤቱታውን እና ተያያዥ ሰነዶችን ቅጂ ለመልስ ሰጭ ማስተላለፍ አለበት፡፡

DRAFT

(3.) መልስ ሰጭ፣ በምክረ-ሐሳብነት የቀረበውን የግልግል ዳኞች አሰያየም ጨምሮ ለተሰጠው ማስጠንቀቂያ በሃያ (20) የሥራ ቀናት ውስጥ መልስ መስጠት አለበት፡፡

(4.) መልስ ሰጭ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ መልስ ካልሰጠ ገበያው ተጨማሪ ሁለት የግልግል ዳኞችን ይሰይማል፤ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የግልግል ዳኝነት ሥነ-ሥርዓቱን አስቀጥሎ መልስ ሰጭ በሌለበት ውሳኔውን የሚሰጥ ይሆናል፡፡

### 6.3. የግልግል ዳኝነት ጉባዔ

የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በገበያው አባላት መካከል እና/ወይም በገበያው አባላትና በደንበኞቻቸው መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመዳኘት ሥልጣን ያለው ገለልተኛ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡

### 6.4. የግልግል ዳኝነት መድረክ

(1.) ሁለቱ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር ገበያው የአለመግባባቱ ወገን በሆነባቸው ጉዳዮች ሁሉ የግልግል ዳኝነቱ ማዕከል የሚሆነው የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት ኢንስቲትዩት ወይም የኢትዮጵያ የማስማማትና የግልግል ዳኝነት ማዕከል ነው፡፡

(2.) በግብይት አባላት መካከል የሚፈጠሩ ሌሎች አለመግባባቶች የክርክሩ ወገኖች የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት ኢንስቲትዩትን ወይም የኢትዮጵያ የማስማማትና የግልግል ዳኝነት ማዕከልን በግልግል ዳኝነት ማዕከልነት እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ፡፡

(3.) በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተጠቀሱት ማዕከላት የግልግል ዳኝነት ደንቦች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

### 6.5. የግልግል ዳኞች ጉባዔ ማቋቋም

(1.) ሁለቱ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒው ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር አለመግባባቶች የሚመሩት ሦስት የግልግል ዳኞች ወዳሉት ጉባዔ ነው፡፡

(2.) ገበያው ተገቢ ነው ብሎ እንደሚያምነው አስፈላጊው ብቃት፣ ልምድና ዕውቀት ያላቸውንና በግልግል ዳኝነት ለማገልገል ብቁ የሆኑ ሰዎችን ስም ዝርዝር ያቀርባል በየጊዜውም ይህን ዝርዝር ያዘምናል፡፡

(3.) እያንዳንዱ ወገን አንድ የግልግል ዳኛ ይሰይማል፡፡ ሁለቱ የግልግል ዳኞች ሦስተኛውን የግልግል ዳኛ ይሰይማሉ፡፡

(4.) መልስ ሰጭ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያው በደረሰው በሃያ (20) የሥራ ቀናት ውስጥ የግልግል ዳኛ(ኞች) ካልሰየመ ገበያው ወይም ለዚሁ የተሰየመው የግልግል ዳኝነት ተቋም ጥያቄ ሲቀርብለት የግልግል ዳኛ (ዳኞቹን) ይሰይማል፡ ፡

### 6.6. የሥነ-ሥርዓት ደንቦችን መወሰን

(1.) ሁለቱ ወገኖች በመስማማት የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ተፈጻሚ የሚያደርገውን የሥነ-ሥርዓት ደንብ መወሰን ወይም ውሳኔ እንዲሰጥበት በኢትዮጵያ ውስጥ ለታወቀ የግልግል ዳኝነት ማዕከል ሊመሩት ይችላሉ፡፡

(2.) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተወሰነ የሥነ-ሥርዓት ደንብ ከሌለ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ተገቢ ነው ብሎ ያሰበውን የሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወስናል፡፡ ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው የተሰጠው የሥነ-ሥርዓት ደንቦችን የመወሰን ሥልጣን ማስረጃዎች ተቀባይነት ያላቸው፣ ተዛማጅነት ያላቸው ስለመሆኑ እንዲሁም የማስረጃዎች አመዛዘን ጉዳዮችንም ይጨምራል፡፡

### 6.7. ተከራካሪ ወገኖችን መስማት ሳያስፈልግ መወሰን

የክርክሩ ወይም የይገባኛል ጥያቄው ልዩነት መጠን ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ወይም ከዚያ ያነሰ ሲሆን ተከራካሪዎቹን ወገኖች መስማት አስፈላጊ አይደለም፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የግልግል ዳኛው(ዎች) ሁለቱም ወገኖች ባቀረቧቸው ሰነዶች ላይ በመመርኮዝ ጉዳዩን ለመወሰን ይችላሉ፣ ሆኖም የግልግል ዳኞች በጽሁፍ በሚመዘግቡት ምክንያቶች በክርክሩ የሁለቱንም ወገኖች ቃል ሊሰሙ ይችላሉ፡፡

DRAFT

### 6.8. ክርክር መስማት

(1.) የግልግል ዳኛው (ዳኞቹ) እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ክርክሩን የሚያቀርብበትን ዕድል በመስጠት ሒደቱን በፍትሐዊነት፣ ያለ አድልዎና በተፋጠነ ሁኔታ ያካሂዳል(ሉ)።

(2.) ተከራካሪ ወገኖች አግባብነት ያላቸውን ሰነዶችና ማስረጃዎች ክርክር ከመስማቱ በፊት መለዋወጥ አለባቸው።

(3.) ክርክር የሚሰማው የጋራ ስምምነት በተደረገበት ወይም በግልግል ዳኛው (ዳኞቹ) በተወሰነ ቦታ ነው። ተከራካሪ ወገኖች በራሳቸው ወይም በሕግ ባለሞያ ተወክለው ሊቀርቡ ይችላሉ።

(4.) የግልግል ዳኛው (ዳኞቹ) የምስክሮችን ምርመራ፣ የማስረጃ አቀራረብ እና የቃል ክርክርን ጨምሮ የክርክር አሰማሙን ሒደት ሊወስኑ ይችላሉ።

(5.) ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ሞያዊ አስተያየት የሚሰጡ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ባለሞያ(ዎች)ን ሊመድብ ይችላል።

### 6.9. ውሳኔ

(1.) ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር የግልግል ዳኞቹ ቁጥር ከአንድ በላይ ሲሆን ውሳኔ የሚሰጠው በአብላጫ ድምጽ ነው። የልዩነት አቋም ተመዝግቦ ይያዛል።

(2.) ከግልግል ዳኖቹ መከከል አንዱ በውሳኔው ላይ ድምጽ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ለተዋዋይ ወገኖች ይህንኑ የሚያሳውቅ ሲሆን ቀሪዎቹ የግልግል ዳኞች ውሳኔውን ይሰጣሉ።

### 6.10. ገዢ ሕግና የዳኝነት ሥልጣን

(1.) የግልግል ዳኝነቱና ሒደቶቹ የሚገዙት በኢትዮጵያ ሕጎች ነው።

(2.) ከግልግል ዳኝነቱ የሚመነጭ ወይም ተያይዞ የሚነሳ ማንኛውም አለመግባባትን ለመዳኘት ብቸኛ ሥልጣን የሚኖራቸው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ናቸው።

### 6.11. ቋንቋ

(1.) ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ሒደቱን ቋንቋ በመስማማት መወሰን ይችላሉ።

(2.) ተከራካሪ ወገኖች በቋንቋ ምርጫ መስማማት ካልቻሉ የግልግል ጉባዔው ለሒደቱ ተገቢ የሆነውን ቋንቋ ሊወስን ይችላል።

DRAFT

## 6.12. ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃዎች

ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር ከተከራካሪ ወገኖች በአንደኛው ጥያቄ ሲቀርብለትና ያለመግባባቱን ጉዳይ በሚመለከት ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ የግልግል ጉባዔው ጊዜያዊ የመጠባበቂያ እርምጃዎች ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 6.13. የሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ መግባት

ማንኛውም በግልግል ጉባዔው ውሳኔ ጥቅሙ ሊነካ የሚችል ሦስተኛ ወገን ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ለግልግል ጉባዔው ማመልከቻውን በማቅረብ ጣልቃ መግባት ይችላል፡፡

## 6.14. ውሳኔዎች

(1.) የግልግል ዳኛው (ዳኞቹ) የክርክር ሒደቱ በተጠናቀቀ በሠላሳ (30) ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ምክንያት በማካተት ውሳኔውን(ያቸውን) በጽሑፍ መስጠት አለበት(ባቸው)፡፡

(2.) የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በጽሑፍ ሆኖ በግልግል ዳኛው (ዳኞቹ) የተፈመረበት መሆን አለበት፡፡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው የተሰጠው ከሁለት በላይ የግልግል ዳኛ ባሉበት ጉባዔ ከሆነ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔውን የሰጡት ዳኞች ፊርማ በቂ ይሆናል፣ ፊርማውን ያልፈረመው የግልግል ዳኛም ያልፈረመበትን ምክንያት ማስቀመጥ አለበት፡፡

(3.) የግልግል ዳኝነት ውሳኔው መጨረሻና በሁሉም ወገኖች ላይ አስገዳጅነት የሚኖረው ሲሆን በግልግል ዳኝነቱ ወቅት የወጡ ወጪዎችን፣ ክፍያዎችንና ኪሳራዎችን የሚመለከቱ ትእዛዞችንም ሊያካትት ይችላል፡፡

(4.) ውሳኔው በማንኛውም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡

DRAFT

## 6.15. የግልግል ዳኝነት ሒደት መቋረጥ

የግልግል ዳኝነቱ ሒደት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

(1.) ከሳሽ ክሱን ሲያቋርጥና ጉባዔው የሚሰጠው ውሳኔ ተከሳሽን የሚጠቅም ካልሆነ፤

(2.) ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ሒደቱን ለማቋረጥ ከተስማሙ፤

(3.) የግልግል ጉባዔው ሒደቱን መቀጠል አላስፈላጊ እንደሆነ ካመነ ወይም በሒደቱ ላለመቀጠል በቂ ምክንያት ካለ፤

(4.) የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ከተላለፈ፤ እና

(5.) በሌሎች ሕጎች በግልጽ የተቀመጡ ምክንያቶች ካሉ፡፡

## 6.16. ምስጢር ጥበቃ

በግልግል ዳኝነት ሒደቱ የተገለጸ መረጃና የክርክር ሒደቶች በምስጢር መጠበቅ አለባቸው፡፡ በሕግ የተቀመጠ ግዴታ ከሌለ በስተቀር ያለ ሁለቱም ወገኖች ፈቃድ ለሦስተኛ ወገኖች መገለጽ የለባቸውም፡፡

## 6.17. የግልግል ዳኝነት ወጪ

1.1. የግልግል ዳኝነቱ ወጪ የሚሸፈነው በተከራካሪ ወገኖች ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ ሲባል ሁለቱም ወገኖች የግልግል ዳኝነቱን ለማካሔድ የሚወጡ ወጪዎችን ለመሸፈን ገበያው ዘንድ ገንዘብ ተቀማጭ ያደርጋሉ፡፡መልስ ሰጭ በዚህ መሠረት ተቀማጭ ለማድረግ ያልቻለ፣ ቸል ያለ ወይም ፈቃደኛ ያልሆነ ከሆነ አመልካች ገንዘቡን ተቀማጭ የማድረግ ኃላፊነት የሚኖርበት ሲሆን በሚሰጠው ውሳኔ መሠረትም ከመልስ ሰጭ ይህንኑ የማስመለስ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

1.2. አንድ የግብይት አባል ገንዘብ ተቀማጭ ማድረግ ካልቻለ፣ ገበያው ለግብይት አባሉ ከሚገባው ገንዘብ ላይ ተቀማጩን ገንዘብ የማስመለስ መብት አለው፡፡

1.3. የግልግል ዳኛው (ኞቹ) የግልግል ዳኝነት ወጪውንና ሒደቱ ከላይ ከተጠቀሱት በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ምክንያት(ቶች) የግልግል ሒደቱ ቢቋረጥ ተከራካሪዎቹ ወገኖች ይህንኑ ወጪ ለመሸፈን ያሉባቸውን ግዴታዎች ይወስናል (ሉ)፡፡

DRAFT

DRAFT

## የአስተዳደራዊ ቅጣቶች ሰንጠረዥ - የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓቶችና ግጭት አፈታት ደንቦች

(1.) የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የ 2017 መጽሐፈ ደንብ (የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓት እና የአለመግባባት አፈታት ደንቦች) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ለሚፈጸሙ ጥፋቶች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው አስተዳደራዊ ቅጣቶች በዚህ ሰንጠረዥ ሥር የተገለጸው ይሆናል፡፡

(2.) የአንድ ደንብ ወይም ሌላ የአሰያየም ልማድ ሲቀየር ስሙ ወይም የአሰያየም ልማዱም በዚህ የቅጣቶች ሰንጠረዥም ወዲያውኑ እንደተቀየረ ይቆጠራል፡፡

(3.) ከአንድ ጥሰት ጋር በተገናኘ ማንኛውም የዕገዳ እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ ዕግዱ የሚነሳው ተያያዥ ወይም ተያያዥ የሆኑ ግዴታዎች በሙሉ ተሟልተው ሲፈጸሙ ብቻ ነው፡፡

| ምዕራፍ | ደንብ | በየግብይት አባል/ተሿሚ እንደራሴ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ቅጣት | በተሿሚ እንደራሴ ወይም በሌላ ሠራተኛ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ቅጣት | ተደራራቢ ገጽታ |
|---|---|---|---|---|
| 1 የቅሬታዎች አፈታት | በምዕራፍ 1፡- "የቅሬታዎች አፈታት" ሥር የሚገኙ ደንቦች በሙሉ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 500,000 — 750,000<br>• ጥሰቱ እስኪታረም ድረስ ወይም ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት እገዳ፤ ከሁለቱ መካከል አንዳቸው ዘግይቶ መጨረሻ የሚከሰተው ይተገበራል፤የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 150,000 — 300,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | ተፈጻሚ አይሆንም |
| 2 | 2.1. ቅሬታን ለገበያው ማቅረብ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 100,000 — ብር 150,000 | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 35,000 — ብር 50,000 | ተፈጻሚ አይደለም |

DRAFT

| ምዕራፍ | ደንብ | በየግብይት አባል/ተሿሚ እንደራሴ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ቅጣት | በተሿሚ እንደራሴ ወይም በሌላ ሠራተኛ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ቅጣት | ተደራራቢ ገጽታ |
|---|---|---|---|---|
| የገበያው የዲሲፕሊን ሥነ-ሥርዓቶች | | • ጥሰቱ እስኪታረም ድረስ ወይም ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት እገዳ፤ ከሁለቱ መካከል አንዳቸው ዘግይቶ መጨረሻ የሚከሰተው ይተገበራል፤<br>• የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | |
| | 2.6. ማስረጃ ማቅረብና በንግድ ሥነ ምግባር ፓነል ፊት መቅረብ | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 100,000 - ብር 150,000<br>• ጥሰቱ እስኪታረም ድረስ ወይም ቢያንስ ለአሥር (10) የሥራ ቀናት እገዳ፤ ከሁለቱ መካከል አንዳቸው ዘግይቶ መጨረሻ የሚከሰተው ይተገበራል፤ የአባልነት ምስክር ወረቀት ስረዛ<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | • በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 35,000 - ብር 50,000<br>• ጊዜያዊ/ዘላቂ የምዝገባ ስረዛ/ማንሳት<br>• ገደብ መጣል እና/ወይም<br>• ጉዳዩን ወደ ወንጀል ክስ ምሥረታ መምራት | N/A ተፈጻሚ አይደለም |

DRAFT

DRAFT